

መንፈሳዊ ውጊያዎች

(የዲያብሎስ ውጊያዎች ደኖ መጽሐፍ)

የግብጽ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ
ብፁዕ አቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊ እንደጸፉት፤

አያሌው ዘኢየሱስ እንደተረጎመው::

የሽፋን ሥዕል:- ዲያቆን ሲራክ ዘኢየሱስ

መስከረም ፲፱፻፺፱ ዓ.ም.

አዲስ አበባ

ምስጋና

- የትርጉሙን ረቂቅ ውድ ጊዜያቸውን መሥዋዕት በማድረግ አንብበው ገንቢ አስተያየታቸውን ለሰጡኝ ለዲያቆን ጥላሁን ደሲላ፣ ለዲያቆን ወንድምሸ ገብሬ፣ ለዲያቆን ሲራክ ዘኢየሱስና ለወንድሜ ደጀኔ ሁንዴ፣
- የእንግሊዘኛውን መጽሐፍ በመስጠት እንድተረጉመው ላበረታታኝና የትርጉሙን ረቂቅ ባለው ውድ ጊዜ አንብቦ ገንቢ አስተያየቱን ለሰጠኝ ለዲያቆን አካለ ወልድ ተሰማ፣
- የኮምፒዩተር ለቀማውን ለሀትመት ካሜራ ዝግጁ ላደረገልኝ ለውድ ውድ ወንድሜ ለአቶ ዘውዱ ተካ፣
- መጽሐፉ ተተርጉሞ እንዲወጣ በተለያየ መንገድ ለረዳችኝ ለውድ እህቴ ዕሌኒ በርሔና ለሌሎችም ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ በሙሉ መንፈሳዊ ምስጋናዬን በእግዚአብሔር ስም አቀርብላቸዋለሁ።

የመጽሐፉ የእንግሊዘኛ ርዕስ: "Spiritual Warfares"

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያንን
ደንብና ሥርዓት ጠብቆ የተዘጋጀ።

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው።
All Rights Reserved

አድራሻ:- ደብረ ብሥራት ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን
ወይም
በስልክ ቁጥሮች - 0911 15 75 96፣ 0911 61 59 15፣

መግቢያ

የማንኛውም ሰው ሕይወት ከውጊያ የተለየ አይደለም። የቅዱሳን አባቶች ሕይወት እንኳ ከመንፈሳዊ ውጊያዎች የተለየ አይደለም። አንዳንዶቹ የእነርሱ ውጊያዎች ውጪያዊ ሲሆኑ ጥቂቶቹ ደግሞ ውስጣዊ ናቸው።

የዲያብሎስ ውጊያዎችን በተመለከተ ቀደም ሲል «የዲያብሎስ ውጊያዎች» በሚል ርዕስ ባሳተምሁት መጽሐፍ ውስጥ ሃያ አምስት የተለያዩ የዲያብሎስ ደባዎችንና አሥራ አንድ የሚሸነፍባቸውን መንገዶች ጠቅሼያለሁ።

ይህን በማስመልከት በዚህ መጽሐፍ የመጀመሪያ ምዕራፍ ውስጥ ጥቂት እላለሁ። ከውጪያዊ ጥቃት፣ ከአካባቢና ከክፉ ባልንጀርነት የሚመጡ ውጊያዎችም ውጪያዊ ውጊያዎች ውስጥ የሚመደቡ ናቸው። በእነዚህ ሁለት ነጥቦች ዙሪያ በዚህ መጽሐፍ የምለው አለኝ። ከዚህ በተጨማሪ "Life of Purity and Repentance" የተባለው መጽሐፌን እንድታነቡ እመክራለሁ።

ውስጣዊ ውጊያዎችን በተመለከተ ትኩረቴ በሁለት ዋና ዋና ነጥቦች ላይ ነው። እነርሱም:- አሳቦችና ምኞቶች ናቸው። አሳቦች ሕሊናን ሊዋጉ ምኞቶች ደግሞ ልብንና ስሜትን ይዋጋሉ። በዚህ መጽሐፍ የመጀመሪያ ምዕራፍ ላይ ከተጠቀሰው በተጨማሪ ስለ አሳቦች ውጊያ በዚሁ መጽሐፍ ሌላ ምዕራፍ ውስጥ ቀርቧል።

በሚቀጥሉት ገጾች ውስጥ ስለ ውስጣዊና ውጪያዊ ውጊያዎች እንድታነቡ እተዋችኋለሁ። ልታውቁት የሚገባው ጉዳይ አሁን የምታነቡት ይህ መጽሐፍ ከመንፈሳዊ ውጊያዎች አጠቃላይ ይዘት ጋር ሲነጻጸር እንደ መግቢያ ብቻ የሚቆጠር መሆኑን ነው።

አቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊ።

ከተርጓሚው

ውድ አንባቢያን ወገኖቼ በሙሉ! ከዚህ መጽሐፍ ቀደም ሲል ከብፁዕ አቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊ መንፈሳዊ መጻሕፍት መካከል «የተራራው ስብከት»፣ «የዲያብሎስ ውጊያዎች»፣ «የነፍስ አርነት»፣ «የተስፋ ሕይወት» እና «መንፈሳዊው ሰው» የተባሉትን አምስት መንፈሳዊ መጻሕፍት እግዚአብሔር ፈቅዶልኝ በተከታታይ ተርጉሜ ማቅረቤ በአናንተ ዘንድ ይታወቃል። ከዚህ በተጨማሪ ከቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ መንፈሳዊ መጻሕፍት መካከል አንዱን «ሀብታምና ድሀ» በሚል ርዕስ ተርጉሜ ማውጣቴ አይዘነጋም።

አሁንም ቸር፣ መሐሪ፣ ይቅር ባይና ርኅሩኅ የሆነው ልዑል እግዚአብሔር ዕድሜና ጤና፣ ብርታትና አውቀት ሆኖኝ ይህን "Spiritual War fares" የተባለውን የብፁዕ አቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊ መንፈሳዊ መጽሐፍ «መንፈሳዊ ውጊያዎች» ብዬ ወደ አማርኛ በመመለስ እንዳቀርብ የማያልት ቸርነቱን ስላበዛልኝ ክብርና ምስጋና ለእርሱ ይድረሰው!

«መንፈሳዊ ውጊያዎች» የተባለው ይህ የብፁዕ አቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊ መንፈሳዊ መጽሐፍ ከዚህ ቀደም «የዲያብሎስ ውጊያዎች» ተብሎ የተተረጎመው መጽሐፍ ሁለተኛ ወይም ተከታይ ክፍል ነው። ሁለቱ መጻሕፍት በእርዕስት ቢቀራረቡም በመጠናቸውና ሊሚያስተላልፉት መልእክት ይለያያሉ።

በዚህ መሠረት «መንፈሳዊ ውጊያዎች» በውስጣዊ ውጊያዎች በመጀመር በውስጡ ዓይነቶቻቸውን፣ ምልክቶቻቸውን፣ ምክንያቶቻቸውንና መፍትሔዎቻቸውን ካብራራ በኋላ ስለ ውጪያዊ ውጊያዎች በተመሳሳይ መልኩ በመግለጽ የሚጠናቀቅ መጽሐፍ ነው። መጽሐፉ በአሥራ አራት ምዕራፎች፣ በስምንት ዐቢይ ርዕሶች፣ በሰማንያ ዘጠኝ ንዑሳን ርዕሶችና በእርባ ዘጠኝ ደቂቅ ርዕሶች እንደ መከፋፈሉ ብዙት ያላቸውና የተለያዩ መንፈሳዊ ፍሬ ነገሮችን ለአንባብያን ያስጨብጣል ብዬ አምናለሁ።

ባለንበት ዘመን በትምህርት፣ በሥራና በሌሎችም ሥጋዊ ጉዳዮች ከመንፈሳዊ ሕይወት አብዝቶ በመራቅ ላይ ላለው ወገኔ መጻሕፍት የበኩላቸውን ድርሻ ያበረክታሉ ብዬ ስለማምን ያለ አስተማሪ የሚያስተምሩ መንፈሳዊ መጻሕፍትን የቅርብ ባልንጀሮቹ እንዲያደርግ እመክራለሁ።

አምላካችን እግዚአብሔር ከውስጥና ከውጪ በሚቃጡብን የዲያብሎስ ውጊያዎች ወድቀን እንዳንቀር እርሱ በምሕረት እጁቹ ያንሳን።

አያሌው ዘኪየሱስ።

ማውጫ

ምዕራፍ አንድ።
በአንተ ውስጥና ከአንተ ውጪ ያሉ ውጊያዎች። . . . 7

ምዕራፍ ሁለት።
የራስ ውጊያ። 21

ምዕራፍ ሦስት።
ባዶነት። 43

ምዕራፍ አራት።
መርሳት። 50

ምዕራፍ አምስት።
ጥርጥር። 57

ምዕራፍ ስድስት።
ፍርሃት። 66

ምዕራፍ ሰባት።
የአሳቦች ውጊያ። 73

ምዕራፍ ስምንት።
ውጪያዊ ገጽታዎች። 88

ምዕራፍ ዘጠኝ።
የአንደበት ኃጢአቶች። 97

ምዕራፍ አሥር።
የልብ ጭካኔ። 105

ምዕራፍ አሥራ አንድ።
መንፈሳዊ ዝለት። 113

ምዕራፍ አሥራ ሁለት።
የጎዘን ውጊያ። 135

ምዕራፍ አሥራ ሦስት።
የውዳሴና የክብር ፍቅር። 157

ምዕራፍ አሥራ አራት።
ጠብ ወይም አለመስማማት። 177

የመጽሐፉ ታሪክ

ከሰው ሕይወት ጋር ከሚዛመዱት ጠቃሚ አርዕስት መካከል መንፈሳዊ ውጊያዎች አንዱ ስለሆነ በዚህ ዙሪያ የተጻፉ የመጻሕፍት ስብስቦችን በአንድ ጥራዝ ማሳተም አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። በዚህ ተከታታይ ጽሑፍ ውስጥ የመጀመሪያ ሆኖ የታተመው መጽሐፍ «የዲያብሎስ ውጊያዎች» ነው።

ሁለተኛ ሆኖ የታተመው መጽሐፍ ይኼኛው ነው። ጽሑፉ እ.አ.አ. በ1960ዎቹ ውስጥ እንደ ስብከት ተሰብኳል። "The love of praise and honour" የሚለውን የመጀመሪያ ርዕስ የሰበክሁት እ.አ.አ. በ1965 ዓ.ም. አስክንድርያ በሚገኘው በቅዱስ ሚናስ ቤተ ክርስቲያን ሲሆን ስብከቱ የተሰበከውም ለአገልጋዮች በተደረገ ጉባኤ ላይ ነበር። ይህ ስብከት "Moharram Baik" በሚገኘው በእመቤታችን ቤተ ክርስቲያን አማካይነት ታትሞ ከወጣ በኋላ በተደጋጋሚ ታትሞ ወጥቷል። ርዕሱ መጠነኛ ለውጥ ተደርጎበት በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ተካቷል።

የዚህ መጽሐፍ አርዕስት በ1985 (እ.አ.አ.) ሙሉ ዓመት ውስጥ "Watani" በተባለ ወርሐዊ መጽሔት በተከታታይ ወጥቷል። አሁን ለሁሉም እንዲዳረስ ስለተፈለገ አንድ መጽሐፍ አድርገን ልናወጣው መርጠናል።

አግዚአብሔር ከፈቀደ «መንፈሳዊ ውጊያዎች» በሚለው ተከታታይ ጽሑፍ ውስጥ የምናሳትማቸው ብዛት ያላቸው ሌሎች አርዕስት አሉን። ከእነዚህ መካከል «ቁጣ» በሚል ርዕስ አንድ መጽሐፍ የሚኖረን ሲሆን በዚህ መጽሐፍ ውስጥ «የአንደበት ኃጢአቶች» በሚል ንዑስ ርዕስ ባጭሩ የተገለጸው ርዕስ በመጽሐፍ ይዘት ይኖረናል።

መንፈሳዊ ውጊያዎችን አስመልክተው አንዳንድ አባቶች በጻፏቸው ጽሑፎቻቸው ውስጥ ነፍስን ስለሚዋጉ ስምንት ውጊያዎች ገልጸዋል። እነርሱም፡- ሆዳምነት፣ ዝሙት፣ ቁጣ፣ ኀዘን፣ ስንፍና፣ የሀብት ምኞት፣ ከንቱ ውዳሴና ክብር ናቸው። እነዚህን አርዕስት አስመልክተው አባቶች ያዘጋጇቸውን ጽሑፎች እንድታነቡ እመክራለሁ።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ አብዛኛዎቹን መንፈሳዊ ውጊያዎች ለማካተት ሞክረናል። ከዚህ በተጨማሪ ስለ ምልክቶችቸው፣ ስለ ምክንያቶቻቸውና ስለ መፍትሔዎቻቸው ለመግለጽ ሙከራ አድርገናል።

ሁልጊዜ ድል በመንሣቱ የሚያዘረን ክርስቶስ ማንኛውንም በጎ ስኬት እንዲያከናውንላችሁ እየተመኘሁ በሦስተኛው ክፍል የመንፈሳዊ ውጊያዎች መጽሐፍ እስክምንገናኝ ድረስ ሰላም ሁኑ።

አቡነ ሺኖዳ ሣልሳዊ።

ምዕራፍ አንድ።

በአንተ ውስጥና ከአንተ ውጪ ያሉ ውጊያዎች።

◆ **ውስጣዊ ውጊያዎች።**

- የአሳብ ውጊያና አሳብን እንዴት መዋጋት ይቻላል።
- የምኞት ውጊያ።

◆ **ውጪያዊ ውጊያዎች።**

- የዲያብሎስ ውጊያዎች።
- ክፉ ባልንጀርነት።
- ጥቃት።
- አካባቢ።

መንፈሳዊ ውጊያዎች ወደ ሰው የሚመጡት ከውስጥ፣ ከዲያብሎስ፣ ከዓለምና ከክፉ ሰዎች ነው።

◆ **ውስጣዊ ውጊያዎች።**

እነዚህ ውጊያዎች ከልብ ምኞት፣ ከአእምሮ አሳብና ከሰውነት እንቅስቃሴ ይመጣሉ።

ውስጣዊ ውጊያ በውጪ ካለ ውጊያ ጉዳቱ የላቀ ነው። ምክንያቱም በውስጣዊው ውጊያ ሰው የገዛ ራሱ ጠላት ስለሚሆን ነው። ሰውየው ስለሚመኝ ውና ሊቋቋመው ስለማይፈልግም ይህ ውጊያ ከባድ ነው።

ከቅዱሳን አንዱ «ንጹሕ ልብ የማይደፈር ምሽግ ነው» ብሎ እንደ ተናገረ በሰው ሕይወት ውስጥ የልብ ንጽሕና ከምንም በላይ ይቆጠራል። ልብ በዓለት ላይ የተመሠረተ ቤትን ይመስላል። ከውጪ የተፈለገውን ያህል ነፋስ ቢነፍስም ምንም ዓይነት ጉዳት ሊያደርስበት አይችልም። ማቴ 7:24-25።

ውስጣዊ ውጊያ የሌለበት ሰው በውጪያዊ ውጊያ ቢጠቃ ለእርሱ ቀላል ስለሚሆን በቀላሉ ሊያሸንፈው ይችላል። ይህ ሊሆን የሚችለውም የእርሱ ልብ እንዲህ ያለውን ነገር ስለማይቀበለው፣ መልስ ሊሰጠው ስለማያዘምና በጀ ስለማይለው ነው።

ምናልባት ውስጣዊ ውጊያ የሚመጣው የአንድ ሰው ተፈጥሮ በኃጢአት ሊጠመድ ሊሆን ይችላል። እዚህ ላይ ሰው ውጊያ የሚመጣበት በልቡና በአሳቡ ውስጥ በተተከሉ የቀደሙ ጉዳዮች ነው።

2. አሳቦችህን ለመምራት ራስህን አለማምድ እንጂ አሳቦችህ አይምሩህ።

3. ሁልጊዜ ሕሊናህን በመንፈሳዊ ነገሮች ሙላ።

ይህን የምታደርግ ከሆነ ዲያብሎስ መጥፎ አሳብ ሊያስተዋውቅህ ሲመጣ እንኳን ደህና መጣህ የሚሰው ሕሊና አያገኝም። እንደ መከላከያ መፍትሔ ይሆንህ ዘንድ ዘወትር ራስህን በሥራ ባተሌ አድርግ። ዲያብሎስ ወደ እርሱ ገብቶ የወደደውን ዘር እንዳይዘራበት ሕሊናህን ባዶ አታድርገው።

መንፈሳዊ ንባብ ሕሊናን በሥራ ለመጥመድና መጥፎ አሳቦችን ለማራቅ ብቻ ሳይሆን ሌላም ታላቅ ጥቅም አለው። ንባብ ሕሊናን በተመስጦ ሊሞላ የሚችል መንፈሳዊ ዘዴ ከመስጠቱም በላይ ተቃዋሚ አሳቦችን የሚያጠፋውንና እግዚአብሔርን መውደድ የሚያስችሰውን ስሜት በልብ ውስጥ ያነሳሳል።

4. ባልጠበቅኸው ሰዓት የኃጢአት አሳብ እንዳይጥልህ የልብህን ፅሕና በመጠበቅ ሁልጊዜ ንቁ ሁን።

አሳቦች ደካማ አንተ ደግሞ ብርቱ በሆናችሁበት ጊዜ አሳቦችን ከጅምሩ አጥፋቸው። አሳቦችን ለጥቂት ጊዜ በሕሊናህ ውስጥ ካቆየሃቸው ወዲያውኑ ሰፍረው ይቆጣጠሩሃል። በአንተ ውስጥ ተደራጅተው ሲሰፍሩ ስለምትደክምና ልትቋቋማቸው ስለማትችል ትወድቃለህ። ስለዚህ አሳቦችን ከአንተ ለማራቅ ንቁና ፈጣን ሁን። የመዝሙረኛውን ቃላትንም አስታውስ፦ «አንቺ ወራዳ የባቢሎን ልጅ ሆይ . . . ሕፃናቶችሽን ይዞ በዓለት ላይ የሚፈጠፍጣቸው የተመሰገነ ነው።» መዝ 136፡8-9።

እዚህ ላይ መዝሙረኛው የሚናገረው የግዞት ምድር የሆነችውንና ልቡን በምርኮ የወሰደችውን ባቢሎንን ነው። ዳዊት «ሕፃናቶችሽን ይዞ . . . » የሚለው ገና ያልዳበሩትን፣ በጅምር ያሉትንና ትናንሾቹን ኃጢአቶች ሲሆን «. . . በዓለት ላይ የሚፈጠፍጣቸው የተመሰገነ ነው።» በሚሉት ቃላት ውስጥ የተጠቀሰው «ዓለት» ደግሞ ክርስቶስ ነው። «ያም ድንጋይ ክርስቶስ ነበረ።» 1ኛ ቆሮ 10፡4።

5. የአሳብ መንፈሳዊ ባሕርይና የአሳብ ይሉኝታ።

ሕሊናህ በጸሎት፣ በተመስጦ፣ በፍቅር ቃላት፣ በውዳሴና በመዝሙር ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ይሆናል። በዚህ ጊዜ ሕሊና በሌሎች የኃጢአት አሳቦች ላለመጠመድ ይሉኝታ ይይዘዋል። በመሆኑም እነዚህን አሳቦች ያስወግዳል። ይህ ደግሞ መንፈሳዊ መፍትሔ ነው። ከላይ የተመለከትነው ከእግዚአብሔር ጋር አንድ የሚያደርግ መፍትሔ ሕሊናን በይሉኝታ የሚይዝ ከሆነ ሕሊናን ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ማድረግ ከኃጢአት አሳቦች የሚጠብቅ መፍትሔ ነው።

6. በሌላ መልኩ ጥቃቶችን ሊያመጡብህ ከሚችሉ የኃጢአት አሳቦች መራቅ አለብህ።

ከማንኛውም ጎጂ ስብሰባ፣ ከማንኛውም ክፉ ባልንጀርነት ወይም ከማንኛውም ግንኙነት ራቅ። መጥፎ አሳብ ሊያስከትሉብህ የሚችሉና ከመንፈሳዊ አሳቦችህ ሊያስወጡህ የሚችሉ አሳቦች ያላቸው ጽሑፎችን ከእንተ ዘንድ አስወግድ። እነዚህን ነገሮች አትስማ፣ አትመልከት፣ ስለ እነርሱም አታውራ። በአጠቃላይ ክፉ አሳብ ሊያመጡብህ የሚችሉ ነገሮችን ከአጠገብህ አስወግድ።

7. ስሜቶችህ የሕሊናህ መግቢያዎች ስለሆኑ ንጹሕ አሳቦችን ይሰጡህ ዘንድ ንጹሕ አድርገህ ጠብቃቸው።

በስሜቶችህ ቸልተኛ ከሆንህ ራስህን ተዋጋው። ራስህን ጠብቅ። ስሜቶችህ ያገልግሉህ እንጂ አይቃወሙህ። ከዚህ በኋላ በቅዱሳን ሥዕላት ላይ ተመስጦ አድርግ፣ ስለ እነርሱ አድምጥ፣ ማኅሌቱንና ቅዳሴውን አድምጥ። በቤተ ክርስቲያን ዙሪያ ያለው በዕጣን፣ በመብራት፣ በቅዱሳን ሥዕላትና በመንፈሳዊ ዜማ የተሞላ ክባቢ አየር ተካፋይ ሁን። እነዚህ ሁሉ ለልብህ መንፈሳዊ አሳቦችን ያቀርባሉ።

8. መልካም ወይም መጥፎ ያልሆኑ የጥርጥር አሳቦችን ተጠንቀቃቸው።

እነዚህ አሳቦች በአብዛኛው ወደ ኃጢአት አሳቦች የሚመሩ ናቸው። ሕሊናውን ሊቆጣጠር የማይችለውን ሰው ሕሊናውን እንደ ወደደው እንዲባዝን ስለሚተወውና በኃጢአት የተሞላ ጉዳይ እንዲያገኝ ስለሚረዳው በእርሱ የተጠመደ ይሆናል። ሕሊናህን በጎ በሆነው በእግዚአብሔር ፍቅር ወይም በሌሎች ጠቃሚ ጉዳዮች ሙላው። ይህም ሥራህን፣ ጥናትህን፣ አገልግሎትህንና ሕሊናህ በሌሎች ጠቃሚ ባልሆኑ ነገሮች እንዳይጠመድ በመጠበቅ ኃላፊነትህን መወጣትህን ያጠቃልላል።

9. በአሳብ ታውከህ ልታሸንፈው ካልቻልህ ከሌሎች ጋር በማውራት ከእርሱ ሽሽተህ ሂድ።

ብቻህን ብትሆንም እንኳ ብቸኝነትህን ትተህ በመውጣት ከሰዎች ጋር ግንኙነት አድርግ። ሕሊናህ በተመሳሳይ ሰዓት በአሳብና በንግግር ሊጠመድ ስለማይችል በግኑኝነትህ ውስጥ ያለው ንግግር የኃጢአት አሳብህን ያጠፋልሃል። በመንፈሳዊ መረዳት ብቸኝነት ማለት ከእግዚአብሔር ጋር መሆን ማለት ነው። ይህ ከክፉ አሳቦች ጋር በብቸኝነት መቆየት በሚለው ከተተረጎመ ከሌሎች ጋር በኅብረት መቆየት በእርግጥ ይሻላል።

10. አሳብን ለማጥፋት የጸሎትን እርዳታ ፈልግ።

ወደ እግዚአብሔርን አንተን የማያስደስት ማንኛውንም ዓይነት አሳብ ከእኛ አርቅልን ብለን እንጸልያለን። አሳብን ስለ መዋጋት የሚገልጸውን መንፈሳዊ መመሪያ ልንነግራችሁ እንወዳለን። እርሱም . . .

11. አሳቦችን ከመዋጋት ይልቅ ከአሳቦች መሸሽ ይሻላል። ምንም እንኳ አዕምሮህን ወጥሮ የያዘውን ክፉ አሳብ ልታሸንፈው ብትችልም እግረ መንገዱን ሊያረክስህ ይችላል።

በታላቅ መሻት ውስጥ ሆነህ «አሳብ እንዴት እንደሚጀምርና እንዴት እንደሚጠናቀቅ አውቃለሁ!» በማለት ራስህን አታታል። እንዲህ ያለው አሳብ ጉዳት ሊያደርስብህ እንደሚችል አንተ ራስህ ጠንቅቀህ ታውቃለህ። ስለሆነም ራስህን ውጤቱን በምታውቀው የክስ ወንበር ላይ አታስቀምጥ። እንዲህ ያለውን ጉዳይ ቀላል አድርገህ በመገመትም «አሳቦችን አሸንፋቸዋለሁ። ስለ እነርሱ የማወራውም ድካማቸውን ለማሳየት ነው!» አትበል። አሳቦች አንተን በማሸነፍ ድካምህን ሊገልጡብህ ይችላሉና።

በመዋጋት ለምን አቅምህን ታዳክማለህ?

በመንፈሳዊ ሕይወትህ ውስጥ ሕሊናህን ብርታት በሚሰጡ በጎና ንጹህ አሳቦች ጥመደው። ሕሊናህን አንተን ሊጠቅሙ በሚችሉ አሳቦች እንጂ ሊጠቅሙ በማይችሉ ተቃዋሚ አሳቦች አትሙላው።

12. አሳቦች እያደጉ ሲሄዱ ወደ ሌላ አሳብ ወይም ወደ ምኞት ይመራሉ። እዚህ ላይ አሳቦች የበለጠ አደገኛ ይሆናሉ። ምክንያቱም ከሕሊና ወደ ልብ፤ከአሳብም ወደ ድርጊት ስለሚሸጋገሩ ነው። በዚሁ ወደ ሌላ ነጥብ እንሸጋገራለን።

+የምኞት ውጊያ።

ብዛት ያላቸው የምኞት ዓይነቶች አሉ። ከእነርሱም መካከል የሥጋ ምኞት፣ የእውቀት ምኞት፣ የሥልጣንና የደረጃ ምኞት፣ የብቀላ ምኞት፣ የበላይነት ምኞት፣ የሀብት ምኞት፣ የባለቤትነት ምኞት፣ የክብር ምኞትና የዝና ምኞት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

እዚህ ላይ ልብ ንብረትነታ ከእግዚአብሔር ይልቅ ወደ ሌላ ስለሚሸጋገር «ልጄ ሆይ ልብህን ስጠኝ . . .» (ምሳ 23:26) ለሚለው የእግዚአብሔር ቃል የምትሰጠው ምላሽ አይኖርህም።

1. በአንድ ምኞት ከተጠቃህ በእርሱ አትግፋ።

ይልቁኑ ልታስወግደው ከመሞከር ጋር «ባንኛችሁት ምኞት ሳይሆን ባሸነፋችሁት ምኞት ደስ ይበላችሁ!» የሚለውን አባባል አስታውስ። ስውን ይበልጥ ደስ የሚያሰኘው ራሱን ማሸነፍ ሲችል ነው። በሌላ ምኞት ከሚመጣ ደስታ ይልቅ ራስን ከማሸነፍ የሚመጣ ደስታ ጥልቅ ነው።

2. ምኞት ቢያሰለችህም ተስፋ አትቁረጥ! ምንም ጥቅም የለውም ብለህም አታስብ!

አንተ ልትመለከተው የሚገባህ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለአንተ የሚያደርግልህን ነገር እንጂ አንተ ለራስህ ልታደርገው ያቃተህን ነገር አይደለም። ጌታ ሳምራዊቷን ሴት ወደ ወንጌል መስካሪነት መግደላዊት ማርያምንም ወደ ቅድስትነት የለወጠ አምላክ ነው። እግዚአብሔር በጸጋው ከሌሎች ጋር እንደሚሠራ ሁሉ ከአንተም ጋር ይሠራል። ስለዚህ ብቻህን እንደምትዋጋ አድርገህ በፍጹም አታስብ።

3. ድል ከተቀዳጁ በኋላ በፊትህ የቀደሙ ውድቀቶችህንና ደካማ ተፈጥሮህን ያሳሳሉብህ ቅዱሳንን አስብ።

እግዚአብሔር ድል የነሡትን እንደ ወደዳቸው አንተንም ይወድሃል። ከሌሎች ጋር ሆኖ እንደሠራውም ከአንተም ጋር ይሠራል። ጥቃት ሲጨምር የእግዚአብሔር ጸጋ ይበልጥ ይጨምራል። ስለዚህ ወደ እግዚአብሔር በመጠጋት የእርሱን እርዳታ ፈልግ።

4. በምኞትህ ውስጥ ስትሆን እግዚአብሔር በምሕረቱ እስኪነበኝህ ድረስ ከእርሱ ጋር በጽናት ታገል።

በጠለቀ ኃጢአት ውስጥ ስትሆን ለመጸለይ አትፈር። አባታችን አዳም ኃጢአት ከሠራ በኋላ ከእግዚአብሔር ፊት በመሸሽ ራሱን ከዛፍ በስተ ጀርባ እንደ ደበቀ አንተም ራስህን አትደበቅ። በወደቅህ ቁጥር እግዚአብሔር እንዲያነሣህ፣ ወደ ንሥሓ እንዲመራህና እንዲያነጻህ በእርሱ ላይ ተጣበቅ። «አቤቱ ጌታዬ ሆይ! አንተ በእኔ ላይ አድረህ ተዋጋ። የእኔንና የአንተን ጠላቶች ድል ንሣቸው! አንተ አትተወኝ!» በለው።

እንዲህም በለው፦ «አቤቱ ጌታዬ ሆይ! በኃጢአት ብወድቅም የአንተ የሆንሁና ከአንተ ጋር የተዛመድሁ ልጅህ ነኝ! ከጋጣህ ብጠፋም የመንጋህ በግ ነኝ! በሩቅ ሀገር የምኖር ልጅህ ነኝ! ከገንዘብ ቦርሳህ ውስጥ ብጠፋም የአንተ ድሪም ነኝ! . . . ጠላት ከአንተ ጋር ሊለየኝ ቢሞክርም እኔ አንተን ፈጽሞ አልረሳህም . . . አንተም እንዲሁ! ምንም እንኳ ከአንተ ብርቅም ከልቤ አላወጣሁህም ወደፊትም አላወጣህም። በአንተ ላይ ኃጢአት ብሠራም እስካሁን ድረስ አወድሃለሁ።

ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ ጌታን በካደ ጊዜ እንዳደረገው አንተም አድርግ። እርሱ ጌታውን «ሰውየውን አላውቀውም . . . » (ማቴ 26:72) ብሎ ከካደ በኋላ ስሜቶቹን በማወቅ በእርሱ ፊት ራሱን በትሕትና ዝቅ አድርጎ እንዲህ ነበር ያለው፦ «ጌታ ሆይ፦ አንተ ሁሉን ታውቃለህ፤ እንድወድህ አንተ ታውቃለህ።» ዮሐ 21:17።

5. ኃጢአት ከእግዚአብሔር ፍቅር እንዲለይህ አይሁን። ይልቁንም ልብህን ለእርሱ ከፍተህ «አቤቱ አምላኬ ሆይ! ይህን ኃጢአት የፈጸምሁት ከድካሜ የተነሣ ነው እንጂ ከጥላቻ ወይም ከክህደት የተነሣ አይደለም!» በለው።

6. እግዚአብሔር ድካምህን እንደሚያውቅና እስካሁን ድረስም እንደሚወድህ እርግጠኛ ሁን! በኃጢአት ውስጥ ብትሆንም እግዚአብሔር ሊያድንህ፣ ወደ እርሱ ሊያቀርብህና ወደ ቀደመ ደረጃህ ሊመልስህ እንደሚሠራ እመን። አዳም የዳነው ንሥሓ ለመግባት ባደረገው ሙከራ ሳይሆን አዳምን በተመለከተው የእግዚአብሔር ቸርነት ነው።

7. የኃጢአት ምኞትህን የሚዛን ልክ በልብህ ውስጥ ያመጣጥን ዘንድ ማንኛውንም ዓይነት መንፈሳዊ ሥራ በመሥራት የክፋታቸውንና የአደጋቸውን መጠን ቀንስ። የምኞትን ኃጢአት እስክታስወግድ ድረስ መልካም ፈቃድ በልብህ ውስጥ ቀስ በቀስ እንደሚያብብ እርግጠኛ ሁን። መንፈስ ቅዱስ በውስጥህ እንደሚሠራ ሲታወቅህ ችላ አትበለው! ከእርሱ ጋር ሥራ እንጂ በምኞትህ ልትቀጥል አትሞክር።

8. ድካምህን ስታውቅ በሌላ ጊዜ ራስህን ለውጊያ አታጋልጥ።

❖ ውጪያዊ ውጊያዎች።

እነዚህ ውጊያዎች የሚመጡት በሚገባ ከሚታወቁ ምንጮች ነው። የሚመጡት ከዲያብሎስና ጠላት ከሆኑ ሰዎች ወይም የቅርብ ወዳጆች ከሆኑ ሰዎች ነው። እነዚህ ውጊያዎች ከዓለም፣ ከቁሳዊ ነገሮች፣ ወይም በውስጡ ጥቃት ከያዘ ከአካባቢ ሊመጡ ይችላሉ።

+የዲያብሎስ ውጊያዎች።

የዲያብሎስ ውጊያዎች ዝግ ብለው የተራዘሙ ወይም ድንገተኛና ከባድ ሊሆኑ ይችላሉ።

ዲያብሎስ ሰለባዎቹን የሚስበው በተራዘመ ለዘብተኛ አቀራረብ ስለሆነ ተጠቂዎቹ ምን ሊመጣባቸው እንደሚችል አያውቁም። ስለሆነም እነዚህን ዝግ ያሉ ውጊያዎቹን አንገነዘባቸውም።

ዲያብሎስ ሕይወታቸው እስኪለወጥ ድረስ መንፈሳዊ ፍቅራቸውን በዝግታ እያሳጣ ወደ ሰፊው የውጊያ ዓውድ ቀስ በቀስ ይጎትታቸዋል። የሚባንኑት ዕድላቸው ካለፈ በኋላ ስለሚሆን ዲያብሎስ ባልተዘጋጁበት ሰዓት ድንገት ይመታቸዋል። ምናልባት ጠቢቡ ሰሎሞን የተወጋው ቅንጦት፣ ድሎት፣ ብዙ ሴቶችና ይሉኝታ ባሰብት በዚህ መንገድ ነው። በመሆኑም ወደቀ። 1ኛ ነገ 11:1-8። የወደቀውም በዕድሜው የመጨረሻ ዘመን ላይ ነው።

ድንገተኛና ከባድ ውጊያዎች አስፈሪ ጣዕረ ሞት ወይም የተሳሳቱ ቅዠቶችን ይመስላሉ። እነዚህ ነገሮች የዲያብሎስ ከንቱ ስሜቶች ናቸው። ታላቁ ቅዱስ እንጦንስ በእነዚህ ውጊያዎች ቢወጋም ድል የነሣቸው በትሕትና፣ ሰይቶ በማወቅና በጸሎት ነው። በዚህ ስላሸነፋቸው ርኩሳን መናፍስት እርሱን በማፈር ከአጠገቡ በነው ጠፍተዋል።

ይህ ይሁን እንጂ እግዚአብሔር አምላክ ሰው ሁሉ በእነዚህ ውጊያዎች እንዲጠቃ አይፈቅድም። ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ «. . . ነገር ግን ከሚቻላችሁ መጠን ይልቅ ትፈተኑ ዘንድ የማይፈቅድ እግዚአብሔር የታመነ ነው።» (1ኛ ቆሮ 10:13።) ብሎ ስለሚናገር ነው።

ከባድ ከሚባሉትና ድንገት ከሚደርሱት ውጊያዎች መካከል በጻድቁ ኢዮብ ላይ የወረደው አንዱ ነው። ኢዮ 1 እና 2። ይህ ውጊያ በእግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ፣ ኢዮብ ሊሸከመው በሚችለው መጠን የተወሰነና በመልካምና በተባረከ መንገድ የተጠናቀቀ ውጊያ ነው። ኢዮ 42። ይሁን እንጂ ሁሉም የዲያብሎስ ውጊያዎች ቅዱስ እንጦንስን እንደ ገጠሙት ማስደንገጫዎችና ማስፈራሪያ ትዕይንቶች ወይም በጻድቁ ኢዮብ ላይ እንደወረደው ቁስልና ጥፋት ያሉ ብቻ አይደሉም።

ከእነዚህ የተለዩ ዲያብሎስ የሚቀሰቅሳቸው ሌሎች ውጊያዎች አሉ። እነዚህም ዲያብሎስ በአሳብ ውስጥ ወደ ሕሊና የሚያስወነጭፋቸው ወይም በልብ ውስጥ የሚያሳድራቸው ውጊያዎች ናቸው። እነዚህ ውጊያዎች ሊጀምሩ በአብዛኛው ደካማ ከመሆናቸውም በላይ ለሰውየው እንግዳ ስለሆኑ ነው። እነዚህ ውጊያዎች ሰውየው ወደ ልቡና ወደ ፍላጎቶቹ ዘልቀው እንዲገቡ መዝጊያውን እስኪከፍትላቸው ድረስ በዚያው ይቆያሉ። ከከፈተላቸው እዚህ ላይ ከፍተኛውን ስህተት ይፈጽማል።

በአንተ ውስጥ ያለውን የእግዚአብሔርን መንግሥት ለሚያጠፋ ጠላት መዝጊያዎችህን መክፈት መንፈሳዊ ክህደት ነው። ይህ ክህደት ወደ ቤትህ ገብቶ ሊቀመጥ በወደደው በእግዚአብሔር ላይ የሚደረግ ክህደት ነው። በእርግጥም የእግዚአብሔር ተቃዋሚ የሆነው ጠላት ከጌታህ ይልቅ በልብህ ውስጥ ገብቶ ይቀመጥ ዘንድ ስለፈቀድህለት ይህ ክህደት ነው። በገዛ ደሙ ለዋጀህና እስከ መጨረሻው ድረስ ለወደደህ ጌታ ይህ ሽፍጥ ነው። እርሱ ለአንተ ቅዱሳት ምሥጢራትን ከመግለጡም በላይ ልብህን የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ አድርጎልሃል። 1ኛ ቆሮ 6:19-20። አንተ ግን ለዲያብሎስ በመታዘዝ ልብህን ከፍተህ የእርሱን ተቃዋሚ አሳቦች መቀበልህ ታላቅ ክህደት ነው። በዚህ ክህደት ምክንያት በአንተ ውስጥ ያለውን የእግዚአብሔርን የጸጋ ሥራ ስለምትቃወም ዲያብሎስ በአንተ ላይ ኃይል ይቀዳጃል።

ውጪያዊ ውጊያዎች ከባድ ናቸው በማለት ምንም ዓይነት ምክንያት አታቅርብ። ይህን የምታደርግ ከሆነ ለእነርሱ እጅህን ስለ ሰጠህ ኃይል የምታሳናጽፋቸው አንተ ትሆናለህ። የምትቃወማቸው ከሆንህ ግን ሐዋርያው እንደ ተናገረ ዲያብሎስ በአንተ ፊት ደካማ ይሆናል። «. . . ዲያብሎስን ግን ተቃወሙ ከእናንተ ይሸሻል።» ያዕ 4:7።

ለእግዚአብሔር ፍቅር ያለውና በእምነት የጸናብርቱ ልብ የሚገነለበሉትን የጠላት ፍላጻዎች ሁሉ ሊያጠፋ ይችላል። ኤፌ 6:16። የቅዱስ ዳዊት ልብ በእምነት ሲበረታ የግዙፉ ጎልያድ ኃይል በእርሱ ፊት ደካማ ሆኗል። 1ኛ ሳሙ 17:26። የነቢዩ ሙሴ ልብ በፊርዖንና በሠራዊቱ ላይ እየበረታ ሲመጣ የጠላቶቻቸው ኃይል እየከሰመ ሄዷል። በዚህ ጊዜ ቀይ ባሕር ሙሴን

አሳስፈራውም። አንተም በውስጥህ ያለው ልብህ ብርቱ እስከ ሆነ ድረስ በዲያብሎስ ውጊያዎች ፊት በጭራሽ ደካማ አትሆንም። ከዚህ በተጨማሪ በነቢያት አድሮ ይናገር በነበረው በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ቃል ትጽናናለህ፦ «ታላቅ ተራራ ሆይ፦ አንተ ምንድር ነህ? በዘሩባቤል ፊት ደልዳላ ሜዳ ትሆናለህ . . . » ዘካ 4:7። እኛ ደካሞች ስንሆን ለዲያብሎስ ሊሰጠው የማይገባውን ክብር እንሰጠዋለን። በዚህም እኛን ሊፈራን ሲገባው በገዛ እጃችን ድፍረቱን እንሰጠዋለን።

የርኩሳን መናፍስት አለቃ የሆነው ዲያብሎስ ከረዳቶቹ አንዱን ወደ አንዱ ክርስቲያን አማኝ እንዲዋጋው ሲልከው ርኩስ መንፈሱ እየተንቀጠቀጠ፦ ከዚህ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያና የእግዚአብሔር አምሳል ከሆነ ሰው ጋር እንዴት እዋጋለሁ? ያድኑት ዘንድ የእግዚአብሔር መላእክት ዙሪያውን የከበቡትን ይህን ብርቱ ሰው እንዴት እዋጋዋለሁ? የእምነትን ጋሻ ወደያዘውና የመዳንንም ራስ ቁር ወዳጠለቀው ሰው እንዴት እቀርባለሁ? ይላል። ኤፌ 6። ከዚህ በተጨማሪ በመስቀል ቅርጽ ቢያማትብኝ ምን እሆናለሁ? አጀቹን ለጸሎት ቢያነሣብኝስ ወዴት አመልጣለሁ? «ሂድ! አንተ ሰይጣን . . . » ብሎ ቢያባርረኝስ ምንኛ አፍራለሁ? በማለት ይጠይቃል።

ይሁን እንጂ ከዚህ በተቃራኒው ርኩስ መንፈሱ እስኪደነቅ ድረስ ያ ሰው እርሱን በመፍራት ከፊቱ ሲሸሽ ይመለከተዋል። ስለሆነም እንዲህ ዓይነቱን ሰው ይንቀዋልም ይጠላዋልም። ከዚህ በኋላ ዲያብሎስ በሶምሶን ላይ እንዳደረገው የዚህን ሰው ፀጉር ይላጫል ዓይኖቹንም ያወጣል። በመጨረሻም በልጆች እያስፈዛበት ወፍጮ ያስፈጨዋል። መሳ 16:19-21።

ርኩሳን መናፍስት በአንተ ላይ ኃይላቸውን ሊያሳዩ ቢሞክሩም አትፍራቸው። ይልቁኑ አንተ የእግዚአብሔር አምሳል ስለ ሆንህ በአነርሱ ፊት ራስህን አክብር።

ለዲያብሎስ ውጊያዎች ዓይነተኛ ምሳሌ ከሚሆኑን መካከል እግዚአብሔርን አለማመንና ተስፋ መቁረጥ ዋና ዋናዎቹ ናቸው። ይሁን እንጂ እነዚህ የእንተ እጅ የሌለባቸውና የአንተ ያልሆኑ ውጪያዊ አሳቦችና ጥቃቶች ስለሆኑ አትፍራቸው።

ዲያብሎስ ወደ ሕሊናህ የሚያስወነጭፋቸው ፍላፃዎች የእግዚአብሔርን ሕልውና፣ ፍቅሩንና ጥበቃውን እንድትጠራጠር የሚያደርጉ ናቸው። የጸሎትህን ውጤታማነትና የቅዱሳንን አማላጅነት የሚያጠራጥሩ አሳቦችም በሕሊናህ ውስጥ ይጨምራል። ይሁን እንጂ አንተ በዚህ አልተደሰትህም ብለህ አሳቦቹን በመቃወም እግዚአብሔር ከአንተ ያርቅልህ ዘንድ ወደ እርሱ ስትጸልይ ዲያብሎስ፦ «እነዚህ ሁሉ አሳቦች በአንተ ውስጥ እያሉ እንዴት ልትድን ትችላለህ?» ይልሃል። ይህ የአሳብ ውጊያ ነው እንጂ በአሳብ የሚመጣ ውድቀት አይደለም። ለጥቂት ደቂቃዎች ብትወድቅም እንኳ ከድካም የተነሣ እንጂ በእግዚአብሔር ባለመታመን አይደለም። ስለዚህ እርሱም ይቅር ይልሃል።

አሳቦችን ወደ ሕሊናህ የሚያመጣ ጽሑፍ እንዳታነብ እመክርሃለሁ። እነዚህን አሳቦች የሚያቀብሉህን ክፉ ግንኙነቶች አስወግድ። ዲያብሎስ በእነዚህ ነገሮችና አሳቦች አንተን ለመዋጋት ሊጠቀምባቸው ስለሚችል ቀድመኽው ብልህ ሁን። ይህ ጉዳይ ወደ ሌላ ርዕስ ይመራናል።

+ክፉ ባልንጀርነት።

እንዲህ ያለው ባልንጀርነት ለመንፈሳዊነትህ፣ ለእምነትህና ለሕሊናህ ጎጂ ነው። አልፎ ተርፎም ሕሊናህንና ስሜቶችህን ሊያጠፋ ይችላል።

የእናታችን የሔዋን የመጀመሪያ ውድቀት ያተከተለው ከአባብ ጋር በመሠረተችው ክፉ ባልንጀርነት ምክንያት ነው። ንጉሥ አክአብ የወደቀው በክፉ ሚስቱ በኤልዛቤል ከንቱ ምክር ነው። ጠቢቡ ሰሎሞን የወደቀውም ባገባቸው አንግዳ ሚስቶቹ አማካይነት ነው።

ስለዚህ የአሳቦቻቸውን ተጽዕኖዎች በእናንተ ላይ በቀላሉ ሊያሳድሩ ስለሚችሉ ባልንጀሮቻችሁን በሚገባ እንድትመርጡ ትመከራላችሁ። የትዳር ጓደኛ የሚሆኗችሁንም በጥንቃቄ እንድትመርጡ ትመከራላችሁ። ምክንያቱም እነርሱ መንፈሳዊነታችሁን ሊክብም ሆነ ሊንድ የሚያስችል የአሳብ ተጽዕኖ በእናንተ ውስጥ ማሳደር ስለሚችሉ ነው።

የቅርብ አጋሮች ከጓደኞች ወይም ከወዳጆች ወይም ከባልንጀሮች የበለጠ ጥልቅና አደገኛ ውጤት ሊያስከትሉ ይችላሉ። ከባልንጀሮች ጋር የምትገናኙት አልፎ አልፎ ሲሆን ከቅርብ አጋሮች ጋር የምትኖሩት ግን እስከ መጨረሻው ድረስ ነው። ስለዚህ ከምንም ነገር አንጻር የእግዚአብሔር ሰው የሆነ አጋር መምረጥ የግድ ነው። ልትደሰቱ የሚገባችሁ በውጪያዊው ገጽታ ሳይሆን በውስጣቸው ባለው ጥልቀት ነው። ይህን አስመልክቶ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጻፈው ቃል እንዲህ ይላል፦ «አትሳቱ፤ክፉ ባልንጀርነት መልካሙን አመል ያጠፋዋልና።» (1ኛ ቆሮ 15:33)፤«. . . ለሰውም ቤተ ሰዎቹ ጠላቶች ይሆኑበታል።» (ማቴ 10:36)።

ለዚህ ምሳሌ የሚሆኑን ልጆቻቸው እንዳይጸሙ፣ እግዚአብሔርን እንዳያመልኩ፣ በጉባኤ ላይ እንዳይሰተፉና በቤተ ክርስቲያን እንዳያገለግሉ የሚከለክሉ ወላጆች ናቸው። አልፎ ተርፎም እነዚህ ወላጆች ልጆቻቸው ራሳቸውን እንዲያስጌጡና በተለያዩ ዓለማዊ መዝናኛዎች እንዲሞላቀቁ የሚመክሩ ናቸው። በመሆኑም ይህን የሚመስለው ቤተሰብ ራሱን እንደ አንድ መንፈሳዊ ቤተሰብ የሚመራ ቤተሰብ አይደለም።

ሌላው ምሳሌ በሚስቱ መንፈሳዊነት እያላገጠ እርስዋን ከራሱ ጋር ወደ ቅጣት የሚመራው መንፈሳዊነት የሌለው ባል ነው። አንዲህ ዓይነቱ ባል ሚስቱ በመንፈሳዊነቷ እንዳትቀጥልና በማንኛውም መንፈሳዊ አገልግሎት ውስጥ እንዳትሳተፍ የሚያግድ ባል ነው። ሌላው ሁሉ ቢቀር የምትጸምበትንና ቅዱስ ቁርባን የምትቀበልበትን ዕድል አይሰጣትም። ጌታ ግን እንዲህ ይላል፦ «ከእኔ

ይልቅ አባቱን ወይም እናቱን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባውም. . . » ማቴ 10:37።

አንድ ሰው ራሱን ከቤተሰቦቹ ወይም ከባልንጀሮቹ መለየት ሊያዳግተው ይችል ይሆናል። ይሁን እንጂ እነርሱን ከመውደድ ይልቅ እግዚአብሔርን ሊወድ ለእነርሱ ከመታዘዝም ለእግዚአብሔር ሊታዘዝ ይገባዋል። እምነቱንና መንፈሳዊነቱን ስለ ወዳጆቹ ሲል መሥዋዕት አድርጎ ማቅረብ የለበትም። አንድ ሰው ምንጊዜም ቢሆን «ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር ልንታዘዝ ይገባናል።» (ሐዋ 5:29) የሚለውን የሐዋርያት ቃል ሊያስታውስ ይገባዋል። ከእግዚአብሔር የሚሻል ወይም ከእርሱ ይበልጥ የሚወደድ ማንም ሊኖር አይገባውም። ከዘላለማዊነትህ የሚበልጥ ምንም ዓይነት ጠቃሚ ነገር አይኖርም።.

ይሁን እንጂ ልትርቃቸው የሚገቡ አንዳንድ ዘመዶች ይኖሩሃል። ይህም መራት በአካል መራት ሳይሆን በሥራቸው፣ በንግግራቸውና በማናቸውም የተሳሳቱ ድርጊቶቻቸው ውስጥ ተባባሪ ባለመሆን ሊሆን ይገባዋል። ይህ በዚህ አንዳለ ክፉ አድራጊ ዘመዶቻቸውንም ሆነ ባልንጀሮቻቸውን ስለ ይሉኝታ ብለው የማይርቁ ሰዎች ብዙዎች ናቸው። በመሆኑም ስለ ይሉኝታቸው የክፉ ሥራዎቻቸው ተባባሪ ይሆናሉ።

መንፈሳዊ ሰው ግን ይሉኝታ ወሰን እንዳለው ያውቃል። ከዚህ በተጨማሪ ከእነዚህ ጥቃቶችና ምክንያቶቻቸው ለመራቅ ጠበቅ ያለ አቋምና ብርቱ ሰብእና ሊኖር ያስፈልጋል።

«ስለ መንገዱ ከመጠየቅህ በፊት ስለ ጓደኛህ ጠይቅ!» የሚለው አባባል ትክክለኛ ነው። ምክንያቱም አንዳንዶቹ ወዳጆችህ ነፍስህን ሊያጠፋ የሚችል መጥፎ ተጽዕኖ ሊያሳድሩ ስለሚችሉ ነው። እነዚህ ሰዎች ለልብህና ለአዕምሮህ አንግዳ የሆኑ መመሪያዎችንና አሳቦችን በማስተዋወቅ ሕይወትህን ከትክክለኛው መንገድ ያስወጣታል።

የአንተ እውነተኛ ጓደኛ ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርብህ መሆኑን አወቅ። እውነተኛ ጓደኛህ መልካም ዝናህን የሚጠብቅና ስለ ድኅንነትህ የሚያስብ ጻድቅና ልባም ሊሆን ይገባዋል። በመቀጠል ሌላኛውን መንፈሳዊ ውጊያ እንመለከታለን።

ጥቃት።

መሰናክል በውጪ የሚገለጥና ለውድቀት የሚዳርጉ የኃጢአት አሳቦችን፣ ድርጊቶችንና ምኞቶችን የሚያስተዋውቅ ነው። መሰናክል ከመስማት፣ ከማየት፣ ከማንበብና ከሌሎች ስሜቶች ሊመጣ ይችላል። አንተ ለሌሎች መሰናክል ከመሆን ይልቅ መሰናክልን በምትችለው መጠን ከአንተ ዘንድ ማስወገድ ይገባሃል።

መሰናክሎች በእኛ ላይ ተጽዕኖ ማሳደር ይችላሉ። ወይም እኛ ስለምንናፋቃቸው እንፈልጋቸዋለን። በእኛ ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩት ውጪያዊ ውጊያዎች ሲሆኑ በናፍቆት የምንፈልጋቸው ደግሞ ውጪያዊ ደስታን የሚፈልጉ ውስጣዊ ውጊያዎች ናቸው። በዚህኛው ውጊያ ውስጥ ውስጣዊና ውጪያዊ

ውጊያዎች ይገናኛሉ። ይህ ተጽዕኖ ከባድ ስለሚሆንም ከእርሱ ማምለጥ ይበልጥ ከባድ ነው።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከእነዚህ መሰናክሎች እንድንርቅ በመለከታዊው ትእዛዙ እንዲህ ብሎናል። «ቀኝ ዐይንህም ብታሰናክልህ አውጥተህ ከአንተ ጣላት . . . ቀኝ እጅህም ብታሰናክልህ ቆርጠህ ከአንተ ጣላት . . . » ማቴ 5:29። በዚህ የጌታ ትእዛዝ ውስጥ ቀኝ ዐይን ተብሎ በምሳሌ የተጠቀሰው ለእኛ የቅርብ ወዳጆች በሆኑት ሰዎች ሲመሰል ቀኝ እጅ የተባለው ደግሞ እኛን አብዝተው በሚረዱን ሰዎች እንደሚመሰል አባቶቻችን ተርጉመውልናል።

ስለሆነም ከእነዚህ ክፉ ሰዎች ጋር ግንኙነት መፍጠር የሰውን ዘላለማዊነት ያሳጣል። ከዚህ በተጨማሪ ሰው ሊቋቋማቸው የሚችላቸውንም ሆነ የማይችላቸውን ውጪያዊ ውጊያዎች ሊያመጡበት ስለሚችሉ ከእነዚህ የቅርብ ሰዎችና ተወዳጆች ሊርቅ ያስፈልገዋል። ዋጋው ምንም ይሁን ምን ዋናው ቁም ነገር ከውጪያዊ ውጊያዎች መራቅ ነው።

በየዕለቱ «. . . ክክፉ አድነን እንጂ ወደ ፈተና አታግባን» (ማቴ 6:12) እያልህ እየጸለይህ በገዛ ፈቃድህ በእነርሱ አትውደቅ። የእሳት እራት በእሳት ተቃጥላ እስክትጠፋ ድረስ በእሳቱ ዙሪያ እንደምታንገበገብ ሁሉ ሰው በዙሪያቸው እንዲዞር የሚስቡ አንዳንድ መሰናክሎች አሉ። አንድ የእሳት እራት ከእርሱ አስቀድመው ብዙ የእሳት እራቶች በእሳት ተቃጥለው እንደ ጠፉ ቢመለከትም እርሱም እንደ ሌሎቹ ተቃጥሎ እስኪጠፋ ድረስ አርፎ አይቀመጥም።

አንድ ሰው መሰናክል ሆኖ ከጣለህ በኋላ እርሱ ያመልጣል። አንተ ግን ትቀጣለህ። አንተ ንስሓ ለመግባት ብትቸገርም እርሱ ግን ንስሓ ሊገባ ይችላል። ስለዚህ ባለህ ኃይልና በውስጥህ ባለው የእግዚአብሔር ጸጋ አሠራር ከመሰናክሎች ራቅ! ይህን በማድረግህም በሚቻልህ ሁሉ ውጪያዊ ውጊያዎችን ታስወግዳለህ።

አንዳንድ ንባቦችም የመሰናክልና የውጪያዊ ውጊያ መገኛዎች ናቸው። ንባብ የሰውን አሳብና ስሜት ከማቃወሱና የእርሱን መመሪያዎች ከመትከሉም በላይ የአንባቢውን ሕይወት ይመራል። ከዚህ በተጨማሪ በግልጽ ስህተት የሆኑና ስለ እነርሱ ማንንም ሳታማክር ልታስወግዳቸው የሚገቡህ የንባብ ዓይነቶች አሉ። አንዳንዶቹ ንባቦች ጥርጥርንና ግራ መጋባትን ሊያመጡ አንዳንዶቹ ደግሞ የተሳሰቱ ስሜቶችንና ምኞቶችን ያመጣሉ።

መንፈሳዊ ሰው ከጎጂ ንባባት መራቁ ብቻ በቂ አይደለም። ይልቁኑ ለእግዚአብሔር ያለውን ፍቅር ጥልቅ ሊያደርጉለት የሚችሉ ንባባትን ማንበብ አለበት። ይህ ደግሞ ከውጪ የሚመጡ ውጊያዎችን ለመከላከል ሁነኛ መፍትሔ ነው። አንድ ሰው በእውቀት ፍቅር ቢወጋ ሁሉም እውቀት ጥቅም እንደሌለው ማወቅ ይገባዋል። አንዳንዱ እውቀት የዋህነቱን ወይም ንጽሕናውን በመለወጥ ለቁሳት ትኩረት እንዲሰጥ ያደርገዋል። ስለሆነም ማንኛውም መንፈሳዊ ሰው ውጊያዎችን ሊያስወግዱ የሚችሉ ጽሑፎችን መርጦ ሊያነብ ይገባዋል።

አካባቢ።

በዚህ ርዕስ ሥር የሰውን አጠቃላይ ሁኔታ እንመለከታለን። ይህም ሰው በሚኖርበት አካባቢ ውስጥ ያለውን አሳብ፣ ልማዱን፣ የኑሮ ሁኔታውን፣ ብዛት ያላቸው መመሪያዎቹን፣ የሚደራደርበትን ሥርዓት፣ በሁሉም ወይም በብዙኃኑ ዘንድ ያለውን ጽንሰ አሳብ ያጠቃልላል።

ይህን በመሰለ አካባቢ ውስጥ ሰው መንፈሳዊ መመሪያዎቹን ሊረዱለት ከማይችሉ ሰዎች ጋር አንግዳ ሆኖ መኖር ለእርሱ በጣም አስቸጋሪ ይሆንበታል። በመሆኑም በዚህ አካባቢ የሚኖር ይህ እውነተኛ ሰው በየዕለቱ ጻድቅ ነፍሱን እያስጨነቀ ይኖራል። 2ኛ ጴጥ 2:8። ከመንፈሳዊው የሕይወት ጎዳና ሳልወጣ እኖራለሁ ብሎ ቢምክርም እንኳ ታላቅ ጥረት እንዲያደርግ ይጠበቅበታል። መንፈሳዊ መንገዴን አጠብቃለሁ ብሎ ከተነሣም ብዛት ላላቸው ውጊያዎች የተጋለጠ ይሆናል። አካባቢውን መለወጥ ከቻለ ይህ የተሻለ ነገር ነው። ካልቻለ ግን ውጊያውን መቋቋም፣ መቃወምና ድል መንሣት አለበት። እግዚአብሔርም ይህን የፍቅር ጥሪቱን አይዘነጋም።

ሕይወታችን ለእውነት መወሰኩር ይገባዋል። ይህንንም በእንደበታችን ብቻ ሳይሆን በተግባራዊ ሕይወታችን ውስጥም ልንመሰክር ይገባናል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «. . . ይህን ዓለም አትምሰሉ።» (ሮሜ 12:2) በማለት መክሮናል። መንፈሳዊ ሕይወት ትግልን፣ ትዕግሥትንና ጽናትን ይፈልጋል።

አንድ ሰው በትግሉ ውስጥ የሚታገለው ብቻውን አይደለም። ሊዋጋም በእግዚአብሔር ጸጋ እየታገዘ እንደሚዋጋ እርግጠኛ መሆን አለበት። በመሆኑም «እስከ መጨረሻ የሚጸና ግን እርሱ ይድናል።» (ማቴ 10:22።) የሚለው ቃል በሕይወቱ ውስጥ ይተረጎማል።

መንፈሳዊ ውጊያዎች ብዛት ስላላቸው ታግለን ድል ልንነሣቸው ይገባናል። ኢየሱስ ክርስቶስ ተዋግተው ድል ለሚነሱት የሚሰጣቸው ስጦታዎች ምንኛ የበዙ ናቸው! ራእይ 2 እና 3።

ስለዚህ በፍርድ ቀን ጻድቅ ፈራጅ የሆነው ጌታ ታግለው ድል ለነሡት የሕይወት አክሊል ሲሰጥ ያለ ዋጋ እንዳትቀር ዛሬ ከእነርሱ ጋር ለመሰለፍ አጥብቀህ ታገል! 2ኛ ጢሞ 4:8። ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለእያንዳንዱ እንደ ራሱ ድካም መጠን ዋጋውን ይከፍለዋል። 1ኛ ቆሮ 3:8።

ምዕራፍ ሁለት።

የራስ ውጊያ።

- የራስነት (የእኔነት) አደገኛነት።
- ራስና ኃጢአት።
- የተሳሳተ ራስ ወዳድነት።
- ጥንታዊ ውጊያ ነው።
- ራስ ወዳድነት ከእግዚአብሔርና ከንስሓ አባት ጋር ይቃረናል።
- ራስን ማግነን።
- ራስን የማምለክ ውጤት።
- የተሳሳተ ራስን ማስደሰት።
- መስጠትና ማንነት።
- በድርድር ውስጥ ያሉ የራስ ስህተቶች።
- ራስን መካድና ራስን መሥዋዕት ማድረግ።
- ራሱን ያጠፋል።
- ደስታን መርሳትና ራስን ድል መንሣት።
- ማንነት በአገልግሎት መስክ ውስጥ።
- ሁለተኛው ምዕራፍና ዝቅተኛው ሥፍራ።
- ራስን መንቀፍ።

የራስ (የእኔነት) አደገኛነት።

ራስነት (እኔነት) የሰው ልጆችን የሚዋጋ ጥንታዊና በጣም አደገኛ ጠላት ነው። አንተ ከራስህ ጋር ከምታደርገው ውጊያ ጋር የሚነጻጸር ውጊያ ዲያብሎስ አያውጅብህም። ትልቁ ችግርህ እኔነት ነው። ራሱን ከውስጥ የሚያሸንፍ ሰው ዓለሙንና ዲያብሎስን ማሸነፍ ይችላል። በራሱ የሚሸነፍና በራሱ ፊት በድካም የሚቆም ከሆነ ግን በማንኛውም ዓይነት ኃጢአት ይወድቃል።

በዓለሙ ውስጥ ያለውን ኃጢአት ከኋላ አንሥተን ብንመረምር እኔነትን በሁሉም የኃጢአት ዓይነቶች ውስጥ እናገኘዋለን። በመሆኑም በውስጡ ያለውን እኔነት ማሸነፍ የሚችል ሰው በማንኛውም መንፈሳዊ ውጊያ ውስጥ ድል አድራጊ ነው። እንዲህ ዓይነቱ ሰው ራሱን እስከከዳና መዝጊያዎቹን ለጠላቶቹ እስካልከፈተ ድረስ ስለ ማንኛውም ውጪያዊ ጠላት ግድ አይሰጠውም። ይህን አስመልክቶ ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ የተናገራቸው ቃላት ምንኛ ድንቅ ናቸው። «ሰው ራሱን ካልጎዳ በስተቀር ማንም ሊጎዳው አይችልም።» ነው ያለው።

ዋናው ጉዳት የእግዚአብሔርን መንግሥትና ውስጣዊ ሰላምን ማጣት ሲሆን አንተ ውስጥህ ብርቱ እስከ ሆነ ድረስ ሁለቱም ወደ አንተ ከውጪ ሊመጡ አይችሉም። እዚህ ላይ አንድ ሰው «ጥቃት ከውጪ አይመጣም? ለምሳሌ፡- ፈተና፣ ምኞት . . . ወይም ሌሎች ውጪያዊ ጥቃቶች አይደሉምን?» ብሎ ሊጠይቅ ይችላል።

የዚህ መልሱ ውጪያዊ ድብደባዎች ወይም ጥቃቶች ወደ አንተ ሊመጡ ቢችሉም በአንተ ላይ ምንም ዓይነት ሥልጣን አይኖራቸውም። በአንተ ላይ

ለመወሰን ኃይልና ሥልጣን ያለው ፈቃድህ ብቻ ነው። ጥቃትን ወይም ፈተናን ትቀበላለህ ወይስ አትቀበልም? ውጪያዊ ውጊያንስ ትቀበላለህ ወይስ አትቀበልም?

ጻድቁ ዮሴፍ እጅግ ከባድ የሆነ ውጪያዊ ውጊያ ከጲጥፋራ ሚስት ቢገጥመውም አልወደቀም። እርሱ ኃጢአትን በልቡ ውስጥ ሰላልተቀበለው ፈተናውንም አልተቀበለውም። ስለሆነም ጥቃቱን ሊቋቋም ችሏል። ዲያብሎስ አሳቦችን ያቀርብልሃል እንጂ ተቀብለህ ተግባራዊ እንድታደርጋቸው አያስገድድህም።

ራስና ኃጢአት።

በዚህ መሠረት በኃጢአት መውደቅ የሚመጣው ከራስ እንጂ ውድቀት ሊያመጡ በሚችሉ ቀላል ፈተናዎች ምክንያት አይደለም። በእርግጥ እንደዚህ ዓይነቶቹን ፈተናዎች ያለ ማቋረጥ ለረዥም ጊዜ መቋቋም በውስጥ ያለ ራስን ሊያዝል ስለሚችል ሰውየው እጹን ሊሰጥ በመጨረሻም ሥ[illegible]ላል።

እዚህ ላይ የራስ ድክመት ቀጥተኛ ምክንያት ሲሆን ጥቃቶች ደግሞ ቀጥተኛ ያልሆኑ ምክንያቶች ናቸው። ስለሆነም በውስጥ ያለው ብርቱ ራስ (ማንነት) ከውጪያዊ ጥቃቶች ሊርቅ ስለሚችል በእነዚህ ፈተናዎች ሊጠቃ ወይም በእነርሱ ፊት የደከመ ሊሆን አይችልም። ይህን አስመልክቶም የመጀመሪያው የዳዊት መዝሙር በኃጢአተኞች ምክር እንዳንሄድና በዋዘኞች ወንበር እንዳንቀመጥ አስጠንቅቆናል። ቅዱስ ጳውሎስም «ከክፉ የጎልማሳነት ምክር ሽሽ . . . » (2ኛ ጢሞ 2:22) በማለት መክሮናል። እዚህ ላይ ሽሽት የሚለው ቃል የሚገልጥልን ውጪያዊ የኃጢአት ተጽዕኖዎችን የማይቀበለውን ንጹሕ ራስን ነው።

በዚህ መሠረት ጻድቁ ዮሴፍ የሸሸው ከድካም ሳይሆን ብርቱ ስለ ነበር ነው። ይህም መልካም ነው። የእርሱ ሽሽት ኃጢአትን መቃወሙንና ከእርሱም መራቁን ያረጋጋጠ ኃይሉ ነው።

ንጹሕ ማንነት እንኳንስ ተራ የውጪ ጥቃትን ቀርቶ የኃጢአት አሳቦችን እንኳ ይቃወማል። እንዲህ ካለው አሳብ ጋር ሙግት አይፈጥርም። ይህ አሳብ በሕሊና ውስጥ ተደላድሎ በመቀመጥ ወደ ራስ ድክመት እንዲያመራ ዕድሉን ካለመስጠቱም በላይ በአፋጣኝ ያስወጣዋል። እዚህ ላይ የሕሊናንና የልብን መዝጊያዎች ከዲያብሎስ በሚቀርቡ የኃጢአት አሳቦች ላይ ጥርቅም አድርጎ ስለሚዘጋ ራስ ብርቱ ነው።

መዝሙረኛው ዳዊት እንዲህ ይላል፦ «ኢየሩሳሌም ሆይ እግዚአብሔርን አመስግኚ፣ጽዮንም ሆይ ለአምላክሽ አልል በይ፣ የደጆችሽን መወርወሪያ አጽንቶአልና፣ ልጆችሽንም በውስጥሽ ባርኮአልና።» መዝ 147:1-2። የሰሎሞንም መዝሙር «እጎቴ ሙሽራ የተቆለፈ ገነት፣ የተዘጋ ምንጭ፣ የታተመም ፈሳሽ ናት።» (መኃ 4:12) በማለት ማንነትን ይባርካል።

«ወፎች ከራስህ በላይ እንዳይበሩ ልትከለክላቸው ባትችልም በፀጉርህ ላይ ጎጆዎቻቸውን እንዳይሠሩ ግን ልትከለክላቸው ትችላለህ።» የሚለው አባባል ምንኛ እውነት ነው። አሳቦች ወደ አንተ መምጣታቸው እርግጥ ነው። ይሁን እንጂ የአንተ አቋም ምንድር ነው? አንተነትህስ ሰምን ያህሉ ታዟል ምን ያህሉንስ ተቃውሟል?

አንድ ቀን ከሆነ ሰው የሚያጓጉ ቃላትን ልትሰማ ትችላለህ። በዚህ ጊዜ የአንተ ምላሽ ምን ይመስላል? በዚህ ትነሣሣለህ ወይስ ጉጉትህን ትቋቋማለህ? ቃላቱ ሌሎችን ሊያነሣሡ ቢችሉም አንተን ሊያነሣሡህ ስለማይችሉ በእርጋታ፣ በጥሞናና በጥበብ መልስ ልትሰጥባቸው ይገባሃል።

እዚህ ላይ ማንነት ከንጽሕናው፣ ከኃይሉና ከጽናቱ አንጻር በጉጉት ፊት ይመዘናል። ሰው በኃጢአት ሲወድቅ የሆነው ሁሉ ከውጪ በመጣ ውጊያ ነው ብሎ መደምደም አይቻልም። በራስ ውስጥ በተገለጠ የውስጥ ውጊያ ሞምር እንጂ። እኛነታችን እግዚአብሔርን ከክዳና በውጪ ላሉ ጠላቶች (ለእግዚአብሔርና ለራሱ ጠላቶች) መዝጊያውን ከከፈተ በኃላፊነቱ ላይ ልንደራደር አንችልም።

እዚህ ላይ አንድ ጥያቄ ልንጠይቅ እንችላለን። ይኸውም፦ «አንተነትህ ለራስህ ወዳጅ ነው ወይስ ጠላት? የአንተ አጋር ነው ወይስ ተቃዋሚ?» ቅዱስ ይስሐቅ የተናገረው አባባል እዚህ ላይ ሊጠቀስ ይችላል። «አንተ ከራስህ ጋር ከታረቅህ ሰማይና ምድር ከአንተ ጋር ይታረቃሉ።» ይህም ማለት አንተ ከሥጋህ፣ ከሕሊናህና ከነፍስህ ጋር የምትታረቅ ከሆነ ሦስቱም በአንድ መንገድ ይኸውም በመንፈሳዊው መንገድ ሊጓዙ ይችላሉ ማለት ነው። በዚህ ጊዜ መንፈስ በሥጋ ላይ ሥጋም በመንፈስ ላይ ሊቀዋወሙ ስለማይችሉ ሰማይና ምድር ከአንተ ጋር ይታረቃሉ ማለት ነው። በዚህ አካሄድም በእግዚአብሔር፣ በሰዎችና በራስህ ላይ ኃጢአት አትሠራም ማለት ነው።

አንድ ሰው ራሱን እንደሚወድ፣ ራሱም እርሱን እንደሚወደውና ሁልጊዜ እንደሚያስደስተው ሊናገር ይችል ይሆናል። እዚህ ላይ ወደ አንድ ጠቃሚ ነጥብ እንሸጋገራለን . . .

የተሳሳተ ራስ ወዳድነት።

ራስ ወዳድነት ማለት ምን ማለት ነው? ይህ ሲባል ራስን እየተንከባከቡ የሚያስፈልገውንና የሚመኘውን ሁሉ ማቅረብ ማለት ነው? ወይስ ራስን ማወደስ፣ ራስን ማክበርና ለራስ ውለታ መዋል ማለት ነው?

ለራስህ እነዚህንና ሌሎችን ነገሮች የምታደርግ ከሆነ ለማንነትህ ያለህ መውደድ የተሳሳተ ራስ ወዳድነት ነው። እውነተኛው ራስ ወዳድነት ራስን በመንፈሳዊ መንገድ መምራት፣ ራስን ከእግዚአብሔር ፍቅር ጋር አንድ ማድረግና ወደ መንግሥቱ መምራት ነው። አንተነትህ ጥፋት ሲሠራ ማጣራት፣ ሲሳሳት መቅጣት፣ የኃጢአት ምኞቶቹን መቃወምና ጠባዩን ማረም እውነተኛ ራስ ወዳድነት ነው።

ይሁን እንጂ የሥጋ ወይም የስሜት ወይም የዓለም ደስታና ምኞት አስፈላጊ ባይሆኑም አንዳንድ ጊዜ ራስ እነዚህን ነገሮች ይመኛል። እዚህ ላይ የምትወጋው በራስህ ነው። ስለሆነም ይህን ውጊያ ባለህ አቅም ሁሉ እየተቃወምህ ጌታ በወንጌሉ የተናገረውን ቃል ዘወትር አስታውስ፦ «. . . በኋላዬ ሊመጣ የሚወድ ቢኖር ራሱን ይካድ መስቀሉንም ዕለት ዕለት ተሸክሞ ይከተለኝ።» ሉቃ 9:23።

ምንም እንኳ ይህ አባባል መስቀሉን ዕለት ዕለት ተሸክሞ የሚከተል ሰው እንደሚያስፈልግ ቢገልጽልንም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከእርሱ ጋር ለመኖር ራስን መካድ ዋናው የቅድስና ሕይወት እንደ ሆነ ሳይገልጽልን አላለፈም። ይህ መስቀል ደግሞ የተሳሳተ ራስ መውደድን ይቃወማል ያሸንፋልም።

የተሳሳተ ራስ መውደድ ያላቸው ሰዎች ብዙ ናቸው። ከተሳሳተ ራስ መውደድ አሠራሮች መካከል አንዱ ራስን ማግነን ነው።

ራስን ማግነን።

አንድ ሰው ራሱን ሁልጊዜ ታላቅና ድንቅ ለማድረግ ይወዳል። ይህን ለማሳካት ሲል የተሳሳተ መንገድ ይከተላል። አንድ ሰው ራሱን ታላቅ ሊያደርግ የሚፈልገው ከውስጥ ሳይሆን ከውጪ ነው። በውጪ የሚገለጡት የታላቅነት ገጽታዎችም ሥልጣንና ማዕረግ፣ ሀብትና ዝና ወይም የሰዎች ውዳሴ ናቸው። እነዚህ ሁሉ ጉዳዮች ከራስ ተፈጥሮና ከንጽሕና ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የላቸውም። እንዲያውም ይህ አጉልቶ የሚያሳየው አለማወቅንና አለመረዳትን ነው። ከዚህ ተቃራኒ በሆነ መንገድ መዝሙረ ዳዊት የሚነግረን ምንም እንኳ ልብስዋ የወርቅ መጎናጸፊያ ቢሆንም ክብሯ እንደ ሆነ ነው። «ለሐሌቦን ንጉሥ ልጅ ሁሉ ክብርዋ ነው።» መዝ 44:13።

ታዲያ ሰው ሁሉ በእርግጥ የሚፈልገውና በውስጥ ሊኖር የሚገባው ታላቅ መንፈሳዊ ክብር ምንድር ነው? ውስጣዊው ክብር ሰው ከተፈጠረ በኋላ በውስጡ የሚያስቀረው እግዚአብሔርን የመምሰል ገጽታ ነው። ዘፍ 1:26-25። የራስ ውስጣዊ ክብር የመንፈስ ፍሬዎች በተባሉት በፍቅር፣ በደስታ፣ በሰላም፣ በትዕግሥት፣ በቸርነት . . . ወዘተ ሊታጀብ ያስፈልጋል። ገላ 5:22። ንጽሕና፣ ቅድስና፣ በነገር ሁሉ አለመወቀስ፣ ትሕትና፣ መስከን፣ ርኅራኄና ብልህ መሆን እውነተኛ ክብር ናቸው። ራሱን በእነዚህ ቅድስናዎች የሚያለማምድ ሰው በእርግጥም በመንፈሳዊነት ራሱን ይወዳል።

የሰዎችን ክብርና አድናቆት ሳያገኝ ራሱን በውዳሴና በሙገሳ ከፍ ከፍ ለሚያደርግ ሰው ይህ ሁሉ ውጪያዊ ገጽታ ስለሆነ መንፈሳዊው ሰው ከዚያ በላይ ከፍ ከፍ ሊል ይገባዋል። ራስ በሌሎች ሲወደስ ምን ዓይነት ጥቅም ሊያገኝ ይችላል? ከዘላለማዊነት ጋር ሲነጻጸር እንዲህ ያለው ውዳሴ ምን ዋጋ ሊኖረው

ይችላል? ውጪያዊ ክብር ራስን ለማግነን መንፈሳዊ መንገድ ነው? ወይስ ብዙዎች የሚወድቁት መንፈሳዊ ውጊያ ነው?

ራስን ማምለክ ወይም ራስን ማድነቅ የዚህ ውጊያ ገጽታ ነው። በዚህ ረገድ አንድ ሰው ራሱን በፊቱና በሰዎች ፊት እንክን ወይም ጉድለት የሌለው ውብ አድርጎ ሊመለከት ይችላል። የእርሱን ማንነት ምንም ዓይነት ስህተት የማይሠራና የማይወድቅ አድርጎ ሊያምን ይጀምራል። እንዲህ ዓይነቱ ሰው ሁልጊዜ በመስተዋት ፊት ሲቆም የራሱን ጥሩ ጎን ሊመለከት የሚወድ ራሱን አድናቂ ሰው ነው። እንዲህ ዓይነቱ ሰው ምንም ቀላል ቢሆኑም በእርሱ ላይ የሚሰነዘሩ ስድቦችን፣ ሂሶችንና ግልጽ የሆኑ አሳቦችን ሊቀበል አይወድም።

እርሱ በሰዎች ሁሉ ፊት ውብና ድንቅ ሆኖ ለመቆየት ስለሚወድ እነዚህ ሁሉ ምስሉን የሚያጠፉበት መስለው ይታዩታል። ይህ ሰው በእርሱ ላይ የሚሰነዘሩ ግልጽ የሆኑ አስተያየቶችን ወይም ሂሶችን ስለማይቀበልና ከነ ጥፋቶቹ ስለሚቆይ ዐመሉን አያርምም ያለበትን ደረጃም አያስተካክልም። በመሆኑም ራስ ወዳድነቱ ከውስጥ ንጽሕና አርቆ ይመራዋል።

በዚህ መሠረት ራስ ወዳድነት ከዚህ አንጻር ሲታይ እውነተኛ ፍቅር ስላልሆነ አደጋን በማቀናጀት የአንድን ሰው የዘላለም ሕይወት ይፈታተናል። ይህ ለራስ ዝና የሆነ ተራ ፍቅር ነው። ገጽታውም የሚታየው ለሰዎች ፊት እንጂ ለዘላለማዊነትና ለንጽሕና አይደለም። በፍቅረ ውዳሴ ራስን የማግነን ሙከራ ብዙዎች የወደቁበት ውጊያ ነው።

ውዳሴን የሚሻ ሰው በሰዎች ስለ ተወደሰ አይረካም። ስለሆነም ስለ ራሱ ብዙ ማውራቱን በመቀጠል ራሱን በሰው ፊት ሊያወድስ ይጀምራል ማለት ነው። ስለ ራሱ በማውራቱ መልካም አያደርግም። ስለ ራሱም እውነት የሆነውን ነገር ሁሉ አይናገርም። የሚናገረው ስለ መልካም ጎኑ፣ ስለ ማሸነፉና ስለ ክብሩ ነው። ይህን በማድረጉም ጉድለቶቹን ይሸሽጋል። እነዚህ ጉድለቶቹን አንድ ሰው ከገለጠበት በተቃራኒው ቆሞ ምክንያት በመደርደር ራሱን ሊከላከል ይሞክራል።

ጥንታዊ ውጊያ ነው።

ይህ ውጊያ ዲያብሎስ ከመጀመሪያ ወላጆቻችን ጋር «. . . እንደ እግዚአብሔር መልካምንና ክፉን የምታውቁ እንድትሆኑ እግዚአብሔር ስለሚያውቅ ነው . . .» (ዘፍ 3:5) በማለት የተጋጠመበት ውጊያ ነው።

ሰው ራሱን ከፍ ከፍ ሊያደርግ ውጊያ ይገጥመዋል። ዲያብሎስም በዚሁ ተመሳሳይ ፈተና ወድቋል። ስለሆነም መለኮታዊው ቃል እንዲህ በማለት ተናግሮታል፦ «አንተም በልብህ፦ ወደ ሰማይ ዐርጋለሁ፣ ዙፋኔንም ከሰማይ ከዋክብት በላይ ከፍ ከፍ አደርጋለሁ፣ . . . በልዑልም እመሰላለሁ አልህ።» ኢሳ 14:13-14። «ዐርጋለሁ»፣ «በላይ»፣ «ከፍ ከፍ» የሚሉት ተደጋጋሚ ቃላት የሚያመለክቱን ራስን የሚያስታብዩ መሆናቸውን ነው። ራስን ከፍ ከፍ ማድረግ «በልዑልም እመሰላለሁ» አስከ ማለት የሚያደርስ ነው።

እንዲህ ካለው ትዕቢት ወይም ውድቀት የሚበልጥ ምን አደጋ ሊኖር ይችላል? ንጉሥ ሄሮድስ በዚህ ውጊያ ተወግቷል። በመሆኑም የእግዚአብሔር መልአክ ስለ መታው በትል ተበልቶ ሞቷል ሰዲያብሉስም ተሰዋቷል። ሐዋ 12:22-23።

ራስን ከፍ ከፍ የማድረግ ሁኔታ ከተገለጡባቸው መንገዶች መካከል ራስን ማጽደቅ አንዱ ነው። ይህ ደግሞ በመጽሐፈ ኢዮብ ውስጥ ተገልጧል:- «ኢዮብም ራሱን ጻድቅ አድርጎ ነበርና እነዚያ ሦስቱ ሰዎች መመለስን ተዉ።» ኢዮ 32:1። ኤሊሁም በዚህ ምክንያት ኢዮብን ገሥጾታል:- «ወይስ በእግዚአብሔር ፊት እኔ ጻድቅ ነኝ ትላለህ?» ኢዮ 35:1።

በጥንት ጊዜ ትዕቢት የተገለጠበት ሌላው መንገድ የባቢሎን ግንብ ነው። ታሪኩ እንደሚነግረን ሕዝቡ እንዲህ ብለው ነበር:- «. . . ኑ ለእኛ ከተማና ራሱ ወደ ሰማይ የሚደርስ ግንብ እንሥራ፤በምድር ላይ ሳንበተንም ስማችንን እናስጠራው . . .» ዘፍ 11:4። እግዚአብሔር ግን የእነዚህን ሰዎች ትዕቢት ቀጥቷል። ቋንቋቸውን በመደበላለቅ በምድር ላይ ሁሉ እንዲበታተኑ አድርጓቸዋል። ይህ ደግሞ ወደ ሌላ ርዕስ ይመራናል . . .

ራስ ወዳድነት ከእግዚአብሔር ጋር ይቃረናል።

ሰው በራሱ ሲታመን ወደ አደገኛ ድርጊት ይሸጋገራል። ይህም ከእግዚአብሔር ተለይቶ ራስን ነጻ ማውጣት ነው። ስለሆነም በራሱ ይመራል ይህንንም መልካም አድርጎ ይመለከተዋል። በመሆኑም እግዚአብሔርን አያማክርም። «እኔ ካወቅሁት ከእግዚአብሔር እውቀትም ሆነ እርዳታ ለምን ያስፈልገኛል?» ብሎ ይናገራል። ስለሆነም በራሱ የተማመነ ሰው የተሸናፊነትን (በእግዚአብሔር) ሕይወት ለመምራት በጣም ይቸገራል።

የተሸናፊነት ሕይወት የአንድን ሰው አመለካከት ብቻ የሚይዝ ልብ የለውም። ስለሆነም ከራስ ጋር ከሚደረግ ውጊያ ጋር ሙሉ ለሙሉ ይቃረናል። እዚህ ላይ የምናስታውሰው በወቅቱ ከእግዚአብሔር ኮብልሎ የሄደውን የነቢዩ ዮናስን ስህተት ነው። እርሱ በዚያ ወቅት የተከተለው ከእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር የሚቃወመውን የተሳሳተ ፈቃዱን ነበር። እግዚአብሔር ነነዌን ሊምር ይህ ዮናስን ስላላስደሰተው በጣም ተቆጥቶ ነበር። በዚህ ምክንያት እግዚአብሔር እንዲህ በማለት ተናገረው:- «. . . በውኑ ትቆጣ ዘንድ ይገባሃልን?» ዮና 4:4።

ሰው በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ ገብቶ እስከ ሞት ድረስ ማማረሩ በእውነት አሳዛኝ ነው። ይህ ግን ራስ ወዳድነት ነው!!! ሌላው ቢቀር ዮናስን የሚያህል ታላቅ ነቢይ እንኳ በራስ ወዳድነት ተፈትኗል።

በራስ ዙሪያ ካሉት የችግር ደረጃዎች መካከል ለእግዚአብሔር ሙሉ እምቢተኝነት ማሳየት አንዱ ነው። እንዳስፈለገን እንኖራለን የሚሉ ሰዎች ይህን ታላቅ ስህተት አስቀምጠዋል። ስለ ምኞታቸው ሲሉ የእግዚአብሔር ሕልውና በእነርሱ የሕልውና መንገድ ላይ እንደ ቆመ አድርገው ያስባሉ።

የእግዚአብሔር ፍቅር የደስታ፣ የፈንጠዝያና የሙሉ ነጻነት ሕይወታቸውን የሚያውክ፤ የፍላጎታቸውንና የራስ ማረጋገጫቸውንም የሚቃወም አድርገው ያስባሉ። ምንም እንኳ መልካም አሳብን፣ ግብረገብነትንና ከሁሉ በላይ የሆነውን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ የሚቃወም ቢሆንም ሊያደርጉ የሚወዱትን ነገር ሁሉ ያደርጋሉ።

በራስ የሚገኝ የተሟላ ነጻነት በራስ ላይ የሚከፈት ውጊያ ከመሆኑም በላይ የሚያነጣጥረው Nihilism (ጥሩ ነገር የለም) ብሎ የሚያምነው እምነት ላይ ሲሆን ፍጻሜው የሚጠቃለለውም (Atheism) (እግዚአብሔር የለም) በሚለው እምነት ላይ ይሆናል። በተለያየ መንገድ ቢሆንም ግባቸው ተመሳሳይ ስለሚሆን አንዳንድ ሰዎች በዚህ እምነት ውስጥ ስለሚገኙ በዚህ ሊጸጸቱ ይገባቸዋል።

እነዚህ ሰዎች ትምህርተ ሃይማኖትን አስመልክተው ለራሳቸው ከገደብ ያለፈ ነጻነት ያወጁ የሥነ መለኮት ምሁራን ናቸው። ማንኛውም ዓይነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት በእነርሱ ዘንድ ተቀባይነት የለውም። ይቃወሙታል ወይም እንደ ተረት ይቆጥሩታል። አንዳንድ ጊዜ ግን እነዚህን የእምነት ቃላት ለእነርሱ እንደሚስማሙ አድርገው ይተረጉሟቸዋል። የኖኅ መርከብ ታሪክ በእነርሱ ሕሊና ውስጥ ተቀባይነት ስለሌለው በእነርሱ ዘንድ ተራ አፈ ታሪክ ነው።

በሌሎች ዓይነት ሰዎች ውስጥ ያለው ማንነት ደግሞ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ቢቃወምም ቀደም ብሎን ከተመለከትነው ተቃውሞ ቀለል ያለ ነው። ለዚህ ምሳሌ የሚሆኑን ሰዎች ስለ ራሳቸው ሲሉ የእግዚአብሔርን ቀን (ሰንበትን) የማያከብሩ ሰዎች ናቸው። ሌሎቹ ደግሞ ስለ ራሳቸውና ስለ ወጪያቸው ሲሉ አሥራት የማያወጡት ናቸው። እንደነዚህ ዓይነቶቹ እኔነታቸው ከእግዚአብሔር ጋር የሚቃወመው ስለ ጠባይ እንጂ ስለ እምነት አይደለም።

ራስ ወዳድነት ከንስሓ አባት ጋር ይቃረናል።

በራሱ አተማመናሰሁ የሚል ሰው የነፍስ አባትን የሚመለከተው አቅልሎ ነው። እርሱ ሁሉንም ነገር እንደሚያውቅና ስሁሉም ችግሮች መፍትሔ አንዳለው አድርጎ ስለሚያስብ የንስሓ አባቱን መመሪያ አይቀበልም። ለእርሱ የተሻለ የሆነውን ስለሚያውቅና በመንፈሳዊ ሕይወቱ እንዴት መቀጠል እንደሚገባው ስለሚረዳ የንስሓ አባቱ እንዲመሩት አይጠይቅም።

እርሱ ከንስሓ አባቱ የሚፈልገው እርሱ በሚሰጠው አሳብ እንዲስማሙ ነው። ይህን በማድረግም የንስሓ አባቱ ሊፈጽም የሚገባውን ሥርዓት አከናውነዋል ብሎ ያምናል። የነፍስ አባቱ እርሱ በሚሰነዝረው አሳብ ካልተስማሙ ይከራከራቸዋል ይሞግታቸዋልም። ገለጻውን በመቀጠልና የንስሓ አባቱ ላቀረቡለት መፍትሔዎች ተግባራዊ ተቃውሞዎቹን በማቅረብ በመጨረሻ የራሱን አሳብ ያጸናል።

ባጭሩ ለራስ ውጊያ የተጋለጠ ሰው ሁልጊዜ እንደ ራሱ ፈቃድ ስለሚመላለስ ለሰው መታዘዝ እጅግ አስቸጋሪ ይሆንበታል። ለራሱ ስለሚያስብ ከሌሎች የሚሰነዘሩ አሳቦች ምንጫቸው ከየትም ይሁን ከየት ለእርሱ ተረት

ተረት ናቸው። በንስሓ አባቱ አንባር የሚያሳየው ጠባይ ይህ ከሆነ በተግባራዊ ሕይወቱ ውስጥ የሚፈጽማቸው መመሪያዎቹም ከዚህ የሚዘሉ አይሆኑም። በመሆኑም በራሴ እተማመናለሁ የሚል ሰው በሥራ ውስጥ ካሉ መርሆዎች ጋር ይጋጫል ማለት ነው። ከዚህ በተጨማሪ በሥራው ውስጥ ጣልቃ ከሚገቡት ባልንጀሮቹና ስሜቶቹ ጋር ይጋጫል።

የራስ ድጋፍ።

ራስን መደገፍና በራስ ያለ ከፍተኛ አመለካከት የሚመጡት ከዚህ በታች በምንመለከታቸው አንዳንድ ምክንያቶች ነው።

- ራስን ወደ መደገፍ የሚያመራው የመጀመሪያ ምክንያት የበላይነት፣ ተሰጥኦ፣ ልዩ ችሎታ ወይም የኃይል ስሜት ነው።

እነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ሰውን ከውስጥ በመዋጋት ሰውየው የተቸረውን ተሰጥኦና ችሎታ ለማሳየት በሚያደርጋቸው የተለያዩ ሙከራዎች ውስጥ ራሳቸውን በውጪ ይገልጣሉ። እንዲህ ዓይነቱ ውጊያ የሚከብደው ሰውየው አንዱን ከሌላው ማበላለጥ ሲጀምር ነው።

እዚህ ላይ ሰውየው እርሱ ከሌሎች ሰዎች በማንኛውም ነገር የተሻለ አድርጎ በመቁጠር ራሱን ይበልጥ የተማረ፣ ይበልጥ የሚያውቅ፣ ይበልጥ ልምድ ያለው፣ ይበልጥ ኃይል ያለው ያደርጋል። ወይም ደግሞ ራሱን በሥዕል፣ በሙዚቃ፣ በግጥም፣ በእጅ ሥራ፣ በቋንቋ . . . ወዘተ የተለየ ተሰጥኦ አድርጎ ለማቅረብ ይሞክራል።

አንድ ሰው በአገልግሎት ውስጥ ከሌሎቹ አገልጋዮች የሚበዙ ችሎታዎች እንዳሉት ሆኖ የሚሰማው ከሆነ እግዚአብሔርን በማገልገል ውስጥ እንኳ ራስ ከሌሎቹ እርሱ ተሰይቶ ሊታይ ይፈልጋል። ለምሳሌ፦ አንድ ሰው ዜማ ለማጥናት የላቀ ችሎታ ሊኖረው ይችላል። ወይም ልዩ ድምፅ ሊኖረው ይችላል። ወይም መጽሐፍ ቅዱስ ለማጥናት የበረታ ሊሆን ይችላል። ወይም ደግሞ የአባቶችን ብሒሎች በመናገር የሚደርስበት አይኖርም። ከዚህ በተጨማሪ በአገልግሎቱ፣ በስብከቱ፣ በአስተዳደሩ ወይም ዕቅድ በማውጣቱ ይበልጥ ውጤታማ ይሆናል። በዚህ ተሰይቶ መታየት ይፈልጋል።

- ራስን ወደ መደገፍ የሚያመራው ሁለተኛው ምክንያት ሥልጣን፣ ክብር፣ ሁበት ወይም ዝና ነው።

እነዚህ ጉዳዮች ራስን ለመደገፍ ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ። ትሑት ሰው ግን ሰዎች ራሳቸውን ለማሳየት፣ ጉራ ለመንዛትና ራሳቸውን ለማስታበይ በእነዚህ የሚጠቀሙ ከሆነ ከእነርሱ ሸሽቶ ያመልጣል።

- ተሰጥኦ በራሱ የራሱ የሆነ አደጋ አለው። ከውስጥ ምናልባትም ከውጪ ተሰጥኦ በልብ ላይ ሊታበይ ይችላል። በመሆኑም ወደ ከንቱ ክብር ውጊያ ይመራል። እዚህ ላይ አንድ ሰው፦ ሰዎች ተአምር የማድረግ ስጦታ እንዴት

ከእግዚአብሔር ሊታደላቸው ቻለ? በተሰይ ስጦታው ሙት የማስነሣትና ዓይን የማብራት ከሆነ? ብሎ ሊጠይቅ ይችላል።

ይህን አስመልክቶ አንድ አባት እንዲህ በማለት ተናግሯል፦ «እግዚአብሔር ስጦታ ከሰጠህ ስጦታህን ልትጠብቅበት የምትችለውን ትሕትና አብሮ እንዲሰጥህ ለምነው። አለበለዚያ ግን ከአንተ እንዲወስደው ጠይቀው።» ከዚህ አንጻር የመንፈስ ፍሬዎችንና የልብ ንጽሕናን ለማግኘት ከመጸለይ ይልቅ እግዚአብሔር በተለያዩ ቋንቋዎች የመናገር ስጦታን እንዲሰጣቸው የሚጠይቁት ሰዎች በጣም ያስደንቃሉ። እንደነዚህ ዓይነቶቹ ሰዎች ይህን ጥያቄ በሚጠይቁበት ወቅት በሕሊናቸው ውስጥ ወደ አፍሪካ በረሀ፣ ወደ ቻይና፣ ወደ ጃፓን ሄደው የመስበክ አሳብ ፈጽሞ አይመላለስም። እነርሱ የሚጠይቁት ስጦታውን ለማግኘት ብቻ ነው።

እንዲህ ያለውን ስጦታ ከመጠየቅ ጀርባ በራስ ላይ የሚመጣ ውጊያ ሊኖር ይችል ይሆን? በእርግጥም አለ። ወንድሜ ሆይ፤ እነዚህ ስጦታዎች ምን ጥቅም ሊሰጡህ ይችላሉ? በአንተ ላይ የታወጁ ጦርነቶች ሊሆኑ ይችላሉ። እነርሱን ባለማግኘትህ ልብህ የሚያዝነው ለምንድር ነው? መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አስቀድማችሁ ጽድቁንና መንግሥቱን ፈልጉ ሌላው ሁሉ ይጨመርላችኋል ብሎ የተናገረውን ቃል በንቃት ልታደምጥ ይገባሃል።

በፈቃደ እግዚአብሔር እነዚህን የላቁ ስጦታዎች የተቀበልን ከሆነ ለእኔ ወይም አኔ ባይነትን የሚያጠፋው ትሕትና አብሮ እንዲሰጠን ልንጸልይ ይገባናል።

ውድ ወንድሜ ሆይ! አንተ በዚህ ውጊያ የምትወጋ ከሆንህ ራስህን ጠይቅ እንጂ ስለ ስጦታ አትጠይቅ! «ይህን ስጦታ ልቀበለው እችላለሁ ወይስ ወደ ትዕቢት በመምራት ዘላለማዊ ሕይወቴን ያሳጣኛል?» ብለህ ጠይቅ።

ራስን የማምለክ ውጤቶች።

በራሴ እተማመናለሁ የሚል ሰው ለእልኸኝነትና ለግትርነት የተጋለጠ ነው። የእርሱ አመለካከት ከሌሎች ሰዎች ሁሉ የሚበልጥ ስለሆነ ማንኛውንም ዓይነት ተቃውሞ አይቀበልም። የሚቃወመው ሰው ለእርሱ ጠላቱ ስለሆነ ይጠላዋል። ስለሆነም ሊያጠፋው ይሞክራል። ካልሆነለትም የተቃዋሚውን አመለካከት ንቆ ይተወዋል። ይህ በአንድ ሰው እውቀት ወይም ችሎታ ውስጥ ያለ የተሳሳተ በራስ መተማመን ነው። ከእንዲህ ዓይነቱ ሰው ጋር መደራደር በጣም ከባድ ነው።

እነዚህ ሰዎች ስለ እነርሱ የሚነገረው ነገር ከመጠናቀቁ በፊት በመካከል ገብተው ያቋርጣሉ ወይም ተናጋሪውን ደጋግመው ያቋርጡታል። ምንም እንኳ ተናጋሪዎቹ የተረጋገጠ ብርቱ ማስረጃ ቢኖራቸውም ሰዎቹ ይህን ከምንም በመቁጠር በራሳቸው አመለካከት ይጸናሉ። ስለሆነም ሰው ሁሉ ከእነዚህ ሰዎች ጋር መነጋገር ምንም ፋይዳ እንደማይኖረው ስለሚያውቅ ከእጠገቡ ያርቃቸዋል ያሰወግዳቸዋልም።

በራሴ እተማመናለሁ የሚል ሰው የመሪ ሥልጣን ካገኘ ጨቋኝ ይሆናል። ይህ የጨቋኝነት ዐመል ደግሞ ከግትርነት የሚመጣ ብቻ ሳይሆን የራስን አመለካከት በጉልበት አስከማስፈጸም የሚጠይቅ ይሆናል።

ይህ በአገልግሎት መስክ ውስጥም ሊከሰት ይችላል። አንዱ አገልጋይ የሌሎቹን አገልጋዮች ሰብአና የሚንቅ ከሆነና ከእነርሱ ጋር መነጋገር ትርፉ ጭቅጭቅና ጊዜን ማባከን ነው ብሎ የሚያምን ከሆነ ሊያደርግ የሚገባውን ውይይት ችላ ይላል። አልፎ ተርፎም «እኔ ይህን ብያለሁና ይህ መሆን አለበት!» በማለት ይናገራል።

እዚህ ላይ ራስን ማምለክ በእርግጠኝነት ወደ ትዕቢት፣ ኩራትና ትምክህት ይመራል። ይህ ሰው እዚህ ደረጃ ላይ ሲደርስ ራስን የማዋረድ፣ የትሕትናንና የጥሞናን ሕይወትን ስለሚንቅ ከጨቋኝነት ወደ አመራር ሰጪነት ይሸጋገራል። ሌላው ራስን የመውደድ ደረጃ የተሳሳተ እርካታ ነው።

የተሳሳተ የራስ ደስታ።

ይህ ደስታ የሚመጣው ከኩራት ሳይሆን ራስን ከማስደሰት ነው። ሁለቱም ጉዳዮች በቅዱስ ዮሐንስ ቃላት ውስጥ ተገልጠዋል፦ «. . . የሥጋ ምኞትና የዓይን አምሮት ስለ ገንዘብም መመካት . . . » 1ኛ ዮሐ 2:16። በዚህ ቋል መሠረት ዝሙት የራስ ውጊያ ሲሆን የምግብ ምኞት ደግሞ ሥጋን ይዋጋል።

የራስ ውጊያ ሥጋንም ሆነ ነፍስን ሊዋጋ ይችላል። የሥጋ ምኞት ጾም ሰመጾም እንቅፋት ነው። ምክንያቱም ለላሙና ለጣሙ ምግቦችና ለወይን ጠጅ ወይም ወደ ሱስ የሚያሸጋግሩ ዕፆች መስገብገብን ስለሚያስከትል ነው። እዚህ ላይ ስለ ሥጋ ምኞት ብዙ መናገር ቢቻልም ርዕሱ የሚነሣበት ጊዜ ስላልደረሰ በዚሁ እንገድበዋለን።

መስጠትና ማንነት።

ራስን መውደድ ሌሎችን ከመውደድ፣ ከመስጠትና መሥዋዕት ሆኖ ከመቅረብ ሕይወት ጋር የሚቃረን ከመሆኑም በላይ ሊያሸነፉት የማይቻል ደንቃራ ነው።

ስለዚህ ምሳሌ የሚሆነን ድሀው አልዓዛርን የረሳው ሰነፉ ባለጸጋ ነው። ሉቃ 16። ሌላ ምሳሌ የሚሆኑን ንፉጎች፣ ገብጋቦች፣ አሥራታቸውን የማይከፍሉ፣ መባ የማያቀርቡና ሁሉንም ነገር ለራሳቸው ብቻ የሚያውሉ ሰዎች ናቸው። ራሱን የሚወድ ሰው ሊሰጥ ቢችልም እንኳ ልባሳው እርሱንና ፍላጎቶቹን ሊጋፋ በማይችልበት ሁኔታ የተገደቡ ይሆናሉ። እርሱ ከትርፉ ሊሰጥ ቢችልም ጌታ እንዳወደሳት እንደዚያች ድሀ መበለት ከዋናው ወይም ያለውን አይሰጥም። ሉቃ 21፡4። የሚሰጠው ከእርሱ ውጪ ያለውን እንጂ ራሱን ፈጽሞ አይሰጥም።

ራሱን የሚወድ ሰው ራሱን ስለ ሌሎች አሳልፎ ሊሰጥ አይችልም። መሥዋዕት ሆኖም አይቀርብም። ለሌሎች በመቆም የሚመጣ አደጋ ከታየው ራሱን ከመካከል ያገላል። ለዚህ ምክንያት የሚሆነው ለእርሱ እርሱነቱ ይበልጥ ጠቃሚ መስሎ ስለሚታየው ነው። በእርግጥም ራስን መውደድ ተሳልፎ ከመሰጠትና መሥዋዕት ከመሆን መስክ እጅግ የራቀ ከመሆኑም በላይ ለሌሎች ለመቆም ድፍረት አይኖረውም።

ማንነት ጊዜ የለኝም በሚል ሰበብ አገልግሎትን ሊገድብ ይችላል። ራሱን የሚወድ ሰው ለድሀ ከትርፉ እንደሚሰጥ ሁሉ ለአገልግሎት የሚሰጠው ጊዜም ከትርፉ የሆነውን ነው። ግዴታዎቹን ላለመፈጸም ሲል ከአገልግሎት ለመራቅ የተለያዩ ምክንያቶች ይደረድራል። የአገልግሎት ጊዜዎቹን ስለሚዘነጋቸውም ውጤታቸው ምንም ይሁን ምን ለሌሎች ጉዳዮች ቅድሚያ ይሰጣል። ይህ ደግሞ በአገልግሎት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ያሳድራል።

ይህን ሁሉ ከተመለከትን በኋላ ስለ ሰማዕትነት ምን ልንል እንችላለን? ራሱን የሚወድ ሰው እርሱነቱ ስለሚያሳሳው በሰማዕትነት ተሳልፎ ሊሰጥ አይችልም። ሰማዕት ግን ራሱን ለእግዚአብሔር ሲል አሳልፎ የሚሰጥ ሰው ነው። በደረጃ ከዚህ ዝቅ የሚለው ሰማዕትነት ሙሉ ጊዜን ለእግዚአብሔር በመስጠት ራስን ሰማዕት አድርጎ መስጠት ነው።

ራስን መስጠት ከፍተኛው የአገልግሎት ደረጃ ነው። በዚህ ደረጃ ውስጥ ራሱን የሰጠ ሰው ሙሉ ጊዜውን ለእግዚአብሔር የሰጠ ስለሚሆን ለራስ ወይም ለእኔ የሚል መስክ በእርሱ ዘንድ ቦታ የለውም። እዚህ ላይ ራስን በመስጠት ውስጥ ጎልቶ የሚታየው እኔነት አይደለም። እውነተኛ ራስን መስጠት ግን በዚህ ውስጥ በሰማዕትነት ጎልቶ ይታያል።

ራሱን የካደ ሰው ያለውን መልካም ነገር ሁሉ ይሰጣል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «ፍቅር . . . ለብቻዬ ይድላኝ አይልም . . .» (1ኛ ቆሮ 13) ብሎ እንደ ተናገረ ራሱን የካደ ሰው ለሌሎች እንጂ ለራሱ መልካም የሆነውን አይፈልግም። ራሱን የሚወድ ሰው ግን መልካሙን ለራሱ ያስቀራል እንጂ ለሌሎች አይሰጥም።

ራስን በመውደድ ዙሪያ ከባዱ ጉዳይ ለሰው አንድ ነገር ከሰጠ በኋላ በጸጸት መልሶ የሚወስድ ሰው ሕይወት ነው። እዚህ ላይ ወደ ሌላ ነጥብ እንገባለን።

በድርድር ውስጥ ያሉ የራስ ስህተቶች፡፡

አንዳንድ ጊዜ ራሱን የሚወድ ሰው ራሱን ለማጽናት ከሌሎች ጋር መታገልን ጠቃሚ አድርጎ ይወስደዋል፡፡ ወደዚህ የሚያስገባው የመጀመሪያው ደረጃ ደግሞ ውድድር ነው፡፡

ውድድር ለኅብረተሰቡ ጥቅም ሲባል የሚደረግ ከሆነ ሁሉም ኅብረተሰቡን ለመጥቀም ስለሚወዳደር ይህ መልካም ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦ «. . . ሁልጊዜ በመልካም ነገር ተፈላጊ ብትሆኑ መልካም ነው፡፡» ገላ 4፡18፡፡ ይሁን እንጂ ውድድር አንዱ ቡድን ሌላውን ቡድን በማንኛውም መንገድ ለማጥፋት እስከ ማድረስ የሚያበቃው ከሆነ ማንነት እዚህ ላይ የሚገለጠው ለሌሎች ባለ የፍቅር ጉድለት ታጅቦ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ከፍ ያለ ደረጃ ላይ ለመድረስ ሁሉም መወዳደሩ መልካም ሆኖ ሳለ አንዱ ሌላውን በውድድር ሲበልጠው ሌላው ጥላቻ ስለሚያተርፍ ራስን የመውደድ አደገኛነት ይገለጣል፡፡ እዚህ ላይ ራስን መውደድ ወደ ቅናትና ጥላቻ ይሸጋገራል፡፡

የታወረ ቅናት እርሱ ብቻ እንጂ ሌሎች ሁሉን እንዲያገኙ አይፈልግም፡፡ ከሁሉም የላቀና ብቻውን ተጽዕኖ የሚያሳድር ለመሆንም ይፈልጋል፡፡ ብቻውን ታላቅ ሆኖ እንዲወደስም ይሻል፡፡ መብራቶች ሁሉ ወደ እርሱ እንዲበሩ እንጂ ወደ ሌሎች እንዲያበሩ አይፈልግም፡፡ ይህ ካልሆነ ማንነት እርሱን በሚበልጠው ወይም የእርሱን ፈለግ በሚከተለው ላይ ጦርነት ያውጃል፡፡

አንዱ ዓይነት ሊወደስ የሚፈልግ ሲሆን ሌላው ዓይነት ደግሞ ብቻውን ሊመሰገን የሚፈልግ ይሆናል፡፡ እዚህ ላይ አደጋው የሚገለጠው ሌሎች በራሳቸው ወይም በሰዎች ላይ ምንም ዓይነት ጥፋት ሳያደርሱ ወቀሳ የሌለባቸውና አፍቃሪዎች ሆነው ሲገኙ ከራስ ተቃውሞ ሲቀርብባቸው ነው፡፡ ይህ ታዋቂ ሰዎች ስለ ታላቅነታቸው ሲሉ በቅናት ምክንያት ለሌሎች የሚያሸክሙት መስቀል ነው፡፡

ይህ ደግሞ ዳዊት ከንጉሥ ሳኦል የተቀበለው፤ጻድቁ ዮሴፍም ከወንድሞቹ የተቀበለው መስቀል ወይም መከራ ነው፡፡ በተመሳሳይ ምክንያት መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ተወለደ ሄሮድስ መከራ አምጥቶበታል፡፡ ፈሪሳውያንም በእርሱ ላይ ተመሳሳይ መከራ የማድረስ ስሜት ነበራቸው፡፡ አስቀድመው ይህንን መከራ ሊያደርሱበት ስላልቻሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ እነርሱ እንዲህ ተብሎ ተጽፎአል፦ «ስለዚህ ፈሪሳውያን እርስ በእርሳቸው፦ አንድስ እንኳ ልታደርጉ እንዳይቻላችሁ ታያላችሁን? እነሆ ዓለሙ በኋላው ተከተሉት ሄዶአል ተባባሉ፡፡» ዮሐ 12፡19፡፡

በአራት ዘፍጥረት ላይ የተጻፈው ቃል ምንኛ ከብድ እንደ ሆነ ተመልከቱ፦ «በአንድነትም ይቀመጡ ዘንድ ምድር አልበቃቸውም . . . » ዘፍ 13፡6፡፡ ራስ የበላይ ለመሆን ከፈለገ የሚወዳደረውን ከማጥፋት ወደኋላ አይልም፡፡ ይህም ኢይዝራኤላዊው ናቡቴን ባስገደለው በንጉሥ አክዓብ ሕይወት ውስጥ ተገልጧል፡፡

ክብርና ውዳሴን አስመልክቶም ከዚህ ጋር ተመሳ ይ የሆነ ነገር ሊባል ይቻላል፡፡ አስቀድመን ራሱን ወዳድ የሆነ ሰው ካለብት ችግሮች መካከል በሰው

ሁሉ እንዲወደስና በእነርሱ ዘንድ ክብር እንዲያገኝ መውደዱ እንደ ሆነ ተመልክተናል፡፡ አሁን የምንመለከተው ዓይነት ግን ይበልጥ አደገኛው ነው፡፡ ይህም እርሱ ብቻ እንዲከበር፣ እንክብካቤ እንዲደረግለትና እንዲወደስ የሚፈልገው ዓይነት ነው፡፡ ይህ ጉዳይ ይበልጥ የሚከፋው እንዲህ ዓይነቱ ስሜት በእርሱ ዙሪያ ካሉት ሰዎች መካከል አንዱ በሌሎች መክበር የሚደሰት ሆኖ ሲመለከት ነው፡፡

ስለሆነም ተመሳሳይ ሙያ ወይም የሥራ መስክ ባላቸው ወይም ለበላይነት በሚፎካከሩ ሰዎች መካከል ቅራኔ አለ ማለት ነው፡፡ ማርያም በመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እግር ሥር ተቀምጣ ትምህርቱን ከመማር ውጪ ምንም ዓይነት ማርታን የሚቃወም ተግባር አልፈጸመችም፡፡ ይሁን እንጂ ከማርታ ወቀሳ አላመለጠችም፡፡ ማርታ እህቷ ማርያምን እንድትወቅስ ያደረጋት በውስጧ ያለው እርሷነቷ ወይም ግለኝነቷ ነው፡፡ «እኔ ብቻዬን ለምን እሠራለሁ? ለምን መጥታ አታግዘኝም? እኔ ይህን ተመስጦ ሳላገኘው እርሷ ለምን በዚህ ልትደሰት ቻለች?» ብላ እንድትጠይቅ ያደረጋት ይህ ራስነቷ ነው፡፡ ሉቃ 10፡40፡፡ ማርታ ከራስነቷ ተነሥታ እህቷ ማርያምን እንደወቀሰቻት በጠፋው ልጅ ታሪክ ውስጥ የሚገኘው ታላቅየው ወንድም ታናሽ ወንድሙን ወቅሶታል፡፡ ሉቃ 15፡፡

ራስ ወዳድነትን አስመልክቶ የሚጠቀሰው ሌላ ነጥብ ራሱን የሚወድ ሰው ራሱን በጭራሽ አለመውቀሱ ነው፡፡ እንዲያውም የራሱን ስህተት በሌሎች ላይ ያሳብባል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ሰው ከፈተና ቢወድቅ መምህሩ ከባድ ጥያቄ ስላመጣብኝ ነው ወይም የፈተና ወረቀቶችን በቀና ልቡ ስላላረማቸው ነው ይላል፡፡ አልፎ ተርፎም ይህን አስመልክቼ ጸሎት ባቀርብም እንኳ እግዚአብሔር አልረዳኝም ብሎ እስከ መናገር ይደርሳል፡፡

እንዲህ ዓይነቱ ሰው ሁልጊዜ እርሱ እንደ ተበደለ አድርጎ ይቆጥራል፡፡ ራሱን የሚወድ ሰው የፈለገውን ካላገኘ ይነጫነጫል፣ ያጉረመርማል፣ ያማርራልም፡፡ ቤተሰቦቹን፣ ኅብረተሰቡንና የሚናኮበትን ዘመን ወይም ጊዜ ያማርራል፡፡ የሌሎችን እንክብካቤም ይከሳል፡፡ ግቡን እንዳይመታ ያደረጉትን ብዙ ምክንያቶችም ይደረድራል፡፡

ይህን ሁሉ እንዲያደርግ ምክንያት የሆነው እርሱነቱ ግን አልተከሰሰም፡፡ ራሱን በገዛ ዐይኖቹ ሲመለከት ወቀሳ የሌለበት አድርጎ ስለሚቆጥር ጥፋቶቹን ሊያርም አይችልም፡፡ ጥፋቱ እየቀጠለ ሲሄድና እርሱም ራሱን ማረም ሲያቅተው ማማረሮቹም ያለ ማቋረጥ ይቀጥላሉ፡፡ የበላይ አለቃ ከሆነ ከበታቹ ያሉ ሪዳቶቹን ጥፋት ያማርራል፤ የበታች ሠራተኛ ከሆነም የበላዩንና አጠገቡ ያሉ የሥራ ባልደረቦቹን ይኮንናል፡፡ በእነዚህ ሰዎች ላይ ምንም ዓይነት ጥፋት ባያገኝም ቤሕጉ፤ በመመሪያውና በመተዳዳሪያ ደንቡ ያማርራል፡፡ በአጭሩ እርሱ ምንም ዓይነት ጥፋት ሊያጠፋ ጥፋቶቹን በተለያዩ ውሸቶችና ምክንያቶች በማለባበስ ለራሱ ይከራከራል ወይም ኃላፊነቱን በሌሎች ያላክላል ወይም የምሩን እንዳልተናገረ አድርጎ ሊያስመስል ይሞክራል፡፡ በመሆኑም ራሱን በመውቀስ ፋንታ ጥፋቶቹን ይሸሽጋል፡፡

ራሱን የሚወድ ሰው ለክብሩ በጣም ይጠነቀቃል። ሌሎችን የሚመዝነው ራሱን ከሚመዝንበት ሚዛን በተለየ ሚዛን ነው። እርሱን ሌሎች ሲናገሩት እያንዳንዷን ቃል በጥንቃቄ ይመረምራል። እርሱ ሌሎችን የሚናገርበትን ቃላት ግን በትክክል አይመርጥም። እርሱ ሌሎችን በማይንከባከብበት እንክብካቤ ሌሎች እንዲንከባከቡት ይፈልጋል።

በሚተኮሱት ጥቂት ገጾች ውስጥ ራስን ስለ መካድ፣ ራስን ስለ ማውገዝና እንዴት ይህን ጠባይ ማግኘት እንደምንችል እንነጋገራለን።

ራስን መካድ።

ታላቁ ምሳሌ . . .

የመጀመሪያው ሰው እግዚአብሔርን መሆን ስለ ተመኘ በራስ ውጊያ ተወግቶ ድል ቢነሣም (ዘፍ 3:5) መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን ስህተቱን በማረም ተፈጥሮአችንን በራሱ ቀድሶታል። ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ? ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ይለናል፦ «. . . የባርያውን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ።» ፊል 2:7።

ጌታ በዚህ ምድር ላይ ሲኖር ራሱን የሚያስጠጋበት ሥፍራ አልነበረውም። «. . . ለቀበሮዎች ጉድጓድ ለሰማይም ወፎችም መሳፈሪያ አሳቸው፤ለሰው ልጅ ግን ራሱን የሚያስጠጋበት የለውም . . . .» ሉቃ 9:58። እርሱ ራሱን ዝቅ አደረገ እንጂ በባለ ሥልጣን ወንበር ላይ አልተቀመጠም። «ተጨነቀ ተሠቃየም አፉንም አልከፈተም . . . ከዓመፀኞችም ጋር ተቆጥሯልና።» ኢሳ 53:7 እና 12።

እርሱ ስለ ራሱ አልተከራከረም። ስለ እኛ ሲል ራሱን አዋርዷል። ራሱን ያዋረደውም እኛን ሊያነሣን ነው። እኛ ጻድቃን እንሆን ዘንድ እርሱ ከዓመፀኞች ጋር ተቆጠረ። እርሱ ስለ እኛ እንጂ ስለ ራሱ አልተጨነቀም። ዮሐንስ የንስሓ ጥምቀት ሲያጠምቅ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መጠመቅ ባይገባውም ለእኛ ምሳሌ ይሆነን ዘንድ ግን ስለ እኛ ተጠምቋል። በመሆኑም ራስን በመካድ ወይም በማዋረድ ውስጥ ሆኖ «አሁንስ ፍቀድልኝ . . . » (ማቴ 3:15) ብሏል።

ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን ዋተወበት ሕይወት ረቹም ስለሆነ በዚህ መጽሐፍ ዘርዝረን ልንዘልቀው አንችልም። ይህን አስመልክቶ በልደቱ ላይ የተደረገውን ተመስጦ የሚናገረውንና "Contemplations on the Nativity" የተባለውን መጽሐፍ ከገጽ 7-28 ልታነቡ ትችላላችሁ። በመቀጠል ሌላውን ራስ መካድ ሕይወት እንመለከታለን።

ራስን መሠዋት።

ራስን መሥዋዕት ማድረግ ለእግዚአብሔር፣ ለቤተ ክርስቲያን፣ ለዘመድ ወይም ለባዕድ ሰው ሊሆን ይችላል። ይህን አስመልክቶ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የተናገራቸው ቃላት ምንኛ ጥልቅ ናቸው! «. . . ነፍሴን በእኔ ዘንድ እንደማትከብር እንደ ከንቱ ነገር እቆጥራለሁ።» ሐዋ 20:24። ስለሆነም እርሱ ራሱን ለአገልግሎት አሳልፎ ሰጥቷል።

«. . . በባሕር ውስጥ ኖርሁ። ብዙ ጊዜ በመንገድ ሄድሁ፤በወንዝ ፍርሃት፣ በወንበዴዎች ፍርሃት፣ በወገኔ በኩል ፍርሃት፣ በአሕዛብ በኩል ፍርሃት፣ በከተማ ፍርሃት፣ በምድረ በዳ ፍርሃት፣ በባሕር ፍርሃት፣ በውሸተኞች ወንድሞች በኩል ፍርሃት ነበረብኝ፤በድካምና በጥረት ብዙ ጊዜ እንቅልፍ በማጣት፣ በራብና በጥም ብዙ ጊዜ በመጦም፣ በብርድና በራቁትነት ነበርሁ።» (2ኛ ቆሮ 11:26-27)፤ «በመከራ፣ በችግር፣ በጭንቀት፣ በመገረፍ፣ በወኅኒ፣ በሁከት፣ በድካም፣ እንቅልፍ በማጣት፣ በመጦም . . .» 2ኛ ቆሮ 6:4-5።

እዚህ ላይ ሐዋርያው ራሱን ዕረፍት የማይፈልግ በማድረግ ለአገልግሎት አሳልፎ እንደ ሰጠ እንመለከታለን። እርሱ ራሱን አሳልፎ የሰጠው በመስዘክ፣ በማስተማርና የጠፋውን በመፈለግ ለመድከም ነው። እርሱ ለሰዎች ብርሃን ለመስጠት እንደሚቀልጠው ሻማ ነው። ለሌሎች መልካም መዓዛ ለማቅረብ እንደሚጨሰው ዕጣንም ነው። በመሆኑም እርሱ ለሌሎች ታላቅ ምሳሌ ነው።

ወንጌልን ለመስበክ ሐዋርያት በሩቅ ሀገራት እንግዶችና መጻተኞች ሆነው ኖረዋል። የእነርሱ ዋና ዓላማ የእግዚአብሔር ቃል ለሁሉም እንዲደርስ ስለሆነ የሰው ሥጋ በሚበሉ ሰዎች መካከል ወንጌልን ሰብከዋል። ስለዚህ ወንድሜ ታገለግል ዘንድ ከተጠራህ ስለ ራስህ ወይም ስለ ምቾትህ ወይም በቁስም ሆነ በገንዘብ ስለሚሆኑ ፍላጎቶችህ አታስብ . . . እግዚአብሔር ሁሉን ሊያደርግ ይቻለዋልና። አሳብህን ሁሉ እግዚአብሔርን ለምትሻው ነፍስህ አስረክብ። ችግር ላለባቸው ክፍላተ ሀገራትና ለዚህ ዓላማ መሳካት ደክመው የሚያገለግላቸው ላጡት ሰዎች ራስህን አሳልፈህ ስጥ።

በአገልግሎት መስክ ላይ ስትሰማራ የሚከተለውን የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ቃል አስታውስ፦ «ነፍሱን የሚያገኝ ያጠፋታል፤ ነፍሱንም ስለ እኔ የሚያጠፋ ያገኛታል።» ማቴ 10:39። የእነዚህ ድንቅ ቃላት ትርጉም ምንድር ነው? ከበስተ ጀርባቸው ያለው መንፈሳዊ ጥልቀት ምንድር ነው? በምን ምሳሌዎች ሊመሰሉ ይችላሉ?

ራሱን ያጠፋል።

ነቢዩ ሙሴ ንግሥናንና የንጉሡን ቤተ መንግሥት ስለ ወገኖቹ ባደረበት የተቀደሰ ቅንዓት በእምነት እምቢ በማለቱ አንዳንዶች ነፍሱን አጥቷል ብለው ሊያስቡ ይችላሉ። «. . . ከግብፅም ብዙ ገንዘብ ይልቅ ስለ ክርስቶስ መነቀፍ እጅግ የሚበልጥ ባለ ጠግነት እንዲሆን አስቧልና፤ለጊዜው በኃጢአት ከሚገኝ ደስታ

ይልቅ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር መከራ መቀበልን መረጠ . . .» ዕብ 11:25-26።

ይሁን እንጂ እነዚህ ሰዎች እንደሚያስቡት ሙሴ ነፍሱን አላጠፋም። ይልቁንም በእርሱ ውስጥ ባለው የእግዚአብሔር ሥራ ሌሎችን ወደ እምነት በመመለስ ነፍሱን እንደ ሌሎቹ ቅዱሳን አግኝቷታል። በመሆኑም በወቅቱ የእምነት ቁንጮ ሊሆን በቅቷል። ከዚህ በተጨማሪ እርሱ በእግዚአብሔር ለተጻፉ ሕግጋት ለመታመን የመጀመሪያው ሰው ነበር። በደብረ ታቦር ተራራ ላይም ከኢየሱስ ክርስቶስና ከኤልያስ ጋር ተገኝቷል። በመሆኑም ያገኘው ታላቅ ክብር ካጣው ተራ ነገር ጋር ፍጹም አይነጻጸርም።

ይሁን እንጂ ሙሴ ከፈርዖን ቤተ መንግሥት ወጥቶ የሄደው ስለዚህ ክብር እያሰበ አልነበረም። እርሱ በዚያን ጊዜ የፈለገው ራሱን ለወገኖቹ መሥዋዕት ማድረግ ነበር። በቤተ መንግሥት ውስጥ ተንቀባሮ በደስታ ከመኖር ይልቅ መከራ መቀበልን መርጧል።

እንዲህ ዓይነቱ ነገር በእግዚአብሔር የተጠራው አባታችን አብርሃምንም አጋጥሞታል። በእርግጥም እርሱ ከአገሩ፣ ከወገኖቹና ከአባቱ ቤት ተለይቶ ወደማያውቀው ሀገር እንዲወጣ የተነገረው ራሱን መሥዋዕት አድርጎ እንዲያቀርብ ነው። ዘፍ 12።

ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር ለሚከብድ ፈተና ጠራው። በዚህም አንድ ልጁን መሥዋዕት እንዲያደርግ ጠየቀው። የአብርሃም መሥዋዕት በዕድሜ ውስጥ ሁሉ የሚያበራ ምስል ሆኖ አልፏል። በመሆኑም እግዚአብሔር ዘሩን እንደ ሰማይ ከዋክብትና እንደ ባሕር አሸዋ አብዝቶለታል። እኛ ሁሉ የአብርሃም ልጆች ነን። ሮሜ 4:11 እና 16። አብርሃም ልጁን ለመሠዋት ቢላዋ የያዘ እጁን ወደ ላይ ሲያነሣ ስለ ራሱ ያስብ ነበርን? አያስብም ነበር! በእርሱ ፊት ስለ ነበረው የእግዚአብሔር ተአዛዝ ብቻ እንጂ ስለ ራሱ አያስብም ነበር። ወዴት እንደሚሄድ ሳያውቅ ከአገሩና ከወገኖቹ ተለይቶ ሲወጣ የነበረው ስሜት ከዚህ ጋር ተመሳሳይ ነበር። ዕብ 11:8።

ይሁን እንጂ መሥዋዕት ለሆነው ለእርሱና ለሌሎችም መሥዋዕት ለሚሆኑ ሁሉ ዋጋቸውን እግዚአብሔር ይከፍላቸዋል። አንተም ራስህን መሥዋዕት አድርገህ አቅርብ። ከዚህ በኋላ አንተነትህ የእግዚአብሔር ታላቅ ወዳጅና በእርሱ ፊት ዋጋ ያለው ይሆናል። በዚህም እግዚአብሔር እንድትጠፋ ላለመፈለጉ እርግጠኛ ሁን። አንተነትህን በብዙ አባዝቶ ሲመልስልህ በእርሱ ውስጥ ራስህን ታገኘዋለህ።

አሁን ራስን መካድ አስመልክቶ ወደ ሌላ ነጥብ እንሸጋገራለን።

ምናኔና ራስን መርሳት።

ብቸኛ ጉዳዩን ለራሱና ለምኞቱ ያዋለ ሰው ጠቢቡ ሰሎሞን ስለ ራሱ እንደ ተናገረው እርሱም ይናገራል፦ «. . . ቤቶችንም አደረግሁ፣ ወይንም ተከልሁ፤ አትክልትና ገነት አደረግሁ . . . ዓይኖቼንም ከፈለጉት ሁሉ አልከለከልኋቸውም . . .» መክ 2:4 እና 10። እዚህ ላይ ራስ ወይም እኔነት ዓለማዊና ሥጋዊ ደስታዎችን ስለ ፈለገ «ነፍሱን የሚያገኝ ያጠፋታል . . . » (ማቴ 10:39) የሚለው የጌታ ቃል በእርሱ ላይ ተግባራዊ ይሆናል።

ከዚህ ቡተለየ ምግብን፣ ልብስንና ሌላውንም ነገር የሚረሱ ሰዎች አሉ። የቅንጦትን ሕይወት የሚመሩ ሰዎች በአልዓዛርና በነዌ ታሪክ ውስጥ የተጠቀሰው ባለጸጋ ሰው እንደ ገጠመውና የወደደውን በምድር እንደ ተቀበለ እነርሱም ለራሳቸው መልካም ነው ያሉትን ነገር በምድር ሳሉ ይቀበላሉ።

በአባቶች መነኮሳት፣ መናንያንና ባሕታውያን ታሪክ ውስጥ ራስ ከነ ምኞቱ የተዘነጋበትን ሕይወት እናገኛለን። በነገሥታት ቤተ መንግስት ውስጥ በምናኔ ከኖሩት መካከል ነቢዩ ዳንኤል አንዱ ምሳሌያችን ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ስለ እርሱ እንዲህ ተብሎ ተጽፎአል፦ «ዳንኤልም በንጉሡ መብልና በሚጠጣው ጠጅ እንዳይረክስ አሰበ . . .» ዳን 1:8። ስለ ጸሙም ዳንኤል እንዲህ በማለት ተናግሯል፦ «ማለፊያ እንጀራም አልበላሁም፣ ሥጋና ጠጅም በአፌ አልገባም፣ ሦስቱም ሳምንት እስኪፈጸም ድረስ ዘይት አልተቀባሁም።» ዳን 10:3።

እዚህ ላይ እንደ ዳንኤል ያለ በንጉሥ ቤተ መንግሥት ውስጥ እየኖረ ከባቄላ በስተቀር ምንም ዓይነት የሳመና የጣመ ምግብ ላለመብላት መወሰኑን ስንመለከት ራስ ወዴት ደረሰ እንላለን። ዳንኤል በአመራር ላይ ያለ ሰው ቢሆንም ማለፊያ እንጀራ እንኳን አልበላም። የጾም ልምምድ ራስን ድል ለመንሣትና በድንግልና ለመኖር የሚደረግ ሙከራ ነው።

ራስን ድል መንሣት።

የሥጋ ምኞትንና ፍላጎትን አስመልክቶ ጾምና ድንግልና ራስን ድል የመንሣት መንገዶች ናቸው። ነፍስን አስመልክቶ የሚጠቀስም ሌላ መንገድ አለ። ራሱን የሚገዛና እርሱነቱን ወደ ዓለማዊ ደስታ ከማዘንበል የሚያግድ ሰው ብፁዕ ነው።

ማንነት ልታይ ልታይ ሲል፣ ጉራውን ሲገልጥና ሊተብት ይችላል። በዚህ ሁሉ ግን ልንቃወመው ይገባናል። ለእኛ ከእግዚአብሔር ጋር መደሰትና መልካም የሆነውን ነገር ለመጪው ሕይወት ብናቆይ የሚሻለን መሆኑን ራሳችንን ልናሳምነው ይገባናል። በዚህ ዓለም ደስታን ለማግኘት በሚፈልጉ ሰዎች ላይ የመድኃኔዓለም ቃል ይመሰክርባቸዋል፦ « . . . እውነት እላችኋለሁ፦ ዋጋቸውን ተቀብለዋል።» ማቴ 6:5።

ስለዚህ በምድር ላይ ያሉ መብቶችህን ሁሉ ለማግኘት አትሞክር። እግዚአብሔር እያንዳንዷ ዕንባህን ከዓይኖችህ ላይ በሚጠርግበት በወዲያኛው ዓለም ቢሆንልህ ይሻልሃልና።

ማንነትህ ወይም ሥጋህ አሁን ላለህበት ዓለም ደስታ የሚያዘም ከሆነ በርትተህ ተከላከላቸው። በራስህ ወይም በሥጋህ ላይ የምትወስደው ይህ እርምጃ ጭካኔ አይደለም፤ለእነርሱ ዘላለማዊ ሕይወትን ማረጋገጫ እንጂ!

ራሱን በዚህ ዓለም ላለ የሚንከባከባት ያጠፋታል። ራስን በጥብቅ ከመቆጣጠር ችላ የሚል ሰው በእርሱ ላይ ኃይል እንዲኖረው ያደርጋል። ስለሆነም ራሱን ለጽድቅ ከሚያለማምደውና የእግዚአብሔርን መንገድ ከሚተገብረው ሰው በተለየ ሁኔታ በመንፈሳዊ ጠባዩ ላይ እንዲያምጽ ያደርገዋል።

ራስን ድል መንሣት የሚሰጠው መንፈሳዊ ደስታ ከሥጋ ደስታ ጋር እንደማይነጻጸር እርግጠኛ ሁን። ከሁሉ በጣም የሚያስደንቀው የራስ ጉራ ሙሉ ለሙሉ መጥፋት በሚገባው በመንፈሳዊ አገልግሎት ውስጥ ከፍ ከፍ ማለቱ ነው።

ማንነት በአገልግሎት መስክ ውስጥ።

አንድ ሰው ሥጋዊ ደስታን ሁሉ ድል አድርጎ ለራሱ በተጠንቀቀ ዘብ መቆሙን ዲያብሎስ ሲመለከት በዚህ ሰው ላይ ሌላ ዓይነት ውጊያ ሊከፍት ይሞክራል። ስለሆነም ማንነት በአገልግሎት መስክ ውስጥ ጉራውን እንዲያሳይ ዕድሉን ይከፍትለታል። ለአንድ ሰው በአገልግሎት ውስጥ ራሱን የሚያከብርበት፣ ጉራውን የሚገልጥበትና በዚህ የሚደሰትበትን ሁኔታ ለማሳየት በጣም ቀላል ነው።

ምንም እንኳ የሚናገራቸው ቃላት ለድኅነት የማያገለግሉና ክስተከቱ ርዕስ ውጪ የሚነገሩ ቢሆኑም ለአንድ ሰው በስብከት የራሱን እውቀት በጉራ ለማሳየትና ተሰጥኦውን ለመግለጥ በጣም ቀላል ነገር ነው። እዚህ ላይ ዲያብሎስ ሰባኪውን በሚያጠፋውና ለአድማጮቹ ምንም ዓይነት ጥቅም በማይሰጠው ስብከት በመደሰት ጥግ ላይ ቆሞ ይስቃል። አንድ አገልጋይ የሚያገለግላቸውን ሰዎች ለእግዚአብሔር ሳይሆን ለራሱ ጥቅም መቅረቡና አንድ ችግር ውስጥ ከገባ አነርሱን በቡድን በማሰባሰብ እንዲረዱት ማስተባበር ለእርሱ ምንኛ ቀላል ነገር ነው! ይህ በመሆኑ ራስ በጣም ይደሰታል!

የዚያኑ ያህል ከእንደዚህ ዓይነቶቹ ሰዎች የተለዩ መንፈሳውያን ሰዎች አሉ። እነዚህ ሰዎች ስብከትን የሚወስዱት አነርሱን እስከ ነፍሳቸው ጥልቀት ድረስ በመውሰድ ካነጻቸው በኋላ ከእግዚአብሔር ጋር አንድ የሚያደርጋቸው መንፈሳዊ ጥረት አድርገው ነው። አነርሱ በተገኘው መንገድ ወይም ዘዴ ሰዎችን የሚያነሣሱት ኃጢአቶቻቸውን እንዲተዉ፣ እግዚአብሔርን እንዲወዱና መልካም የሆነውን ሁሉ እንዲፈጽሙ ነው።

እነዚህን የመሰሉ መንፈሳዊ ሰዎችን የሚያሳስባቸው መንፈሳዊው ዓላማ ብቻ ነው። አድማጮችን «እገሌ አዋቂ ሰባኪ ነው!» በሚያሰኘው ስብከትና «ንስሐ ልንገባ እንፈልጋለን . . .» በሚያሰኘው ስብከት መካከል ከፍተኛ ልዩነት አለ። ዋናው ቁም ነገር ራሱን ሰባኪ፣ መምህር ወይም ወንጌላዊ መሆን አይደለም። ትክክለኛው ዓላማ ነፍሳትን ማዳን ነው። የተዋጣለት ሰባኪ የሚባለው ነፍሳትን ለእግዚአብሔር የሚያሰባስበው እንጂ ከአድማጮቹ ውዳሴን የሚያሰባስበው ሰባኪ አይደለም። ይህን አስመልክቶ መዝሙረኛው ዳዊት የተናገረው ቃል ምንኛ ድንቅ ነው! «ለእኛ አይደለም፣ አቤቱ ለእኛ አይደለም፣ ነገር ግን ለስምህ፣ ስለ ምሕረትህ፣ ስለ እውነትህም ምስጋና ስጥ።» መዝ 113:9።

ስብከት የሚጠቅመው ራስንና በራስ ውስጥ ያሉ ውጊያዎችን ለራስ ገልጦ ለማሳየት፣ ራስን ለመውቀስ፣ ራስን ለማስተማርና ራስን ለማሸነፍ ነው። ስብከት ማለት በፍርድ ቀን አንድ ሰው እኔ ይህን አላውቅም ብሎ ራሱን የሚወቅስበትን እውቀት ማስጨበጥ ማለት አይደለም። እያንዳንዱ ሰባኪ ስብከቱን በሚሰጥበት ጊዜ ከራሱነቱ ርቆ ሌሎችን በማዳን ላይ ቢያተኩር ብዙዎችን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለማሰገባት ምክንያት በሆነ ነበር።

በአገልግሎት መስክ ውስጥ ምሳሌ የሚሆነን መጥምቁ ዮሐንስ ስለ ጌታ «እርሱ ሊልቅ እኔ ግን ላንስ ያስፈልጋል።» (ዮሐ 3:30) ብሎ የተናገረው ቃል እጅግ ታላቅ ነው። ይህን በማድረጉም ዮሐንስ የሰዎችን ፍቅር ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ በመመለስ ራሱን ሸሽጓል። ምክንያቱም እርሱ የመጣው ስለ ጌታ ሊመሰክር እንጂ ስለ ራሱ ሊመሰክር ስላልሆነ ነው። «ሁሉ በእርሱ በኩል እንዲያምኑ ይህ ስለ ብርሃን ይመሰክር ዘንድ ለምስክር መጣ።» ዮሐ 1:7።

መጥምቁ ዮሐንስ የመጣው ሕዝቡ ሁሉ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲቀበሉት ለማዘጋጀት ነው። «እርሱም የተዘጋጁትን ሕዝብ ለጌታ እንዲያሰናዳ . . .» ሉቃ 1:17። እርሱ ራሱን በመደበቅ መልእክት ውስጥ ተሳክቶለታል።

እዚህ ላይ አገልግሎት የተሳካ የሚሆንባቸውን ሁለት እውነታዎች እንጠቅሳለን።

1- እግዚአብሔር ዓላማ ሊሆን ይገባል።

2- እግዚአብሔር መንገዱ ሊሆን ይገባል። ይህ በመሆኑም ማንነት እግዚአብሔር ዓላማውም ሆነ መንገዱ ሊሆን አይገባውም።

ይህን የምንለው ብዙ ሰዎች በአገልግሎት ውስጥ አብዝተው የሚታመኑት በራሳቸው ስለሆነ ነው። የሚታመኑት ጠባያቸውንና የሚናገሯቸው ቃላቶቻቸውን ተቀባይ በሚያስገኙላቸው በእውቀታቸው፣ በግል ተጽእኖአቸው፣ በዝናቸውና በክብራቸው ነው። ታዲያ እግዚአብሔር በዚህ ውስጥ ወዴት አለ?

እግዚአብሔር በአገልግሎት ውስጥ ከሌለ ደግሞ አገልግሎቱ ይወድቅና ራሱ ይገለጣል። ጸሎት እየቀነሰ ሲሄድም እግዚአብሔር አገልግሎቱን ስለማይባርከው እየደከመ ይሄዳል።

የመንፈሳዊ ሰዎችን አገልግሎት እግዚአብሔር ስለሚባርከውና ከእነርሱ ጋር ስለሚሠራ እንዲሁ ይታወቃል። ስለሆነም እግዚአብሔር እያንዳንዷን እርምጃ ይጠብቃል እንጂ ከአገሌና ከአገሉ ጋር አይሠራም።

ከዚህ በተጨማሪ በአገልግሎት መስክ ውስጥ ሰላም፣ ፍቅርና መተባበር አሉ። በዚህ ውስጥ እግዚአብሔር ይታይ ዘንድ እያንዳንዱ ራሱን መደበቅ ብቻ ሳይሆን ሌሎች ከእርሱ ይልቅ እንዲታዩ ሌላውን ከፊቱ ማስቀደም አለበት። በሌላ በኩል በአገልግሎት ውስጥ የጳውሎስ ነኝ የአጵሎስ ነኝ የሚሉ ካሉ ራስ ስለሚገለጥ መለያየት ተከትሎ ይመጣል።

ጌታ ሐዋርያቱ በመካከላቸው ማን እንደሚበልጥ ለመለየት ሲፎካከሩ ስለ ተመለከተ ሁሉም እኔነትን ከአጠገባቸው ያርቁ ዘንድ እንዲህ በማለት መክሮአቸው ነበር፦ «በእናንተስ እንዲህ አይደለም፤ነገር ግን ማንም ከእናንተ ታላቅ ሊሆን የሚወድ የእናንተ አገልጋይ ይሁን . . . እንዲሁም የሰው ልጅ ሊያገለግል ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም።» ማቴ 20፡26-28። ከዚህ በተጨማሪ «በወንድሞችህ መካከል በተቀመጥህ ጊዜ ሁሉ ታናሻቸውና አገልጋያቸው ሆነህ ተቀመጥ።» የሚለውን የአንድ መንፈሳዊ አባት ብሒል በጥሞና ልትመለከቱት ይገባችኋል።

የበላይነትን መውደድ አገልግሎትን ገድሎ የሚቀብር ክፉ ውጊያ ነው። ራስን ከመውደድ የሚመጡት ውድድርና ጉራም የሚያመሩት ተመሳሳይ ወደ ሆነ ፍጻሜ ነው። ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለዚህ ሁሉ መፍትሔ ይሆን ዘንድ የሰጠን መመሪያ ቃል «. . . በዝቅተኛው ስፍራ ተቀመጥ» (ሉቃ 14:10) የሚለው ነው።

ዝቅተኛው ስፍራ።

እዚህ ላይ ልንገልጽ የምንወደው ቦታውን ሳይሆን ማዕረጉን ነው። አንተ ባለህበት ቦታ ላይ ካሉት ሁሉ ራስህን በጣም ጠቃሚ አድርገህ አትገምት። የእንተን አሳብ ወይም ውሳኔ ወይም ሥልጣን ከሁሉም የሚልቅ አድርገህ አታስብ። ከሌሎቹ ሁሉ አንተ የምትደመጥ ወይም የምትከበር አድርገህ አትቁጠር። ይህ ካልሆነልህ የምትናደድና የምትቆጣ ትሆናለህና።

ለራስህ ክብር አትስጥ። ሌሎች እንዲያከብሩህም አታስገድዳቸው። በአንተ ውስጥ ያለውን የዋህነትና ትሕትና ተመልክተው ቢያከብሩህ ግን መልካም ነው። ክብር ከሰዎች ልብ በገዛ ፈቃድ ወይም ውዴታ የሚመጣ ስለሆነ ሰዎች እንዲያከብሩህ አታስገድዳቸው። አንድ ሰው እንዲታዘዝህ ልታስገድደው ትችላለህ። እንዲያከብርህ ግን አታስገድደውም። በሁለቱም ጉዳዮች ላይ ኃይል እንደ ራስ አገዛዝ ይቆጠራል።

ከሌሎች ጋር በምታደርገው ድርድር ውስጥ የነፋስ ሽውታ ሁን እንጂ ማዕበል አትሁን። የብዙዎች መገለጫ ኃይል ስለሆነ እነርሱ የሚመሰሉት በማዕበል ነው። የነፋስ ሽውታ የሚወክለው ግን ራሱን በካደ ሰው ውስጥ ያሉትን የዋህነትና ትሕትና ነው። ከዚህ በተጨማሪ ከሌሎች ጋር በምታደርገው ድርድር ውስጥ ለራስህ አታድላ።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ «. . . እርስ በእርሳችሁ ተከባበሩ . . .» (ሮሜ 12:10) ይላል። እንዲህ ያለው መከባበር ከልብ ጥልቀት፣ ከልብ ትሕትና እና ያለ ምንም ሽንገላ መሆን አለበት።

ሌላው ከሰዎች ጋር በሚደረግ ድርድር ውስጥ ያለው ጉዳይ ኢየሱስ ክርስቶስ በተራራው ስብከቱ ውስጥ የተናገረው ቃል ነው።

ሁለተኛው ምዕራፍ።

ጌታ እንዲህ ብሏል፦ «. . . እጀ ጠባብህንም እንዲወስድ ለሚወድ መጎናጸፊያህን ደግሞ ተውለት፤ማንም ሰው አንድ ምዕራፍ ትሄድ ዘንድ ቢያስገድድህ ሁለተኛውን ከእርሱ ጋር ሂድ።» ማቴ 5:40-41። ከዚህ ጋር ተመሳሳይ በሆነው ትዕዛዙ ውስጥ «. . . ዳሩ ግን ቀኝ ጉንጭህን በጥፊ ለሚመታህ ሁሉ ሁለተኛውን ደግሞ አዙርለት» ብሏል። ማቴ 5:39። በእነዚህ ሁሉ ጌታ፦ «ተበደሉ እንጂ አትበድሉ፤ተሰቀሉ እንጂ የምትሰቅሉ አትሁኑ፤እናንተ አትበቀሉ!» የሚል ነው የሚመስለው።

በዚህች ምድር ላይ እኔነት መብቱን በተቻለ ፍጥነት በራሱ ለማስከበር ነው የሚፈልገው። ኢየሱስ ክርስቶስ ግን ራስን በመካድ ስብከቱ ውስጥ «. . . ክፉውን አትቃወሙ» (ማቴ 5:39።) በማለት አስተምሯል። መብትህን ለማስከበር ወይም ለመበቀል ራስህን አታነሣሣ። ይህን በማስመልከት መጽሐፍ ቅዱስ «. . . ራሳችሁ አትበቀሉ፣ ለቁጣው ፈንታ ስጡ እንጂ፣ በቀል የእኔ ነው . . .» (ሮሜ 12:19) በማለት ይመክረናል። ከዚህ በተጨማሪ መጽሐፍ ቅዱስ «ፍቅር ብቻዬን ይድላኝ አያሰኝም . . .» (1ኛ ቆሮ 13:5) ብሎ ይናገራል። በቀል የእግዚአብሔር ከሆነ ይህን ከእርሱ ለማግኘት አትፈልጉ። ፍቅር ብቻዬን ይድላኝ የማይለው ለምንድር ነው? ለዚህ ምክንያቱ ከራስነት ስለ ተራቆተ ነው።

ራስህን የማታከብር ከሆንህ በተመሳሳይ መልኩ ራስህን መንቀፍ አለብህ። በአንድ ሰው ድርድር ውስጥ የችግሮች ሁሉ ችግር የሆነው ራስን ሙሉ ለሙሉ ትክክል አድርጎ ማቅረብ ነው።

ራስን መንቀፍ።

ራሱን የማይነቅፍ ሰው እርሱ ትክክል እንደ ሆነና እንዳልተሳሳተ አድርጎ ስለሚያስብ ምንም ዓይነት ስህተት ቢሠራ እንኳ ይቅርታ አይጠይቅም። ከወንድሙ ጋር ሲጋጭ ከእርሱ ጋር ለመታረቅ ራሱን አያነሣሣም። እርቁ እንዲመጣ የሚፈልገው ከሌላ ወገን ነው። ግን ለምን? ይህን የሚያመጣው ማንነት ነው! ሌላው ቢቀር እኔነቱ ምንም ዓይነት ስህተት እንዳልሠራ አድርጎ ስለሚያሳምነው ስህተቱን በእግዚአብሔር ፊት እንኳ አይናዘዝም።

ራስን መንቀፍ የሚመጣው ከትሕትና ሲሆን ትሕትና ደግሞ ራስን ወደ መካድ ይመራል። ትሑት ያልሆነ ሰው ራሱን አይነቅፍም አይኮንንምም። ሁልጊዜ የሚነቅፈውም ሆነ የሚኮንነው ሌሎችን ነው። እንዲህ ዓይነቱን ሰው ለምን ሌሎችን እንደሚነቅፍ ብትጠይቁት ይህን በማለታችሁ ብቻ እንኳ ይገሥጻችኋል።

አንድ ራሱን ምንጊዜም በዓለማዊ ዘዴዎች የማያነላና የማያከብር ሰው ዋናውና ተቀዳሚው ዓላማው ራሱን ከስህተትና ከጥፋት ማንጻት ነው። እንዲህ ዓይነቱ ሰው ሁልጊዜ ራሱን ይወቅሳል፣ ስህተቶቹን ይመረምራል፣ ለስህተቶቹም ማስተካከያ ይወስዳል።

በአንድ ወቅት ጻጻሱ ቴዎፊለስ መነኮሳት አባቶች የሚኖሩበትን በአት ሲጎበኙ የዚያ ቦታ አስጎብኚ ለሆኑት መነኩሴ በዚህ ሳሉ ስለገጇቸው ቅድስናዎች ሲጠይቋቸው «አመኑኝ አባቴ! ከሁሉም ነገር በላይ ራስን ከመውቀስ የሚበልጥ ቅድስና የለም!» በማለት መልሰውላቸዋል። ይህ አንድ ሰው ራሱን ብቻ እንጂ ሌሎች ሰዎችን፣ አካባቢውንና እግዚአብሔርን የማይወቅስበት መንፈሳዊ መንገድ ነው።

ራሱን በዚህ ዓለም ላለ የወቀሰ ሰው በወዲያኛው ዓለም ከመወቀስ ይድናል። ሰው ራሱን የሚወቅስበት ምክንያት ወደ ንስሓ ለመቅረብ ነው። ንስሓ ከገባ ደግሞ እግዚአብሔር ኃጢአቱን ይቅር ይለዋል። ራስን ከማክበር አንፃር ራሱን የማይወቅሰው ሰው ግን ሳይሻሻል በኃጢአት ውስጥ በመወቀስ ይኖራል።

ቅዱስ እንጦንስ «እኛ ራሳችንን ከወቀስን ዳኛው በእኛ ይደሰታል።» ብሎ የተናገረው ቃል ምንኛ እውነት ነው! ከዚህ በመቀጠልም «እኛ ኃጢአቶቻችንን የምናስታውሳቸው ከሆነ እግዘአብሔር ይረሳልናል፤ እኛ ኃጢአቶቻችንን የምንዘነጋቸው ከሆነ ግን እግዚአብሔር ያስታውሰናል።» በማለት ተናግሯል።

ራስን መውቀስ ከሰዎች ጋር ለመታረቅ ይረዳናል። ሰውን «አንተ ትክክል ነህ። ይህን ጉዳይ አስመልክቼ የተሳሳትሁት እኔ ነኝ . . . » በማለት ይቅርታ መጠየቅ ትችላለህ። እነዚህ ቃላት የወንድምህን ቁጣ ስለሚገቱት ይታረቅሃል። ይህን ሳታደርግ ራስህን ነጻ ለማውጣት የምትከራከር ከሆነ ግን ጠላት ስህተትህን ለማጋለጥ ማንም አይደርስበትም።

ይህን አስመልክቶ ቅዱስ መቃርስ የተናገረው አባባል ምንኛ ድንቅ ነው! «ወንድሜ ሆይ! ሌሎች ሳይወቅሱህ በፊት አንተ ራስህን ውቀስ!»

ምዕራፍ ሦስት።

ባዶነት

- ትርፍ ጊዜ።
- የሕሊና ባዶነት።
- መንፈሳዊ ባዶነት።
- የስብእና ባዶነት።
- ስሜትን የሚነካ ባዶነት።

በመንፈሳዊ መስክ ላይ ሰውን ብዛት ያላቸው መንፈሳዊ ውጊያዎች ሊገጥሙት ይችላሉ። ከእነዚህ መካከል አንዳንዶቹ ከውስጥ፣ ሌሎቹ ከውጪ፣ ሌሎቹ ከዲያብሎስ፣ ሌሎቹ ደግሞ ከአካባቢ የሚመጡ ናቸው።
ባዶነት የተለያዩ ዓይነቶች አሉት።

ትርፍ ጊዜ።

ሥራ የፈታ ሰው ደካማ ነው። ሰው ትርፍ ጊዜውን በተሳሳተ መንገድ ለማጥፋት ከመረጠ ትርፍ ጊዜያት ወደተለያዩ መንፈሳዊ ስህተቶች ሊመሩት ይችላሉ።

እግዚአብሔር አምላክ አባታችን አዳምን ከፈጠረው በኋላ ያለ ምንም ሥራ እንዲሁ አልተወውም። ይህን አስመልክቶ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦ «እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ወስዶ ያበጃትም ይጠብቃትም ዘንድ በዔድን ገነት አኖረው።» ዘፍ 2፡15። በገነት ውስጥ ለኑሮ የሚያስፈልጉ ነገሮች በሙላት ስለ ነበሩ አዳምና ሔዋን ሥራ የሠሩት ኑሮአቸውን ለማሳካት አልነበረም። ያለ ሥራ መቀመጣቸው ችግር ባያመጣባቸውም እንኳ ያለ ሥራ እንዲቀመጡ አልተፈለገም ነበር። እነርሱ ያለ ሥራ በተቀመጡ ጊዜ ኃጢአት ሳይፈትናቸው አልቀረም። በዚያን ጊዜ በሥራ ተጠምደው ቢሆን ኖሮ ሰይጣን ሊያዋራቸውም ሆነ ሊፈትናቸው ዕድሉን አያገኝም ነበር።

ሌላው ቢቀር መነኮሳት እንኳ ሥራን የሕይወታቸው ክፍል አድርገው ሊሠሩ ይገባቸዋል። ይሁን እንጂ ይህ መንፈሳዊ ተግባራቸውን በማይሻማ መልኩ ሊሆን ያስፈልጋል። "The Paradise of Monks" በሚለው መጽሐፍ ውስጥ የእጅ ሥራ እስከ አሁን ድረስ በመነኮሳት አባቶች የሚተገበር ቋሚ ሥራ እንደ ሆነ እናነባለን። አንድ መነኩሴ የምንኩስና ሕይወቱን ሲጀምር ሙሉ ጊዜውን በጸሎት የሚያሳልፍበት አቅም አይኖረውም። በዚህ መሠረት ትርፍ ጊዜ ሕይወቱን እንዳያጠፋው በሚኖርበት ገዳም ሥራ ይሰጠዋል። ሥራ መነኩሴው በገዳሙ አገልግሎት ውስጥ እንዲሳተፍና ለወንድሞቹ ፍቅር እንዲያሳይ ይረዳዋል። ከዚህ በተጨማሪ ከወንድሞቹ ጋር በመነጋገር ስህተቱን እንዲያውቅና እንዲያርምም ያግዘዋል።

ትርፍ ጊዜ በሰው ላይ የመሰላቸትና የመታከት ስሜት ከመፍጠሩም በላይ ሰውየው ራሱን ዘና በማድረግ መደሰቻውን እንዲፈልግ ያደርገዋል። በዚህ ጊዜ የተሳሳተ መደሰቻ ሊመርጥ ይችላል። አንድ ሰው ከሌሎች ሰዎች ጋር ከንቱ

ወሬ በማውራት የራሱንና የእነርሱን ጊዜ ከማጥፋቱም በላይ ያደክማቸዋል። ከዚህ በተጨማሪ ወደ መዝናኛ ሥፍራዎች፣ ወደ ቡና ቤቶችና ወደ ካፌቴሪያዎች በመሄድ የተሳሳቱ ሥራዎችን ሊፈጽም ይችላል። አንዳንዶች ደግሞ ምንም ዓይነት ዓላማ ለሌለው ጉዳይ «ነፋስ እንቀበል!» በማለት ይንቀዋለላሉ።

ከዚህ ሌላ አንድ ሰው ትርፍ ጊዜውን ከሌሎች ጋር በማሳለፍ የእርሱንም የእነርሱንም ጊዜ በከንቱ ያሳልፋል። እንዲህ ባለው ጊዜ ማሳለፍ ውስጥ ያለ ሥራ መቀመጡ ለእርሱም ሆነ ለሌሎች ሕይወት ብዙ ጥቅም ሊያስገኝ የሚችለውን ጊዜ በከንቱ እንዲባክን ያደርጋል።

ጊዜውን የሚያባክን ሰው የሕይወቱን ዋጋ ያልተረዳ ለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም። ምናልባትም ሊያሳካ የሚፈልገው ታላቅ ዓላማ የሌለው ሰው ሊሆን ይችላል። ከዚህ በተቃራኒው ታላቅ ዓላማውን ከፊት ለፊቱ በማስቀደም ይህንኑ ዓላማውን ይጨብጥ ዘንድ ሙሉ ጊዜውን በዚህ ላይ የሚያሳልፍ ሰው አለ። ይህ ሰው አሁን ካለው ጊዜ በተጨማሪ ሌላ ጊዜ አንዲያገኝ ይፈልጋል። ይሁን እንጂ አያገኝም።

ሰለሆነም የእናንተንና የልጆቻችሁን ትርፍ ጊዜ ጥቅም በሚያስገኝ ነገር ላይ ልታሳልፉት ይገባችኋል። ምናልባት አንዳንዴ በልጆች በሚፈጠር ሁካታ ስለምትናደዱ ለእነርሱ ግብረገብ በማስተማር ውስጥ እነርሱን ትወቅሳላችሁ፣ ትገሥጻላችሁ፣ በእነርሱ ላይ ትጮኻላችሁም። በመቀጠልም ትእዛዛቶቻችሁንና ክልከላዎቻችሁን፣ ማስፈራሪያዎቻችሁንና ቅጣቶቻችሁን ታወርዱባቸዋላችሁ። ለልጆች ዓይነተኛው ችግር ግን ትርፍ ጊዜ ነው። ስለሆነም ትርፍ ጊዜዎቻቸውን በትክክል እንዲጠቀሙ ካደረጋችሁ እነርሱም እናንተም ችግሩን ልታቃልሉ ትችላላችሁ። ስለዚህ ልጆቻችሁ ትርፍ ጊዜዎቻቸውን በሚጠቅም ጉዳይ ላይ እንዴት ማሳለፍ እንዳለባቸውና እናንተም በዚህ እንዴት ልትደላደሉ እንደምትችሉ አስቡ።

እዚህ ላይ አንድ ጥያቄ ልጠይቃችሁ . . . «ትርፍ ጊዜያችሁን የምታሳልፉት እንዴት ነው? በትክክለኛው መንገድ ነው? በሚጠቅም መንገድ ነው? እንዴት ነው?»

እንደዚህ ያለውን ጊዜ የምታሳልፉት ለመንፈሳዊና ለአዕምሮአዊ ዕድገት ነው ወይስ ሌሎችን ለማገልገል ወይስ ለማይጎዳ ደስታ ወይስ ለሰዎች ፍቅር ለማሳየት ወይስ እነርሱን በመጠየቅ ነው? ትርፍ ጊዜያችሁን የምታሳልፉት ሙሉ ጊዜያችሁን በሚወስደውና የተጣለባችሁን ኃላፊነት እንዳትወጡ የሚያደርጋችሁን ሬዲዮ በማዳመጥና ቴሌቪዥን በመመልከት ነው? እዚህ ላይ ሌላ አንድ ጥያቄ ልጠይቃችሁ . . . የትርፍ ጊዜን ችግር ለማከም በምታደርጉት ጥረት ውስጥ መንፈሳዊ ባዶነት ውስጥ ትወድቃላችሁ?

የሕሊና ባዶነት።

አንዳንዱ ትርፍ ጊዜ ሕሊና ያለ ሥራ ወደሚቆይበት ወደ አዕምሮ ባዶነት ሊመራ ይችላል። በዚህ ጊዜ ዲያብሎስ ሕሊናን በመቆጣጠር አሳቡን

ያስገባል። እዚህ ላይ «የሰነፍ ሰው ሕሊና የዲያብሎስ ቤተ መከራ ነው» የሚለው አባባል ሊጠቀስ ይችላል።

በመሆኑም ያለ ሥራ የሚሆን ምናኔ ወይም ብቸኝነት አደገኛ ነው። ሕሊናን የሚቆጣጠረው መንፈሳዊ አሳብ ከሌለ ፍሰጋውን ሰቆ በመውጣት በኃጢአት አሳብ ይሞላል። የምናኔ መንፈሳዊ ትርጉም ከእግዚአብሔር ጋር ብቻ መሆን ማለት ነው እንጂ ባዶነት ማለት አይደለም። ሌላው የሕሊና ባዶነት ዓይነት የእውቀት ይዝውም የጠቃሚ እውቀት ጉድለት ነው።

ሕሊናውን በጠቃሚ መንፈሳዊና ለእርሱ በሚበጁ አጠቃላይ ባሕሳዊ ጉዳዮች የማያሳድግ ሰው በሕሊና ባዶነት ውስጥ ስለሚወድቅ ለሰዎች የሚናገረውን ጠቃሚ ወይም ጥልቅ ነገር ያጣል። ሴት ልጅን ማስተማር ወድቃበት ከነበረው ከጨለማው ዘመን የአዕምሮ ባዶነት እንድትወጣ አድርጓታል። በየሀገሩ የሚኖሩ ሰዎችን ማስተማርም ከሕሊና ባዶነት አዘቅት ውስጥ አውጥቷቸዋል።

ለሰዎች የሚነገራቸው ነገር ባዶ እስካልሆነ ድረስ ቃሉን አስተምሮ እነርሱን ከሕሊና ባዶነት ማውጣት በጣም አስፈላጊ ነገር ነው። ትምህርቶቻቸውንና ስብከቶቻቸውን አዘጋጅተው ለመቅረብ የማይጠነቀቁ አገልጋዮች የሚያጋጥማቸው ባዶነት ነው። እነርሱ ለአድማጮቻቸው የሚያቀርቡት እንዳችም ጠቃሚ ነገር የላቸውም። እነዚህ ሰዎች ጥልቀት የሌለው፣ ጉጉት የ ግያመጣ፣ ተጽእኖ የማያሳድር፣ የተለመደና ተደጋጋሚ ትምህርት ስለሚያቀርቡ ባዶ ለሆኑ ሰዎች ናቸው። ልክ እንደ እነርሱ በውስጣቸው መንፈስ ቅዱስ ሳይኖረ ታይታን ሊያቀርቡ የሚፈልጉ ሰዎች አሉ። ወደ ልብ የማይገባ ተራ እውነትና መረጃ መንፈስን ባዶ ያደርጋል። ይህ ደግሞ ወደሚቀጥለው ርዕስ ያስገባናል።

መንፈሳዊ ባዶነት።

እግዚአብሔር አምላክ በመጀመሪያው ሰው ውስጥ ያለችውን ነፍስ የፈጠረው በምሳሌውና በአርአያው ነው። ስለሆነም ከእርሱ በስተቀር ይህቺን ነፍስ ሊያስደስታት የሚችል ማንም የለም። ከእግዚአብሔር ፍቅር ተለይታ የምትኖር ነፍስ ባዶነት ይለማታል። ምንም ዓይነት ነገር ቢቀርብላትም ሊያስደስታት አይችልም።

ሙሉ ጊዜያቸው በተለያዩ ጉዳዮች የተያዘባቸው፣ ታላቅ እቅድ የሚያከናውኑና ብርቱ ኃላፊነቶቻቸውን የሚፈጽሙ ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ። እነዚህ ሰዎች በጣም ሰፊ እውቀትና ጥልቅ ጥናት ያጠኑ ሰዎች ቢሆኑም የሚኖሩት በመንፈሳዊ ባዶነት ውስጥ ነው። እነዚህ ሰዎች በሚያደርጉት ምንም ዓይነት ነገር በእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ የተፈጠሩ ነፍሳቸውን ማስደሰት አይችሉም። እነርሱ የሕይወታቸውን ጊዜ በትግል የሚያሳልፉት ከብዙዎቹ እቅዶቻቸው መካከል በጣም ጥቂቱን ብቻ ለማከናወን ነው።

እነርሱን በልባቸው ውስጥ ያለ ፍላጎት ነገር ግን እነርሱ ያልተገነዘቡት የመንፈሳዊ ስሜት ባዶነት ሁልጊዜ ይቆጠቁጣቸዋል። ከእግዚአብሔር ጋር

በሚኖር ጥብቅ ግንኙነትና ለእርሱ በሚሆን ፍቅር ካልሆነ በስተቀር ይህ ፍሳሳት ሊረካ አይችልም። የእነዚህ ሰዎች ነፍስ ከሥጋቸውና ከበስባሹ ሰውነታቸው ተለይታ ስትሄድ በእርግጥም በዚያን ጊዜ ምን ያህል ባዶ እንደ ነበሩ ያውቃሉ። ይህን ባዶነት በውስጡ ያለፉበት ዓለማዊ ልምድ ሊሞላው አይችልም። ስለዚህ ካሁን በኋላ በዚህ ዓለም ውስጥ ስንኖር «መንፈስ ይሙላባችሁ . . .» (ኤፌ 5:18) ለሚለው ለሐዋርያው ለቅዱስ ጳውሎስ ቃል ታዛዦች ነን።

ልብህን በእግዚአብሔር ሳትሞላ ሕይወትህን ብዛት ባላቸው ነገሮች ብትሞላ አንዳችም የሚጠቅምህ ነገር አይኖርም። ሰው ወደ ማሽንነት ተለውጦ ሁልጊዜ ያለ መንፈስ በእንቅስቃሴና በኃይል የሚሽከረከር መሆኑ ምንኛ ቀላል ነው? ይህ ሰው ምንም የበዙ ሥራዎችን የሠራ ቢሆንና የነበረው ጊዜ በሥራ የተወጠረ ቢሆንም ይህ ሰው ባዶ መሆኑን እግዚአብሔር ቁልቁል ይመለከተዋል። ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር ለሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን አለቃ የተናገረውን ቃል ይሰማል። «ሀብታም ነኝና ባለ ጠጋ ሆኜአለሁ አንድም አያስፈልገኝም የምትል ስለ ሆንህ ጎስቋላና ምስኪን፣ ድሀም፣ ዕውርም፣ የተተራቆትህም መሆንህን ስለማታውቅ . . .» ራዕ 3:17።

ስለሆነም በእግዚአብሔር ፍቅርና እውቀት የተሞላህ ሁን። ምክንያቱም ልብህ ከእግዚአብሔር፣ ከፍቅሩና ከእውቀቱ ከተለየች ነፍስህ ባዶነት ስለሚሰማት ነው። እግዚአብሔር መልካም መሆኑን ቀምሶ ማየት ለአንተ ስላልሆነልህ ነው እንጂ በእርሱ ትሞላ ነበር። አንተ ብትቀምስ ደግሞ ለሌሎች ሞልተህ ታፈስ ነበር። በአንተ ውስጥ ያለው ፍቅር የአነርሱንም ልብ በፍቅር ይሞላል። በአንተ ውስጥ ያለው ሰላም ሕይወታቸውን በሰላም ይሞላል። በአነርሱ ዘንድ ያለው መንፈስም በመንፈስ እንዲኖሩ ይመራቸዋል።

እግዚአብሔር ዘላለማዊ ሕይወት ይሰጣቸው ዘንድ ነፍሶቻችሁ ወደ ሰማይ ሲያርጉ መመለክቱ ምንኛ ውብና ድንቅ ነው! የሚያርጉት በፍቅር፣ በደስታ፣ በሰላም፣ በአምነትና በሌሎቹም የመንፈስ ፍሬዎች ታጅበው ነው። ገላ 5:22። ለዛፍ የሚያስፈልጉትን ውኃና ፍግ ከሰጣችሁት የምትፈልጉትን ፍሬና አበባ ሊሰጣችሁ ይችላል። እናንተም ነፍሶቻችሁ በመንፈስ ፍሬዎች ይሞሉ ዘንድ መንፈሳዊውን ምግብ ልትበሉ ይገባችኋል።

አሁን የመንፈስ ባዶነት ይሰማችኋል? ከተሰማችሁ በማንኛውም የእግዚአብሔር ጸጋ ተሞሉ። ለነፍሳችሁ ጥልቅ መንፈሳዊ መመሪያ አቅርቡላት። ከሁሉም በላይ ደግሞ ለቃለ እግዚአብሔር ቅድሚያ ስጡ። ነፍሳችሁ የምትሻውን መንፈሳዊ ተመስጦ፣ ጸሎት፣ ዜማና መዝሙር አቅርቡላት። ኤፌ 5:19። ነፍሳችሁን ከእግዚአብሔር ጸጋ በማሳጣት ባዶዋን አትተዉአት።

የመንፈስ ብርታት ሰብእናን ሲያበረታ የመንፈስ ባዶነት ግን ወደ ሰብእና እጦት ይመራል። ይህም የሰብእና ባዶነት ወደሚለው ርዕስ ያሸጋግረናል።

የሰብእና ባዶነት።

አንድ ሰው ሰብዕናው ባዶ ሲሆን፣ በማኅበረሰቡ ውስጥ ዋጋ ሲያጣ፣ ፍሬ አልባ ሲሆንና ለውጥ ማምጣት ሲሳነው መመልከት ምንኛ ከባድ ነገር ነው! አንድ ሰው እንዲህ ያለው ስሜት በውስጡ እንዳለ ሲታወቀውና ሰብእናውን፣ ጥልቀቱን፣ አሳቡን፣ እውቀቱን፣ ኃይሉን ማጣቱን ሲመለከት መንፈስ ደካማ መሆኑን ይረዳል። በዚህ ጊዜ የበታችነት ስሜት ስለሚሰማው ይህን ጉድለቱን በሌላ ጉድለት ለመሸሸግ ይሞክራል። የሰብእናውን ባዶነት በመሙላት ፋንታ የመጀመሪያ ባዶነቱን ለመሸፈን በሚያደርገው ጥረት በሕይወቱ ውስጥ ሌላ ባዶነት ይደምራል። ይህም ከንቱ ነው . . . የዚህ የተሳሳተ መፍትሔ አሠራሮች ምንድር ናቸው?

አንድ ሰው ይህ ባዶነቱ እንዳይሰማው ሲፈልግ ራሱን በቁም ቅዠት ሊያስደስት ይሞክራል። በመሆኑም ይህ ሰው የሚኖረው በሕልማዊው ዓለም ላይ እንጂ በእውነተኛው ላይ አይደለም። እነዚህ ሕልሞች ግን ለእርሱ ምንም የሚጠቅሙት ነገር የለም። ምክንያቱም እርሱ ከቁም ቅዠቱ ሲነቃ ማንኛውም ዓይነት ሕልም ሊቀይረው ከማይችለው የሚያም እውነታ ጋር እንዲፋጠጥ ስለሚያደርገው ነው። ሌላው ሰው ደግሞ ማውራቱ ስብእናውን የሚቀይርለት ይመስል የባዶነት ስሜቱን ብዙ በማውራትና በመለፍለፍ ለማከም ይሞክራል። ሰዎች የዚህ ዓይነቱን ሰው ወሬ ሥራ አስፈቺ አድርገው ስለሚመለከቱት በእርሱ ይሰላቻሉ።

ሰው ባዶ ሰብእናውን ለመሸሸግ ሲሞክር በሰዎች ፊት ራሱን ማወደስ ይጀምራል። እንዲህ ዓይነቱ ሰው እርሱ የሠራቸውን «ታላላቅ» ሥራዎቹ ወይም ሌሎች የሠሩትን ሥራ እርሱ እንደሠራው አድርጎ በሰዎች ፊት ያቀርባል። አልፎ ተርፎም የሰዎችን ሂስ ሙሉ ለሙሉ በመደፍጠጥ እነርሱን አዋርዶ እርሱ የሚልቀውን እውቀት እንደ ጨበጠና ከሂስ በላይ እንደ ሆነ ለማሳየት ይሞክራል። እርሱ ምንም አለመሥራቱን ሲመከሉት የእነርሱ እንቅስቃሴ ስለሚያናድደው የእነርሱን ሥራ ይቃወማል። ወይም በመጀነን ተቀምጦ ባዶነቱን በሀብትና በማሸብረቅ በመደበቅ በመልኩና በድምፁ ኩራቱን ሊገልጥ ይወዳል።

ከዚህ ጋር ተመሳሳይ የሆነችው ምሳሌ ሴት ደግሞ ባዶ ሰብእናዋን በማጌጥ፣ በመኪኗል፣ ወርቅና ሌሎች የከበሩ ጌጣ ጌጦችን በማጥለቅ ለመሸሸግ የምትሞክረዋ ናት። ይህን አስመልክቶ ዳዊት የሚናገረው ግን ተቃራኒውን ነው። «ለሐሴቦን ንጉሥ ልጅ ግን ሁሉ ክብርዋ ነው።» መዝ 44:13። ይህቺ ልጅ የኖረችበት ያ ማኅበረሰብ በሰብእና ባዶነት ለተጎዳው ለዚህ ማኅበረሰብ ሕሊናውን ሊይዝ የሚችልና ሥራ ፈት የሆነ ችሎታውን እንዲጠቀም ያደርግ ዘንድ እመኛ ለሁ። እያንዳንዱ ሰው የግል ችሎታውን ፈልጎ በማግኘት ለበጎ ነገር እንዲጠቀምበት እመኛለሁ። የሰብእና ባዶነት የሚሰማው ማንኛውም ሰው አውነቱን ለመሸሸግ የተሳሳቱ ዘዴዎችን ከመጠቀም ይልቅ ባዶነቱን ቢሞላ ይሻለዋል።

እያንዳንዱ ሰው በየዕለቱ ዛሬ ምን የሚጠቅም ሥራ ሠራሁ ብሎ ራሱን መጠየቅ አለበት። ከዚህ በኋላ ራሱን ለማስደሰት ብቻ ሳይሆን ከፍቅር በሆነ

መነሣሣት ጎብረተሰቡንና መልካም የሆነውን ሁሉ ለማስደሰት መድከም አለበት። በዚህ ምክንያት መደሰትን አስቦበት ሳይሆን እንዲሁ ዝም ብሎ ይደሰታል። እያንዳንዱ ሰው ባለው ኃይል ሁሉ ሊያገኘው የሚሞክረው ታላቅ ዓላማ እንዲኖረው እመኛለሁ። ዓላማው መንፈሳዊና ጠቃሚ እስከሆነ ድረስ እርሱን ለማግኘት መሥራቱ ሰውየውን ስለ ባዶነት ከማሰብ ያድነዋል።

እዚህ ላይ መልካም ምኞት ባዶነት እንዳይሰማ የሚያደርግ ዓይነተኛ መፍትሔ ሊሆን ይችላል። ይህ ሊሆን የሚችለውም ተገቢና ነጻ በሆነ መንገድ ከራስ ወዳድነትና ከግብዝነት የራቀ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው። ባዶነትን አስመልክቶ የተጠቀሰው ሌላ ነጥብ የሚከተለው ነው።

ስሜትን የሚነካ ባዶነት።

ይህ ሁለት ዓይነት ነው . . .

• የመጀመሪያው ዓይነት በውስጡ ሁሉን የሚችል ልብ ያለው ሰው ቢሆንም ማንም ይህንን ሊሞላለት ያልቻለ ሰው ነው።

ይህ ሰው ፍቅሩን ሊለግስ ቢፈልግም ለማን እንደሚለግስ ግን አያውቅም። ስለሆነም ከመስጠት አንጻር ባዶነት ይሰማዋል። ይሁን እንጂ ይህን ሰው አክሞ መመለስ ቀላል ነው። እንዲህ ዓይነቱ ሰው በአገልግሎት መስክ ውስጥ ፍቅሩን በመለገሱ ደስታ እንደሚሰማው ምንም ጥርጥር የለውም። ሕፃናትን፣ እናትና አባት የሌላቸውን ልጆች፣ የተቸገሩትን፣ ድሆችን፣ አካል ጉዳተኞችን፣ የታመሙትንና ችግር ያለባቸውን ሰዎች ሁሉ ማገልገል ልቡን ያስደስተዋል። እዚህ ላይ ግን ስሜት የሚነካ ባዶነት ያለባቸው ሰዎች እንዳያፈነግጡ ላስጠነቅቅ እወዳለሁ።

• ሁለተኛ ዓይነቶቹ ደግሞ ፍቅርን የሚፈልጉ ሆነው በሰዎች ሊፈቀሩ የማይችሉ ሰዎች ናቸው።

ለእነዚህ ሰዎች ምሳሌ የምትሆነን ፍቅር በጠፋበት ቤተሰብ ውስጥ የምትኖር ልጃገረድ ናት። የዚህች ልጅ አባት ቁጥጥር መጥፎ ስለሆነ ሁልጊዜ ይቆጣታል ይገሥጻታልም። እናቷም ጨካኝ ስለ ሆነች ከእርሷ ምንም ዓይነት ርኅራኄ አታገኝም። ከወላጆቻቸው ወይም ከቤተሰቦቻቸው ምንም ዓይነት ፍቅር ወይም ርኅራኄ ባለማግኘታቸው አፈንግጠው የሚወጡ ልጃገረዶች ብዙ ናቸው።

እንዲህ ባለው የስነ ልቦና ሁኔታ ውስጥ ያለችው ልጃገረድ የተሳሳተ ፍቅር የሚሰጣት ሰው ላይ ወይም ይህን የሚመስል ፍቅር ላይ ልትወድቅ ትችላለች። ቢሆንም ግን እርሷ የምትፈልገው የሚያፈቅራትን ማንኛውንም ዓይነት ልብ ስለሆነ ይህን ፍቅር ሳታመነታ ትቀበላለች። እዚህ ላይ ወላጆች ወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸው ከእነርሱ ፍቅር በማጣት እንዳያፈነግጡ ለልጆቻቸው ፍቅር እንዲሰጡአቸው እንመክራለን። ከዚሁ ጋር ልጆችም ከወላጆቻቸው

ሊያገኙት የሚፈልጉትን ፍቅር በተገቢው መንገድ መፈለግ እንዳለባቸው እናሳስባለን።

በእርግጥም እንደዚህ ያለውን ፍቅር በእግዚአብሔርና በመንግሥቱ ውስጥ፣ በንጹሕ የየዋህነት ጓደኝነት ውስጥ፣ በአገልግሎት መስክና በመስጠት ውስጥ ያገኙታል። ለሌሎች ሰዎች የተቀደሰ ፍቅርና ርኅራኄ የሚሰጥ ሰው በተመሳሳይ ጊዜ እርሱ ከሰጠው ፍቅርና ርኅራኄ የሚበልጥ ፍቅር ለእርሱ ይኖረዋል። ዋናው ነጥብ ሊናገሩም ሆነ ሊሰጡ ልብን ጥልቅ በሆነ ስሜት መሙላት ነው። መስጠት ማለት ደግሞ በሌላ መልኩ መቀበል ማለት ነው።

ነቢዩ ዳዊት በዮናታን ጓደኝነት ውስጥ ያገኘው ፍቅር ከሴት ፍቅር የሚበልጥ ፍቅር ነበር። 2ኛ ሳሙ 1:26። ጌታ የሚወደው ቅዱስ ዮሐንስ ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ያገኘው ፍቅር በዓለም ውስጥ ካለው ፍቅር እጅግ የሚበልጥ ፍቅር ነው። በምናኔና በድንግልና የኖሩ ቅዱሳን በእግዚአብሔር ፍቅር ውስጥ ያገኙት ዓለሙንና በውስጡ ያለውን ሁሉ እንዲረሱ ያደረገ ታላቅ ፍቅር ነው።

«የእግዚአብሔር ፍቅር ከሰዎች ፍቅርና ከሰው ሰውኛ ጉዳዮች ነጥሎኛ ል።» በማለት የተናገረው መንፈሳዊ አባት ብሒል ምንኛ ድንቅ ነው!

አሁን ስለ ባዶነት ሊነገር የሚገባውን ሁሉ የተናገርን ይመስላችኋልን? አልተናገርንም። ከእነዚህ ሌላ ሊባሉ የሚችሉ ሌሎች ብዙ ነገሮች እንዳሉ ምንም ጥርጥር የለውም።

ምዕራፍ አራት፡፡

መርሳት፡፡

- የምንረሳቸው ነገሮች ምንድር ናቸው?
- እግዚአብሔር ያስታውሰናል፡፡
- ቤተ ክርስቲያን ታስታውሰናለች፡፡
- የማስታወስ ጥቂት ጥቅሞች፡፡
- በምድር ላይ ስላለ ቆይታህ አስታውስ፡፡
- ድካምህን አስታውስ፡፡
- ጥያቄ፡፡

የምንረሳቸው ነገሮች ምንድር ናቸው?

አንድ ቅዱስ አባት፡- «ከእያንዳንዱ ኃጢአት ፊት ምኞት፣ አለመገንዘብ ወይም መርሳት አሉ፡፡» በማለት ተናግሯል፡፡ ዛሬ መርሳት ወደ ውድቀት የሚያደርስ መንፈሳዊ ውጊያ ስለ መሆኑ ከእናንተ ጋር እነጋገራለሁ፡፡

በኃጢአት ጊዜ እግዚአብሔርን፣ ትእዛዛቱንና መንፈሳዊ ሕይወታችንን ሙሉ ለሙሉ እንረሳለን፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሞትንና ዘላለማዊነትን እንዘነጋለን፡፡ ኃጢአትን ስንሠራ የሚመለከቱንን መላእክትና ቅዱሳንም እንረሳቸዋለን፡፡ አንድ ሰው እነዚህን ሁሉ የሚያስታውስ ከሆነ ኃጢአትን አይፈጽምም ወይም ጊዜውን ያራዝመዋል ወይም ያፍራል ወይም ይፈራል ወይም ደግሞ ከእርሱ ይርቃል፡፡ በእርግጥም ኃጢአት ሲፈጸም እነዚህ ሁሉ ነገሮች ትዝ አይሉም፡፡

ለመርሳት አንድ ሰው በዲያብሎስ ወይም በምኞት ወይም በመሸት ሙሉ ለሙሉ መደንዘዝ አለበት፡፡ ሰው ይረሳል ወይም ለመርሳቱ ምክንያት ይፈጥራል ወይም ማንም ስለ እግዚአብሔር፣ ስለ ትእዛዛቱና ስለ ዘላለማዊነት እንዲያስታውሰው አይፈልግም፡፡ በጾምና በበዓላት ጊዜ እነዚህ ቀናት የተቀደሱ መሆናቸውን ይረሳል፡፡ የተቀደሱ መካናትንም ይረሳል፡፡ እርሱ ራሱ እግዚአብሔር የሚያድርበት የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ መሆኑን ይረሳል፡፡ የጌታው የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ስለ እርሱ መፍሰሱን ይረሳል፡፡ ለእግዚአብሔር የገባውን ስዕለትና ቃል ኪዳን ይረሳል፡፡

አንድ ሰባኪ በስብከቱ ውስጥ እነዚህን ሁሉ ነገሮች ለሕዝቡ በማስታወስ በፍርሃት ወይም በእፍረት ወይም በይሉኝታ ራሳቸውን ከመውደቅ በላይ እንዲጠብቁ ካላደረገ የስብከት ጥቅሙ ምንድር ነው?

እግዚአብሔር ያስታውሰናል፡፡

እግዚአብሔር የመርሳትን ጉዳት ስለሚያውቅ እኛን ሊያድነን ይሻዳል፡፡ በመሆኑም ወደ ራሳችን የምንመለስበትንና እኛነታችንን የምናውቅባቸውን ብዙ ነገሮች ሰጥቶናል፡፡ እግዚአብሔር መርሳታችንን የሚያክምባቸው እነዚህ ነገሮች ምንድር ናቸው?

የጽድቅን መንገድ እንድናስታውስ እግዚአብሔር ሕሊናን በእኛ ውስጥ ፈጥሯል፡፡ እግዚአብሔር በልባችን ሰሌዳ ላይ ሕጉን ስለ ጻፈ ሕሊና «የተፈጥሮ ሕግ» በመባል ተጠርቷል፡፡

ለምሳሌ ጻድቁ ዮሴፍ «. . . እንዴት ይህን ትልቅ ክፉ ነገር አደርጋለሁ? በእግዚአብሔር ፊት እንዴት ኃጢአትን እሠራለሁ?» (ዘፍ 39:9) ብሎ በተናገረ ጊዜ የተጻፈ ሕግ በሰዎች ዘንድ አልነበረም፡፡ ይሁን እንጂ በዚያን ጊዜ ያልተጻፈው ሕግ ይኸውም የተፈጥሮ ሕግ በእርሱ ውስጥ ስለ ነበረ ጉዳዩ ኃጢአት መሆኑን አስታውሶታል፡፡

ሰዎች የተፈጥሮውን ሕግ መርሳት ሲጀምሩ እግዚአብሔር የመጀመሪያውን የተጻፈ ሕግ በነቢዩ ሙሴ በኩል ሰጣቸው፡፡ እግዚአብሔር ይህን ሕግ እንዳንረሳውና ሁልጊዜ በፊታችን እንድናደርገው ትእዛዝ ሰጥቶናል፡፡ እንዲህ ነው ያለን፡- «እኔም ዛሬ አንተን የማዝዘውን ይህን ቃል በልብህ ያዝ፡፡ ለልጆችህም አስተምረው፣ በቤትህም ስትቀመጥ፣ በመንገድም ስትሄድ፣ ስትተኛም፣ ተጫወተው፡፡ በእጅህም ምልክት አድርገህ እሰረው፣ በዓይኖችህም መካከል እንደ ክታብ ይሁንልህ፡፡ በቤትህም መቃኖች በደጃፍህም በሮች ላይ ጻፈው፡፡» ዘዳ 6:6-9፡፡

ይህ ሁሉ እንዲጸፍ ያስፈለገው እኛ ትእዛዛትን እንዳንረሳ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ እግዚአብሔር በትእዛዛቱ ላይ ቀንና ሌሊት በተመስጠ እንድንቆይ አዝዞናል፡፡ ይህን በማስመልከት ነቢዩ ዳዊት እንዲህ በማለት ተናግሯል፡- «ሕግህ ተድላዬ ባይሆን ኖሮ በጉስቁልናዬ በጠፋሁ ነበር፡፡» መዝ 118:92፡፡ ስለ ጻድቅ ሰውም በመዝሙሩ ውስጥ እንዲህ ብሏል፡- «ነገር ግን በእግዚአብሔር ሕግ ደስ ይለዋል፣ ሕጉንም በቀንና በሌሊት ያስባል፡፡ እርሱም በውሃ ፈሳሾች ዳር እንደ ተተከለች . . . ዛፍ ይሆናል፡፡» መዝ 1:2-3፡፡

ለነዌ ልጅ ኢያሱ እግዚአብሔር የተናገረውን ቃል አድምጡ፡- «የዚህ ሕግ መጽሐፍ ከአፍህ አይለይ፤ነገር ግን የተጻፈበትን ሁሉ ትጠብቅና ታደርግ ዘንድ በቀንም በሌሊትም አስበው . . .» ኢያ 1:8፡፡ አምስቱ የሕግጋት መጻሕፍት ለሕዝቡ ስለበዙባቸው እግዚአብሔር እምላክ በኦሪት ዘዳግም መጽሐፍ ውስጥ በማጠቃለል እንዲያስታውሷቸው ረድቷቸዋል፡፡ ቀደም ሲል የዚህ መጽሐፍ ቅጂ ለእያንዳንዱ ንጉሥ ከተሰጠው በኋላ መላልሶ በማንበብ በመርሳት ምክንያት ኃጢአት እንዳይሠራ ይደረግ ነበር፡፡ በቤተ መቅደስና በምኩራብ ውስጥ ትእዛዛቱ ዓመቱን ሙሉ ለሕዝቡ እየታደሉ በመነበብ እንዳይረሱ ይደረግ ነበር፡፡

እስከ ዛሬ ድረስ በእያንዳንዱ ቅዳሴና ጸሎት ውስጥ ትእዛዛቱን እንዳንረሳቸው በቤተ ክርስቲያን ሊነበቡ እንሰማለን፡፡ ሕዝቡ እንዳይረሱ እግዚአብሔር ነቢያትንና ሐዋርያትን ወደ እነርሱ ይልክ ነበር፡፡ መንፈስ ቅዱስንም በመላክ እርሱ ያስተማራቸውን ያሳስባቸው ነበር፡፡ «. . . አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል፤እኔም የነገርኋችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል፡፡» ዮሐ 14:26፡፡

ለዚሁ ተመሳሳይ ዓላማ እግዚአብሔር መምህራንን፣ ሰባክያንንና በክህነት ማዕርግ ውስጥ ያሉትን ሁሉ ሕዝቡ የእግዚአብሔርን ቃል እንዳይረሱ

ያሳስቧቸው ዘንድ ወደ እነርሱ ልኳቸዋል። እነዚህን ሰዎች እግዚአብሔር የቃሉ አገልጋዮች ብሎ ሲጠራቸው ቅዱስ ጳውሎስ ደግሞ ስለ እነርሱና ስለ ራሱ እንዲህ ብሏል፦ «እንግዲህ እግዚአብሔር በእኛ እንደሚማለድ ስለ ክርስቶስ መልእክተኞች ነን፤ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብሰን ስለ ክርስቶስ እንለምናለን።» 2ኛ ቆሮ 5:20።

ቅዱስ ኤቫግሬዎስ የተናገራቸው ቃላትም ድንቅ ናቸው! «ማንኛውም አሳብ በተዋጋህ ጊዜ ከትእዛዛት መካከል አንዱን ከፊት ለፊትህ አስቀምጥ። በዚህ ጊዜ የሚወጋህ ስለሚደክም ታሸንፈዋለህ።» በዚህ ዓይነት መንገድ ከትእዛዛት ኃይል፣ እውቀትና ደስታ ስታገኝ አንተን የሚያጠቃህን አሳብ ለይተህ ስለምታውቀው ከአጠገብህ ታርቀዋለህ። እኛን ከማጽናናት አኳያ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የሚናገረውን ቃል አድምጥ፦ «የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነውና፤የሚሠራም ሁለት አፍ ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅ የተሳለ ነው . . .» ዕብ 4:12።

እግዚአብሔር ላለመርሳት የሚጠቅሙንን ሌሎች ዘዴዎችም ሰጥቶናል። እነርሱም የተሰዩ ቀናትና በዓላት ናቸው። ለምሳሌ፦ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ እኛ የተሰቀለበትን ቀን ለማስታወስና ስቅለቱን አስመልክቶ የሚታሰቡንን የተቀደሱ አሳቦችን በሕሊናችን ለማመላለስ ይረዳን ዘንድ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ሰሙነ ህማማት ዓመታዊ በዓል ሆኖ እንዲከበር ቀናቱን ቀምራ ሰጥታናለች። ረቡዕና ዓርብን ደግሞ በየሳምንቱ እንዲታሰቡ አድርጋ ሰጥታናለች።

ስለ እኛ የፈሰሰው ቅዱስ ደም ኃጢአት ስንሠራ ስለሚያሳፍረን እርሱን እንዳንረሳው ቤተ ክርስቲያን ታሳስበናለች። የማይጸም ሰው ሊረሳ ይችላል። ያለ መረዳት የሚጸም ወይም በጥልቀት የማይጸም ሰውም ይረሳል። በየሰዓታቱ የሚጸለዩ ጸሎታትን የማይጸልይ ሰውም ይረሳል። መንፈሳዊ ዘዴዎችን በማይለማመዱ ሰዎች ዘንድ መውደቅ እጅግ ቀላል ነው።

ቤተ ክርስቲያን ታስታውሰናለች።

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በየወሩና በየዓመቱ የሚከበሩ በዓላት የእምነትን እውነታ ያስታውሱናል። ኃጢአት እንዳንሠራ የሚያግዱን መንፈሳዊ ስሜቶቻችንንም በውስጣችን ያነሣሡልናል። ስለ ጸም፣ ስለ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት፣ ስለ ጸሎት፣ ስለ ሚፍ፣ ስለ ቅዱሳት ሥዕላትና ስለ ዕጣን ተመሳሳይ ነገር መናገር ይቻላል።

በዚህ መሠረት የጸም ቀናት ከእኛ ብዙ ውጊያዎችን የሚያርቁልን መንፈሳዊ ቀናት ናቸው። ለምግብ ብቻ ሳይሆን ለማንኛውም ነገር መንፈስ ሥጋዊ ፍላጎቶችን እንደሚያሸንፍ ያስታውሱናል። ቅዱሳት ሥዕላት የቅዱሳንን ሕይወትና ጥውም መዓዛ ያለው የኑሮአቸውን መንገድ ምሳሌ አድርገን እንድንወስድ ያስታውሱናል። መብራት የዓለም ብርሃን እንደሆንን ሊያስታውሰን (ማቴ 5:14) ሚፍ ወይም ሻማ ደግሞ ለሌሎች ብርሃን ለመስጠት እኛ ራሳችንን ስለሠዋዕት አድርገን ማቅረብ እንዳለብን ያስታውሰናል። ብርሃን ቅዱሳን መላእክትን ያስታውሰናል።

ከዚህ በተጨማሪ ብርሃን ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን በሰማይ እኛን ደግሞ በሰማይ እንደምናበራ ከዋክብት አድርጎ እንደሚመስለን ያስታውሰናል። የእግዚአብሔር ቃል ዓይንን የሚያበራ ብርሃን መሆኑንም ያስታውሰናል። መዝ 18። ነቢዩ ዳዊት እንደተናገረው የእግዚአብሔር ሕግ የመንገዳችን ብርሃን መሆኑን ያስታውሰናል። «ሕግህ ለእግሬ መብራት ለመንገዴ ብርሃን ነው።» መዝ 118:105። ቅዳሴም የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ሕይወት፣ ሞቱንና በዓለም ላይ ለመፍረድ ተመልሶ መምጣቱን ያስታውሰናል። ከዚህ በተጨማሪ ምጽአቱን እንድንጠባበቅና ሕይወት የሚሰጡን የመለኮታዊ ምሥጢራቱ ተካፋዮች እንሆን ዘንድ እንድንዘጋጅ ያስታውሰናል።

የማስታወስ ጥቂት ጥቅሞች።

እግዚአብሔር አምላክ ለአዳም፣ ለሔዋንና ለልጆቻቸው እንዳደረገው ማስታወስ ኃጢአት እንዳንሠራ ይረዳናል። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው። ይህ ሞት ደግሞ በተከፈለልን ዋጋ ከእኛ ተወግዷል። ምንም እንኳ ለድኅነታችን ፍጹምና በቂ ዋጋ ቢከፈልም እግዚአብሔር ለአዳም በፊቱ ወዝ እንጀራን እንዲበላ ሔዋን ደግሞ በጭንቅ እንድትወልድ ቅጣት ጥሎባቸዋል። ዘፍ 3:19 እና 16።

ከድኅነት በኋላ እንኳ እግዚአብሔር ይህን ቅጣት ጠብቆ ያቆየው የቀደመ ጥፋታችንን በማስታወስ አሁን ለምንሠራው ኃጢአት ንስሓ በመግባት ትሑታን እንድንሆን ነው። የእግዚአብሔር ፍቅር ሁሉንም ይቅር ይላል። ይሁን እንጂ ኃጢአት እርግማንና ሞት እንደሚያመጣብን እንዳንረሳ የቅጣት መኖር ለእኛ አስፈላጊ ነው። ስለሆነም በቅጣት ምክንያት ማማረራችን ለእኛ ተገቢ አይደለም። ይልቁንም በመንፈሳዊ መንገድ ከቅጣት መጠቀም እንጂ።

ኃጢአትን ማስታወስ ጠቃሚ መሆኑን ቅዱስ ዳዊት እንዲህ በማለት ተናግሯል፦ «. . . ኃጢአቴም ሁልጊዜ በፊቴ ነውና።» መዝ 50:3። ኃጢአቶቻችንን የምናስታውሳቸው ንስሓ እንድንገባባቸውና ትሑታን እንድንሆንባቸው ነው። ከንስሓ በኋላ በመንፈሳዊነት የተፈሰገው ከፍተኛ ደረጃ ላይ ብንደርስም እንኳ ራሳችንን ከፍ ከፍ እንድናደርግ አልተፈቀደልንም።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እስከ ሦስተኛው ሰማይ ድረስ ከተነጠቀ በኋላ እንኳ ቤተ ክርስቲያንን ማሳደዱን ስላልረሳ እንዲህ በማለት ተናግሯል፦ «እኔ ከሐዋርያት ሁሉ የማንስ ነኝና የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ስላሳደድሁ ሐዋርያ ተብዬ ልጠራ የማይገባኝ . . . » 1ኛ ቆሮ 15:9። ከዚህ ሌላ ኃጢአቶቻችንን የማንረሳቸው ለምንድር ነው?

ኃጢአቶቻችንን የማንረሳቸው ለወደቁት እንድንራራላቸውና እኛም ዳግመኛ እንዳንወድቅ ራሳችንን እንድንጠብቅ ነው። ዕብ 13:3። ከዚህ ሌላ ኃጢአቶቻችንን የምናስታውሳቸው እግዚአብሔር እነርሱን እንዲረሳልን ወይም ይቅር እንዲልልን ነው። ይህን አስመልክቶ ቅዱስ እንጦንስ «እኛ ኃጢአቶቻችን የምንረሳቸው ከሆነ እግዚአብሔር እነርሱን ያስታውሰናል። እኛ ኃጢአቶቻችን

የምናስታውሳቸው ከሆነ ደግሞ እግዚአብሔር ይረሳልናል።» በማለት ተናግሯል። ይህ ሲባል ግን እግዚአብሔር ኃጢአቶቼን ስለረሳልኝ ወይም ኃጢአቶቼ ስለ ጠፉልኝ እኔ ልርሳቸው ለማለት አይደለም። አንተ ከነቢዩ ዳዊትና ከቅዱስ ጳውሎስ አትበልጥም! ሁለቱም ይቅር ከተባሉ በኋላ ኃጢአቶቻቸውን አስታውሰዋልና።

ኃጢአትህን መርሳት እንደሌለብህ ሁሉ እግዚአብሔር ለአንተ ያለውን የፍቅር ቸርነትም መርሳት የለብህም። እነዚህን መርሳት ከአንተ ምስጋናህን ከማጥፋቱም በላይ ለእግዚአብሔር ያለህን ፍቅር ይቀንስብሃል። እነዚህ ሁለት ጉዳዮች ደግሞ ለመንፈሳዊ ሕይወትህ በጣም አደገኞች ናቸው።

እግዚአብሔር አምላክ ሕዝቡ የዮርዳኖስን ወንዝ መሻገራቸውን እንዳይረሱ ድንጋይ እንዲያቆሙ አዝዞአቸዋል። ኢያ 4:9። ቀይ ባሕርን በመዝሙር መሻገራችንንም አንዘነጋም ብለዋል። ያቆጠቆጠችው የእሮን በትርና መናው ማስታወሻ ይሆኑ ዘንድ ከምስክሩ ታቦት ጋር ተቀምጠዋል።

የእግዚአብሔርን የፍቅር ቸርነትና ለእርሱ የገባኸውን ስዕለት አትርሳ! እነዚህ ለመንፈሳዊነትህ ጠቃሚ ናቸውና። አንተ በችግር ውስጥ ስትሆን ለእግዚአብሔር የገባኸውን ቃል ኪዳንና እርሱ ኃጢአቶችህን ማጥፋቱን አስታውስ። ንስሓ በገባህና ቅዱስ ቁርባን በተቀበልህ ቁጥር ለእርሱ የገባኸውን ቃል ኪዳኖች በማስታወስ ከዚህ በኋላ ልትሠራ ስላሰብኸው ኃጢአት አፈር።

ቅዱሳን ሰዎች እግዚአብሔር ለእነርሱ ያደረገውን የፍቅር ቸርነት አልረሱም። አንተም የእርሱን ፍቅር ከፊትህ የምታስቀድም ከሆንህ ፍቅሩ በልብህ ውስጥ ይቀጣጠላል። ቅድስት ቤተ ክርስቲያን የምስጋና ጸሎትን ለሁሉም ጸሎቶች መግቢያ አድርጋ ያዘጋጀችልን የእግዚአብሔርን የፍቅር ቸርነት እንድናስታውስ ነው። ከዚህ ጸሎት በማስከተል በግል ጸሎትህ ዝርዝር ውስጥ እግዚአብሔርን እንደምትወደው ጨምረህ መግለጽ ትችላለህ። ይህን በማድረግህም ስለ ፍቅሩ ስለምታፍር ኃጢአት አትሠራም።

ከዚህ በተጨማሪ በፍርሃትና በጭንቀት ውስጥ እንዳትወድቅ እግዚአብሔር ለአንተ የገባቸው ቃል ኪዳንና የሚያደርግልህን ጥበቃ አትርሳ። ችግር በገጠመህ ጊዜ ሁሉ እግዚአብሔር አባትህ እንደሚጠብቅህና እንደሚንከባከብህ አስታውስ። ይህን አስመልክቶ እርሱ የተናገረውን ቃል አስታውስ፦ «በሕይወትህ ዕድሜ ሁሉ ማንም አይቋቋምህም . . . አልጥልህም አልተውህምም።» (ኢያ 1:5)፤«. . . እኔ ከአንተ ጋር ነኝ፤ማንም ክፉ ሊያደርግብህ የሚነሣ የለምና አትፍራ . . .» (ሐዋ 18:10)፤«በአጠገብህ ሺህ በቀኝህም አሥር ሺህ ይወድቃሉ፤ወደ አንተ ግን አይቀርብም።» መዝ 90:7።

የሚፈራና የሚጨነቅ ሰው ዳእግዚአብሔርን ፍቅርና ቃል ኪዳን የረሳ ሰው ለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም። ሰው ቢረሳ እንኳ ክነቢዩ ዳዊት ጋር ሆኖ ለእግዚአብሔር እንዲህ በማለት ይናገር፦ «ለባሪያህ ተስፋ ያስደረግኸው ቃልህን አስብ። . . . ይህች በመከራዬ ደስ አሰኘችኝ።» መዝ 118:49 እና 50። ይህ ሁሉ በፈተና ጊዜ ከሚመጣ ከጥርጥር ውጊያ ሊታደግህ ይችላል። ስለዚህ

እግዚአብሔር ለአንተ በሠራው ሥራ ላይ መተማመንን፣ ተስፋንና ጥልቅ እምነትን የሚያረጋግጡ ጥቅሶችን በልብህ አጥናቸው። ከዚህ በኋላ በሕሊናህ ውስጥ አስቀምጣቸውና እንዳትረሳቸው መላልሰህ ድገማቸው። ይህን በማድረግህም በጌታ ደስ ይልሃል ትደላደላለህም።

ከዚህ በማስከተል ፈጽሞ ልትረሳው የማይገባህን ጉዳይ እንመለከታለን።

በምድር ላይ ስላለ ቆይታህ አስታውስ።

ነቢዩ ዳዊት በጸሎቱ ውስጥ «እኔ በምድር እንግዳ ነኝ፤ትእዛዛትህን ከእኔ አትሰውር።» (መዝ 118:19)፤«እኔ በምድር ላይ እንግዳ ነኝና፤እንደ አባቶቼም እንግዳ ነኝና።» (መዝ 38:12) እያለ በዚህ ጉዳይ ላይ በተመሰጠ ይቆይ ነበር።

የመለየት ስሜት ዳዊትን ስለ ሞት እንዲያስታውስ አድርጎታል። ነቢዩ ከማስታወስ ተጠቅሟል ማለት ነው። በመሆኑም እንዲህ እያለ ይጸልይ ነበር፦ «ለቤቱ ፍጻሜዬን አስታውቀኝ፣ የዘመኔ ቁጥሮች ምን ያህል እንደ ሆኑ፣ እኔ ምን ያህል ወደ ኋላ እንደምቀር አውቅ ዘንድ።» መዝ 38:4። እንዲህ ዓይነቱ ስሜት የነበረው በነቢዩ ዳዊት ውስጥ ብቻ አልነበረም። በሁሉም ቅዱሳን አባቶች ውስጥ እንጂ። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ይህን አስመልክቶ እንዲህ ብሏል፦ «እነዚህ ሁሉ አምነው ሞቱ . . . እንግዶችና መጻተኞች እንዲሆኑ ታመኑ።»፤«. . . አሁን ግን የሚበልጠውን እርሱም ሰማያዊ አገር ይናፍቃሉ።» ዕብ 11:13 እና 16። ዘላለማዊነትን ማስታወስ ኃጢአት ከመሥራት ስለሚጠብቅ መናንያን አባቶች ሁሉ ሞታቸውን እያሰቡ ይኖራሉ። የመጨረሻው ነጥባችን ድካምን ስለ ማስታወስ ነው።

ድካምህን አስታውስ።

ድካምህን ስታስታውስ ከኃጢአትና ከሌሎች ጥቃቶች ቀለበት ትርቃለህ። ከዚህ በተጨማሪ ራስህን ስለምትጠብቅ በሕይወትህ ጥብቅ ከመሆንህም በላይ በመንፈሳዊ ተጋድሎዎችህ ስኬታማ ትሆናለህ። ጉራ የሚነዙ ሰዎች ይወድቃሉ። ስለ ኃጢአት ግን እንዲህ ተብሎ ተጽፎአል፦ «ወግታ የጣለቻቸው ብዙ ናቸውና፤እርስዋም የገደለቻቸው እጅግ ብዙ ናቸው።» ምሳ 7:26።

ድካሙን የተገነዘበ ሰው ግን ትሑት ነው። ትሕትና ደግሞ በዲያብሎስ የሚፈራ ከባድ መሣሪያ ነው። ትሑት ሰው የእግዚአብሔርን እርዳታ ለማግኘት ይጸልያል። ሰው ውጊያውን ድል እንዲነሣ የሚያግዘው መሣሪያ ደግሞ ጸሎት ነው።

ይህን ሁሉ በማወቅ ጎጂ መርሳቶችን ተቃወም። መርሳትንም ለራስህ ጥቅም ተጠቀምበት። ለምሳሌ፦ የሌሎችን ጤናማ ያልሆነ እንክብካቤ፣ የሠራኸውን መልካም ሥራ፣ የዓለምን ከንቱ ጉዳዮችና የጠላት ዲያብሎስን ማስፈራሪያዎች እርሳቸው አታስታውሳቸውም።

ጥያቄ።

ማስታወስንና መርሳትን አስመልክቶ አንዳንድ ሰዎች ኃጢአቶቻቸውን ሁልጊዜ በፊታቸው አድርገው የሚያስታውሷቸው ከሆነ በሚያስታውሷቸው ኃጢአቶቻቸው ተመልሰው እንደሚወድቁ ይናገራሉ። ይህን አስመልክተውም ይጠይቃሉ። ኃጢአቶችን ማስታወስ ማለት ግን አንድ ሰው አንዲያዝንና እንዲወድቅ የሚያደርጉትን የኃጢአት ዝርዝሮችን በአርግጥ ያስታውስ ማለት አይደለም።

ምዕራፍ አምስት።

ጥርጥር።

- ጥርጥርና ጉዳቶቹ።
- የጥርጥር ዓይነቶች።
  - እግዚአብሔርን መጠራጠር።
  - ዳግማን መጠራጠር።
  - ባልንጀሮችን መጠራጠር።
  - ሰዎችን መጠራጠር።
  - ቅድስናን መጠራጠር።
  - ራስን መጠራጠር።
  - አገልግሎትን መጠራጠር።
- የጥርጥር ምክንያቶች።
  - የራስ ተፈጥሮ።
  - ቀናነትና ጥልቀት።
  - ፍርሃት።
  - የዲያብሎስ ውጊያዎች።
  - አካባቢ።
  - ራስን በአንድ ጉዳይ መወሰን።
  - የተራዘመ ጊዜ።
  - በመከራ የሚመጣ ጥርጥር።
  - ስህተቶችን በአንድ መጠቅለል።
- ከከንቱ ስሜት የሚመጣ ጥርጥር።

ጥርጥርና ጉዳቶቹ።

ጥርጥር የእምነትና የጽናት ጉድለት ነው። ይህ በመሆኑም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ጴጥሮስን፦ «. . . አንተ እምነት የጎደለህ፤ስለ ምን ተጠራጠርህ?» ብሎታል። ማቴ 14:31። ጥርጥር ያለ መጽናት፣ ግልጽ ያልሆነ ራእይና ያለማመን ደረጃ ነው።

ጥርጥር ለሕሊና እና ለልብ ሲኦል ነው። ጥርጥር ወደ ሰው በቀላሉ ሊገባ ይችላል። ከዚያ ሰው ግን በቀላሉ አይወጣም። ከዚህ በተጨማሪ ጥርጥር በመጨረሻ ሲገለጥ ድብቅ ውጤት ትቶ ሊያልፍ ይችላል። ጥርጥር የሰውን ለዘላለም መደላደል ያሳጣል። ተአምር በጥርጥር ምክንያት አይገለጥም። ይሁን እንጂ እምነት ላላቸው ነገር ግን ተራ ለሚባሉ ሰዎች ይከሰታል።

ጥርጥር ዘላቂ ከሆነ ወደ በሽታነት ወይም ወደተወሳሰቡ መጥፎ ውጤቶች ሊ ውጥ ይችላል። ጥርጥር ነርቭን በማጥቃት ወደ ግራ መጋባትና ወደ በዛ አሳብ ከመምራቱም በላይ እንቅልፍ ይከለክላል። ከዚህ በተጨማሪ ውጤቱ ወደ ማመንታት፣ ወደ ይሉኝታና በነገሮች ላይ ወዳለመወሰን ያደርሳል።

የጥርጥር ዓይነቶች፡፡

ምሳሌ የሚሆኑን ጥቂት የጥርጥር ዓይነቶች አሉ፡፡ እነርሱም፡- እምነትን፣ እግዚአብሔርን፣ ዶግማን፣ ሰዎችን፣ ጓደኞችን፣ ራስን፣ ቅድስናን፣ ንስሓን፣ አገልግሎትንና የሕይወትን ነገር መጠራጠር ናቸው፡፡

1- እግዚአብሔርን መጠራጠር፡፡

ጥርጥሩ በእግዚአብሔር ሕልውና ላይ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ በአንድ ወቅት በዲያብሎስ የተጠነሰሰ ረቂቅ ውጊያ ነው፡፡ ውጊያው በሰው ሕይወት ውስጥ ጣልቃ የሚገባ ውጊያ ነው፡፡ ይህ የሚመጣውም በዚህ ዙሪያ የተጻፉ መጻሕፍትን ከማንበብ፣ እግዚአብሔር የሰም ብለው ከሚያምኑ ሰዎች ጋር ከመወዳጀትና ከሕሊና በላይ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ከመወያየት ነው፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ውጊያ ከተለያዩ የፍልስፍና እና የሳይንስ የምርምር መስኮች ወይም ስለ ህዋና አፈጣጠሩ ከተጻፈ ታሪክ ሊመጣ ይችላል፡፡ ወይም ደግሞ ታዋቂ ሰመሆን ፈልገው ሰዎችን ከሚቃወሙ ሰዎች ይህ ውጊያ ሊመጣ ይችላል፡፡

ምናልባት ጥርጥር የእግዚአብሔርን ሕልውና ከመጠራጠር ላይነሣ ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ እርዳታውንና ጥበቃውን፣ፍቅሩንና ቃል ኪዳኑን ወይም የጸሎትን ጥቅም ተንተርሶ ሊነሣ ይችላል፡፡ እግዚአብሔር ያዕቆብን ሰመባረክ የገባውን ቃል ኪዳን ርብቃ ስለ ተጠራጠረች ይስሐቅን ለማታለል ሰው ሰውኛውን የማታለል ዘዴ ተጠቅማለች፡፡ ዘፍ 27፡፡

አባታችን አብርሃምም እግዚአብሔር ዘርህን እንደ ምድር አሸዋና እንደ ሰማይ ከዋክብት አበዛዋለሁ ብሎ የገባለትን ቃል ኪዳን ስለ ተጠራጠረ ሰው ሰውኛ ጠባዩን ገልጧል፡፡ ዘፍ 16፡፡

2- ዶግማን መጠራጠር፡፡

የዚህ ጥርጥር ውጤት የሚመጣው በሌሎች የእምነት ድርጅቶች አማካይነት ነው፡፡ የጸና እምነት የሌለው ሰው የእነርሱን ስብሰባ በመካፈል፣ የእነርሱን መጻሕፍትና በራሪ ጹሑፎች በማንበብ የውጤቱ ተካፋይ ይሆናል፡፡ ሰምሳሌ አንድ ሰው በጀሀቫውያኖች መካከል ተገኝቶ ስብከት ሲያዳምጥ ይችላል ወይም አርቶዶክሳውያን ባልሆኑ ሰዎች ስብከት ተጽዕኖ ሊደርስበት ይችላል፡፡ እነዚህን በማድረጉ ጥርጣሬ ወደዚህ ሰው ልብና ሕሊና ዘልቆ ይገባል፡፡

ሰው በእምነቱ ጽኑ ሊሆን ይገባዋል፡፡ የሐዋርያው የቅዱስ ጴጥሮስ ቃላት ምንኛ ድንቅ እንደሆኑ ተመልከት፡- «በእናንተ ስላለ ተስፋ ምክንያት ለሚጠይቋችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ዘወትር የተዘጋጃችሁ ሁኑ፡፡» 1ኛ ጴጥ 3፡15፡፡ በመሆኑም አንድ ሰው ስለ እምነቱ በዓለት ላይ እንደ ተመሠረተ ቤት ጽኑ ሊሆን ይገባዋል፡፡ አንዳንድ ሰዎች የደግማ ጥናት ስለሚከብድ ከመንፈሳዊነት የተራቆተ ነው በማለት ያሳምኑሃል፡፡ ማጥናትህን ካቆምህ በኋላ ከአንድ አስቸጋሪ ጥያቄ ጋር ስትጋፈጥ ጥርጥር ውስጥ ትገባለህ፡፡ እኛ የምንመክርህ ግን መንፈሳዊ

መጻሕፍትን፣ የደግማ መጻሕፍትንና የሥነ መለኮትን መጻሕፍትን እንድታነብ ነው፡፡

3- ባልንጀሮችን መጠራጠር፡፡

ይህ የሚመጣው በራስ ከመተማመን ወይም ከፍቅር እጦት ነው፡፡ አንድ ሰው ሌላውን ሰው በአውነት ከወደደው በእርሱ ስለሚተማመን አይጠራጠርም፡፡

የዚህ ችግር መፍትሔው ፊት ለፊት፣ በግልጽና በፍቅር መነጋገር ነው፡፡ አንድ ሰው ከሰው በሰማው ወሬ ወይም ሐሜት መጎዳት ስለሌለበት የሰማውን ሁሉ ማመን የለበትም፡፡ ምክንያቱም ብዙ ጊዜ ግልጽ ከሆኑ መረጃዎች ይልቅ ሐሜት ጉዳቱ ስለሚከፋ ነው፡፡ ስለዚህ አንተ ከሰውየው ሰምተህ እስካላረጋገጥህ ድረስ ማንንም መወንጀል ወይም ማውገዝ ሃሰብህም፡፡

4- ሰዎችን መጠራጠር፡፡

አንተ የግለሰብን ስህተት በሌሎች ሰዎች ላይ ልታመካኝ ትችል ይሆናል፡፡ ሰምሳሌ አንዱ የአንድን ሰው ስህተት በቡድን ባሉ ሰዎች ላይ ሊያሳብብ ይችላል፡፡ ምንም እንኳ በቤተሰቡ መካከል የሚኖሩ ጥቂት ጸድቃን ቢኖሩም የቤተሰቡ አባል የሆነ የአንድ ሰው ውድቀት በጠቅላላው ቤተሰብ መካከል ጥርጥር ያመጣል፡፡ ጥርጥር ከዚህ አልፎ ተርፎ በሰዎች ሁሉ ወይም በሀገር ደረጃ ሊመጣ ይችላል፡፡

5- ቅድስናን መጠራጠር፡፡

አንድ ሰው የጸም አስፈላጊነቱ ምኑ ላይ ነው? የሥጋ ቅድስና ምን ዋጋ አለው? የመቆጠብ ጥቅም ምን ይፈይዳል? የድንግልና ጥቅሙስ ምንድር ነው? እግዚአብሔር ከእኛ ጸሎትን ሳይጠባበቅ የሚያድነን ከሆነ ጸሎት ማድረሱ ጥቅሙ ምኑ ላይ ነው? በማለት በጥርጥር ሊሞላችሁ ይችላል፡፡
እንደዚህ ዓይነቱ ሰው «የቅድስና ጥቅሞች ምንድር ናቸው? ተራ ተግባራት ወይም ሕግጋት ናቸው እኮ!! ሰው ደግሞ በሕግ አይጸድቅም!!» ብሎ እስከመናገር ሊደርስ ይችላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ «እስካመንህ ድረስ የወደድኸውን ማድረግ ስለምትችል ምንም ዓይነት ቅጣት አይደርስብህም! ሌላው ቢቀር ሰባት ጊዜ ብትወድቅ እንኳ ሰባት ጊዜ ልትነሣ ትችላለህ፡፡» በማለት ይናገራል፡፡

ጥርጥር የቱ ተፈቅዷል የትኛውስ ተከልክሏል አስከሚለው መሠረተ አሳብና ሞራል ድረስ ዘልቆ በመግባት ሊንሰራፋ ይችላል፡፡ ጥርጥር ዘመናዊ የፈጠራ ግኝቶችን ማለትም እንደ ቴሌቪዥን፣ ሬዲዮ፣ ሲኒማና ሙዚቃን አስመልክቶ ተፈቅደዋል ወይስ ተከልክለዋል? በማለት ሊያጠራጥር ይችላል፡፡ በጎበረተሰቡ መካከል እንግዳና አዲስ የሆኑ ነገሮችን ማለትም እንደ እርግዝና መከላከያንና ክማኅፀን ውጪ ተረግዘው የሚወለዱ ልጆችን በማስመልከት ጥርጥር ሊያጭሩ ይችላል፡፡

እንዲህ ያሉት ነገሮች እንደ መንፈስ፣ እንደ መረዳትና እንደ ጥናት ጥልቀት እንጂ እንደ ፊደል ባይሆኑ መልካም ነው፡፡ ለምሳሌ ሲኒማ ሊፈቀድም ሆነ ሊከለከል የሚገባው ከሚሰጠው ጥቅምና ጉዳት አንጻር ተመዝኖ ነው፡፡

ቴሌቪዥንን፣ ሬዲዮንን፣ ቪዲዮን፣ ሙዚቃንና ተውኔትን አስመልክቶ ተመሳሳይ ነገር ሊነገር ይችላል። እነርሱን የምንጠቀምባቸው ለበጎ ነው ወይስ ለክፉ? ብሎ መጠየቅ ብልህነት ነው።

6- ራስን መጠራጠር።

አንዳንድ ጊዜ ሰው ራሱን ስለሚጠራጠር በራሱ አይተማመንም። ከዚህ በተጨማሪ በአቅሙና በችሎታው አይተማመንም። ለዚህ ምሳሌ የሚሆነን ጥሩ ውጤት ለማምጣት የሚጠራጠር ወይም በቂ የፈተና ሰዓት የለኝም ብሎ የሚጠራጠር ተማሪ ነው። ትክክል ይሁን ስህተት የገዛ ጠባዩን የሚጠራጠር ሰው ራሱን ይጠረጥራል። በጎበረተሰቡ ዘንድ መወደዱን ወይም መጠላቱን የሚጠራጠርም ራሱን ይጠራጠራል።

ራስን መጠራጠር የታየው በልጆች ላይ ከሆነ ልጁን በማወደስና በማበረታታት በራሱ እንዲተማመን ማድረግ ያስፈልጋል። ጭካኔና ቁጣ የተሞላበት አያያዝ ሰው ራሱን ይጠራጠር ዘንድ ይመሩታል። ሌላው ቢቀር ያደጉ ልጆችም ማበረታቻና በጎ ቃላትን ይፈልጋሉ። ሲታመሙ ወይም ሲጨነቁ ወይም ችግር ሲገጥማቸው ወይም በፈተና ተስፋ ቆርጠው እንዳይወድቁ ወይም «ምንም ዋጋ የለኝም. . . ጠፍቼያለሁ!!» በሚሉበት ጊዜ ሊያጽናኗቸውና ሊያስደስቷቸው የሚችሉ ቃላትን ይፈልጋሉ።

ሰው የሚጠብቀውን ዕድል ፋንታ ይጠራጠራል። በመሆኑም ለእርሱ የሚበጀውን ወይም ትክክል የሆነውን በሚያሰውቀው በኑሮ ዘዴው ላይ ይጠራጠራል። የሚበጀው ትዳር ነው ወይስ ድንግልና? የምንኩስና ሕይወት ወይስ የአገልግሎት ሕይወት? በዚህኛው መንገድ ይቆማል ወይስ አይቆምም? በምርጫው ይጸናል ወይስ ይጸጸታል? አንድ የሆነ ጥናት ወይም ሥራ ለእርሱ ይመቸዋል ወይስ አይመቸውም?

እነዚህ ሁሉ ተራ ጥያቄዎች ወይም ሰውን የሚያስጨንቁና ግራ የሚያጋቡ ጥርጥሮች ሆነው ይለወጣሉ። በመሆኑም ሰውየውን ወደ ጥርጥር ስለሚመሩት በራሱ የማይወስን ሰው ይሆናል። እንዲህ ዓይነቱ ሰው ምናልባት ለችግሩ ለሰዎች ቢያማክርም ብዙዎችን ሊያጠራጥር ይችላል።

ጥርጥር አንዳንድ ሰዎች ጠቃሚ የመፍትሔ ውሳኔ ሊያስተላልፉ ባሰቡበት ቀን በመንገዳቸው ላይ ደንቃራ ሆኖ ይቆማል። በዚህ ጊዜ መንገዳቸው ድንግዝግዝ ስለሚሆን በጥርጥር ፊት ግራ ተጋብተው ይቆማሉ። ግብን፣ ዘዴንና መንፈሳዊ ዓላማዎችን አስመልክቶ ጽናት ሊኖር ያስፈልጋል። ከዚህ በተጨማሪ የሰው እውቀት፣ ራስን በእውነት መመርመርና አመለካከቶችንና ችሎታዎችን ማመጣጠን ወሳኝ ነገሮች ናቸው። ኃይልን ከመጠርጠር በተቃራኒ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የሚያጽናኑ ቃላትን ተናግሯል። «ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ።» ፊል 4:13።

7- አገልግሎትን መጠራጠር።

አንድ አገልጋይ አገልግሎቴ ስኬታማ ነው ወይስ የወደቀ? አገልግሎቴ መቀጠል ነው ያለበት ወይስ ማቋረጥ? በሚሉት ነጥቦች ዙሪያ አብዝቶ ይጠራጠራል። ይህ ሊመጣ የሚችለው ፈጥኖ የሚደርሰውን ፍሬ ለማየት ከመጓጓት ነው። ፍሬውን ማየት ካልቻለ ግን የአገልግሎቱን ስኬታማነት ይጠራጠራል።

ይህን አስመልክተን ከተከል አስተዳደግ ትምህርት ልንወስድ እንችላለን። አንድ ዘር ለማደግ፣ ለመጠንከርና ዛፍ ለመሆን ጊዜ ያስፈልገዋል። የቅዱስ አውግስጢን እናት ምንም ዓይነት ፍሬ ባትመለከትም ረገጭም ጸሎቶቿን ማቅረቧን በርትታ ቀጠለች እንጂ አልተጠራጠረችም።

የጥርጥር ምክንያቶች።

የጥርጥር ምክንያቶች ውስጣዊ ወይም ከራስ የሚመጡ ወይም ውጪያዊ ሊሆኑ ይችላሉ። ወደሚያጸና መፍትሔ ለመድረስ እንችል ዘንድ በእነዚህ ምክንያቶች ዙሪያ እንነጋገራለን።

1- ከራስ ጠባይ።

ለምሳሌ የአንድ ሰው ሰብእና ያልተረጋጋ ወይም ውስብስብ ሲሆን በቀላሉ በጥርጥር ውስጥ ሊወድቅ ይችላል። ወይም ሊተማመን የሚችል ባለመሆኑ የአስተሳሰብ መንገዱ ወደ ጥርጥር ይመራዋል። አስተሳሰቡ ጠባብ ስለሚሆንም ከጥርጥር ሌላ ምንም የሚታየው ነገር አይኖርም። ሰፋ ያለ አስተሳሰብ ቢኖረው ግን ጥርጥሮቹ ይጠፋሉ።

2- ገራገርነትና ጥልቀት።

አንድ ሰው ገራገርና ሁሉን የሚያምን ከሆነ የጥርጥር ማዕበል ውስጥ አይወድቅም። ከዚሁ ጋር ተመሳሳይ የሆነው ገራገር ሰው ግን የተነገረውን በሙሉ ቢቀበልም ጥርጥር ውስጥ ይወድቃል። ለምሳሌ ይህ ሰው አንዱ ወደ እርሱ ቀርቦ ጓደኛው በእርሱ ላይ ስህተት እንዳገኘ አድርጎ ቢያወራለት ይህን ስለሚያምን ጓደኛውን ይጠረጥረዋል።

ገራገር ሰው በሰዎች ሊታለል ይችላል። በመሆኑም ገራገርነቱ እምነትና ዶግማን አስመልክቶ እንዲጠራጠር ይመራዋል። በሁለቱም ውጤቶች (በእምነትና በጥርጥር) ላይ በተመሳሳይ ጊዜ የሚደርስ አጥልቆ አሳቢ ሰው የሚገጥመው ዕጣ ተመሳሳይ ነው። ይህ ሰው ግን በጥልቅ አሳቡ ውስጥ የጥርጥርን ስህተቶች ስለሚያገኝ ሊያጠፋቸው ይችላል።

አንዳንድ ጊዜ ግን ጥልቅ አሳብ ወደ ምክንያታዊነት ስለሚመራ የልብን ገራገርነት ያሳጣል። ከዚህ በኋላ ይህ ሰው መለኮታዊና መንፈሳዊ ምሥጢራትን

በውሱን ሕሊናው አቅም ሊረዳቸው ስለሚናፍቅ ጥርጥር ውስጥ ይወድቃል። ብዙ ጊዜ ፊላስፎች ጥርጥር ውስጥ የሚወድቁት በዚህ ምክንያት ነው።

3- ፍርሃት።

ብዙ ጊዜ ፍርሃትና ጥርጥር አይነጣጠሉም። አንዱ ለሌላው ምክንያትም ውጤትም ሊሆን ይችላል። ፍርሃት ወደ ጥርጥር ይመራል። ጥርጥር ደግሞ ፍርሃትን ያስከትላል።

ቅዱስ ጴጥሮስ በባሕር ላይ መራመድ ከጀመረ በኋላ ስለ ተጠራጠረ መጠራጠሩ ፍርሃትን አስከትሎበታል። ፍርሃቱ እየጨመረ ሲመጣም መስጠም ስለ ጀመረ ድምፁን አውጥቶ ጮኋል።

4- የዲያብሎስ ውጊያዎች።

ጥርጥር ከዲያብሎስ የሚቃጣ ጥንታዊ ውጊያ ነው። እርሱ የመጀመሪያ ወላጆቻችንን ወደተተከለከለችው ዛፍ በጥርጥር መርቷቸዋል የመብላታቸውን ውጤትም እንዲጠራጠሩ አድርጓቸዋል። ይህ ደግሞ እግዚአብሔርን ያዘዛቸውን ትእዛዝ እንዲጠራጠሩ አድርጓቸዋል።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ዲያብሎስ በጥርጥር ሊዋጋው ቢሞክርም ስላልቻለ ወድቋል። በመስቀል ላይ እያለም እንዲህ ብሎታል፦ «. . . የእግዚአብሔር ልጅስ ከሆንህ ከመስቀል ውረድ . . .» ማቴ 27:40። ዲያብሎስ ቅዱስ እንጦስን በጥርጥር ከምንኩስና ለማራቅ ሞክሮ ነበር። ሰው በሞቱ አፋፍ ላይ እያለ እንኳ ዲያብሎስ ወደ ቅጣት ሊያስገባው ስለሚፈልግ ጥርጥርን ያቀርብለታል።

ዲያብሎስ ዓለሙን ሊያጠቃው የሚችለውን ጥርጥር ባለፉት በሺዎች በሚቆጠሩ ዓመታት ውስጥ ከማወቁም በላይ እንዴት በእነርሱ መዋጋት እንሚችልም በሚገባ ያውቃል። ስለሆነም በሁሉም ነገር ላይ ጥርጣሬን ይተክላል። እርሱ እምነትን እንኳ ያጠራጥራል። ሌላውን ለማደናገር ከሌሎች ጋር ይወዳጃል። ሌላውን ደግሞ ያለፍራል። ጥርጥር ከዲያብሎስ ብቻ ሳይሆን ከእካባቢም ይመጣል።

5- አካባቢ።

መግደላዊት ማርያም መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ከትንሣኤው በኋላ ብትመለከተውና እርሱም ቢያነጋግራት እንኳ አይሁድ በየሥፍራው በነዙት የተሳሳተ አሉባልታና ጥርጥር መካከል ራስዋን ስታገኝ ተጠራጥራ ነበር። ዮሐ 20።

ጥርጥር የተጠራጣሪ ባልንጀራ ከመሆንም ይመጣል። እምነትና መታመን ከአማኝና ከጽኑ ጓደኛ እንደሚወረስ ሁሉ ጥርጥርም ከተጠራጣሪ ባልንጀራ ይወረሳል። ስለሆነም ከእነዚህ ሰዎች ጋር ባልንጀራ ከመሆን ራቅ! ይህን

ልታደርግ ባትችል እንኳ ንግግራቸውን በንቃት በማዳመጥ የሚሉትን በሙሉ አትመናቸው።

የጥርጥር ምንጮች ከሆኑትና ጥርጥርን ከሚያነሳሱት ነገሮች መካከል አንዱ ንባብ ነው። ጥርጥር ያሰባቸውን መጻሕፍት ሙሉ ለሙሉ ከአንተ ዘንድ አስወግድ። ሊገነቡህ የሚችሉ መጻሕፍትን መርጠህ አንብብ እንጂ እምነትህንና ሞራልህን የሚያጠፉ መጻሕፍትን አታንብብ።

አንዳንድ ጸሐፊዎች የጸኑ ጻድቃንን በመቃወም በአንባብያን ውስጥ ጥርጥርን ያነሣሣሉ። ይህን ሲያደርጉ ሌሎች የማያውቁትን እነርሱ እንደሚረዱት አድርገው ያቀርባሉ። ሌላው የጥርጥር ምንጭ በአብዛኛው ሐሰት ሆኖ የሚገኘው ሐሜት ነው። ስለዚህ በዚህ ዙሪያ የሚነገሩ ወሬዎችን አትመን። አንተም እነዚህን ሐሜቶች እንደ ገደል ማሚቶ ደጋግመህ አታስተጋባ! ይህን የምታደርግ ከሆንህ በጥርጥር የተሞላህ ሰው ትሆናለህ።

6- ራስን በአንድ ጉዳይ ላይ መወሰን።

የጥርጥር ምክንያቶች ከሆኑት መካከል የሚከተሉት ይገኛሉ . . .

አንድ ጓደኛህ በጋበዝከው ግብዣ ላይ ላይገኝ ይችላል። ምንም እንኳ ባደኛህ በግብዣህ ላይ ያልተገኘበት በቂ ምክንያት ሊኖረው ቢችልም አንተ አለመምጣቱን የአንተን ስሜት ሆነ ብሎ ለማዋረድ አድርገህ ከቆጠርኸው በጥርጥር ትሞላለህ።

ወደ ቤቱ አምሽቶ የሚመለስ ባል ያላት ሚስት ያልሆነውን ነገር ምክንያት አድርጋ የምታስብ ከሆነ ጥርጥር ወደ ሕሊናዋ ይገባል። እነዚህ ሴቶች ራሳቸውን በአንድ ጉዳይ ላይ መወሰናቸው የሚያስደንቅ ነው። በጣም የሚገርመው ደግሞ የሚመርጡት ምክንያት የሚያስጨንቃቸውንና አሳባቸውን ግራ የሚያጋባውን መሆኑ ነው።

ሌላዋ ምሳሌ ደግሞ አምሽታ ወደ ቤቷ የምትገባዋ ሴት ልጅ ናት። እናቷ ምናልባት አደጋ ደርሶባት ይሆናል ወይም ተጠልፋ ሊሆን ይችላል ወይም ሌላ ክፉ ነገር አጋጥሟት ሊሆን ይችላል በማለት ታስባለች። ልጇ ተመልሳ እስክምትመጣ ድረስ በጭንቀት ውስጥ ትቆያለች። ወይም ልጇ እስክነ ጭራሹ እንደማትመለስ አድርጋ ልትጠራጠር ትችላለች።

7- የተራዘመ ጊዜ።

ከዚህ አንጻር የአባታችን የአብርሃምን ጉዳይ ስንመለከት እርሱ ለረዥም ዓመታት ምንም ልጅ ሳያገኝ ቆይቷል። አንድ መከራ ወይም ችግር ገጥሞአቸው ለረዥም ጊዜ ያለ ምንም መፍትሔ የሚቆዩ ሰዎችም በዚህ ውስጥ የሚካተቱ ናቸው።

8- በመከራ የሚመጣ ጥርጥር፡፡

ጌዴዎን በጥርጥር ውስጥ በነበረ ጊዜ የእግዚአብሔርን መልአክ የጠየቀው ጥያቄ ለዚህ ምሳሌ ይሆነናል፡- «. . . እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ይህ ነገር ሁሉ ለምን ደረሰብን? አባቶቻችንስ እግዚአብሔር ከግብጽ አውጥቶናል ብለው ይነግሩን የነበረ ተአምራቱ ወዴት አለ?» መሳ 6፡13፡፡ ሌላው የጥርጥር ምሳሌያችን ደግሞ እስራኤላውያን በምድረ በዳ በነበሩ ጊዜና በቀይ ባሕር ፊት ለፊት በቆሙ ጊዜ የተጠራጠሩት ጥርጥር ነው፡፡ ዘጸ 14፡፡

ከፊት የተጋረጠ ታላቅ አደጋ ወይም መከራ ሰውን ጥርጥር ውስጥ እንዲወድቅ ያደርገዋል፡፡ የእስራኤል ሠራዊት በግዙፉ ጎልያድ ፊት የነበራቸው የጥርጥር ስሜት ከዚህ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ነቢዩ ዳዊት ግን ከሠራዊቱ በተለየ አቋም ምንም ዓይነት ጥርጥር ሳያድርበት በሙሉ ልብ ሆኖ ጎልያድን «እግዚአብሔር ዛሬ አንተን በእጄ አሳልፎ ይሰጣል . . .» (1ኛ ሳሙ 17፡46) በማለት ተናግሮ ገድሎታል፡፡

መከራ ለረዥም ጊዜ ሲራዘምና አንድ ሰው በጥርጥር ማዕበል ውስጥ ሲወድቅ የእግዚአብሔርን ምሕረት ይጠራጠራል፡፡ ወይም ደግሞ ሰውየው በእርሱ ላይ ጥንቆላ እንደተደረገበት አድርጎ ስለሚቆጥር የሚመጣበትን ችግር ለማስቆም ወደ ጠንቋዮች ቤት ይሄዳል፡፡ መከራና ረዥም ጊዜ በአሳብና በጥርጥር ያልተሞላ ብርቱ ልብ ይፈልጋል፡፡

9- ስህተቶችን በአንድ መጠቅለል፡፡

ለምሳሌ በእናቷና በአባቷ ንትርክና ጭቅጭቅ በተሞላ ቤት ውስጥ የምትኖር አንዲት ልጃገረድ እርሷም ትዳር ስትይዝ እንደ ወላጆቿ እንደምትሆን አድርጋ ስለምትቆጥር ትዳርን ትፈራለች፡፡ ስለሆነም አያንዳንዱን ባል የምትመለከተው አባቷ በእናቷ ላይ እንደሚያደርሰው ያለ ተመሳሳይ ችግር በእርሷም ላይ እንደሚያደርስባት አድርጋ ነው፡፡

ለጓደኛው የነገረው ምሥጢር አደባባይ ውጥቶ ሲወራ የሚሰማው ሰው ጓደኞቹን በሙሉ ስለሚጠረጥር ታማኝነታቸውንም ይጠራጠራል፡፡ ይህ ሰው የቅርቡ የሆነውን ጨምሮ ለጓደኞቹ ሁሉ ምሥጢሩን ስለማያካፍል ራሱን ወዳድ ሰው ይሆናል፡፡ የቅርብ ጓደኛውን ሲመለከትም በልቡ «ይኼም እንደ ሌሎቹ ያደርጋል» በማለት ይናገራል፡፡

ሁሉም ሰው እንደዚህ ያደርጋል ብሎ መጠርጠር ትክክል አይደለም፡፡ ይህን የሚያደርገው ሰው ግን «የዚህ አገር ሰዎች ሁሉ ንፉጎች ናቸው!» ወይም ደግሞ «ከዚያ አገር ሚስት አታግቡ!» በማለት ይናገራል፡፡ እንዲህ ያለው አሳብ በዚህ ሰው ሕሊና ውስጥ የተተከለው በአንድ ሰው ላይ የተመለከተውን ስህተት ለሁሉም ማጠቃለያ አድርጎ ስለሰጠ ነው፡፡

ከከንቱ ስሜት የሚመጣ ጥርጥር፡፡

አንድ ሰው ከአሥራ ሦስት ቁጥር በስተ ጀርባ የተሰወረ ክፋት አለ ብሎ ያምናል፡፡ ስለሆነም አሥራ ሦስት ቁጥርን ይዞ የሚመጣውን ቀንና ማንኛውንም ነገር ይጠራጠራል፡፡

የቤቱ ቁጥር አሥራ ሦስት ቁጥርን ያካተተ ከሆነ ወይም በስልክ ቁጥሩ ውስጥ አሥራ ሦስት ቁጥር ካለ ወይም ደግሞ ሥራ ለመቀጠር የሚያስገባው ማመልከቻ ውስጥ ይህ ቁጥር ካለ አይቀናኝም ብሎ ስለሚያስብ ይጠራጠራል፡፡ ይህ የጥርጥር አሳብ በሕሊናው ውስጥ እየጎላ ሲመጣ በራሱ የማይተማመን ሰው ይሆናል፡፡ ከዚህ በኋላ እንዲህ ያለውን እምነት ከሕሊናው ውስጥ ለማውጣት አስቸጋሪ ይሆንበታል፡፡

ምዕራፍ ስድስት::

ፍርሃት::

- ሁለት አጠቃላይ አሳቦች::
- ቅዱስ ፍርሃት::
- የተፈጥሮ ፍርሃት::
- ሞትን መፍራት::
- ሰዎችን መፍራት::
- ዲያብሎስን መፍራት::
- ያለ ምክንያት መፍራት::
- መፍትሔው::

ሁለት አጠቃላይ አሳቦች::

ፍርሃትን በተመለከተ ሁለት ጠቃሚ አሳቦች በሕሊናችን ውስጥ ይመጣሉ:: እነርሱም:-

1- ቅዱስ ፍርሃት ስላለ ፍርሃት ሁሉ ኃጢአት ወይም ውጊያ አይደለም::

2- የመጀመሪያ ወላጆቻችን ኃጢአት ከመሥራታቸው በፊት ፍርሃት በሰው ልጆች ተፈጥሮ ውስጥ አልነበረም::

እግዚአብሔር ከፈጠረው በኋላ አዳም ያለ ምንም ፍርሃት ከዱር አውሬዎች ጋር ይኖር ነበር:: ከእግዚአብሔር ጋር የነበረው ግንኙነትም ከፍርሃት የተለየ ነበር:: ኃጢአት ከሠራ በኋላ ግን በጣም ስለ ፈራ ራሱን በዛፎች መካከል ደብቆ እግዚአብሔርን እንዲህ ነበር ያለው:- «. . . በገነት ድምፅህን ሰማሁ፤ዕራቁቴንም ስለ ሆንሁ ፈራሁ . . .» ዘፍ 3:10::

ቃየን ወንድሙ አቤልን ከገደለው በኋላ የፍርሃት በሽታ እየጨመረ ስለ መጣ ወደ ሽብር ተለውጧል:: ቃየን ለእግዚአብሔር የተናገረው እንዲህ በማለት ነበር:- «እነሆ ዛሬ ከምድር ፊት አሳደድኸኝ፤ከፊትህም እሰወራለሁ፤በምድር ላይ ኩብሳይና ተቅበዝባዥ እሆናለሁ፤የሚያገኘኝም ሁሉ ይገድለኛል::» ዘፍ 4:14::

ከዚህ በኋላ ፍርሃት የሥነ ልቦና በሽታ ስለሆነ ወደ ሰው ተፈጥሮ ገባ:: ከዚያም ለፍርሃት የተለያዩ ምክንያቶችና ውጤቶች ብቅ ብቅ ማለት ጀመሩ:: ቀጥሎም ፍርሃት ዲያብሎስ የሰው ልጆችን የሚዋጋበት መንፈሳዊ ውጊያ ሆነ:: ከዚህ በኋላም ፍርሃት፣ ስጋት፣ ድንጋጤ፣ ጭንቀትና ሽብር የሚባሉ የፍርሃት ደረጃዎች ወጡ:: ሰው ከፍተኛ ፍርሃት ካደረበት ሕሊናውን መሳትና አልፎ ተርፎም ይሞት ጀመር:: በፍርሃት ምክንያት ነርቮቹ መሽመድመድ ሰውነቱም ይንቀጠቀጥ ጀመር::

ቅዱስ ፍርሃት::

ይህ ፍርሃት በሚከተሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላት ተገልጦአል:- «የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው . . .» (መዝ 110:10፤ምሳ 9:10::)፤«. . . በእንግድነታችሁ ዘመን በፍርሃት ኑሩ::» (1ኛ ጴጥ 1:17::) መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም እንዲህ ብሏል:- «ሥጋንም የሚገድሉትን ነፍስን ግን መግደል የማይቻላቸውን አትፍሩ፤ይልቅስ ነፍስንም ሥጋንም በገሃነም ሊያጠፋ የሚቻለውን ፍሩ::»፤«አምን አላችኋለሁ እርሱን ፍሩ::» (ማቴ 10:28፤ሉቃ 12:5::)

እዚህ ላይ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሁለት የፍርሃት ዓይነቶችን በፊታችን ገልጦልናል:: እነርሱም የሚያስፈልግ ፍርሃትና የተሳሳተ ፍርሃት ናቸው::

እግዚአብሔርን መፍራት እርሱን ወደ ማክበርና ለእርሱ ወደ መታዘዝ ያደርሰናል:: ከዚህ በተጨማሪ ትእዛዛቱን ለመጠበቅ፣ እርሱን ለማፍቀርና በንስሓ ሕይወት ለመመራት ይጠቅመናል:: ይሁን እንጂ ዛሬ የምናተኩረው መንፈሳዊ ውጊያዎች በሚለው ዐቢይ ርዕስ ላይ ስለሆነ ቅዱስ ፍርሃትን በዚህ እናጠቃልለዋለን::

የተፈጥሮ ፍርሃት::

አንድ የሥነ ልቦና አዋቂ ፍርሃት በሦስት ምክንያቶች ሊገለጥ ይችላል በማለት ተናግሯል:: እነርሱም:- በጨለማ፣ ባልታወቀ ነገርና በድንገተኛ እንቅስቃሴ ናቸው::

እነዚህ ሦስት ምክንያቶች በአንደኛው ምክንያት ይሸውም ባልታወቀ ነገር ጥላ ሥር ሊጠቃለሉ ይችላሉ:: ከጨለማ በስተጀርባ አንድ ያልታወቀ ነገር ተሸሽጎ እንዳለ ሁሉ ከድንገተኛ እንቅስቃሴ በስተጀርባም አንድ ያልታወቀ ምክንያት አለ:: ይሁን እንጂ አንዳንድ ሰዎች ጨለማንም ሆነ ድንገተኛ እንቅስቃሴን አይፈሩም:: መንፈሳዊነት በእነዚህ ሰዎች ዘንድ የለም::

ሞትን መፍራት::

ብዙ ሰዎች መጎዳትን ስለሚፈሩ ሞትንና የሞትን ምክንያቶች ይፈራሉ:: ሞትን የማይፈሩ ሰዎች ጥቂት ናቸው:: የሞት ፍርሃት ግን በራሱ የማይታወቅ ፍርሃት ነው:: ሰው ሞትን ቀደም ሲል አይቶት የማያውቀው ነገር ነው:: ከሞት በኋላ ያለው ነገርም አይታወቅም:: ሰው ሞትን የሚፈራው እንዴት እንደሚሞትና ነፍሱ እንዴት ከእርሱ ተለይታ እንደምትሄድ ስለማያውቅ ነው:: እነዚህ ሁሉ ነገሮች ሰውን ያስፈሩታል::

ከዚህ በተቃራኒ ከሞት በኋላ ባለ መዳረሻው እርግጠኛ የሆነ ሰው ግን ሞትን ይናፍቀዋል እንጂ አይፈራውም:: በመሆኑም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ በማለት ተናግሯል:- «. . . ልሄድ ከክርስቶስም ጋር ልኖር እናፍቃለሁ፤ከሁሉ ይልቅ እጅግ የሚሻል ነውና . . .» ፊል 1:23:: ከኢየሱስ

ክርስቶስ በስተ ቀኝ የተሰቀለው ወንበዴ « . . . እውነት እልሃለሁ፡- ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ» (ሉቃ 23:43) የሚለውን ቃል ኪዳን ከሰማ በኋላ ሞት እንዳሳስፈራው ምንም ጥርጥር የለውም፡፡ ስምያን አረጋዊም ሞትን ስላልፈራ ጌታ እንዲያሰናብተው እንዲህ በማለት ጥያቄ አቅርቧል፡- «ጌታ ሆይ፡- አሁን እንደ ቃልህ ባሪያህን በሰላም ታሰናብተዋለህ፤ዓይኖቼ በሰዎች ሁሉ ፊት ያዘጋጀኸውን ማዳንህን ተመልክተዋልና . . .» ሉቃ 2:29-30፡፡

ሞትን የሚፈራ ሰው ንስሓ ያልገባና ያልተዘጋጀ ከመሆኑም በላይ ይህን ዓለም የሚወድ ሰው ነው፡፡ ይህ ሁሉ የሚገልጠው ኃጢአትን ነው፡፡ ሞትን መፍራት ያለ ነገር ቢሆንም ወደ ፍርሃት የሚመሩት ምክንያቶች ግን ኃጢአት ናቸው፡፡ በትሕትናቸው የሚታወቁ ቅዱሳን ራሳቸውን ኃጢአተኞች አድርገው ስለሚቆጥሩ ሞትን ይፈራሉ፡፡ ሞትን መፍራት ሰውን ለዚህ ያዘጋጀዋል ወይም ከዚህ ያርቀዋል፡፡ መንፈሳዊ ሰው በንስሓና በእግዚአብሔር ፍቅር ለሞት የተዘጋጀ ይሆናል፡፡ ስለሆነም ፍርሃት ከርሱ ስለሚርቅ ሰላሙን ከእግዚአብሔር ያገኛል፡፡

ዲያብሎስ ግን ሞትን መፍራትን የሚያጠምደውን ሰው በተቃራኒው አቅጣጫ ለመጣል ይጠቀምበታል፡፡ እርሱ ስለባውን ከሞት እንዲሸሽ ካደረገው በኋላ ስለ ሞት ምንም ዓይነት ወሬ እንዳያወራና ሞትን አስመልክተው የሚወሩ አስጨናቂ ወሬዎችን እንዳይሰማ ያደርገውና የሕይወትን አስደሳች ጎን ወደ እርሱ ያሰገባል፡፡

ሁኔታቸው በአስጊ ሁኔታ ላይ ያለና ለሞት የቀረቡ የአንዳንድ የታመሙ ሰዎች ዘመዶችና ሐኪሞች በእነርሱ ፊት ሞት የተባለውን አስፈሪ ነገር ማንሳት አለመፈለጋቸው ያሳዝናል፡፡ ሕመማቸውን ሙሉ ለሙሉ ይረሱ ዘንድ ይዋሹዋቸዋል፣ በሚያስደስቱ ወሬዎች ያረጋጓቸዋል፣ ያዝናኗቸዋል፣ ያስቋቸዋልም፡፡ ይህን በማድረጋቸው የሞትን ፍርሃት ሊያቀሉላቸው ቢችሉም ሞት ግን ባልጠበቁት ሰዓት በመምጣት አንዳች ሳይዘጋጁ ይወስዳቸዋል፡፡

ዲያብሎስም «መሞትህ ካልቀረ በቀረህ ጊዜ በሚቻልህ ሁሉ ሕይወትህን አስደስታት!» በማለት ሰለባውን ይፈታተነዋል፡፡ ይህ «ነገ እንሞታለንና እንብላና እንጠጣ፡፡» (1ኛ ቆሮ 15:32) የሚሉት የአነ ሆድ አምላኩ አስተሳሰብ ነው፡፡ እዚህ ላይ ሞትን መፍራት አንድ መውጊያ ሞትን ማስወገድ ደግሞ ሌላ መውጊያ መሆኑን እንመለከታለን፡፡ ዲያብሎስ የሚዋጋው በሁለቱም መንገድ ነው፡፡ ሰውየው በመሞቱ አርግጠኛ መሆኑን ዲያብሎስ ሊያውቅ ንስሓ እንዳይገባና ራሱን እንዳያዘጋጅ ለመከላከል በሌላ ዓይነት ውጊያ ይዋጋዋል፡፡

ዲያብሎስ ሞትን መፍራት የሰውን ሕሊና የሚያሸመደምደው አድርጎ በማሳየት ሰውየው ለዘላለማዊነቱ ይዘጋጅ ዘንድ እንዳይችል እንዲህ ባለው ፍርሃት ውስጥ እንዲኖር ያደርገዋል፡፡ ይህ ሰው መሪር ሞትን እስከነ ሕማሙ ሊያየው የሚችለው ብቸኛ ሥዕል አድርጎ ያቀርብለታል፡፡ በዚህ ውስጥ ከሕይወቱ፣ ከሚወዳቸውና ከደስታዎቹ ጋር እንደሚያጣቸው ያሳዩዋል፡፡ ተስፋ መቁረጥንና ሕመምን በማሳየት ዘላለማዊነትንና ለዘላለማዊ ሕይወት መዘጋጀትን እንዳያስብ ያደርገዋል፡፡

በሌላ መልኩ ዲያብሎስ ሞትን መፍራት ሰውን ወደ ክፉ ኃጢአቶች ለመወርወር የሚጠቀምባቸው አድርጎ ያቀርባቸዋል፡፡ ከእነዚህ የከፉ ኃጢአቶች መካከል እምነትን መካድ አንዱ ነው፡፡ እዚህ ላይ ለማዕታት የተሸለ ሕይወት ለመውረስና ከእግዚአብሔር፣ ከመላእክቱና ከቅዱሳኑ ጋር ለመኖር ይናፍቁ ስለ ነበር ሞትን ይቀበሉ ዘንድ በጣም ይናፍቁ ነበር፡፡

የዘላለማዊነት ፍቅር ልብ ሞትን እንዳይፈራ ከመርዳቱም በላይ የዝግጁነት መንፈስን ያድላል፡፡ ስለ ዘላለማዊነት፣ ስለ ሰማያዊቷ ኢየሩሳሌም፣ ድንቅ ስለሆነው ትጉሃኤና በመንፈስ ስለ መኖር ተነጋገሩ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የእግዚአብሔር ልጆች ሊመሰጡባቸው በሚገቧቸው የተለያዩ ድንቅ ርዕሶች ላይ ተወያዩ፡፡ የእነዚህ ርዕሶች ተጽእኖ ወደ ልባችሁ፣ አሳቦቻችሁና ስሜቶቻችሁ በጥልቀት ይግባ፡፡

ሞትን የሚፈሩ ሰዎች ሁሉ ሞትን የሚያመጣውን በሽታ ይፈራሉ፡፡ በሽታን የሚፈራ ሰው ማመርቀዝን፣ ጥቃቅን ነፍሳትንና የሰውነትን ድካም ይፈራል፡፡ አንድ ሰው ራሱን ከእነዚህ ምክንያቶች ለመጠበቅ የሚሞክረው ሁሉን እንዲጠራጠር በሚያደርገው በበዛ ፍርሃት ተከቦ ስለሚሆን ይህ በራሱ በሽታ ይሆንበታል፡፡

ዲያብሎስ የበሽታዎችን ፍርሃት በመጠቀም ሰውን ወደ ዓለማዊ ምኞት ይወረውረዋል፡፡ ስለሆነም ሰውነቱ እንዲያገግም በሚል ሰበብ ፕሮቲንነት ያላቸውን ምግቦች እንዲበላ፣ እንዲጠጣ፣ የስፖርት እንቅስቃሴ እንዲያደርግ፣ እንዲዝናና፣ ችግር እንዳያስብ፣ ጥቂት እንዲሠራ፣ ጉልበቱን እንዲቆጥብ፣ ጥረቱንም እንዳያጎላ ይመክረዋል፡፡ ይህ ደግሞ ሰውየው ሊፈጽማቸው የሚገቡትን ጠቃሚ መንፈሳዊ ጉዳዮችን እንዲዘነጋ ያደርገዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለእገልግሎቱ ታማኝ ስለማይሆንም የታመሙትን መጠየቅ ይዘነጋል፡፡ ጤንነቱ ከማንኛውም መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ይልቅ ለእርሱ ግቡ ይሆናል፡፡

ይህ ይሁን እንጂ ለሞት ብቸኛ ምክንያት የሚሆነው በሽታ ብቻ አይደለም፡፡ ለምሳሌ ወታደሮች በድፍረትና በወኔ ይሞታሉ፡፡ የሞት ፍርሀት ወደ ሰው ልብ ዘልቆ ከገባ ግን ድፍረቱንና ወኔውን ስለሚሰልበው ፈሪ ያደርገዋል፣ መንፈሱን ያጻክመዋል፣ በጎ የሆኑ ሰብእናዎቹንም ያራቁትበታል፡፡ ይህን አስመልክቶ ቅዱስ አውግስጢን የተናገረው አባባል አለ፡- «በውስጤ ምንም እንደማልፈራና ምንም እንደማልመኝ ሲታወቀኝ በዓለም ጫፍ ላይ እቀመጣለሁ፡፡»

ሰዎችን መፍራት፡፡

ይህ ደካማ ነፍሳትን የሚያጠቃ ሌላ መንፈሳዊ ውጊያ ነው፡፡ ለሰዎችን የሚፈሩትን ያህል እግዚአብሔርን የማይፈሩ ሰዎች ስላሉ እነርሱ ጥፋታቸውን ይጥትታሉ፡፡ እነርሱ ሰዎችን በጣም ብርቱዎች አድርገው ስለሚቆጥሩ ጥቃት ያደርሱብናል፣ ሥራችንን ያሳጡናል፣ ለችግር ወይም ለመከራ ያጋልጡናል፣ ያዋርዱናል፣ ተስፋችንን ይቃወማሉ በማለት ያስባሉ፡፡ ስለሆነም ለእነርሱ የሚሰጡት ግንዛቤ ከፍተኛ ነው፡፡

ዲያብሎስ ከዚህ ፍርሃት ተጠቃሚ ስለሚሆን እነዚህን ሰዎች ወደ ሽንገላ፣ ወደ ጥርጥርና መስሎ ወደ መታየት ያስገባቸዋል። እነዚህ ሰዎች ፍቅርና የሰዎችን ማረጋገጫ አግኝተናል ብለው ስለሚያስቡ ቢያንስ ቢያንስ ጉዳታቸውን አስቀርተናል ይላሉ። በመሆኑም ምንም ዋጋ እንደሌላቸውና እንደተናቁ ሆነው ይታያሉ። እነዚህ ሰዎች ሰዎችን ለማስደሰት ሲሉ ክፉውን በጎ፣ በጎውንም ክፉ ይላሉ። ከዚህ በተጨማሪ የእነርሱ ጠላቶች የእርሱ ጠላቶች፣ የእነርሱ ወዳጆችም የእርሱ ወዳጆች ይሆናሉ።

በዚህ መሠረት በፍርሃት ምክንያት መመሪያና ቁም ነገር ይጠፋሉ። ሌላው ቢቀር በዚህ ምክንያት እምነት እንኳ ይጠፋል። ሰው የሚወዳትን ልጅ ስለ ፍርሃት ሲል ይክዳል።

እንዲህ ባለው ጉዳይ ውስጥ ሰው «. . . ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር ልንታዘዝ ይገባል።» (ሐዋ 5:29) የሚለውን ቅዱስ ቃል ይዘነጋል። ከዚህ በተጨማሪ «ጎጥኡን የሚያጸድቅና በጻድቁ ላይ የሚፈርድ ሁለቱ በእግዚአብሔር ዘንድ አስጸያፊዎች ናቸው።» (ምሳ 17:15) የሚለውን የእግዚአብሔር ቃል ይረሳዋል። ይህ ሰው ምንም ዓይነት የተሳሳተ ሥራ ቢሠራ ወይም አሳቡን ሕሊናው ሊቀበለው ቢችገርም የእርሱ ብቸኛ ጉዳይ መዳኑ ላይ ብቻ ይሆናል።

ሰዎች በፍርሃትና በደካማ መንፈስ ውስጥ ሲሆኑ ስለሚያደርጉት ነገር በአረብኛ የተጻፈ ግጥም አለ።

«በምድራቸው ላይ ስላለህ አስደስታቸው!
በቤታቸው ውስጥ ስላለህ ጥፋታቸውን ሸፍንላቸው!
በሰፈራቸው ውስጥ ስላለህም እጅ ንሳቸው!»

እንዲህ ዓይነቱ ሰው ሌሎች የሚሠሩትን ይሠራል እነርሱ የሚናገሩትንም ይናገራል። በማንኛውም ጊዜ ሁኔታዎችን ተመልክቶ ሊቀየርም ይችላል። ይህን ሰው የፍርሃት ማዕበል እያላተመ ሲወስደው የሚመራው በፍርሃት እንጂ በሕሊናው አይደለም። እንዲህ ዓይነቱን ሰው ስለ መንፈሳዊ መመሪያዎች አንስተህ ብትወቅሰው [ምን ላደርግ እችላለሁ? ሕይወቴ ያለችው በእነዚህ ሰዎች እጅ ላይ ነው!] በማለት ይመልስልሃል። አንተም ሕይወቱ ያለችው በእግዚአብሔር እጆች ላይ ብቻ እንደ ሆነ ስትነግረው በእውነትና በተግባር ሳይሆን እንዲሁ በአንደበትህ ብቻ የምታናግረው ይመስለዋል።

በእውነትም በውጪ ካሉ ፍርሃቶቻቸው በውስጥ ያለ እምነታቸው እጅግ የቀነሰ አድርጎ በማሳየት ዲያብሎስ በፍርሃት የሚያጠፋቸው ሰዎች ብዙዎች ናቸው። ብዙዎች ሰዎች ሊጎዱን ይችላሉ በሚል ፍርሃት ብቻ ሳይሆን በዓለም ያሉ ፍላጎቶቻቸው በእነዚህ ሰዎች እጆች ውስጥ ስላሉና የሚሰጧቸውም ሆነ የሚነሷቸው እነርሱ እንደሆኑ አድርገው ስለሚያምኑ ከእግዚአብሔር ይልቅ ሰዎችን ያመልካሉ። ከምኞቶቹ ቁጥጥር በታች የወደቀ ሰው ምኞቶቹን ላለማጣት ስለሚፈራ ማዕበሉን ተከትሎ ይጠፋል።

እንደነዚህ ዓይነቶቹ ሰዎች የሚፈሩት የሥራ መመሪያዎቻቸውን ወይም የማግኘታቸውን ምንጮች ብቻ አይደለም የደስታዎቻቸውን ምንጮች ጭምር እንጂ! እዚህ ላይ የሚወድቁ ሰዎችን ብዙ ስህተቶች እንመለከታለን። ፈንጠዝያን መውደድ የመጀመሪያው ስህተት ሲሆን ይህን ፈንጠዝያ ማጣት ደግሞ ሁለተኛው

ስህተት ነው። ይህን ደስታ ወይም ፈንጠዝያ ሊከለክሏቸው የሚችሉትን ሰዎች መሸንገል ሦስተኛው ስህተት ሲሆን ያለማቋረጥ በደስታ ውስጥ ለመኖር መመኘት ደግሞ አራተኛው ስህተት ነው። እንዲህ . . . እንዲህ እያለ ይቀጥላል።

አንዳንዶቹ ስህተቶቻቸውን የሚገልጡትን ሰዎች ይፈራሉ። ስለሆነም እነዚህን ሰዎች ስለሚፈሯቸው የእነርሱን አፍ ለማዘጋት ሲሉ በማስደሰት ሊደልሏቸው ይሞክራሉ። ወይም ደግሞ ዲያብሎስ በእነርሱ ላይ አንድ የሆነ ወንጀል እንዲሠሩ በማነሣሣት ወደ ጥፋት ይመራቸዋል። ለምሳሌ፡- ሴባ ሲሰርቅ የተመለከተውን ሰው ሊገድል ይችላል። አመንዝራ የሆነ ሰውም ኃጢአቱን የሚያጋልጥበትን ሰው ሊገድል ይችላል። ይህን በመሰሉ ጉዳዮች ውስጥ ጉልበተኛው ገዳዩ አይደለም። ይልቁኑ እንዲህ ያለው ገዳይ ሰነፍና ፈሪ ገዳይ ነው።

በአጠቃላይ ሰዎች የሚፈሩት ከእነርሱ ይልቅ በእውቀት፣ ፈጥኖ በማጥቃት ችሎታ፣ በብቀላና ወጥመዶችን በማድመጥ ከእነርሱ የላቀ ጉልበት ያላቸውን ሰዎች ነው። ይህን እንጂ ሰዎችን መፍራት የበለጠ ተጎጂዎች ያደርጋቸዋል። ሌሎች ሊቃወሟቸው እንደማይችሉ አድርገው ስለሚያስቡ ያጠቋቸዋል ያለማቋረጥም ያስፈራሯቸዋል። የሚጠቁት ሰዎችም ከፍርሃት የተነሣ ፈቃዳቸውን ይበልጥ ሊፈጽሙላቸው ይጀምራሉ። ይህን በማድረጋቸውም ለበለጠ አደጋዎች ይጋለጣሉ። ይህ ድርጊትም ተመላልሶ የሚመጣ ይሆናል።

ዲያብሎስን መፍራት።

ዲያብሎስን ስትፈራ፣ እርሱን ለመዋጋት ተስፋ ስትቆርጥ ወይም እርሱን መቋቋም ሊያቅትህ እጅህን ለእርሱ ትሰጣለህ። በዚህ ጊዜ ስለፈራኸው ብቻ ይደሰታል። ራስህን በሁሉም የውጊያ ዓውድ ላይ ተሸናፊ አድርገህ ስለምትቆጥርም በርትተህ አትታገለውም። ሐዋርያው ግን ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገላ አንበሳ በሰዎች ዙሪያ እየዞረ ስለሆነ ልናደርገው የሚገባንን ነገር የገለጸልን እንዲህ በማለት ነው፡- «. . . በእምነት ጸንታችሁ ተቃወሙት።» 1ኛ ጴጥ 5:9።

ዲያብሎስ የሚያስፈራ ገጽታዎችን ጨምሮ ብዛት ባላቸው የተለያዩ ማስፈራሪያዎች እየተገለጠ ቅዱስ አንጦንስን ሊያስፈራራው ቢሞክርም አልተሳካለትም። አባ አንጦንስ በቅሪተ አፅም የተሞላ መቃብር ውስጥ ለማደር አልፈራም። ታላቁ አባ መቃርስም በተንተራሰው የራስ ቅል ውስጥ ያደሩ ርኩሳን መናስፍት ሲያናግሩት ምንም አልፈራቸውም። ቅዱሳን አባቶቻችን ዲያብሎስን ስላልፈሩት ድል አድርገውታል። በርኩሳን መናፍስት ላይ ለእነርሱ ኃይል የሰጠ እግዚአብሔር ለእኛም ኃይሉን ሰጥቶናል።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገራቸው ቃላት በእውነት ምንኛ ድንቅ ናቸው! «. . . ሰይጣንን እንደ መብረቅ ከሰማይ ሲወድቅ አየሁ።» ሉቃ 10:18። ስለዚህ ከሚዋጋህ ኃይል የሚበልጥ መለኮታዊ ኃይል ስላለህ ርኩሳን መናፍስትን አትፍራቸው። ከዚህ በተጨማሪ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ «. . . ነገር ግን ከሚቻላችሁ መጠን ይልቅ ትፈተኑ ዘንድ የማይፈቅድ እግዚአብሔር የታመነ ነው . . .» (1ኛ ቆሮ 10:13) የሚል ቃል ስለ ተጻፈ ዲያብሎስን አትፍሩት።

በጻድቁ ኢዮብ ታሪክ ውስጥ እንደምንመለከተው ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ ሰይጣን ጫፍህን ሊነካ አይችልም። ዲያብሎስ እንዲፈትንህ እግዚአብሔር የሚፈቅድለት በአንተ ኃይል ድል በምታደርጋቸው ነገሮች ብቻ ነው። ስለዚህ ለዲያብሎስ ካለው የበለጠ ግምት አትስጠው። ልትፈራው በማይገባህ መጠንም አትፍራው። አንተ ራስህን ዘብ ሆነህ ጠብቅ እንጂ እርሱን አትፍራ።

ያለ በቂ ምክንያት መፍራት።

ብዙዎች የሚፈሩት ያለ ምንም በቂ ምክንያት ነው። የእነርሱ ፍርሃት ወይ የልጅ አሊያም የበሽታ ነው። ትንሽ ልጅ በቤቱ ውስጥ ምንም የሚያስፈራ ነገር ሳይኖር ሌቦች ወይም ጭራቆች እንዳሉ አድርጎ ስለሚያስብ ይፈራል። ትላልቅ ሰዎችም በምድር ላይ የሌለ ነገር እያለሙ ይፈራሉ ወይም በቅዠት በተሞላ የታመመ ሕሊናቸው የፈጠሩትን በምድር ላይ የሌለ ነገር እያሰቡ ይፈራሉ።

ይህን የመሰሉ የተወሳሰቡ የሥነ ልቦና በሽታ ዓይነቶች የታመመውን ሰው ሊያጠቁት የሚመጡ ሰዎች እንዳሉ አድርገው ያስፈራሩታል። በእርግጥ እርሱን የሚጎዱት ነገሮች ግን የሥነ ልቦና በሽታዎቹ ናቸው።
ፍርሃት ርኩሳን መናፍስት በሚያመጧቸው ምክንያቶች ይነሣል። ይህም ማለት ሰውየውን በፍርሃት በመሙላት ወይም የሌሉ ጥርጥሮችን በሕሊናው በመትከል አንድ ሰው እንዳጠመደበት፣ እንደሚከታተለውና ሊያጠቃው እንደሚሞክር አድርጎ ያሳስበዋል።

መፍትሔው።

እግዚአብሔር ለሰው «አኔ ከአንተ ጋር ነኝ፣ ማንም ክፉ ሊያደርግብህ የሚነሣብህ የለምና አትፍራ . . .» (ሐዋ 18፡10) በማለት የገባውን ቃል ኪዳን ማስታወስ አስፈላጊ ነው። ከዚህ በተጨማሪ የእግዚአብሔርን ጥበቃና እርዳታም ማስታወስም ያስፈልጋል።

እምነት ፍርሃትን ያስወግዳል። የፈራን ሰው መለኮታዊው ኃይል እንደሚጠብቀውም እምነቱ ያስታውሰዋል። ይህን አስመልክቶ ነቢዩ ዳዊት የተናገራቸው ቃላት ምንኛ ድንቅ ናቸው! «በሞት ጥላ መካከል እንኳ ብሄድ አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉን አልፈራም።» መዝ 22፡4።

ምዕራፍ ሰባት።

የአሳቦች ውጊያ።

- የተሳሳቱ አሳቦች።
- ክፉ ትዝታን ማስወገድ።
- የአሳብ ጅማሬ።
- የኃጢአት አሳብ መገኛዎች።
- ውጊያና ውድቀት።
- ወደ ውድቀት የሚመሩ ነገሮች።
- የአሳብ የውጊያ ዓይነቶች።
- አሳብን የመያዝ ጉዳት።
- የአሳብ ባርነት።
- አሳብን እንዴት ማሸነፍ ይቻላል?
- ጥያቄና መልስ።

የተሳሳቱ አሳቦች።

ሰው በመንፈሱ፣ በሥጋው፣ በነፍሱ፣ በሕሊናው፣ በስሜቱና በሁሉንተናው ንጹሕ ሆኖ ሊኖር ይገባዋል። አንተን የማያስደስት ማንኛውም ዓይነት አሳብ ከእኛ ይራቅ እንዲህ ብለን ወደ እግዚአብሔር እንጸልያለን። በጸሎታችን ውስጥም፡- «አንተ ነፍሳችንን፣ ሥጋችንን፣ መንፈሳችንንና አሳባችንን አንጻ።» እንላለን። በዚህ መሠረት አሳብ ሊነጻ ያስፈልገዋል ማለት ነው።

በሕሊና ውስጥ የሚመላለሱት የተሳሳቱ አሳቦች ቁጣ፣ ብቀላ፣ ትዕቢት፣ ኩራት፣ ከንቱ ውዳሴ፣ የቁም ቅዠት፣ የምቀኝነት አሳቦች፣ ቅናት፣ ዓለማዊ ምኞቶች፣ ዝሙት፣ ርኩሰትና እነዚህን የመሰሉት ናቸው። ስለሆነም ለመንጻቅ ሞትን የሚያወርሰን ክፉ ትዝታ ከእኛ ይራቅ በማለት እንጸልያለን። ስለሆነም ክፉ አሳብ መንፈሳዊ ሞትን ስለሚያመጣብን ትዝታው በሕሊናችን ውስጥ ሊቀር አይገባውም።

ክፉ ትዝታን ማስወገድ።

የሌሎች ሰዎችን ኃጢአቶች ማስታወስ እነርሱን በመርገም ወይም በማንቋሸሽ ወይም በማዋረድ እንድንወድቅ ያደርገናል። በአንተ ላይ የመጣውን የሰዎችን ጥቃት ማስታወስህ እነርሱን እንድትጠላቸው፣ ቁጣ ውስጥ እንድትገባና በእነርሱ ላይ የብቀላ እርምጃ እንድትወስድ በማድረግ ይጥልሃል። እንዲህ ያለውን የሥጋ ኃጢአት ማስታወስህ ሕሊናህን ስለሚያጎድፈው ወደ ሥጋ ምኞት መልሶ ይከትሃል።

ክፉ ነገርን ያለማቋረጥ ማስታወስ የሰውን ማንነትና የማያገናዝብ ሕሊናውን ይጨነጉታል። እነዚህ የተሳሳቱ አሳቦች በሰው ሕሊና ውስጥ ሲያድሩ ክፉ ኃሳቦች፣ ክፉ ጥርጣሬዎች፣ ክፉ ማመንታቶችና ክፉ ምኞቶች ሆነው ይንሰራፋሉ። ከዚህ ሌላ ኃጢአቶች በሕልም መልክ ይገለጣሉ።

ስለዚህ ክፉ አሳብ ራቅ! ራስህን ለመገሠጽ ስትፈልግ እንኳ ልታስታውሳቸው አትሞክር! ምን ሊመጣ እንደሚችል እንዴት ልታውቅ ትችላለህ? አሳብ በተግሣጽ ሰበብ ወደ ሕሊናህ ከገባ በኋላ ወደ ውስጣዊ ውጊያነት ይለወጣል። በዚህ ጊዜ በሕሊናህ ውስጥ የክፋት ትዕይንቶች የሚገለጡት ንስሓ እንድትገባባቸው ሳይሆን ወደ ስሜትና ምኞት ተለውጠው ነው።

አንድ ሰው «እኔ ኃጢአቶቼን በፊቴ በማድረግ ንስሓ ለመግባትና ትሑት ለመሆን እችል ዘንድ ራሴን መገሠጽ የለብኝም?» ብሎ ሊጠይቅ ይችላል? ለዚህ መልሱ «ኃጢአትህን ጠቅሰል ባለ መልኩ ልታስታውስ ትችላለህ። ይሁን እንጂ አጓጊ በሆኑ ዝርዝር ጉዳዮች ለመጠቃት እንዳይሆን መጠንቀቅ ያስፈልጋል። እንዲህ ያለው ጉዳይ በተለይም ሰውየው የሰሜትንና የምኞትን ኃጢአቶች ሙሉ ለሙሉ ያላስወገደና ሙሉ ንጽሕናን ያላገኘ ከሆነ በድጋሚ እነዚህ ኃጢአቶች ሊዋጉት ይችላሉ። የእነዚህን ኃጢአቶች ዝርዝር ማስታወስ ከጀመርህ ራስህን ወደ እነርሱ ጉያ መልሰህ ትከታለህ።

በኃጢአት ምክንያት ራስን መገሠጽ በሕሊናህ ውስጥ አንድ አሳብ ለማስቀረት የሚደረግ ተራ የዲያብሎስ ማጭበርበር ነው። ዲያብሎስ ይህን የተቀደሰ ዕድል (ራስን መገሠጽ) በመጠቀም ሰውን በተቃራኒው አቅጣጫ እንዲጓዝ የሚያደርግ ዘዴው ነው።

የአሳብ ጅማሬ።

የኃጢአት አሳብ በኃጢአት ላይጀምር ይችላል . . . ቢጀምርና ራሱን የሚያጋልጥ ከሆነ ንጹሕ ልብ ከእርሱ ይሸሻል ወይም ያጠፋዋል ወይም ደግሞ በዚያ እንዳያድር ባገኘው ዘዴ ሁሉ ይቃወመዋል። ስለዚህ በማታለል ሊጀምር ይችላል። ስለሆነም በተቀደሰ ቅንዓት የተቃጠለ በማስመሰል የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመገንባት ይነሣል። በመቀጠልም ሊታደሱ የሚገቧቸውን ስህተቶች ወደ ማጥናት ይሸጋገራል። ከዚያም ይህን ስህተት ወደፈጸሙት ሰዎች ያልፋል። ይህን ካደረገ በኋላ እነርሱን ለማደስ ወይም ለማረም ከሚል ፍላጎት በመነሣት በእነርሱ ላይ ጭካኔ ሊያሳይ ይጀምራል። እዚህ ደረጃ ላይ ሲደርስ ሕሊናው እነርሱን በመርገም፣ በመቆጣት፣ በመጥላትና ከእነርሱ በመራቅ የተሞላ ይሆናል። አሳብ ራሱን የሚገልጠው እዚህ ደረጃ ላይ ሲደርስ ነው።

አሳብ በተለየ መንገድ ሊጀምር ይችላል። ለምሳሌ ለወደቁት ርኅራኄ በማሳየትና እነርሱን ለማዳን በሚደረግ ጥረት ውስጥ አሳብ ሊገለጥ ይችላል። እዚህ ላይ አንድ ሰው ውድቀትን፣ ቆይታውን፣ ምክንያቶቹንና ታሪኮቹን ወደኋላ መለስ ብሎ ሊያጤን ይጀምራል። በዚህ ጊዜ ሰውየው በዚህ ሁሉ በመመሰጥ ሌላው ሰውየው በወደቀበት ተመሳሳይ አሳብ ውስጥ እርሱም ይወድቃል። ከዚህ በመነሣት ማንኛውም ሰው ሌሎችን ለማዳን ወይም በተሃድሶ ለመለወጥ ብቃት ይኖረዋል ብለን አንናገርም።

አንድ የኃጢአት አሳብ በኃጢአትነቱ ላይጀምር ይችላል። ሊጀምር በድካም ሊጀምር ይችላል። እንዲህ ያለውን አሳብ በቀላሉ እንደምታሸንፈው ትገምታለህ። አብዝተህ በውስጥህ የምትጠብቀውና የምትሟገተው ከሆነ ግን

ይበልጥ እየጠበቀ ስለሚሄድ ተጽዕኖውን ያሳድርብሃል። ይህን የሚያደርገውም በውስጥህ ባለው የተቀደሰ ቦታ ላይ እጁን እንዲጭን አንተ ኃይሉን ስለ ሰጠኸው ነው።

አሳብን በውስጥህ ጠበቅኸው ማለት ትፈልገዋለህ ማለት ነው። ትፈልገዋለህ ማለት ደግሞ ከውስጥህ ልታጠፋው አልቻልህም ማለት ነው። አሳብን ማቆየት በሰሜቶችህ ላይ ተጽዕኖውን በኃይል ያሳድራል። በዚህ ጊዜ ስለምትደክም በመጀመሪያ በአሳብ ፊት ለመቆም ያስቻለህን ኃይልህን አሁን ታጣዋለህ። አሳብም በዚህ ሰዓት የሚኖረው አቅም በመጀመሪያ ከነበረው ድካም የሚልቅ ይሆናል። አሁን ውጊያው የተመጣጠነ ስለማይሆን በዚህ ውጊያ ለማሸነፍ ታላቅ ብርታትና ጥረት ያስፈልጋል።

አሳብ በእናታችን በሔዋን ውስጥ ሲጀምር ተራ ጥያቄ ስለ ነበር ከእርስዋ ይልቅ ደካማ ነበር። በዚህ ጊዜ እርሷ ይህን አሳብ ልታፈርሰው ትችል ነበር። እግዚአብሔር ከፍራዋ «አትብሉ» ማለቱን ብቻ ሳይሆን «አትንኩት» ማለቱን ሔዋን ለሰይጣን ነግራዋለች። ዘፍ 3። ይሁን እንጂ ሔዋን በኃጢአት ከተሞላ አሳብ ጋር ስትደራደር ላልተቋረጡ ውትወታዎቹና ለማባበሉ ስለ ተጋለጠች ልትደክም ጀመረች። በውስጧ የነበረው አሳብ ወደ ጥርጥር በመጨረሻም ወደ ምኞት ስለ ተሸመጠ እጇን ዘርግታ ፍሬውን በመቁረጥ በላች። ስለሆነም እርሷ ወድቃ ሌሎች ብዙዎችን ጣለች።

ቃየን የገጠመውም ከዚህ ጋር ተመሳሳይ ነው። እግዚአብሔር እምላክ ለቃየን ኃጢአት በደጁ ስለምታደባ መልካም በመሥራት ሊያሸንፋት እንደሚችል ነግሮት ነበር። ዘፍ 4:7። ይሁን እንጂ አሳብ ተጽዕኖ አሳድሮ ወደ ልቡ ዘልቆ ሰሰገባና ስለ ሞገተው በመጨረሻ እጁን ይዞ በመምራት ከወሰደው በኋላ ወንድሙን እንዲገድል አበቃው። ኃጢአት ከደካማነት ተነሥቶ በአንተ ላይ የበላይ የሚሆንበት ሌላው ምክንያት የሚከተለው ነው።

የኃጢአትን አሳብ ከአንተ ለማስወገድ ቸልተኛ ከሆንህ እግዚአብሔርን የሚቃወም አሳብ በውስጥህ ጠብቀህ በማቆየትህ እርሱን ትክደዋለህ። የኃይልህ መገኛ የሆነው ጸጋ እግዚአብሔር ከአንተ የመራቁ ነገር የዚህ ውጤት ይሆናል። ከዚህ በኋላ የመውደቅህ ነገር ቀላል ነው። በውስጥህ የጠበቅኸው አሳብ ኩራት ወይም በራስ መታመን ከሆነ አሁንም የእግዚአብሔር ጸጋ ከአንተ ይርቃል። እንዲህ ያለው አካሄድ አንተ ከአሳብህ እንደምትበልጥና በፈለግኸው ጊዜ ሁሉ ከአንተ ልታጠፋው እንደምትችል አድርጎ ያሳምንሃል።

ስለሆነም ጸጋ እግዚአብሔር ከአንተ መራቁ ድካምህን ስለሚያሳውቅህ ወደፊት ከማንኛውም ዓይነት የኃጢአት አሳብ እንድትርቅ ያደርግሃል። በመሆኑም አሳብን ድል የምትነሣው በአስመሳይ ኃይል ወይም ለማጥፋት በሚደረግ የውሸት ትሑታ ሳይሆን በትሕትና ነው።

በመጨረሻም ወደ ሕሊናህ የገባው ደካማ አሳብ የሚያሸንፍህ ብቻህን ሆነህ ስለምትዋጋው ነው። እግዚአብሔር ከዚህ ውጊያ እንዲያድንህ በጸሎት

አትጠይቀውም። ከላይ ኃይል ለማገኘት ስትፈልግ ራስህን በትእምርተ መስቀል ማማተብን ስለምትዘነጋ ነው።

የኃጢአት አሳብ መገኛዎች።

1- አንድ አሳብ ከቀደመ አሳብ ሊመጣ ይችላል።

አሳቦች ራሳቸውን የሚመስሉ ሌሎች አሳቦችን ያስገኛሉ እንጂ መካን አይደሉም። ምናልባት ከጥቂት ቀናት በፊት የተጀመረ አሳብ ዛሬ ሊጠናቀቅ ይፈልግ ይሆናል። ወይም ደግሞ ተጀምሮ ያልተጠናቀቀ ትረካ ይጠናቀቅ ዘንድ ዝርዝር መግለጫዎች እንዲሰጡበት ከመጓጓት የሚመጣ ፍላጎት ይሆናል። አንተ ግን እነዚህን ከመሰሉ ጉዳዮች ራቅ!

2- የኃጢአት አሳብ ከሆነ አንድ ልምድ ሊመጣ ይችላል።

3- ንቁ ባልሆነው ሕሊናህ ውስጥ የሠፈሩት ጥቂት ታሪኮች፣ ስሜቶችና ፍላጎቶች ንቁ ባልሆነው ሕሊናህ ውስጥ እየተከሰቱም ሊሞግቱህ ይችላሉ።

ስለዚህ ንቁ ያልሆነው ሕሊናህን ንጹሕ አድርገህ ለመጠበቅ ተጠንቀቅ! ከዚህ በተጨማሪ የሕሊናህን ንጽሕና የሚያውኩ ነገሮችን በውስጡ አታከማች! የቆዩ ኃጢአቶችና ጥቃቶች በውስጡ ካሉም አትጠቀምባቸው። ይህን የምታደርግ ከሆነ በጊዜ ርዝመት ይወገዳሉ። አንተ ከረሳሃቸውም አዲስና ንጹሕ አሳቦች በእነርሱ ቦታ ላይ ይተካሉ።

4- ንቁ ያልሆነው ሕሊና ከተለያዩ ምንጮች ማለትም ከማንበብ፣ ከመስማት፣ ከመመልከትና ከፍላጎቶች አሳብ ሊያከማች ይችላል። ስለዚህ ስታነብ፣ ስታዳምጥ፣ ስትመለከትና ስታስብ ልብህን በንጽህና ለመጠበቅ ተጠንቀቅ! ልክ ቅዱስ ይስሐቅ እንደተናገረው ፍላጎቶችህና ስሜቶችህም ንጹህ ይሁኑ!

5- ስሜቶች የአሳብ መግቢያዎች ናቸው። «ምድርን ሁሉ ዞርሁአት በአርስዋም ተመላለስሁ . . .» (ኢዮ 1:7) የሚሉትን ስሜቶች ልትጠነቀቃቸው ይገባሃል። እነዚህ አሳቦች በየስፍራው እየተዘዋወሩ የተለያዩ አሳቦችን ከሚታዩ ክፉ እይታዎች፣ ከሚሰሙ ክፉ ነገሮችና ከማናቸውም ከሚሸተቱ ወይም ከሚዳሰሱ ነገሮች ወደ ሕሊና ይዘው ይመጣሉ።

ንጹሕ የሆኑ ስሜቶች የሚያፈልቁት ንጹሕ አሳቦችን ሲሆን የጎደፉ ስሜቶች የሚያፈልቁትም የጎደፉ አሳቦችን ነው። የተጣደፉ ስሜቶች መጨረሻም ከዚሁ ጋር ተመሳሳይ ነው። ስሜትን መቆጣጠር አሳብን ለመቆጣጠር እንደሚረዳ ምንም ጥርጥር የለውም። የሕሊና ንጽሕናን የሚያገኝ ሰው ስሜቶቹን ሊጠብቅና መንፈሳዊ ጥንቃቄ ለማድረግ ራሱ ሊያስለምድ ይገባዋል።

6- የኃጢአት አሳብ ከዲያብሎስ ወይም ከሰዎች ሊመጣ ይችላል። በምድር ላይ ታላቅ ጠቢብ የነበረው የዳዊት ልጅ ሰሎሞን ከጊዜ በኋላ በቁባቶቹ አሳብ ተጽዕኖ ደርሶበት ነበር።

ብዙ ባሎች በእናቶቻቸውና በእህቶቻቸው አማካይነት ሚስቶቻቸውን አስመልክተው በጆሮዎቻቸው ውስጥ በሚንቆረቆሩላቸው አሳቦች ትዳራቸው ፈርሷል። እንዲህ ዓይነቱ ሰው ከትዳር ጓደኛው ጋር በእጮኝነት ሕይወት ውስጥ ወይም በመጀመሪያዎቹ የጋብቻ ወራቶች ውስጥ ሲኖሩ ፈጽሞ ያልነበሩ አዳዲስ አሳቦች ወደ ሕሊናው ሲገቡ ተጽዕኖ ያሳድሩበታል። ብዙ ሚስቶችም ቤተሰቦቻቸው ከሚሰጧቸው ምክሮች የተነሣ ይወድቃሉ።

እንግዳ አሳቦች ወደ ሰው የሚመጡት ከውጪ ቢሆንም ተፈጥሮውንና ጠባዩን ሊቀይሩ ይችላሉ። ስለዚህ በየጊዜው ጠባይህን መርምር። እንግዳ የሆኑ አሳቦችን አመለካከት ሳትመረምር በመከተል ከማንኛውም ሰው ግፊት ወይም ተጽዕኖ በታች አትሁን። እንዲህ ዓይነቱ ጉዳይ በእንዳንድ መንፈሳዊ መሪዎች ወይም አስተማሪዎች ላይ ሊገሰጥ ይችላል። የእነዚህ ሰዎች አፍቃሪዎች ወይም ደቀ መዛሙርት ምንም እንኳ አመለካከቶቻቸው የተሳሳቱ ወይም በኃጢአት የተሞሉ ቢሆኑም የእነርሱን ቃላት እንደ ካርቦን ኮፒ በመድገም በእነርሱ አስተሳሰብ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ናቸው።

7- አስተሳሰቦች ከዲያብሎስ ወደ አንድ ሰው ሕሊና በአሳብ መልክ ተወርውረው ሊመጡ ይችላሉ። ስለዚህ ሰው አንድ አሳብ ከእግዚአብሔር ወይም ከዲያብሎስ መምጣቱን መለየት አለበት። ሰውየው የመለየት ስጦታው ከሌለው ይህ ስጦታ ካላቸው ሰዎች ምክር መጠየቅ አለበት። ዲያብሎስ ሰዎች አሳቦቹን ይቀበሉት ዘንድ አያስገድዳቸውም። እርሱ አሳቦቹን የሚያቀርበው በማባበል ነው። ይህን ደግሞ በቀደሙ አባቶቻችን ላይ ፈጽሞታል።

ይህን አስመልክቶ ሐዋርያው «. . . በእምነት ጸንታችሁ ተቃወሙት።» (1ኛ ጴጥ 5:9) ብሎ እንደተናገረ መንፈሳዊ ሰው የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚቃወመውን ማንኛውንም ዓይነት አሳብ መቃወም አለበት።

ውጊያና ውድቀት።

ወደ ሰው ሕሊና የሚመጣ ማንኛውም ዓይነት የኃጢአት አሳብ ኃጢአት አይደለም። ይህ አሳብ ውጊያ ሊሆንም ይችላል። በውጊያና በውድቀት መካከል ደግሞ ልዩነት አለ።

በመንፈሳዊ ውጊያ ውስጥ ለረዥም ጊዜ በሕሊና ላይ ከባድ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ የኃጢአት አሳቦች ሊኖሩ ይችላሉ። አንድ ሰው እነዚህን አሳቦች አልቀበላቸውም ብሎ ባለ ኃይሉ ቢቃወማቸውም በድጋሚ እንዲቀበላቸው ይጫኑታል። በአሳብ መውደቅ ማለት ሰው አሳብን ከተቀበለ በኋላ አይቃወመውም፣ ቢቃወመውም መሸነፍንና ደስታን በሚገልጥ ድካም ውስጥ በመሆን ነው ማለት ነው።

የኃጢአትን አሳብ መቀበል እግዚአብሔርን እንደ መካድ ይቆጠራል። ምክንያቱም የልብን መዝጊያዎች ለእግዚአብሔር ጠላቶች መክፈትና በእርሱ ቦታ ላይ እነርሱን እንደመተካት ስለሚቆጠር ነው። አንዲህ ባለው ሁኔታ ሰው ቤተ

መቅደስ የተባለ ሰውነቱን በማርከስ ይህንኑ የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ ያረክሳል። 1ኛ ቆሮ 3፡16። «ብርሃንም ከጨለማ ጋር ምን ኅብረት አለው?» (1ኛ ቆሮ 6፡14) የሚል ቃል ስለ ተጻፈም የእግዚአብሔር መንፈስ ከልቡ ይወጣል።

በአሳብ መውደቅ ውስጥ ሰው አሳብን ይደግፈዋል፣ ያሳድገዋል፣ ያበረታዋል፣ ይጠብቀዋል ሌላም አሳብ ይጨምርለታል። ሰው ከአሳብ ጋር ሲያብር ከእርሱ ጋር አንድ መንፈስ ይሆናል። በዚህ ጊዜ እንደ ውጊያ በሚጀምረው አሳብና ከሚወድቀው ከዚህ ሰው በሚወጣው አሳብ መካከል ያለውን ልዩነት መለየት ያቅተዋል። ከገዛ ልቡና ሕሊናው የሚወጣውን አሳብ መለየት ያዳግተዋል።

ውድቀትን የሚያስከትለው አሳብ የምኞት ወይም የፍላጎት ውጤት ነው። ምኞትና አሳብ ደግሞ እንደ ምክንያትና እንደ ውጤት እርስ በእርሳቸው ይደጋገፋሉ። የኃጢአት አሳብ በምኞት ይገለጣል። ምኞት ደግሞ ወደ ኃጢአት አሳብ ይመራል። አንዱ ለሌላው ምክንያት ወይም ውጤት ነው። ሁለቱም በአንድ መስመር ላይ እርስ በእርሳቸው ይረጭዳሉ። በዚህ አካሄድ በውጪ ያለ አሳብ በውስጥ ካለ አሳብ ጋር ይተባበራል።

ወደ ውድቀት የሚመሩ ነገሮች።

በአሳብ ምክንያት ሌሎች ወደ ውድቀት የሚመሩ ነገሮች አሉ። እነርሱም፦ መዝናናት፣ ዕረፍት፣ ድካም፣ መሸነፍ፣ ፍላጎትና ወግ ማውራት ናቸው።

1- አንድ ሰው በኃጢአት አሳብ እየተወጋ በዕረፍትና በመዝናናት ውስጥ ከቆየ የአሳቡ ኃይል እየበረታ ስለሚሄድ በቀላሉ ሊጥለው ይችላል። ዕረፍትን አስመልክቶ አሳብ ይህን ሰው የሚያገኘው ያለ ምንም መቋቋም ወይም መከላከያ ብቻውን ነው። እዚህ ላይ የሚጠቀስ «የሰነፍ ሰው አእምሮ የሰይጣን ቤተ መከራ ነው!» የሚል አባባል አለ። መጽሐፍ ቅዱስም ዲያብሎስ ወደዚህ ቤት እንደሚመጣ ይናገራል። «. . . ሲመጣም ተጠርጉም አጊጦም ያገኘዋል። ከዚያ ወዲያ ይሄድና ከእርሱ የከፉትን ሌሎችን ሰባት አጋንንት ከእርሱ ጋር ይይዛል፤ ገብተውም በዚያ ይኖራሉ . . .» ሉቃ 11፡24-25።

ስለዚህ በዕረፍት ላይ ስትሆን ወደ አንተ ከሚመጡ አሳቦች ራስህን ጠብቅ። ሕሊናህን ባዶ አለማስቀረት ግን የሚሻል ነገር ነው። የሕሊና የተፈጥሮ ጠባይ ያለ ማቋረጥ መሥራት ነው። በማንኛውም ጊዜ በሚጠቅሙ ወይም ምንም ፋይዳ በሌላቸው ነገሮች ይወጠራል። ያም ሆነ ይህ መሥራቱን አያቆምም።

2- በመዝናናት ጊዜ ሕሊና ስለ ማንኛውም ነገር ማለትም ስለ ተለያዩ ወጎች፣ ወሬዎችና አሳቦች ሊያስብ ይችላል። በዚህ ጊዜ ዲያብሎስ አጋጣሚውን በመጠቀም ወደ ሰውየው ሕሊና የኃጢአትን አሳብ ወይም ወደ ኃጢአት የሚያመራ አሳብን ያስገባል። ይህን የሚያደርገውም ምንም ሳይታወቅ ነው። እዚህ ላይ ሰውየው ይህ አሳብ በሕሊናው ውስጥ ከመደላደሉ በፊት ፈጥኖ በመንቃት ሊያስወግደው ይገባዋል። ስትዝናና ራስህን ወደ ኃጢአት በማይመሩና

በለከኑ ጉዳዮች ውስጥ ማላለፍ ለአንተ ይበጅሃል። በእርግጥም መዝናናት ማለት ነርቭን ማፍታታት ማለት ነው እንጂ ራስን በአሳብ ባሕር ውስጥ መወርወር ማለት አይደለም።

3- መንፈሳዊ ድካም በአሳብ ወደሚመጣ ውድቀት ይመራል። በዚህ ጉዳይ ዙሪያ አንድ ሰው ሊቃወም ስለማይችል ለአሳብ ይሸነፋል።

ስለዚህ መንፈሳዊ የሆነ አንድ ሰው በደከመ ጊዜ ይበልጥ ሊጠነቀቅና ይበልጥ ሊነቃ ይገባዋል። ራሱን በሚገባ በትጋት ሊጠብቅ በዚያው ተመሳሳይ ጊዜ ደግሞ ራሱን ሊያበረቱና ከድካሙ ሊያላቅቁት የሚችሉ ማናቸውም ዓይነት መንፈሳዊ ምግቦች ሊወሰድ ያስፈልገዋል። የድካምን ሁኔታዎች ሙሉ ለሙሉ ተቃወማቸው። በዚህ ጊዜም ከጥቃት ምክንያቶችና አሳቦች ሽሽ!

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ነገር ግን ሸሽታችሁ በክረምት ወይም በሰንበት እንዳይሆን ጸልዩ . . .» (ማቴ 24:20) በማለት የተናገረው ይህን ለመሰለው ሽሽት ነው። «በክረምት» ተብሎ የተጠቀሰው ቃል ምሳሌ የሚያመለክተን መነሣሣት የሌለበትን መንፈሳዊ ቅዝቃዜ ሲሆን «በሰንበት» የሚለው ቃል ደግሞ ዕረፍትንና ራስን ማዝናናትን ለማመልከት የተጠቀሰው ነው። ሁለቱም ሁኔታዎች አደገኞች ናቸው።

4- ምንም ቢደክምህ እንኳ እጅ አትስጥ። ነጻ የሚያወጣንና ስለ አንተ ዲያብሎስን የሚገሥጸልህን ኃይል ከላይ እስክትቀበል ድረስ ባለጋራህን በጽናት ተዋጋው። ታላቁን ካህን ኢያሱን ሰይጣን በእግዚአብሔር ፊት በከሰሰው ጊዜ እግዚአብሔር ስለ እርሱ የተናገረው እንዲህ በማለት ነበር፦ «. . . ሰይጣን ሆይ፣ እግዚአብሔር ይገሥጽህ . . . እግዚአብሔር ይገሥጽህ፤ በውኑ ይህ ከእሳት የተነጠቀ ትንታግ አይደለምን?» ዘካ 3:2።

ድካም ሰው ዲያብሎስን ለመቃወም እርዳታ የሚጠይቅበት ምክንያት ሆኖ ይቀርባል እንጂ ድካም የውድቀት ምክንያት ሆኖ አይቀርብም። በሚቀጥለው ርዕስ ሥር አሳብን ስለ መቃወም እንነጋገራለን።

5- የኃጢአት ወጎችን የማውራት ፍቅር አይኑርህ። እንዲህ ያለውን ነገር የምትወድ ከሆንህ መንፈሳዊነትህን የሚጎዳና በኃጢአት የተሞሉ ፍላጎቶችህን የሚያረኩ ወጎችን በመፍጠር የምትደሰት ሰው ትሆናለህ።

በዚህ ጊዜ ኃጢአቱ ውስጣዊ ወይም ከውስጥ የሚወጣ ወይም ከተሰጥኦ የሚመጣ ነው። ወጎችን መፍጠር የሚወዱ ሰዎች የወጎቹን መግቢያ ራሳቸው ይሰጣሉ ወይም ዲያብሎስ መነሻ አሳቡን ይሰጣቸውና እነርሱ መጨረሻ የሌለው ወግ አድርገው እንዲተርኩት ያደርጋቸዋል። እዚህ ላይ አሳቦች የኃጢአት ፍላጎቶችን የሚያረኩ ተግባራት ይሆናሉ። ለዚህ ምሳሌ የሚሆኑን አሳቦች የብቀላ፣ የዝሙት ወይም የቁም ቅዠት አሳቦች ናቸው።

የአሳብ የውጊያ ዓይነቶች፡፡

- ሦስት ዓይነት ሰዎች፡፡

በአሳብ የሚጨነቁ ሰዎች ሦስት ዓይነት ናቸው፡፡ እነርሱም፡-

1- አሳብን የሚፈልጉ ሰዎች፡፡

2- ከአሳብ ጋር ተደራድረው አሳብን በውስጣቸው የሚያቆዩ ሰዎች፡፡

3- የበለጸገ አይታ ኖሯቸው አሳቦችንና ወጎችን የሚፈጥሩ ሰዎች ናቸው፡፡

ሦስቱም ዓይነት ሰዎች ሕሊናዎቻቸው በአንድ በሆነ ኃጢአት ዙሪያ ስለሚያጠነጥን በአሳብ በጣም ይጨነቃሉ፡፡ ይህ የሚሆንበት ምክንያትም እነርሱ አሳብን ያለ ምንም ተቃውሞ እንኳን ደህና መጣህ ብለው በውስጣቸው ስለሚቀበሉት ነው፡፡

አሳብን የሚፈልጉ ሰዎች፡፡

እነዚህ ሰዎች አሳብ ወደ እነርሱ እንዲመጣ አይጠብቁም በአሳብም አይጨነቁም . . . እነርሱ አሳብን ያስጨንቁታል እንጂ፡፡ እነርሱ የአሳብን ምንጮች ይፈልጋሉ፡፡ የአሳብን ምክንያቶችም ይፈልጋሉ፡፡ እነርሱ ሕሊናዎቻቸውን የሚመግቡ ምክንያቶችን ለማግኘት በሚል ሰበብ ስሜቶቻቸውን በሁሉም አቅጣጫ ይልካሉ፡፡ በዚህ ይደሰታሉ ይህን ማድረጋቸውንም ይናፍቁታል፡፡

እንደነዚህ ዓይነቶቹ ሰዎች የሰዎችን ወሬና ምሥጢር ለማግኘት ይጓጓሉ፡፡ ስለ እነዚህ ጉዳዮች በማውራት ውስጥ ደስታን ከማግኘታቸውም በላይ በሚሰሟቸው ጉዳዮች ላይ የራሳቸውን አስተያየትና ድምዳሜ ጨምረው ይሰጣሉ፡፡ ይህን በማድረጋቸውም መንፈሳዊነታቸውን የሚጎዱ አሳቦችን በሕሊናቸው መጋዘን ውስጥ ያከማቻሉ፡፡

እነዚህ ሰዎች የሚወድቁት በሁለት ዓይነት ኃጢአቶች ላይ ሲሆን እነርሱም የአንደበትና የሕሊና ኃጢአቶች ናቸው፡፡ አንዱ ሌላውን ሲደግፈው ሌላው ደግሞ ለአንዱን ምክንያት ይሆናል፡፡ ከእነዚህ ሰዎች አንዱ ወዳጁን ወይም ባልንጀራውን ሲያገኘው «ምን አዲስ ዜና አለህ? በአገሌና በአገሉ ላይ ምን ደረሰ? እገሌስ ምን አደረገ? አንተ የሰማኸውና የተመለከትኸው ምንድር ነው? ለዚህ ሁሉ አንተ ምን ትላለህ? ከዚህ ሌላ ምን የምታውቀው ነገር አለህ?» በማለት ይጠይቀዋል፡፡

አንዲህ ያለው ሰው በላሚቱ ውስጥ ያለውን ወተት ምንም ሳያስቀር እንደሚያልብ አንድ ገበሬ እርሱም ባልንጀራው የሚያውቀውን ነገር ምንም ሳያስቀር አንድ በአንድ እንዲነግረው የሚፈልግ ነው፡፡ እንዲህ በማድረጉም ራሱን

ከመጉዳቱም በላይ የሌሎችን ምሥጢራት በማውጣት እነርሱንም ይጎዳል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ሰው የሰዎችን ወሬ ማዳመጥ ይወዳል፡፡ እግረ መንገዱንም ከሚያገኛቸው ሰዎች ሁሉ የሆነ መረጃ ለማግኘት ይሞክራል፡፡ ከሌሎች ጋር ሰመመገብ በአንድ ማዕድ ላይ ከተቀመጠ ሌላው ሰው ምን እንደሚበላና እንዴት እንደሚበላ ለማወቅ ዐይኖቹን ያቅበዘብዛል፡፡ የሚወደውንና የማይወደውንም ይለያል፡፡ የግል ጉዳዮችን ሳይቀር እያንዳንዱን ሌላ ጉዳይ በራሱ መንገድ ይወስዳል፡፡

ይህ ሰው የሆነ አንድ መጥፎ ነገር ሲፈጸም ፈጥኖ ለመስማት የሚያሳየው መጣደፍና ከዚህ በተቃራኒው አንድ የሆነ በጎ ነገር ሲፈጸም ለመስማት ቸልተኛ መሆኑ እጅግ አስገራሚ ጠባዩ ነው፡፡ ወሬዎችን፣ ምሥጢራትንና አሳቦችን ለመሰብሰብ ሕሊናው ዕረፍት የለውም፡፡ ስለማይደክመውም «. . . በምድር ላይ ዞርሁ በእርስዋም ተመላለስሁ . . .» (ኢዮ 2:2) በማለት ይመልሳል፡፡

ይህን ሰው «ይህ ለአንተ ምን ይጠቅምሃል? ለአንተ ይህን ሁሉ ማወቅ ምን የሚያተርፍልህ ነገር አለ?» ብላችሁ ብትጠይቁት ምንም ዓይነት መልስ አታገኙም፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ነገር ወደ ልማድ የተለወጠና ለአንዳንዶች የተፈጥሮአቸው አንድ ክፍል የሆነ በሽታ ነው፡፡ እንዲህ ያለውን ሰው አሳቦቹን ምን እንደሚያመጣቸው ልትጠይቁት ትችላላችሁ? ይህ ግን ለእርሱ ጠባዩ ነው፡፡

ብዙዎች ራሳቸውንም ሆነ ሌሎችን የሚጎዱት በዚህ ጉጉታቸውና የሌሎችን ምሥጢር ለመግለጥ በሚያደርጉት ሙከራ ነው፡፡ ይህና ሌሎች ሙከራዎች ግን ትክክለኛ ሙከራዎች አይደሉም፡፡ ምናልባት ግን አንተ «አሳቦች ከእኔ ውስጥ ሳይሆን ከሌሎች ዘንድ የሚመጡብኝ ከሆነና እኔ ሰለባ ከሆንሁ ግድረግ የምችለው ምንድር ነው?» ብለህ ልትጠይቅ ትችል ይሆናል፡፡ የዚህ መልሱ የኃጢአትን አሳብ ልትሰማውም ሆነ ልታስበው፣ ልታነበውም ሆነ እርሱን ለመመልከተህ ከሌላ ሰው ጋር ልታወራው፣ በአጠቃላይ ከእርሱ ጋር ምንም ዓይነት ድርድር ልታደርግ አይገባህም የሚል ነው፡፡

ከአሳብ ጋር አትደራደር፡፡

ብንም ዓይነት አሳብ ከአንተ ጋር እና በአንተ ውስጥ አይኑር! ይልቁኑም ፈጥነህ ከአንተ ዘንድ አጥፋው፡፡ አሳቦችን እንኳንስ በልብህ በጆሮዎችህ ውስጥ ልታሳድራቸው አይገባህም፡፡ በሚቻልህ አቅም ሁሉ አሳብን ከሚያመጡብህ ጉዳዮች ራቅ! ከቁጥጥር በላይ በሆኑ ምክንያቶች እንድትሰማቸው ከተገደድህ አታዳምጣቸው፡፡ እንደነዚህ ያሉ ንግግሮች ሲደረጉ ራስህን በሌላ ነገር ጥመድ! ጥቃት የሚያደርሱ ቃላቶች ሲሰነዝሩ ብትሰማም እንኳ ከእነርሱ ጋር አትሟገት፡፡

እንድትሰማው የተገደድኸው የኃጢአት ንግግር ጉቁ በሆነው አዕምሮህ ውስጥ ተተክሎ ሲቀር ስለሚችል ስለ እርሱ ድጋሚ አትስማ፡፡ በመጀመሪያው የዳዊት መዝሙር ውስጥ የክፉዎችን ምክርና የዋዘኞችን ወንበር ከአንተ እንድታስወግድ የሚያዙህን ቃላት ዘወትር አስታውሳቸው፡፡ ስለዚህ ከአሳብ ወይም ከምክንያቶቹ ጋር አትደራደር፡፡ አሳብን ሊያስከትሉ የሚችሉ ወሬዎችን

በጆሮዎችህ ውስጥ የሚያንቆረቁርልህን ሰው ወይም መልኩና ጠባዩ አሳቦችን የሚያነሣሣ ሰውን ከአጠገብህ አርቅ።

ነቢዩ ዳዊት ከአሳብ ምክንያቶች ጋር በተደራደረ ጊዜ የወደቀው በአሳብ ብቻ አልነበረም፤ከዚህ በከበዱና በከፉ ጉዳዮች እንጂ። በሶምሶንና በሌሎችም ብርቱ ሰዎች ላይ ይኸው ተመሳሳይ ችግር ደርሷል። ንጉሥ አክአብ የኢይዝራኤላዊውን የናቡቴን የወይን ቦታ ለመውሰድ ታውኳል። አሳቡ እያደገ ሲሄድ የሌሎችን ድርሻ የመካፈል ምኞቱ ከፍ እያለ መጣ። በዚህ በሚነድ አሳት ላይ ሚስቱ ኤልዛቤል ነዳጅ ስትከልስበት ንጉሥ አክአብ ከተራ አሳብ ወደ ግፍ፣ ዝርፊያና ግድያ ተሸጋገረ።

ስለዚህ አሳቦችን ለማጥፋት ቸልተኛ ከሆንህ ማንኛውም አሳብ መካን ስላልሆነ ሌሎች አሳቦችን ይወልድልሃል። አሳብ ራሱን የሚመስል አሳብ ወይም ሌላ ዓይነት አሳብ ማፍለቅ ይችላል። ከዚህ በተጨማሪ አሳብ ጽኑ ፍላጎትን ወይም ምኞትን ወይም የተሰያዩ መጥፎ ስሜቶችን ወይም በቀላሉ ሊጠፉ የማይችሉ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ኃጢአቶችን ሊያፈልቅም ይችላል። በዚህ መንገድ አሳብ የአንድ ቤተሰብ ጎሳቅ አባት ይሆናል።

ስለሆነም አሳብ በውስጥህ ኣድጎ መንሰራፋት ከመጀመሩና ፈቃድህን ከመቆጣጠሩ በፊት አስወግደው። አሳብ አድጎ ከመጠንከሩ በፊት በጅምሩ ማጥፋት ቀላል ነው። የኃጢአት አሳብ ኦስቀድሞ የሚፈትንህ ልብህ ምን ያህል ንጹሕ እንደሆነና ውስጥህ ከእርሱ ጋር ለመደራደር ምን ያህል እንደተዘጋጀ በማወቅ ነው። ከእርሱ ጋር ለመደራደር የማትፈልግ መሆንህን ሲያውቅ አንተ አሳቦችን የምትወድ ቀላል ሰው አለመሆንህን ስለሚረዳ ትቶህ ይሄዳል። ከአንተ ጋር ለመቆየት ቢፈልግም እንኳ በውስጥህ ንጽሕና ደኅማ ይሆናል።

መዝጊያዎችህን ዝጋ።

ለአሳብ በርህን እንዳትከፈት ተጠንቀቅ። ለአንድ አሳብ በርህን ከፈትህለት ማለት እጅህን ዘርግተህ ልትቀበለው፣ ልትታዘዘውና ጌታህን ለመካድ ዝግጁ ሆነሃል ማለት ነው። በሰሎሞን መዝሙር ውስጥ ስለተጠቀሰችው ድንግል የተጻፈውን ቃል ልታስታወስ ይገባሃል። «እኅቴ ሙሽራ የተቆለፈ ገነት፣ የተዘጋ ምንጭ፣ የታተመ ፈሳሽ ናት።» መኃ 4:12። እርስዋ የሕሊና ደጇን ለሚያንኳኳ ማንኛውም ዓይነት ክፉ አሳብ የተዘጋች ናት። እርስዋ የልቧን ደጆች ለሚያንኳኳ ለማንኛውም ዓይነት የምኞት አሳብ የተቆለፈች ናት። እርሷ ለማንም አትከፈትም . . . እርሷ ደጀቿን የምትከፍተው ለነጹና ለተቀደሱ አሳቦች ብቻ ነው።

የኃጢአትን አሳብ በተመለከተ ቅዱሳን መላእክት ለእርሷ የሚዘምሩላትን ዝማሬ ታዳምጣለች፦ «ኢየሩሳሌም ሆይ እግዚአብሔርን አመስግኚ፤ጽዮንም ሆይ ለአምላክሽ እልል በይ፤የደጆችሽን መወርወሪያ አጽንቷልና፤ልጆችሽን በአንቺ ውስጥ ባርኮአልና።» መዝ 146:12-13። የተዘጉት ደጃፎች ቅድስና ያላት ነፍስ ደጃፎች ሲሆኑ እነርሱን ለሚያንኳኩ የጠላት አሳቦች ሁሉ አይከፈቱም። እርሷ ለእግዚአብሔር የታመነች ነፍስ ስለ ሆነች እርሱ በውስጧ ያሉ ልጆቿን

ባርኮላታል። ለእርሷ የተወለዱት እነዚህ ልጆች የተገኙት ከመንፈስ ቅዱስ ይኸውም ከቅዱስ አሳብ ነው።

ደጃፎችህን በኃጢአት አሳብ ላይ ዝጋ! ምክንያቱም እስኪጠናቀቅ ድረስ ስለማይረጋጋ ነው። አሳብ መንገዱን ያስተካክል ዘንድ በምኞት የሚላክ የምኞት ታዛዥና ተራ ባሪያ ነው። አሳብ እንዲህ ሆኖ መቆየት አስቸጋሪ ስለሚሆንበት ይበልጥ አደገኛ ወደ ሆነ ደረጃ ያድጋል። በጠላት ውጊያዎች ውስጥ አሳብ አንድ ደረጃ ነው። በመሆኑም ይህ ደረጃ ምን ያህል አደገኛ እንደ ሆነ ወደማታውቀው ሌላ ደረጃ ስለሚያሸጋግርህ በጣም ጠንቃቃ ሰው መሆን አለብህ።

የአሳብ እድገት ከስሜቶች ወደ ሕሊና ከዚያም ወደ ልብ ከዚያም ወደ ፈቃድ ነው። አሳብን ለጥቂት ጊዜ በጆሮዎችህ ውስጥ ካቆየኸው ቀስ ብሎ እየዳኸ ወደ ሕሊናህ ይገባል። በዚያም ከፈጠራ ጋር ስለሚገናኝ ብዙ ልጆችን ያፈራል። ከዚህ በመቀጠልም አሳብ በውስጥህ በማደግ ወደ ልብህ፣ ወደ ስሜቶችህ፣ ወደ ፍላጎቶችህና ወደ ምኞቶችህ ይጎለምሳል። በዚህ ጊዜ ውጊያው ወደ ከፍተኛ ደረጃ ይደርሳል ማለት ነው።

በመሆኑም ከአሳብ ጋር ስትደራደር እርሱ በአንተ ላይ ኃይል ይኖረዋል። ምክንያቱም በውስጥህ ያሉትን የአንተን ምሽጎች ለብሮ ካሰፈ በኋላ ወደ ልብህ ከተማ ከሰዎቹ ጋር ስለሚገባ ነው። እንዲህ ያለው ደረጃ ለአንተ ምንኛ አደገኛ ነው! በእርግጥም እዚህ ደረጃ ላይ ስትደርስ በገዛ ልብህ ትወጋለህ ወይም ለሁለት ዓይነት ውጊያዎች ትጋለጣለህ፤ከውስጥና ከውጪ። ውስጣዊው ውጊያ ከውጪያዊው ይጠነክራል። አሳብ አብዝቶ ተስፋ የሚያደርገው ወደ ልብህ ለመድረስ ነው። በዚያ ልጆቹን በዙሪያው ሰብስቦ በአንተ ላይ ያምፃል። የእርሱ ልጆች ደግሞ የልብ ምኞቶች ናቸው።

ልብ በአሳብ እጆች ላይ ከወደቀ ፈቃድ ፈጥኖ ይማረካል። ምክንያቱም ልብ ፈቃድን አብዝቶ ስለሚጫነው ነው። ፈቃድ ብርቱ ሆኖ ሊቆይ የሚችለው ልብ ብርቱ ሲሆንና አሳብ ውጪያዊ ሲሆን ነው። ልብ ደካማ ሆነ ማለት ግን ፈቃድም እንዲሁ ደካማ ይሆናል ማለት ነው። ጸጋ የፈቃድን ኃይል ከላይ ካልጠየቀ ያለ ምንም ችግር እጅ ስለሚሰጥ በቀላሉ በሥራ በሚገለጽ ኃጢአት ላይ ይወድቃል። ስለዚህ አደገኛ ደረጃ ላይ ከመድረስህ በፊት መዝጊያዎችህን አስቀድመህ ዝጋ! ቅዱስ ዶርቴዎስ እንዲህ ብሏል፦ «አንዲት አነስተኛ ችግኝ መንቀል ቀላል ነው። ትልቅ ዛፍ እስክትሆን ድረስ ችላ ካልኻት ግን ለመነቀል አስቸጋሪ ትሆንብሃለች።» ስለሆነም አሳቦች ወደ አንተ ለመራመድ ገና የመጀመሪያው ደረጃ ላይ ሳሉ ነቅለህ በመጣል ከመዝሙረኛው ጋር «ሕፃናቶችሽን ይዞ በዓለት ላይ የሚፈጠፍጣቸው የተመሰገነ ነው።» (መዝ 136:9) በማለት ዘምር! ይህም ማለት አሳቦች ገና ትናንሽ እያሉ ወይም ከማደጋቸው በፊት በዓለት ላይ ፈጥፍጣቸው ማለት ሲሆን ዓለቱም ክርስቶስ ነው። «. . . ያም ዓለት ክርስቶስ ነበረ።» 1ኛ ቆሮ 10:4።

አሳብን የመያዝ ጉዳት፡፡

እስቀድመን እንደተናገርን አንድ ሰው ክፉ አሳብን ፈጥኖ ካላስወገደው በእርሱ ላይ ኃይል ስለሚኖረው በውስጡ ተደላድሎ ይቀመጣል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ወደ ልቡና ወደ ፈቃዱ ስለሚደርስ ነፍሱን በማወክ ሌሎች አሳቦችንና ኃጢአቶችን ያፈራል፡፡

ምንም እንኳ አንድ ሰው የሞትና ሽረት ውጊያ በማድረግ አሳብን ቢያሸንፈውም ውጊያው ለረዥም ጊዜ መራዘሙ እርግጥ ነው፡፡ የተራዘመ መንፈሳዊ ውጊያ ደግሞ ሰውን ስለሚያሰላቸውና በእርሱ ፊት ደካማ የመሆን ስሜት እንዲሰማው ስለሚያደርገው ተስፋ ወደ መቁረጥና እጁን ወደ መስጠት አፋፍ ያደርሰዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ከአሳብ ጋር ለረዥም ጊዜ መዋጋት አሳብ ንቁ ባልሆነው ሕሊናችን ውስጥ እንዲተከል ምክንያት ይሆናል፡፡ አልፎ ተርፎም ሕሊና በውስጡ ሊይዛቸው የማይፈልጋቸውን አሳቦች በማስገባት በመጨረሻ ወደ ሌላ አሳቦች፣ ምኞቶች፣ ሕልሞችና ጥርጥሮች እንዲመራ ያደርጉታል፡፡ ምንም እንኳ አንድ ሰው በመጨረሻ ድል ሲነሣ ቢችልም ውጊያው ሕሊናውን ያቆሽሽበታል፡፡

አሳብ በሰው ሕሊና ውስጥ ተጽዕኖዎችን፣ ቅራኔዎችንና ስሜቶችን ለማስገባት የሚችለው እንዲህ ባለው መንገድ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ስሜቶችን ተስፋ በማስቆረጥ በልብና በሰውነት ላይ ጠባሳ ጥሎ ያልፋል፡፡

አሳብ ሰውነትን ያጠቃል፡፡ ለምሳሌ ጠላት ዲያብሎስ በአንድ ሰውና በሌላ አንድ ሰው መካከል ተፈጥሮ የነበረ ጠብን ያስታውሳል፡፡ ዲያብሎስ ጠቡን እንዲያስታውስ ያደረገው ሰው ይህን አሳብ ወዲያውኑ ከሕሊናው ማስወገድ ሲገባው የጠቡን ዝርዝር ሁኔታዎች ማሰላሰል ይጀምራል፡፡ በዚህ ጊዜ ሰውነቱ ይግላል፣ ደሙ በሥሮቹ ውስጥ በከፍተኛ ግፊት ይመላለሳሉ፣ ዓይኖቹ ይቀላሉ፣ ገጽታውም ይቀፋል፡፡ እዚህ ደረጃ ላይ ሲደርስ ራሱን እንዴት እንደሚበቀል ማሰብ ይጀምራል፡፡

ነቢዩ ዳዊት የአሳቦችን ተጽዕኖዎች የገለጸው እንዲህ በማለት ነው፡- «አቤቱ እስከ መቼ ፈጽመህ ትረሳኛለህ? እስከ መቼስ ፊትህን ከእኔ ትሰውራለህ? እስከ መቼ በነፍሴ እመካከራለሁ? ትካዜስ እስከ መቼ ሁልጊዜ ይሆናል? እስከ መቼ ጠላቴ በላዬ ላይ ይጓደዳል? . . . ጠላቴ አሸነፍሁት እንዳይል የሚያስጨንቁኝም እኔ ብናወጥ ደስ እንዳይላቸው፤ ለሞትም እንዳልተኛ ዓይኖቼን አብራ፡፡» መዝ 12፡1-4፡፡

በዚህ መሠረት አሳብ ወዴት እንደሚመራህና ማብቂያው የቱ ዘንድ እንደሚሆን ስለማታውቅ ከአሳብ ሽሽ በውስጥህም አትያዘው፡፡ ከአሳብ የሚደረግ ሽሽት የልብን ትሕትና ይገልጻል፡፡ ትሕትና ደግሞ ሰው ዲያብሎስን የሚያሸንፍበት ታላቅ መሣሪያ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ሰው ከአሳብ ጋር ለመዋጋት በራሱ ኃይልና እውቀት የሚታመን ከሆነ ጸጋ እግዚአብሔር ለተወሰኑ ጊዜያት

በተፋፋመው ውጊያ ውስጥ ይተወውና ብጥብጡን እንዲያውቅ ዝም ብሎ ይመለከተዋል፡፡ ምናልባት በዚህ ጊዜ በድጋሚ ኃይል እንዲሰጠው ላይጠይቅ ይችላል፡፡ ከዚህ በኋላ በገዛ ራሱ ፈቃድ ከመታመን ይልቅ በእግዚአብሔር ፈቃድ፣ ኃይልና ጽናት ይታመናል፡፡

ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር ሰዎች በውጊያዎች እንዲጠቁ የሚፈቅደው ትሕትናን ገንዘብ እንዲያደርጉ ነው፡፡ ዲያብሎስን አንተ ከእርሱ ጋር መከራከርህን እንደ መጥላት ያለ ምንም የሚያበሳጨው ነገር የለም፡፡ ለውድቀት የመጀመሪያ ደረጃ የነበረው የሔዋንና የአባብ ክርክር ነው፡፡ በንግግራቸው መካከል ዲያብሎስ የሔዋንን ስሜትና ሕሊና ለመምራት ስለ ቻለ እርስዋ በእጁ ቁጥጥርና ተጽዕኖ ውስጥ ያለች አሻንጉሊት ሆናለች፡፡

ከክፉ አሳብ ጋር በምታደርገው ድርድር ድንገት በእርሱ ክልል ውስጥ ትገባለህ፡፡ በዚህ ጊዜ ቢያንስ ቢያንስ ድርድሩን ላትቃወም ትችላለህ፡፡ ብዙ የኃጢአት ግንኙነቶች በክርክርና በመቃወም ይጀመሩና እጅ በመስጠት ይጠቃለላሉ፡፡ ስለሆነም ከአሳብ ጋር መከራከርን መቃወምና በአንተ ላይ ተጽዕኖ እንዳያሳድር ማገድ በአንተ ዘንድ በመጀመሪያ ሊደረግ የሚገባው ፈጣን እርምጃ መሆን አለበት፡፡

አሳብን ልተቀበለው ብትችልም ልታስወጣው ግን አትችልም፡፡ ስለ ነም እርሱን አለመቀበልና ከእርሱ ጋር አለመደራደር ውይይት የማያስፈ ው መፍትሔ ነው፡፡ አሳብን መያዝ አሳብን የበላይ ሊያደርገው ይችላል፡፡ ለረ ጅም ጊዜ የሚቆይ ከሆነ ደግሞ ሰው የእርሱ ባሪያ ይሆናል፡፡

የአሳብ ባርነት፡፡

አሳብ ሰውን ሊቆጣጠረው የሚመራው ወደ ውድቀት ብቻ ሳይሆን ከዚያ በበለጠ ወደማያቋረጥ መማረክና ባርነት ነው፡፡ አሳብ ወደ ልብ መድረሱን ሲያውቅና ሰውየው ሊፈልገው ያለማቋረጥ ያንኳኳል፡፡ ባሪያ ባደረገው በሰውየ ሕሊና ውስጥ አሳብ ለቀናትና ለሳምንታት ሊቆይ ይችላል፡፡ በየጊዜው አዲስ የሆኑና ከእርሱ ጋር የሚቆዩ ነገሮችን በማስገባት መልካም የሆኑ አሳቦችን ይደመስሳል፡፡ በዚህ ጊዜ ሰውየው በሕሊናው ውስጥ አሳብ እንደ ያዘ ይተኛል ጠዋት ሲነቃም አሳብ እንደ ያዘ ይነቃል፡፡ ወደ ሥራው ሲያዘግምም ሆነ ሥራውን ሲሠራ አሳቡ ከእርሱ ጋር አብሮት ይቆያል፡፡

ታዲያ ሰው አሳብን እንዴት ሊያሸንፈው ይችላል?

አሳብን እንዴት ማሸነፍ ይቻላል?

የመጀመሪያው ዘዴ «ከህክምና ጥንቃቄ ይሻላል» የሚለውን አባባል ያጎላል፡፡ ሁልጊዜ የመከላከልን ቦታ አትያዝ፡፡ ምክንያቱም በመከላከል ውስጥ አንድ ጊዜ ታሸንፋለህ በሌላ ጊዜ ደግሞ ትሸነፋለህና፡፡ ስለዚህ ልብህን ከአሳብ በሚጠብቁ ቀና መንፈሳዊ ሥራዎች ውስጥህን ጤናማ አድርግ፡፡

ለራስህ ብርቱና የማያቋርጥ መንፈሳዊ መርሐ ግብር ነድፈህ አውጣ። ይህ መርሐ ግብር ጸሎትን፣ መዝሙራትን፣ መንፈሳዊ ንባባትን፣ ተመስጦዎችን፣ መንፈሳዊ ስብሰባዎችን፣ መንፈሳዊ ወዳጅነትን እንዲሁም ልብህን በንጹሕ ስሜት ሊሞሉ የሚችሉና ዘላቂነት ያላቸው መንፈሳዊ ምግቦችን ያካተተ ይሁን። በዚህ ጊዜ የኔታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቃል በአንተ ላይ ተግባራዊ ይሆናል፦ «መልካም ሰው ከልብ መልካም መዝገብ መልካሙን ያወጣል፤ክፉ ሰውም ከልብ ክፉ መዝገብ ክፉውን ያወጣል።» ሉቃ 6:45።

ከዚህ በኋላ ልብህ የአሳቦች መገኛ ምንጭ ይሆናል። አሳብህ መንፈሳዊ ከሆነ መንፈሳዊ አሳቦችን ከልብህ ታመነጫለህ። ከውጪ ክፉ አሳቦች ወደ ልብህ የሚመጡ ከሆነ ግን ልብህ አይቀበላቸውም። ለልባችን ተገቢውን እንክብካቤ ብናደርግለት መልካም ነው። ሕይወታችንን ከክፉ አሳቦች ጋር በመታገል ከማሳለፍ ይልቅ ልባችንን የመንፈሳዊ ጉዳዮች መጋዘን ብናደርገው የተሻለ ይሆናል።

ዘወትር ሕሊናህን በንጹሕና በመንፈሳዊ አሳብ ባተሌ የምታደርገው ከሆነ ክፉ አሳቦች በአንተ ውስጥ ቦታ ስለማይኖራቸው ከእነርሱ ጋር ውጊያ ማድረግ እንደማያስፈልግህ እርግጠኛ ሁን።

ክፉ አሳቦች ሰውን በአብዛኛው የሚያውኩት በሚዝልበት ጊዜ መሆኑን እዚህ ላይ እንገነዘባለን። ሕሊና ከማንኛውም መንፈሳዊ ተግባር የተራቆተ ከሆነ ዲያብሎስ ወደ አርሱ በመምጣት በውስጡ ተደላድሎ ይቀመጣል። ነገር ግን ሕሊና በጸሎት፣ በመንፈሳዊ ንባብ ወይም በመንፈሳዊ ተመስጦ ባተሌ ከሆነ አሳቦች ሊያሸንፉት አይችሉም። እዚህ ነጥብ ላይ 'በመንፈሳዊነቱ ንቁ የሆነ ሰውን አሳቦች ሊዋጉት አይችሉም?' ብላችሁ ልትጠይቁ ትችላላችሁ። ለዚህ መልሱ 'ሊዋጉት ይችላሉ፤ነገር ግን ሊያሸንፉትም ሆነ ሊያውኩት አይችሉም' የሚል ነው።

ቅዱሳን በአሳቦች ተወግተዋል። ይሁን እንጂ በእነርሱ አልታወኩም አልተሸነፉምም። ይልቁኑም ከቅዱስ ጳውሎስ ጋር ሆነው «. . . ለክርስቶስም ለመታዘዝ አእምሮን ሁሉ እንማርካለን . . .» (2ኛ ቆሮ 10:5) ይሉ ነበር።

ራስን በመንፈሳዊ ጉዳዮች ባተሌ ማድረግ በተለይም በጥልቅ ጉዳዮች ላይ በሥራ መወጠር ማንኛውንም ዓይነት አሳብ ሊያስወግድ ይችላል። እንዲሁ በግርድፉ የሆነ ንባብና ጸሎት ግን አሳብን ሊያስወግድ አይችልም። ጥልቅ በሆነ መንፈሳዊነት ውስጥ የምትኖር ከሆነ አሳቦች በጸጋ እግዚአብሔር ከአንተ ይወገዳሉ።

ጥያቄና መልስ።

ጥያቄ፦ ኃጢአቶቼን ባሰብሁ ቁጥር በእነርሱ ድጋሚ እወድቃለሁ። ታዲያ አሁንም የሚጠበቅብኝ እንደ ነቢዩ ዳዊት «ኃጢአቴም ሁልጊዜ በፊቴ ነውና።» (መዝ 50:3) ማለት ነውን?

መልስ፦ በእነዚህ ቃላት የሚያውኩህን የጥቃት ዝርዝሮች ታስታውስ ዘንድ ሆነ ተብሎ የተደረገ ነገር የለም። ስለሆነም በእነዚህ ቃላት ልታስታውስ የሚያስፈልግህ የኃጢአቶችህን ዝርዝር ሁኔታዎች ሳይሆን አጠቃላይ አሳቡን ነው። ከዚህ በተጨማሪ የምኞት ኃጢአቶች ብቻቸውን ሰውን በቀደሙ ኃጢአቶቹ እንደሚዋጉት ቅዱሳን አባቶች ተናግረዋል።

ለምሳሌ አንተ አንድ የሆነ ሥልጣን ለማግኘት ትናፍቅ ይሆናል ወይም የወደድኸውን ነገር ለማግኘት ትመኝ ይሆናል ወይም ደግሞ በሥጋ ምኞት ትወድቅ ይሆናል። በዚህ ጊዜ የእነዚህን ኃጢአቶች ዝርዝር ማስታወስህ ሊያውክህ ይችላል። ልክ እንደዚሁ በስሜት ኃጢአት ማለትም በቁጣ ወይም በቅናት ወይም ለመበቀል በመመኘት ኃጢአት ልትወድቅ ትችላለህ። የእነዚህ ኃጢአቶች ዝርዝር ማስታወስህም ሊያውክህ ይችላል።

እነዚህን ኃጢአቶች አስመልክተን ስንጸልይ ሞትን የሚያስከትልብን የኃጢአት ትዝታ ከእኛ ይራቅ! እንላለን። ስለሆነም ኃጢአቶችህን በትሕትና ልታስታውሳቸው የምትችለው ንስሓ ልትገባባቸውና ትሑት ልትሆንላቸው ነው።

ይሁን እንጂ የኃጢአት ትዝታ ሕሊናህን የሚያረክሰው ከሆነ፣ በድጋሚ ወደ ልብህ መጥፎ ምኞት የሚያስገባ ከሆነ፣ ቁጣን - ቅናትንና ለመበቀል መመኘትህን የሚያነሣሣብህ ከሆነ ወይም ደግሞ የዓለምን ፍቅር የሚያቀርብልህ ከሆነ ኃጢአትን ከማስታወስ ሽሽ! የኃጢአት ትዝታ የግብ መንገድ ነውና። ማንኛውንም መንፈሳዊ ልምምድ በብልሃት አከናውን እንጂ ቅድስናን የሚመለከት ፊደልን አትከተል።

ምዕራፍ ስምንት

ውጪያዊ ገጽታዎች

- በብሉይ ኪዳንና በአዲስ ኪዳን ተወግሏል።
- ውስጣዊ እንጂ ውጪያዊ ንጽሕና አያስፈልግም።
- ውጪውንም መርሳት የለብንም።
- ቅድስናን አስመልክተው የሚደረጉ ልምምዶች።
- ስለ እግዚአብሔር እንጂ ስለ ሰው አይደለም።

በብሉይ ኪዳንና በአዲስ ኪዳን ተወግሏል።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የውጪያዊ ገጽታን ፍቅር በማውገዝ ለግብዞቹ ለጻፎችና ለፈሪሳውያን በተግሣጽ ቃል እንዲህ ብሎአቸዋል፦ «አናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን፤በውስጡ ቅሚያና ስስት ሞልቶ ሶ፦ የጽዋውንና የወጭቱን ውጭ ስለምታጠሩ ወዮላችሁ። . . . [illegible] ጻፎችና ፈሪሳውያን በውጭ አምረው የሚታዩ በውስጥ ግን የሙታን አጥንት ርኩሰትም ሁሉ የተሞሉ በኖራ የተለሰኑ መቃብሮችን ስለምትመስሉ ወዮላችሁ።» ማቴ 23:25፤27።

በብሉይ ኪዳንም የእግዚአብሔር አመለካከት ተመሳሳይ ነበር። እግዚአብሔር አምላክ የአይሁድን የሃይማኖት መግለጫዎች አይቀበላቸውም። በመሆኑም በጉባኤ መሰብሰባቸውን፣ በዓላቶቻቸውን፣ ጾማቸውን፣ ጸሎታቸውን፣ ዕጣናቸውንና መሥዋዕታቸውን በንጹሕ ልባቸው ስለማያቀርቡት ሙሉ ለሙሉ አይቀበላቸውም ነበር።

በትንቢተ ኢሳይያስ ውስጥ እግዚአብሔር አይሁድን እንዲህ ብሏቸዋል፦ «የመሥዋዕታችሁ ብዛት ለእኔ ምን ይጠቅመኛል? . . . የሚቃጠለውን የአውራ በግ መሥዋዕትንና የፍሪዳን ስብ ጠግቤያለሁ. . . በጉባኤም መሰብሰባችሁን አልወድድም . . . ዕጣን በእኔ ዘንድ አጸያፊ ነው፤ መባዎቻችሁንና በዓላቶችችሁን ነፍሴ ጠልታለች፤ሸክም ሆነውብኛል፤ ልታገሣቸውም ደክሜያለሁ። እኛችሁንም ወደ እኔ ብትዘረጉ ዓይኔን ከእናንተ እሰውራለሁ፤ ልመናንም ብታበዙ አልሰማችሁም፤እጆቻችሁ ደም ተሞልተዋል።» ኢሳ 1:11-15።

እግዚአብሔር አምላክ ከምንም ነገር አስቀድሞ የሚመለከተው የውጪ ገጽታን ሳይሆን ልብን ነው። ይህን አስመልክቶ እንዲህ ብሎናል፦ «አጥብቀህ ልብህን ጠብቅ፤ የሕይወት መውጫ ከእርሱ ነውና።»፤«ልጄ ሆይ ልብህን ስጠኝ፤ዓይኖችህም መንገዴን ይውደዱ።» ምሳ 4:23፤23:26።

መልካም ሥራ ከልብና በፍቅር ካልሆነ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት የለውም። እግዚአብሔር የሚወደው ውጪያዊ ገጽታዎችን ሳይሆን ውስጣዊ ስብእናን ነው። እርሱ የሚወደው የሰውን በጎና ጥልቅ ስሜት እንዲሁም ፍቅርን እንጂ ምንም ፋይዳ የሌላቸውን ውጪያዊ ድርጊቶችን አይደለም።

ከንጹሕ ወይም ከትሑት ልብ የሚቀርብ ጸሎት ተቀባይነት አለው። የክፉ ሰው ጸሎት ግን በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት የለውም። በዚህ መሠረት

እግዚአብሔር የተቀበለው የቀራጩን ጸሎት ነው። የፈሪሳዊው ጸሎት በኩራት፣ በጉራና ሌሎችን በመርገም የተሞላ ስለ ነበር እግዚአብሔር አልተቀበለውም። ከዚህ በተጨማሪ እግዚአብሔር «እጆቻችሁ ደም ተሞልተዋልና።» (ኢሳ 1:15) ያላቸውን ሰዎች ጸሎት አልተቀበለም።

ይህን በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይለናል፦ «የኃጥኣን መሥዋዕት በእግዚአብሔር ዘንድ አስጸያፊ ነው።» (ምሳ 15:8)፣ «የኃጥኣን መሥዋዕት አስጸያፊ ነው፤ ይልቁንም በክፉ አሳብ ሲያቀርቡት አስጸያፊ ነው።» (ምሳ 21:27)፣ ሕግን ከመስማት ጆሮውን የሚመልስ ጸሎቱ አስጸያፊ ናት።» ምሳ 28:9። በዚህ መሠረት ትኩረታችን ሊሆን የሚገባው የማንኛውም ውጪያዊ ንጽሕና መገኛ በሆነው በውስጣዊው ንጽህና ላይ ነው።

ውስጣዊ እንጂ ውጪያዊ ንጽሕና አያስፈልግም።

አንዳንድ ጊዜ አንዳንድ ሰባኬያን፣ አለቆችና መምህራን ሁሉንም ነገር ለውጪያዊው ንጽሕና በመስጠት በዚያ ላይ ሲያተኩሩ ይስተዋላሉ። ይህን በአንዲት ልጃገረድ ላይ ምሳሌ አድርገን ብንወስድ ሰዎች ውጪያዊ ገጽታዋን በመመልከት ቀሚሷ ያምራል ወይስ አያምርም፣ ያደረገቻቸው ጌጣጌጦች ውድ ናቸው ወይስ ርካሽ በማለት ያነጻጽራሉ። በስብከታቸው ውስጥ እነዚህን በመሰሉ ተራና ኃላፊ ጉዳዮች ላይ ሲያተኩሩ ይታያሉ።

እነዚህ ሰዎች በልብ ውስጥ ያለውን ውስጣዊ መነሣሣት በመርሳት ትሕትና ወደጎደለው ሕይወት ይገባሉ። ትኩረት የሚያስፈልገው ለውስጣዊው ጉዳይ ነው። ይህም እግዚአብሔርን በመውደድ፣ ቅድስናን በመውደድና የልብ ንጽሕናን በመውደድ ላይ ሊሆን ይገባል። ልብ ንጹሕ ሲሆን ልጃገረዲቷ ውድ በሆኑ ጌጣጌጦቿ እንድታጌጥ የሚመሯትን መነሣሣቶች ያጠፋሳታል። በዚህ ጊዜ እርሷ ራሷ እነዚህን ገጽታዎቿን ሙሉ ለሙሉ ትረሳቸዋለች።

ተግሣጽ፣ ብጥብጥና ጫና ጸባይን ለመለወጥ የሚረዱ ምክንያቶች አይደሉም። የሚለውጡት ውጪያዊ ገጽታዎችን ብቻ ነው። ልብ ግን ተመሳሳይ ፍላጎቶቹንና ምኞቶቹን እንደ ያዘ ያለ ምንም ለውጥ ይቆያል። እንዲያውም በፊት ከነበሩት ጸባዮቹ ሌላ ማጉረምረም፣ የሰውን ስሜት መጫንና ጥርጥር ተጨማሪ ሆነው ይመጣሉ። ከዚህ በተቃራኒ ልብ ንጹሕ ከሆነ ማንኛውንም ዓይነት ጠቃሚ ምክር ይቀበላል፣ ያመሰግናል ከዚህም በሚበልጡ መንፈሳዊ መንገዶችም ያከናውናቸዋል።

ሌላው ምሳሌያችን ፀጉሩን የሚያሳድግና አሮጌ ልብሶችን የሚለብስ ወጣት ነው። እንዲህ ያለው ነገር ከአንድ ሃይማኖተኛ ወጣት የሚጠበቅ ምግባር አይደለም። እንዲህ ዓይነቱ ሰው ‘ወንድነት’ ማለት ምን ማለት እንደሆነና የብርቱ ስብእና መገለጫዎች ምን እንደሆኑ የማያውቅ ሰው ስለሆነ ከሰዎች ዘንድ ክብር ሊያገኝ አይችልም። ከዚህ ሁሉ በላይ የልብ ንጽሕናን እንዴት ሊያገኝ ይችላል? አይችልም። አንተ ግን እነዚህ ሁሉ ትክክል አለመሆናቸውን ሙሉ ለሙሉ ስትረዳ እነዚህን ስህተቶች ያለ ምንም ተግሣጽና ኃይል ከአንተ ዘንድ ልታስወግዳቸው ትችላለህ።

የወጪቱ ውስጥ በቆሻሻ ተሞልቶ ውጪውን ማጥራት ምንም ጥቅም የለውም። ውስጥን ማጥራት ይበልጥ ጽኑና ጥብቅ ሊሆን ያስፈልጋል። ይህ በሚሆንበት ጊዜም በውስጡና በውጪው መካከል ምንም ዓይነት ቅራኔ ሳይፈጠር ስለሚሆን ለውጡ እርግጠኛ ለውጥ ነው። በዚህ ጊዜ አንድ ሰው ከውጪያዊ ግፊት ለማምለጥ ሲል ምንም ዓይነት ጫና አይደርስበትም።

በውጪ ለሚንለጡ ስህተቶች የሚመሩትን ውስጣዊ ምክንያቶች ለማከም የሚያስችለንን መንገድ እንፈልግ። ውሸትን እንደ ምሳሌ አድርገን እንውሰድ። የሚዋሽን ሰው ስለ ውሸት በመስበክ ወይም ስለ ውሸቱ በመገሠጽ መለወጥ ይቻላል? ለእርሱም ሆነ ለሚያመጣው ለውጥ ውጤታማነት የዋሸባቸውን ምክንያቶች ፈልጎ ማወቅ ይበልጥ ጠቃሚ አይደለምን? ይህ ሰው የዋሸው ከፍርሃት ወይም ከጉራ ወይም ከስንፍና ወይም አንድ የሆነ ጥቅም ለማግኘት ከሚደረጉ ምክንያቶች ሊሆን ይችላል። እንዲህ ዓይነቱ ነገር ከቸልተኝነት ወይም ከልማድ የሚመጣ ከሆነም ያለ ምንም ምክንያት ይዋሻል። በሰዎች ላይ መቀለድ የሚያስደስተው ከሆነም ሰፈዝና ለጊልት ሲል ይዋሻል።

ስለሆነም የመዋሸትን ምክንያቶች ፈልገን በማግኘት ልናክማቸው ያስፈልጋል። መዋሸት መልካም አለመሆኑንም ለሚዋሸው ሰው ማሳመን አለብን። ከውሸት እንዲላቀቅም ተግባራዊ የሆኑ ምክንያቶችን ልንሰጠው ወይም ውሸትን የሚተኩ ትክክለኛ አማራጮችን ልናቀርብለት ይገባናል። ለምሳሌ ለተጠየቀው ጥያቄ መልስ ከመስጠት ወይም ሌላ ጥያቄ ከማቅረብ ራሱን በመቆጠብ ዝም ማለት ይችላል። ስህተትን በውሸት ከመሸፋፈን ይልቅ ለተሠራው ስህተት ይቅርታ መጠየቅ ይበልጣል። ጉራና በሌሎች ሰዎች ላይ ማፌዝ ትክክል አለመሆኑን እመን። ከዚህ በተጨማሪ እውነተኛ ሰው በመሆን ውስጥ ከሰዎች እምነትና ክብር ለማግኘትህ እርግጠኛ ሁን።

በዚህ ዓይነት መንገድ የውስጡንና የውጪውን ስህተት ማስወገድ እንችላለን። በዚህ መሠረት የውጪውን ሙሉ ለሙሉ መዘንጋት የለብንም። ግን እንዴትና ለምን?

ውጪውንም መርሳት የለብንም።

ስለ ውስጠኛው መጨነቅ አለብን ማለት ውጪያዊ ድርጊቶቻችንን መዘንጋት አለብን ማለት አይደለም። እኛ ለሌሎች ምሳሌዎች መሆን አንጂ በተሳሳቱ ሥራዎቻችን ልናጠፋቸው አይገባንም። ይህን አስመልክቶ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ ብሎናል፦ «መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ።» ማቴ 5:16። የዚህ ቃል ዋና ዓላማ ልናከብር የሚገባን አግዚአብሔርን እንጂ እኛን እንዳልሆነ ለማስተማር ነው።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም እንዲህ ብሎናል፦ «. . . በሰው ሁሉ ፊት መልካም የሆነውን አስቡ።» ሮሜ 12:17። የእግዚአብሔር ልጆች ሊሆኑ የሚገባቸው እንደዚህ ነው። ይህን አስመልክቶም ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ

«ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኃጢአትን አያደርግም . . . የእግዚአብሔር ልጆች . . . በዚህ የተገለጡ ናቸው . . .» (1ኛ ዮሐ 3:9፤10) ብሎ ነግሮናል።

መሰናክልን አስመልክቶ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «. . . ማሰናከያ ሳይመጣ አይቀርምና፤ነገር ግን በእርሱ ጠንቅ ማሰናከያ ለሚመጣበት ሰው ወዮለት።» (ማቴ 18:7) ብሏል።

ከሚከተሉት ሁለት ነጥቦች አንጻር አንድ ሰው በውጪው መልካም ጠባይ ሊኖረው ያስፈልጋል፦

1- ይህ ሊሆን የሚችለውም አግዚአብሔርን ከማክበር የተነሣ እንጂ ራስን ከማክበር አንጻር አይደለም።

2- ከውስጣዊ የልብ ንጽሕና የተነሣ ውጪያዊ ጠባይ ተፈጥሮአዊ ሊሆን ይችላል።

ውስጣዊ የልብ ንጽሕና ከውስጥ ካላገኘህ ይህን ለማግኘት ራስህን አበርታ። ሰው በልቡ ሞልቶ ካለው አፉ ይናገራልና የሚለው ቃል ምንኛ እውነት ነው! አንዳንድ ሰዎችን ከማክበር አንጻር ውስጣዊ ስሜቶችህ ገና ያልነጹ ከሆኑ በአንደበትህ በእነርሱ ላይ ኃጢአት ለመሥራትህ ምክንያት አይሆንም። ይህን የምታደርግ ከሆነ ልብህና አንደበትህ በአንድ ይፈረጃሉ። በዚህ ጊዜ አንደበትህን ከጥፋት ታድን ዘንድ ልትጠነቀቅ ይገባሃል። ቀስ በቀስም ልብህን እንደ አንደበትህ ልትገራው ትችላለህ።

አንድ ሰው መልካም እንዲሠራ መጫንና የሰዎችን ክብርና ፍቅር እንዲያገኝ ማድረግ የውጪያዊ መልካም ጠባይ አስፈላጊ ክፍሎች ናቸው። ይህን ማድረግ ደግሞ ራስን አጥብቆ መቆጣጠር እንጂ ግብዝነት አይደለም። ራስን በውጪ መቆጣጠር ጠቃሚም አስፈላጊም ነው። ሰው የንጽሕና ሕይወትን እንዲያገኝ ከወደደ ይህ ሊረዳው የሚችል አንዱ የልምምድ መንገድ ነው። የውጪያዊው ተገቢ ገጽታ ከውስጣዊው ጋር የተስማማ ይሆን ዘንድ ውስጣዊውን አጽዳ። ይህ ነገር ከውስጠኛው ጋር ተነጻጽሮ መልካም ካልሆነ ግን እንዳትወድቅ ይሁን። አንተ ከውስጥም ሆነ ከውጪ ንጹሕ ልትሆን ያስፈልግሃል። ስለዚህ ሁለቱንም ለማግኘት ሞክር። ከአንዱ ጫፍ ከጀመርህ ከሁለተኛውም ጫፍ ጀምር።

በውጪ የራስህ ዘብ መሆንህ የሚደገፍ ነገር ቢሆንም በዚህ ብቻ የምትደሰት አትሁን! ውስጣዊውን ንጽሕናም ጨምረህ ያዝ። ከሁሉም የጎደቀ ሥራዎች መካከል ይህ ቀዳሚ ልምምድህ ይሁን።

ቅድስናን አስመልክተው የሚደረጉ ልምምዶች።

ለምሳሌ ጾምን ውጪያዊ ጠባይና ውስጣዊ ድርጊት አድርገን በምሳሌ ልንወስደው እንችላለን። ጾም ሥጋ ከሚፈልገው ምኞት የሚከለከልበትና ለተወሰኑ ሰዓታት ከምግብ የሚታቀብበት ተራ ውጪያዊ ጽድቅ አይደለም። ሰው ስህተት ከመሥራት የሚከለከልበትም እንጂ። በመሆኑም ሥጋን መቆጣጠር ራስን ከመቆጣጠር ጋር አቻ ለአቻ ሊጓዝ ይችላል። ሰው በውስጥ ካለው መንፈሳዊ

ደረጃ ላይ ካልደረሰ ግን ጸሙን ቢያፈርስ ወይም ያገኘውን ቢበላ ይሻለዋል ማለት አይደለም። ይህን የሚያደርግ ከሆነ ሰውየው የሚወድቀው በሥጋም በነፍስም ነው። ስለሆነም ሰው በውስጡ ያለ ልቡን በውጪ ከሚጸመው ሥጋው ጋር አንድ ለማድረግ ሊያለማምደው ያስፈልገዋል። ይህ ደግሞ ትግል፣ ጊዜና ልምምድ የሚጠይቅ ቢሆንም ሰውየው ይህን በእግዚአብሔር ጸጋ ሊያገኘው ይችላል።

እዚህ ላይ ውጪያዊውንና ውስጣዊውን ደረጃ የምናነጻጽርበት ሚዛን ማስቀመጥ ያስፈልገናል። የዚህ ሚዛን መመሪያም የሚዛኑ አንድ ወገን ከሌላኛው አንድ ወገን ከፍ የሚል ከሆነ ዝቅ ያለውን ወገን ከፍ ወዳለው ወገን ከፍ ማድረግ ነው በሚለው የሚወሰን ነው።

እግዚአብሔር ልብን ስለሚመለከት ተገቢ በሆነ ውጪያዊ ጠባይ ብቻ አትደሰት። ምንጊዜም ልብህን ለማንጻት ታገል! በውጪ ያለ መልካም ጠባይህን ውስጣዊውን መልካም ድርጊትህን ለማግኘት የምታለማምድበት ወይም የምታዘጋጅበት ቀላል መንገድ አድርገህ ውሰደው።

ብዙ ጊዜ ውጪያዊው ንጽሕና ለውስጣዊው ንጽሕና ምክንያት ነው። ለምሳሌ፦ አንድ ወጣት ከውስጣዊ ሥጋ ምኞትና ለንጽሕና ከማይስማሙ ተራ ስሜቶች ጋር ትግል ሲገጥም ውጊያው የሚያስጨንቁና የረከሱ ሕልሞች ሊያሳየው ይችላል። ታዲያ እንዲህ ያለው ሰው በውጪ ሊያሳይ የሚገባው ጠባይ ውስጡ ከውጪው ጋር ያለውን መስማማት የሚያረጋግጥ መሆን አለበት ማለት ነው? ይህ ሊሆን አይችልም። ይህ ካልሆነልኝ የሚል ከሆነ ግን ራሱን ሊያጠፋ ይችላል። ከዚህ በተጨማሪ የሕሊናንና የልብን ኃጢአቶች ከመጨመር ሌላ የድርጊት፣ የስሜትና የሥጋ ኃጢአቶችን ይጨምራል።

እንዲህ ዓይነቱ ሰው በውጪ ለራሱ ዘብ ሆኖ በንቃት መጠበቁ ውስጣዊውን ንጽሕና እንዲያገኝ ይረዳዋል። በመሆኑም ከውጪ ብቻ ራሱን በመጠበቁ አይደሰትም። ስለሆነም ተስፋ በመቁረጥ ውስጥ ሆነህ «ውስጤ ንጹሕ እስካልሆነ ድረስ ውጪዬ ቢነጻ ምን ጥቅም አለው? አሳቤ ዘማዊ እስከሆነ ድረስ የሰውነቴ ድንግልና ጥቅም ምኑ ላይ ነው?» አትበል። እንዲህ እንድትል የሚያደርግህ ተስፋ በመቁረጥና ቢኃጢአት ውስጥ እንድትወድቅ የሚጋብዝህ የዲያብሎስ ውጊያ ነው። ውጪያዊ መቋቋምህ ኃጢአትን መካድህን ያመለክታል። በዚሁ ላይ ታዲያ አሳብን መቋቋምህን ጨምረህ ያዝ። በመጨረሻም እግዚአብሔር አንተን ለመርዳት ጸጋውን እንደሚልክልህ እርግጠኛ ሁን!

በውጪ ስላለ መታመንህ በእርሱ እስክተጠለልህና የእርሱን እርዳታ እስክጠየቅህ ድረስ እግዚአብሔር ይረዳሃል። ጥቂት በተባለው ውጪያዊው ንጽሕና ታማኝ ከሆንህ እግዚአብሔር ብዙ የተባለውን ውስጣዊ ንጽሕና ለአንተ ያድልሃል። ታዲያ በዚሁ ተመሳሳይ ጊዜ እግዚአብሔር ልብን እንደሚፈልግ አትዘንጋ። በውስጥህም መታገልን አታቋርጥ። የውስጥ አሳቦችን በመቃወም ወደ ውጊያው ዓውድ ግባ! ይህን ካደረግህ የሥጋንና የስሜትን ውጊያ ድል እንደነሣህ የውስጥ አሳቦችንም ድል ትነሣለህ።

እነዚህ ሁለት ነገሮች እርስ በእርስ ይደጋገፋሉ። በውጪ ያለ ግንዛቤህ በውስጥህ ካሉ ብዛት ያላቸው ውጊያዎች ይጠብቅሃል። ሌላው ቢቀር በተመሳሳይ ጊዜ በሁለት የውጊያ ዓውዶች ላይ አትሳተፍም። ውጪያዊው ግንዛቤህ በሕይወትህ ዘመን ሁሉ ለራስህ ዘብ እንድትቆም ከማድረጉም በላይ ውስጣዊው ግንዛቤ እንድትለማመድ ይረዳሃል። በዚህ ሁሉ ላይ እግዚአብሔር ስለ ታማኝነት ዋጋ አድርጎ ከላይ የሚልክልህ ጸጋ ይደመርልሃል።

ጀማሪ ሰዎች ውጪያዊ ውጊያን በማሸነፋቸው ሊደሰቱ ይችላሉ። ጥቂት ቆይተውም ወደ ልብና ወደ ሕሊና ንጽሕና ወደሚመሩትና ይበልጥ ከባድና ጥልቅ ወደ ሆኑት ውስጣዊ ውጊያዎች ይሸጋገራሉ። በዚህም ልብ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ይሆናል። የልብ ንጽሕና ማለት ኃጢአትን መቃወምና መጥላት ማለት ነው። የልብ ንጽሕናን ያገኘ ሰው ውጪያዊ ውጊያዎችን ድል ለመንሣት ይህ ይረዳዋል። ስለሆነም እንደነዚህ ዓይነቶቹ ውጊያዎች በእርሱ ላይ ምንም ዓይነት ኃይል አይኖራቸውም ማለት ነው።

ኃጢአት ወደ ሰው የሚመጣው እርሱ በማይገነዘበው በሕልም ከሆነ ? ያልሆነው ሕሊናው ሙሉ ለሙሉ ስለሚነቃ ይቃወመዋል። ስለሆነም ልቡ ሕሊናው ኃጢአትን ስለሚቃወሙት በሕልሙ እንኳ ቢሆን ኃጢአት አይሠራም። ምናልባት ኃጢአት ይፈጸም ዘንድ ሰውየውን የገድ የሚጫነው ከሆነ ልቡ ኃጢአትን ለመሥራት ስለ ተቃወመው ሙሉ ለሙሉ ይነቃል። በዚህ ጊዜ «. . . ኃጢአትን ሊያደርግ አይችልም።» (1ኛ ዮሐ 3:9) የሚለውና ሐዋርያው ቅዱስ ዮሐንስ የተናገረው የእግዚአብሔር ቃል በእርሱ ተግባራዊ ይሆናል።

የዚህን ቃል ማብራሪያ ሐዋርያው ሲናገር «. . . ዘሩ በእርሱ ይኖራልና . . .» ብሏል። ከዚህም በተጨማሪ «. . . ነገር ግን ከእግዚአብሔር የተወለደው ራሱን እንዲጠብቅ ክፉም እንዳይነካው እናውቃለን።» (1ኛ ዮሐ 5:18) በማለት ተናግሯል።

ልብ ንጹሕ ሊሆን ሁሉም የጽድቅ ሥራዎቹ መንፈሳዊ መነሣሣት ይኖራቸዋል። ከዚህ ሁሉ በላይ ሁሉም የሚከናወኑት ስለ እግዚአብሔር ብቻ ተብለው ይሆናል።

ስለ እግዚአብሔር እንጂ ስለ ሰው አይደለም።

አንድ ሰው መልካም የሚሠራው በሌላው ወይም በሌሎች ዓይን ፊት ከፍ ብሎ እንዲታይ መሆን የለበትም። በሰውም ሆነ በሰዎች ፊት ቢያደርገውም ሁለቱም ድርጊት የሚጠቃለሉት ወደ ግብዝነት በሚመሩት በከንቱ ውዳሴ ኃጢአት ውስጥ ነው። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ጻፎችና ስለ ፈሪሳውያን የተናገረው ቃል እውነት ነው . . . «ለሰውም እንዲታዩ ሥራቸውን ሁሉ ያደርጋሉ . . .» ማቴ 23:5።

በመሆኑም እነርሱ የውጪ ገጽታዎችን በመውደድ ኃጢአት ይወድቃሉ። ማንኛውንም ዓይነት መልካም ሥራ ቢያደርጉም እንኳ ሥራው እውነተኛ መልካም ሥራ አይደለም። ምክንያቱም መልካም ሥራ የተባለው ሥራ ራስን

ከመውደድና ከንቱ ውዳሴን ከመውደድ ጋር የተዋሀደ ስለሆነ ዓላማው ንጹሕ አይደለም። ዓላማው የእግዚአብሔር ፍቅር አይደለም። መልካም የሆነውን መውደድ ለራሱ ብቻ እንጂ ለሌላው ስላልሆነ ይህ ጤናማነት አይደለም። እዚህ ላይ አንድ ሰው፡- «ሰዎች እንዳያዩን ወይም ላደረግነው ነገር እንዳያመሰግኑን ሲባል በሰዎች ፊት መልካም ማድረግ የለብንም ማለት ነውን?» ብሎ ሊጠይቅ ይችላል። መጽሐፍ ቅዱስ «በሰው ሁሉ ፊት መልካም የሆነውን አስቡ. . .» (ሮሜ 12:17) ብሎ ስለሚናገር በእርግጥ መልካም የሆነውን ነገር ሁሉ ማድረግ አለብን።

ስለ ምስጋና ስንነጋገር ሐዋርያትና ቅዱሳን አባቶች በሰዎች መመስገናቸውን እናነሳለን። እነርሱ ከሞቱ በኋላ እንኳ በሰዎች እየተመሰገኑ ነው። ይህ ግን ኃጢአት አይደለም። ጻድቅ ሰው ስለ ሰዎች ውዳሴ ሲል መልካም ማድረጉን መተዉ ምክንያታዊ አያደርገውም። ታዲያ እነዚህን ሁሉና በትእዛዛት ውስጥ መልካም ማድረግን በምሥጢር ሶሶ መፈጸም የተጠቀሱትን ቃላት ጎን ለጎን ማስኬድ የምንችለው እንዴት ነው?

ይህን አስመልክቶ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ ይለናል፡- «አንተ ግን ስትጸልይ ወደ እልፍኝህ ግባ፤መዝጊያህንም ዘግተህ በስውር ላለው አባትህ ጸልይ፤በስውር የሚያይ አባትህም በግልጥ ያስረክብሃል።» (ማቴ 6:6።)፤«አንተ ግን ምጽዋት ስታደርግ ምጽዋትህ በስውር እንዲሆን ቀኝህ የምትሠራውን ግራህ አትወቅ . . .» (ማቴ 6:3)፤«አንተ ግን ስትጦም በስውር ላለው አባትህ እንጂ እንደ ጦመኛ ለሰዎች እንዳትታይ ራስህን ተቀባ ፊትህንም ታጠብ . . .» ማቴ 6:18።

እነዚህን ቃላት ከሕይወታችን ጋር የምናስማማቸው እንዴት ነው?

1- የምትችለውን ያህል መልካም ሥራህን በስውር አድርግ። ብዙ ጊዜ ይህን ለማድረግ ሊያዳግትህ ይችላል። ምክንያቱም ወደ ቤተ ክርስቲያን የምትሄደው፣ የምትጸልየው፣ ጉባኤ የምትካፈለው፣ የምትቆርበው፣ አጽዋማትን የምትጾመው፣ በሰዎች ሁሉ ፊት ስለሆነ ነው። ምናልባትም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለህ አገልግሎት በሰዎች ፊት የሚታወቅ ሊሆን ይችላል። አንዳንድ ጊዜ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለው ነዳያንን የመመገብ ምጽዋት በሰዎች ፊት የሚታወቅ ይሆናል። እነዚህን ጉዳዮች መፈጸም የምትችለው እንዴት ነው?

2- አንተ የሠራኸውን መልካም ሥራ ሰዎች ቢያውቁ ኃጢአት አይደለም። ኃጢአት የሚሆነው የመልካም ሥራን ዓላማ ሰዎች እንዲመለከቱትና አንተን በዚህ ምክንያት እንዲያወድሱህ ማድረግህ ነው። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «አንግዲህ ምጽዋት ስታደርግ ግብዞች በሰው ዘንድ ሊከብሩ በምኵራብ በመንገድም እንደሚያደርጉ በፊትህ መለከት አታስነፋ . . .» (ማቴ 6:2) ብሎ የተናገረው ይህን ለማስረዳት ስለወደደ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ ብሏል፡- «. . . ለሰው ይታዩ ዘንድ በምኵራብና በመንገድ ማዕዘን ቆመው መጸለይን ይወዳሉ . . .» ማቴ 6:5። ከዚሁ ጋር በተዛመደም «. . . ለሰዎች እንደ ጦመኛ ሊታዩ ፊታቸውን ያጠፋሉና . . .» (ማቴ 6:16)።

ከዚህ በግልጽ የምንረዳው ዓላማው በሰዎች እንዲታይና ምስጋናም ከእነርሱ እንዲቀርብበት በማሰብ የተደረገ መሆኑን ነው። እንዲህ ያለው ነገር ልታይ ልታይ ባይነት ወይም ውጪያዊ ገጽታን መውደድ ይባላል። ስለሆነም መልካም ሥራን ልታይ ልታይ ባይነትን በማስወገድ ከልብህ ልትሠራ ይገባሃል። ዓላማህን ሰውር እንጂ ከሰዎች ምስጋና ለማግኘት ለታይታ አታቅርበው። እንዲህ ካለው ነገር ራቅ። ከዚህ በኋላ ሰዎች የሠራኸውን መልካም ሥራ ቢያውቁትም እንኳ ብዙ አትጨነቅ።

3- ከሰዎች እይታ ተከለል። ካወቁ ግን ይህ ልብህን አያውከው። ድርጊቱን ለመርሳት ሞክር እንጂ ትኩረት አትስጠው። ከዚህ አንጻር ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ስለ ራሱና ስለ ወንድሞቹ አገልግሎት እንዲህ በማለት ተናግሯል፡- «. . . በክፉ ወሬና በመልካም ወሬ ራሳችንን እናሚጥናለን . . .» 2ኛ ቆሮ 6:8። የሐዋርያው ልብ በመልካምም ሆነ በክፉ ወሬ አልታወከም። ታላቁ አባት ቅዱስ መቃርስ እንዲህ ብሏል፡- «ለክብርም ሆነ ለውርደት ምንም ዓይነት ጥንቃቄ እንደማያደርግ እንደ ሞተ ሰው ሁን!»

4- ምስጋና ወደ ጆሮህ ደርሶ በአንተ ከተደመጠ ወደ ልብህ እንዳ ባ አትፍቀድለት። ይልቁኑም ይህን ስለምታሸንፍበት ስለ ድካምህና ስለ ኃጢአትህ አስታውስ።

5- ግልጽ በሆኑ ድርጊቶችህ ውስጥ እንኳ አንዳንድ ነገሮችን ልትሰውር ትችላለህ። ለምሳሌ ሰዎች መጸምህን ሊያውቁ ይችላሉ። ይሁን እንጂ በቀን ውስጥ ለምን ያህል ሰዓት እንደምትጸምና ምን ዓይነት ምግብ እንደምትመገብ መሰወር ትችላለህ። ጥቂቶች ይህንን ቢያውቁም ብዙዎች ግን ይህን እንዲያውቁ አትፍቀድላቸው። ምጽዋትን አስመልክቶም ይህ ሊደረግ ይችላል። ይህም ማለት ሰዎች መስጠትህን እንጂ ምን እንደሰጠህ አይወቁ ማለት ነው። ሰዎች መጸለይህን ያውቃሉ እንጂ በምትጸልይበት ጊዜ ልብህ ያለበትን ሁኔታ ሊያውቁ አይችሉም።

አንዳንዶች በጉባኤ በሚደረጉ ጸሎቶች ላይ ለምሳሌ በቅዳሴ ውስጥ ካህናት የሚጸልዩትን ጸሎት ሊያውቁ ይችላሉ። ይህን በማስመልከት እኔ ካህኑን የምመክረው በዙሪያው የሚያደምጡት ሰዎች መኖራቸውን ሙሉ ለሙሉ እንዲረሳና በእግዚአብሔር ፊት በመቆሙ ላይ ብቻ ትኩረት እንዲያደርግ ነው። ይህን በሚያደርግበት ጊዜም ሰዎች ቢሰሙትም ባይሰሙትም እርሱ ከጌታው ጋር መነጋገሩን ብቻ ያስባል።

ካህኑ የሚያዳምጡትን ሰዎች ለማስደሰት በማሰብ የሚጸልይ ከሆነ ግን በታይታ ኃጢአት ይወድቃል። በዚህ ጊዜ ጸሎቱን የሚያደርሰው ለእግዚአብሔር ሳይሆን, ለሰዎችና ለራሱ ነው። ብዙ አገልግሎቶችን የሚሰጥ ከሆነና በልቡ በእነዚህ አገልግሎቶች ሰዎችን ለማስደሰት የሚጥር ከሆነ ለውድቀት የተጋለጠ ሰው ነው። መንግሥተ ሰማያትን ለማግኘት የማይጥር ካህንም መጨረሻው ውድቀት ነው። ይህ ካህን ውድቀቱ በታይታ ይሆናል። እነዚህ ሁሉ ድርጊቶች ተራ እንቅስቃሴዎች ከሆኑ መንፈሳዊነት የጎደላቸው ፕሮጀክቶች ይሆናሉ።

ይህን ርዕስ አስመልክቶ ብዙ መናገር ቢቻልም በዚሁ እንደመድመዋለን። ጸጋ እግዚአብሔር ጥቂት እንድንናር የሚፈቅድልን ከሆነ በሌላ ጊዜ እንደምንመለስበት ተስፋ እናደርጋለን።

ምዕራፍ ዘጠኝ።

የእንደበት ኃጢአቶች።

- የእንደበት አደጋዎች።
- የእንደበት ጥፋቶች።
- ጠቃሚ አስተያየት።
- ከልብ የሚወጡ ኃጢአቶች።
- ሁለተኛው ወይም ሦስተኛው ኃጢአት።
- ከሰው ቁጥጥር የሚገኙ ውጤቶች።
- በንግግር ውስጥ ያሉ ጥንቃቄዎች።

የእንደበት አደጋዎች።

እንደበት መልካሙንም ሆነ ክፉውን የሚያደርግ በሁለት ወገን የተሳለ ሰይፍ ነው። እንደበትን አስመልክቶ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦ «. . . ከቃልህ የተነሣ ትጸድቃለህና ከቃልህም የተነሣ ትኮነናለህና።» ማቴ 12:37።

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለክፉው ባሪያ እንዲህ ነው ያለው፦ «. . . አፍህ በተናገረው እፈርድብሃለሁ።» ሉቃ 19:22። ነቢዩ ዳዊትም የንጉሥ ሳኦልን ሞት ለነገረው ብላቴና እንዲህ ብሎት ነበር፦ «እግዚአብሔር የቀባውን እኔ ገድያለሁ ብሎ አፍህ በላይህ መስክሮአልና ደምህ በራስህ ላይ ይሁን . . .» 2ኛ ሳሙ 1:16። ቅዱስ ጴጥሮስ ጌታውን አላውቀውም ብሎ ሲናገር በዚያ ቆመው የነበሩ «. . . አነጋገርህ ይገልጥሃል. . .» (ማቴ 26:73) ብለውት ነበር።

ጌታ ስለ ከንቱ ንግግር እንዲህ ብሎ ተናግሯል፦ «. . . ሰዎች ስለሚናገሩት ስለ ከንቱ ነገር ሁሉ በፍርድ ቀን መልስ ይሰጡበታል።» ማቴ 12:36። ከንቱ ቃል ክፉ ብቻ አይደለም፣ምንም ጥቅም የሌለው ቃል እንጂ። እግዚአብሔር አምላክ እንደበትን የፈጠረው ለሥራ እንጂ ለከንቱ አይደለም። የእንደበት ተግባር ስህተት መሥራት ብቻ አይደለም። ቀና የሆነውን የመሥራት ዐቢይ ተግባርም በእርሱ ዘንድ አለ። ይህ ባይሆን አንድ ማሽን ጉዳት ከማድረስ በስተቀር ሌላ ምንም የለውም ብሎ እንደመናገር ይቆጠራል። ወይም ደግሞ ቀና የሆነውን ብቻ ይሠራል እንደ ማለት ይሆናል። እንደበትም እንዲሁ ነው።

ከእንደበት ኃጢአቶች መካከል ከንቱ ንግግር አንዱ ነው። ከንቱ ንግግር ማለት እንደበትን ለተሳሳተ ጥቅም ማዋል ማለት ነው። ይህም ንዴት ባለበት ሁኔታ ውስጥ ይገለጣል። ከዚህ በተጨማሪ ከንቱ ንግግር የአድማጩንም ሆነ የተናጋሪውን ጊዜ ያለ ምንም ጥቅም ያባክናል። ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብም ስለ እንደበት በተናገረበት ምዕራፍ ውስጥ እንደበት ሊጠቅምም ሊጎዳም እንደሚችል ለመግለጽ እንዲህ ብሏል፦ «ምንጭስ ከአንድ አፍ የሚጣፍጥንና የሚመርን ውኃ ያመነጫልን?» ያዕ 3:11። ይኸው ሐዋርያ ስለ እንደበት አደጋ በዝርዝር ሲገልጽ «. . . በቃል የማይሰናከል ማንም ቢኖር እርሱ ሥጋውን ሁሉ ደግሞ ሊገታ የሚችል ፍጹም ሰው ነው።» ያዕ 3:2። ከዚሁ አስከትሎም እንዲህ ይላል፦ «እንደበትም እሳት ነው። እንደበት በብልቶቻችን መካከል ዓመፀኛ ሆኖአል፤ሥጋን

ይህን ርዕስ አስመልክቶ ብዙ መናገር ቢቻልም በዚሁ እንደመድመዋለን። ጸጋ እግዚአብሔር ጥቂት እንድንናር የሚፈቅድልን ከሆነ በሌላ ጊዜ እንደምንመለስበት ተስፋ እናደርጋለን።

ምዕራፍ ዘጠኝ።

የእንደበት ኃጢአቶች።

- የእንደበት አደጋዎች።
- የእንደበት ጥፋቶች።
- ጠቃሚ አስተያየት።
- ከልብ የሚወጡ ኃጢአቶች።
- ሁለተኛው ወይም ሦስተኛው ኃጢአት።
- ከሰው ቁጥጥር የሚገኙ ውጤቶች።
- በንግግር ውስጥ ያሉ ጥንቃቄዎች።

የእንደበት አደጋዎች።

እንደበት መልካሙንም ሆነ ክፉውን የሚያደርግ በሁለት ወገን የተሳለ ሰይፍ ነው። እንደበትን አስመልክቶ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦ «. . . ከቃልህ የተነሣ ትጸድቃለህና ከቃልህም የተነሣ ትኮነናለህና።» ማቴ 12:37።

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለክፉው ባሪያ እንዲህ ነው ያለው፦ «. . . አፍህ በተናገረው እፈርድብሃለሁ።» ሉቃ 19:22። ነቢዩ ዳዊትም የንጉሥ ሳኦልን ሞት ለነገረው ብላቴና እንዲህ ብሎት ነበር፦ «እግዚአብሔር የቀባውን እኔ ገድያለሁ ብሎ አፍህ በላይህ መስክሮአልና ደምህ በራስህ ላይ ይሁን . . .» 2ኛ ሳሙ 1:16። ቅዱስ ጴጥሮስ ጌታውን አላውቀውም ብሎ ሲናገር በዚያ ቆመው የነበሩ «. . . አነጋገርህ ይገልጥሃል. . .» (ማቴ 26:73) ብለውት ነበር።

ጌታ ስለ ከንቱ ንግግር እንዲህ ብሎ ተናግሯል፦ «. . . ሰዎች ስለሚናገሩት ስለ ከንቱ ነገር. ሁሉ በፍርድ ቀን መልስ ይሰጡበታል።» ማቴ 12:36። ከንቱ ቃል ክፉ ብቻ አይደለም፤ምንም ጥቅም የሌለው ቃል እንጂ። እግዚአብሔር አምላክ አንደበትን የፈጠረው ለሥራ እንጂ ለከንቱ አይደለም። የአንደበት ተግባር ስህተት መሥራት ብቻ አይደለም። ቀና የሆነውን የመሥራት ዐቢይ ተግባርም በእርሱ ዘንድ አለ። ይህ ባይሆን አንድ ማሽን ጉዳት ከማድረስ በስተቀር ሌላ ምንም የለውም ብሎ እንደመናገር ይቆጠራል። ወይም ደግሞ ቀና የሆነውን ብቻ ይሠራል እንደ ማለት ይሆናል። አንደበትም እንዲሁ ነው።

ከአንደበት ኃጢአቶች መካከል ከንቱ ንግግር አንዱ ነው። ከንቱ ንግግር ማለት አንደበትን ለተሳሳተ ጥቅም ማዋል ማለት ነው። ይህም ንዴት ባለበት ሁኔታ ውስጥ ይገለጣል። ከዚህ በተጨማሪ ከንቱ ንግግር የአድማጩንም ሆነ የተናጋሪውን ጊዜ ያለ ምንም ጥቅም ያባክናል። ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብም ስለ አንደበት በተናገረበት ምዕራፍ ውስጥ እንደበት ሊጠቅምም ሊጎዳም እንደሚችል ለመግለጽ እንዲህ ብሏል፦ «ምንጭስ ከአንድ አፍ የሚጣፍጥንና የሚመርን ውኃ ያመነጫልን?» ያዕ 3:11። ይኸው ሐዋርያ ስለ አንደበት አደጋ በዝርዝር ሲገልጽ «. . . በቃል የማይሰናከል ማንም ቢኖር እርሱ ሥጋውን ሁሉ ደግሞ ሊገታ የሚችል ፍጹም ሰው ነው።» ያዕ 3:2። ከዚሁ አስከትሎም እንዲህ ይላል፦ «አንደበትም እሳት ነው። አንደበት በብልቶቻችን መካከል ዓመፀኛ ሆኖአል፤ሥጋን

ሁሉ ያሳድፋልና፤የፍጥረትንም ሩጫ ያቃጥላል፤ በገሃነምም ይቃጠላል።» *ያዕ* 3:5-6።

አንደበት በጣም አደገኛ ስለሆነ ኃጢአቱ ጉድፍና ርኩሰት ነው። ከዚህ አንጻር መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲናገር «. . . ሰውን የሚያረክሰው ወደ አፍ የሚገባ አይደለም፤ከአፍ የሚወጣው ግን ሰውን የሚያረክሰው ይህ ነው . . . » ብሏል። ማቴ 15:11። በዚህ መሠረት ርኩሰት የዝሙት ኃጢአት ብቻ ሳይሆን የአንደበትም ኃጢአት ነው። ይኼ ደግሞ የአንደበት ኃጢአቶች ምን ያህል አደገኛ እንደሆኑ ይገልጽልናል። ይህን አደገኛነቱን ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ የገለጸው የሚገድል መርዝ፣ ውሳዋይ ክፋት፣ ዓመፀኛ ዓለም፣ ሥጋን ሁሉ የሚያሳድፍ፣ የፍጥረትን ሩጫ የሚያቃጥልና በገሃነም የሚቃጠል በማለት ነው።

የአንደበት ጥፋቶች።

አንደበት የሚወድቅባቸው ኃጢአቶችና ጥፋቶች ብዙና የማይቆጠሩ ናቸው። ከእነዚህም መካከል የሚከተሉትን መጥቀስ ይቻላል።

- የኩራት ኃጢአቶች።

ጉራ፣ የራስ ምክንያት፣ እልህ፣ ክርክር፣ ሌሎች ሲናገሩ ማቋረጥና ወደ ራስ የተሳሳተ ንግግር መምራት በእነዚህ ኃጢአቶች ውስጥ ይጠቃለላሉ።

- ውሸትን ያዘሉ ኃጢአቶች።

የእነዚህ ኃጢአቶች ምሳሌዎች ዓይን ያወጡ ውሸቶች፣ ማጋነን፣ ከፊል ውሸቶች፣ መዘላበድ፣ ማጭበርበር፣ ማሳሳት፣ የሐሰት ፈጠራዎች፣ የሐሰት ምስክርነት፣ ጥርጥርና ማታለል ናቸው።

- ፍቅርን የሚጸረሩ ኃጢአቶች።

እነዚህ ስድቦች፣ ቁጣ፣ ማዋረድ፣ ሌሎችን መንቀፍ፣ በሌሎች ላይ ማፌዝ፣ ሐሜት፣ ሴራ፣ የሚፈታተኑ ቃላት፣ ስላቅ፣ የሌሎችን ምሥጢር አደባባይ ማውጣት፣ ከኃላፊነት መሸሸና ኃላፊነትን በሌሎች ትከሻ ላይ መጣል እንዲሁም ስም ማጥፋትን ማስፋፋት ናቸው።

- የጭካኔ ኃጢአቶች።

መጉዳት፣ የሌሎችን ስሜት የማይጠብቁ ቃላትን መወርወር፣ መፈታተንና እንዲሰጉ ማድረግ በዚህ ውስጥ ይጠቃለላሉ።

- የጎደፉ ቃላት።

እነዚህ ቃላት በመጥፎ ታሪኮች፣ በጋጠወጥ ቀልዶች፣ በአሳፋሪ ዘፈን፣ በዝሙት ቃላት፣ በሚፈታተኑ ቃላት፣ በአሳፋሪ ቃላት፣ ትሕትና በጎደለው ስድ ጠባይ ውስጥ የሚገለጡና ማንኛውንም አፋራም ጆሮ የሚያሳፍሩ ቃላት ናቸው።

- እምነትን የሚመለከቱ የአንደበት ኃጢአቶች።

የእነዚህ ምሳሌዎች የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ የሚያነሱ ቃላት፣ ሃይማኖትንና ዶግማን አስመልክተው ጥርጥር የሚያስፋፉ ቃላት፣ ኑፋቄንና ክህደትን በማስፋፋት አማኞችን በተሳሳቱ መንገዶች የሚመሩ ቃላት ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ የእግዚአብሔርን ስም ለከንቱ በመጠቀም የሰዎችን ሕሊና በጥንቆላ ማሰር ሌሎቹ ምሳሌዎች ናቸው።

- የነፍስን ጥፋት የሚያቀርቡ ኃጢአቶች።

እነዚህ ቃላት ባልት፣ የሀሰት ውዳሴዎች፣ የሌሎችን ስህተት ማረጋገጥ፣ እኩል መናገር፣ ከጊዜው ጋር ማዝመም፣ ጥርጥር፣ ፌዝ፣ ማጉረምረምና ማማረር ናቸው።

ጠቃሚ አስተያየት።

ሙሉ ለሙሉ ባይመስሉም የአንደበት ኃጢአቶችን የሚመስሉ ኃጢአቶች አሉ። ስለ እነዚህ ኃጢአቶች ስንናገር የምንናገረው ስለ ተጻፉ ወይም ስለ ታተሙ ጽሑፎች ነው። እነዚህ ኃጢአቶችና ውጊያዎች ከአንደበት ኃጢአቶች ጋር ተመሳሳይ ቢሆኑም አንዳንድ ጊዜ የከፉ ይሆናሉ። በእነዚህ ጽሑፎች ውስጥ ያሉትን ቃላት የጻፈው ሰው ተጠያቂ ቢሆንም እርሱ ግን ኃላፊነቱን እንደሚሸከም አያውቅም። ይህን በቃልም አደረገው በጽሑፍ ኃጢአቱ እኩል ነው።

ኃጢአቱ አንድ ስለሆነ አንድን ሰው በቃልህ ስደብከውም በጽሑፍ አንድ ነው። ሰውየውን ማቅለልህና በውስጡ የሚኖረው ስሜት ተመሳሳይ ነው። ስነ ልቦናዊ መነሣሣቶቹም ተመሳሳይ ናቸው። የዚህ ተግባር ኃላፊነት ብቸኛ ልዩነት ስድቡ በቃል ሳይሆን በጽሑፍ መሆኑ ላይ ነው። ምናልባት ይህ የሚሆንበት ምክንያት ሰውየውን ፊት ለፊት ከማግኘት ይልቅ በጽሑፍ ማግኘት ስለሚቀል ነው። አብዛኛውን ጊዜ ሰዎች በሰዎች ፊት ሊናገሯቸው የማይደፍሯቸውን ቃላት በጽሑፍ መግለጽ ይቀናቸዋል።

ለማንኛውም ግን የአንደበት ኃጢአቶች አቻ ለአቻ የሚነጻጸሯቸው ሌሎች ኃጢአቶችን ከመግለጣቸውም በላይ ወደ እነርሱ ይመራሉ። እነዚህ ኃጢአቶች ደግሞ ከልብ የሚወጡ ኃጢአቶች ናቸው።

ከልብ የሚወጡ ኃጢአቶች።

አንድ ሰው ሊናደድ ይችላል። በንዴቱ ውስጥ ደግሞ ከባድና ጸያፍ ቃላትን ሊወረውር ይችላል። ባልንጀራዎቹ ግን ጥፋቶቹን እያወቁ 'እርሱ ልቡ ንጹሕ ነው' በማለት ስለ እርሱ ይናገራሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ንጹሕ ልብ የሚያወጣው ንጹህ ቃላት ነው ብሎ ስለሚናገር እንዲህ ያለው የሰዎች ምስክርነት ሙሉ ለሙሉ የተሳሳተ ነው። ቃሉ እንዲህ ነው የሚለው፦ «በልብ ሞልቶ ከተረፈው አፍ ይናገራልና።» (ማቴ 12:34)፤ «መልካም ሰው ከልቡ መልካም መዝገብ መልካም ነገርን ያወጣል፤ክፉ ሰውም ከክፉ መዝገብ ክፉ ነገር ያወጣል። . . . ዛፍ ከፍሬዋ ትታወቃለችና» ማቴ 12:35እና33።

ስለሆነም የኃጢአት ቃላት የሚገልጡት ኃጢአተኛ ልብን ነው። እዚህ ላይ የአንደበት ኃጢአት ኃጢአቱ ድርብ ነው። መጥፎ ቃላት ጨካኝ ልብን ሲገልጡ እብሪተኛ ቃላትም ትዕቢተኛ ልብን ያሳያሉ። ልክ እንደዚሁ መጥፎ ቃላት ግድየለሽ ልብን ሲያሳዩ በክፋት የተሞሉ ቃላትም በርኩሰት የተያዘ ልብን ይገልጣሉ። ስለሆነም ንግግሩን ሊያርም የሚወድ ሰው ሁሉ አስቀድሞ ልቡን ሊያርም ይገባዋል። ይህ ካልሆነ እንዲህ ዓይነቱ ሰው በሽንገላ ኃጢአት ይወድቃል። ሰውየው እዚህ ደረጃ ላይ ከደረሰ ደግሞ የልቡን ስሜት የሚቃወሙ ቃላትን ሊያወጣ ወይም ከተናገረው ጋር የማይስማሙ ውስጣዊ ስሜቶቹን ለማሳየት ይሞክራል።

በዚህ መሠረት የአንደበት ኃጢአቶች እንዲያው ተራ የአንደበት ኃጢአቶች ብቻ ሳይሆኑ የድምር ኃጢአቶች ውጤት ናቸው። ብዙ ጊዜ የአንደበት ኃጢአት ወደ ሰው የሚመጣው በሁለተኛው ወይም በሦስተኛው ደረጃ ነው።

ሁለተኛው ወይም ሦስተኛው ኃጢአት።

ለምሳሌ መዋሸትን እንደ ምሳሌ አድርገን እንውሰድ። መዋሸት አንደኛ ኃጢአት የሆነበት ጊዜ የለም። ብዙ ጊዜ ወይም ሁልጊዜ የሚወለደው ከአናት ኃጢአት ነው።

ሰው የሚዋሸው የቀደመ ኃጢአቱን ለመደበቅ ነው። ብዙ ጊዜ መዋሸት ሦስተኛ ተብሎ በሚጠቀሰው በፍርሃት ይታጀባል። በዚህ መሠረት ሰው ሁለተኛ በተባለው ኃጢአት ይኸውም በፍርሃት ተከቦ ሊደብቅ በሚፈልገው ኃጢአት ውስጥ ይኖራል። እነዚህ ሁለት ኃጢአቶች ደግሞ ውሸት በተባለው ኃጢአት ውስጥ ይጠቃለላሉ። በአብዛኛው ሰው ለካህናት አባቶች የሚናዘዘው መዋሸቱን እንጂ የቀሩትን ሁለት ኃጢአቶች አይደለም።

ቁጣ ሦስተኛ ወይም አራተኛ ኃጢአት ነው። በሰው ቁጣ ውስጥ የሚገለጡት መጥፎ ቃላት እንዲሁ የሚመጡ አይደሉም። መገኛቸው ከሌሎች ኃጢአቶች ማለትም ራስን ከመውደድ፣ ክብርን ከመፈለግ፣ ጥቅምን ከማግኘት፣ ካለመቻቻል፣ ከጭካኔ፣ ሰውን ከመጥላት ወይም ካለማክበር ነው። እነዚህ የተደራረቡ ኃጢአቶች መጥፎ ቃላት እንዲወጡ ያደርጋሉ። ይህ ደግሞ የሚቀጥለውን ኃጢአት ወደመፈጸም ይመራል።

ራሱን ከቁጣና መጥፎ ቃላት ከመናገር ለማዳን የሚፈልግ ሰው በመጀመሪያ ልቡን ከቀደሙት ኃጢአቶች ማንጻት ያስፈልገዋል። ቁጣንና መጥፎ ቃላትን አስመልክቶ ሰው ቁጣውን ይሸፍንለት ዘንድ ሰራሱ ምክንያት የሚደረድር ከሆነ ግን እነዚሁ ምክንያቶች ወደሚቀጥለው ኃጢአት ይኸውም ሰራስ ምክንያት ወደ መስጠት ኃጢአት ይሸጋገራል።

መንፈሳዊ ሰው ግን ራሱን ይወቅሳል እንጂ ሰራሱ ምክንያት አይሰጥም። ስለ ሌሎቹ የአንደበት ኃጢአቶችም ከዚሁ ጋር የሚመሳሰል ሊባል ይችላል። እያንዳንዳቸውን ብንገነዘባቸው በውስጣቸው የተለያዩ ኃጢአቶችን ይዘዋል። በመሆኑም ሁሉም ድምር ወይም ውሁድ ኃጢአቶች ናቸው ማለት ነው።

ከሰው ቁጥጥር የሚመጡ ውጤቶች።

1- የመጀመሪያው ውጤት የተናገርኸውን ቃል ተስፋፍቶ እንዳይወጣ ማድረግ ነው።

ስለ ተናገርኸውና ምክንያት ስለ ሰጠኸው ቃል ንስሐ ልትገባበት ትችላለህ። ጉዳዩ ከቁጥጥርህ ውጪ የሚሆነው ግን ቃሉ በሰዎች ዘንድ ከተደመጠ በኋላ የሚመጣው ውጤት ነው። እዚህ ላይ የአንደበት ኃጢአቶች ከሕሊና እና ከልብ ኃጢአቶች ይለያል። ምክንያቱም ሕሊና እና ልብ በውስጥህ ሆነው የሚጎዱት አንተን ብቻ እንጂ ሌሎችን ስላልሆነ ነው።

2- ሁለተኛው ውጤት የአንደበት ኃጢአት የተፈጸመባቸው ሰዎች ውጤት ነው።

ለምሳሌ በአንድ ሰው ላይ ቅሬታ ሊያድርብህ ይችላል። በዚህ ምክንያት በሰውየው ላይ ከባድ ስሜትን ያዘለ ክፉ ፈቃድ ከአንተ ጋር ስለሚሰነብት በልብህ ውስጥ ለረዥም ጊዜ ይቆያል። ይህ ግን በአንተና በእርሱ መካከል ያለውን ግንኙነት መጥፎ ወይም የከፋ አያደርገውም። ይሁን እንጂ ስሜቶችህን ሌሎችን ሊያጠቁ በሚችሉ ቃላት የምትገልጥ ከሆነ ወደ መልካም ደረጃ አትደርስም።

ይህ ጉዳይ በአንተ ውስጥ ኃጢአት መሆኑ ይቀርና ወደ ውጪያዊ ግንኙነት ይጎለምሳል። ይህን ግኑኝነት ለማደስ ብትሞክርም አይሳካልህም። ያስቀየምኸውን ሰው ለመታረቅ ብትፈልግም እንኳ እርሱ ፈቃደኛ አይሆንልህም። የተናገርሃቸው ቃላት በልቡ ውስጥ ቅያሜን ስላሳደሩ በቀላሉ ይቅር ሊልህ አይችሉ ም።

ምናልባት ቅያሜ ያሳደሩበትን ቃላት ያደመጡት ሰዎች ብዙ ከሆኑ የጥቃቱ አድማስ የሰፋ ይሆናል። ሌሎቹ ሰዎች ስለ እርሱ ስለሚቆጩና ለአንተ ያላቸው አመለካከት ስለሚጎድፍ ይርቁሃል። ከዚህ በኋላ ያስቀየምኸው ሰው ሊታረቅህ ቢችል እንኳ ሰውየውን ያስቀየሙትን ቃላት የሰሙት ሰዎች ግን ሊታረቁህ አይችሉም። ሌላው ቢቀር ያስቀየምኸውና የታረቅኸው ሰው ይቅር

ቢልህም ስለ አንተ ያለው የቅሬታ አመለካከት ከውስጡ በቀላሉ ታጥቦ ሊወጣ አይችልም።

ልክ እንደዚሁ ቃላትህ የሚጎዱ ከሆኑ ውጤታቸውም ጥልቅ ነው። ውጤታቸው የጎላ የሚሆነው ድምፅህና የፊትህ ገጽታ እንደ ቃላቶችህ አስከፊ ሲሆኑ ነው። እንዲህ ዓይነቱ ነገር ጉዳዩን የበለጠ ውስብስብ ያደርገዋል። ስለሆነም በማንኛውም ጊዜ ስትናገር የሰዎች ትዝታ የሰማውን ሳይረሳ እንደሚቆይ በማወቅ ተናገር። ውስጣዊ ስሜቶችህን በራስህ ልትወጣቸው ብትችልም የሚሰማህን ሰው ስሜትና ፍላጎት መጠበቅ አለመቻልህ ግን በጣም አሳዛኝ ሆኖ ይቀራል። እርሱ ስለ አንተ ምን እንደሚያስብ ማወቁ፣ ሌሎች በዚህ ዓይነት መንገድ መናገርህን ሲሰሙ ምን እንደሚሰማቸው መረዳቱና የተናገርሃቸውን ቃላት ተቃራኒ መገንዘባቸው ምንም ግድ አይሰጥህም። ይሁን እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ብሎ ይመሰክርህብሃል፦ «. . . ከቃልህ የተነሣ ትጸድቃለህና ከቃልህም የተነሣ ትኮነናለህ።» ማቴ 12:37።

3- ሦስተኛው ውጤት አንተ እነዚህን ለመሰሉ ኃጢአቶች ንስሓ ብትገባም ያደመጠህ ሰው ግን ንስሓ ሊገባ አለመቻሉ ነው። በመሆኑም እግዚአብሔር ደሙን ከአንተ እጅ ይፈልጋል። የምትናገራቸው ቃላት በዚህ ሰው ሕሊና እና ልብ ውስጥ አንድ ኃጢአት ሊያነሣሡ ይችላሉ። ቃላቶችህ ጥርጥርን የሚያነሣሡ ከሆነ ኃጢአቱ የጥርጥር ኃጢአት ሆኖ ይገለጣል። የዚህ ሰው ልብ አንተ ክፉ ተናግረህ ባስቀየምካቸው ሰዎች ላይ የሚኖረው አመለካከት ስለሚቀየር አነጋገርህ እርሱን በተሳሳተ መንገድ እንዳሳመነው ያውቃል። በዚህ ጊዜ አስቀድመህ የተናገርካቸውን አሳፋሪ ታሪኮችና ፀያፍ ቀልዶች ደጋግሞ ስለሚናገራቸው የሚደርስበት ጉዳት የከፋ ይሆናል። እርሱን የሚሰሙትም እነዚህኑ ደጋግመው በመናገር የሚደርስባቸው ጉዳትም ከእርሱ ጋር ተመሳሳይ ይሆናል።

ይህ ሁሉ ጥፋት ከደረሰ በኋላ አንተ ለፈጸምካቸው የአንደበት ኃጢአቶች ንስሓ ብትገባም የሰማህ ሰው ግን አይገባም። በዚህ ጊዜ ምን ልታደርግ ትችላለህ? በአንተ ምክንያት ኃጢአት የፈጸመውን ሰው ኃጢአቶችስ እንዴት ልታክማቸው ትችላለህ? ወይስ አንተ ንስሓ ብትገባም ኃጢአቶቹ በአንተ ላይ እንዲቆጠሩ በመፍቀድ የሚመጣውን ቅጣት ለመቀበል ቆርጠሃል!?

አንተ የአንደበት ኃጢአቶችህ በቆይታ የሚያመጡብህን ውጤቶች ስለማትገነዘባቸውና ስለማታስታውሳቸው ንስሓ አትገባባቸውም። ከእነዚህ ሌላ አንተ የማታውቃቸው ሆነው ቅጣት የምትቀበልባቸው ሌሎች ኃጢአቶችም ሊኖሩብህ ይችላሉ። ሰዎች ይመሩበት ዘንድ የተሳሳተ መመሪያ ከሰጠህ በኋላ አንተ የሰጠኸው መመሪያ ትክክል አለመሆኑን በማወቅ ራስህን ማረምህና ሌሎች ይህን የሕይወታቸው መርህ አድርገው ሲዘልቁበት መመልከት ምንኛ ቀላል ነገር ነው!

በእርግጥም የአንደበት ኃጢአቶች መካኖች ስላልሆኑ ሌሎች ብዙ ኃጢአቶችን መውለድ ይችላሉ። የአንደበት ኃጢአቶች ክባድ መሆናቸውን ለማወቅ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተራራው ስብከቱ ውስጥ

የተናገረውን በጥሞና መመልከት ያስፈልጋል። «እኔ ግን እላችኋለሁ፤በወንድሙ ላይ የሚቆጣ ሁሉ ፍርድ ይገባዋል፤ወንድሙንም ጨርቃም የሚለው ሁሉ የሸንጎ ፍርድ ይገባዋል፤ደንቆሮ የሚለውም ሁሉ የገሃነም እሳት ፍርድ ይገባዋል።» ማቴ 5:22። «ጨርቃም» የሚለው ቃል ክብርን ከሚያጎድሉት ቃላት መካከል የከፋው እንደ ሆነ ቅዱስ አውግስጢን ተናግሯል።

ስለዚህ ሰው ከአንደበት ኃጢአቶች፣ በጭካኔ ከተሞሉ ቃላት፣ ከአሽሙርና ከፌዝ ቃላት ራሱን መጠበቅ አለበት።

በንግግር ውስጥ ያሉ ጥንቃቄዎች።

የመጀመሪያው ጥንቃቄ በዝግታ መናገር ነው። ስመናገር ችኩል አትሁን፤ በተለይም በጭንቀት ወይም በንዴት ውስጥ ስትሆን። ምክንያቱም በዚህ ጊዜ ራስህን መቆጣጠር ስለማትችልና ቃላቶችን በጥንቃቄ መምረጥ ስለሚሳንህ ለጥፋት የተጋለጥህ ስለምትሆን ነው። እዚህ ላይ የሐዋርያው የቅዱስ ያዕቆብን ቃል ላስታውሳችሁ እወዳለሁ፦ «. . . ሰው ሁሉ ስመስማት የፈጠነ፣ ስመናገርም የዘገየ፣ ለቁጣም የዘገየ ይሁን፤የሰው ቁጣ የእግዚአብሔርን ጽድቅ አይሠራምና።» ያዕ 1:19-20።

በዚህ መሠረት ስትናደዱ ፈጣን መልስ አትስጡ፣ አትናገሩ፣ ውሸትም ከአንደበታችሁ አይውጣ። በዚህ ጊዜ መልስ የሚሰጠው ስሜታችሁ እንጂ ሕሊናችሁ ወይም ልባችሁ ስላልሆነ ተረጋጉ! መነሣሣታችሁ ለአናንተም ሆነ ለሚያደምጡአችሁ ሰዎች አደገኛ ስለሚሆን ውጤቶቹን ለማስተካከል ይሳናችኋል። አንተ ለሌሎች አሰቃ ወይም አባት ከሆንህ ያለ ምንም አስገዳጅ ምክንያት ወይም የሌሎችን ስሜት ሳትረዳ ለመናገር ለራስህ መብት አትስጠው።

ብዙ ጊዜ አለቆችና ከፍ ባለ ሥልጣን ላይ ያሉ ሰዎች ሊኖራቸው ከሚገባቸው በላይ ለራሳቸው መብት ይሰጣሉ። በመሆኑም ከአነርሱ በዕድሜ ለሚያንሱት ሌሎች ሰዎች ስሜት ምንም ግድ አይሰጣቸውም። ስለሆነም ከአነርሱ በማዕረግ የሚያንሱትን መገሠጽ፣ ማረምና ማስተማርን የበላይነታቸው መብት አድርገው ይወስዱታል። ለእነርሱ «ነገር ግን ሁሉ በአገባብና በሥርዓት ይሁን።» (1ኛ ቆሮ 14:40) የሚለውንና «በአናንተ ዘንድ ሁሉ በፍቅር ይሁን።» (1ኛ ቆሮ 16:14) የሚለውን የሐዋርያውን ቃል እናስታውሳቸዋለን። ከዚህ በተጨማሪ «ብኅነት» የተባለውን የመንፈስ ፍሬ እንዳይዘነጉትም እናሳስባቸዋለን። ታላላቆች ታናናሾቻቸውን ስለ መገሠጽ ሲሉ ብቻ የእግዚአብሔርን መንግሥት ማጣታቸው አሳዛኝ ነገር ነው።

ታላላቆች የሆኑትና ከፍ ባለ የሥልጣን ወንበር ላይ የተቀመጡት የእነዚህ ሰዎች ሌላው አሳዛኝ ነገራቸው እነርሱ ሕግጋትን ከመከተል ራሳቸውን ነጻ ማውጣታቸው ነው። እነርሱ ከሕግ በላይ የሆኑ ይመስል ትሑታን፣ የዋሆች፣ የተረጋጉና ጨዋዎች እንዲሆኑ እግዚአብሔር እንደማይፈልግ አድርገው ያስባሉ። እናንተ ግን ራሳችሁን ታላላቆች አታድርጉ። በአነጋገራችሁም ሁልጊዜ ጠንቃቆች ሁኑ!

ብዙ ቅዱሳን አባቶች ለአንደበት ኃጢአት መፍትሔ የሚሆነው ዝምታ መሆኑን ተረድተዋል። ይህን አስመልክቶ ነቢዩ ዳዊት እንዲህ ብሏል፦ «አቤቱ ለአፌ ጠባቂ አኑር፤የከንፈሮቼንም መዝጊያ ጠብቅ።» መዝ 140:3። የነገሥታትን ልጆች ያስተምር የነበረው ቅዱስ አርሳኒዎስም፦ «ብዙ ጊዜ ተናግሬያለሁ ብዙ ጊዜም ንስሓ ገብቼአለሁ፤ለዝምታ ግን ንስሓ ገብቼ አላውቅም።» በማለት ተናግሯል።

ስለሆነም ዝምታን ተለማመድ። ከተናገርህም ለጥብቅ ጉዳይ ይሁን። ንግግርህም አጭር ሆኖ ዝግ ባለ ድምፅ የተካተተ ይሁን። ከዚህ በተጨማሪ ይህን በማስመልከት ስለ መድኃኒታችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የተጻፈውን ድንቅ ቃል አስታውስ፦ «አይከራከርም፣ አይጮህምም፣ ድምፁንም በአደባባይ የሚሰማ የለም።» ማቴ 12:19።

ሌሎችን ለማስተማር አትጓጓ። ስለ እውቀትህ መናገርንና ስለ ችሎታህ አንስተህ ማውራትን ከአንተ ዘንድ አርቅ። ማንኛውም ዓይነት ስህተት ቢሆን በተለይም ሃይማኖት ነክ የሆኑ ጉዳዮችን አስመልክተው የሚሰነዘሩ ከሆኑ የሰዎችን ስሜት ከመጉዳት ባለፈ ውጤታቸው እጅግ የከፋ ይሆናል። ይህን በማስመልከት ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ እንዲህ ብሎናል፦ «ወንድሞቼ ሆይ፤ከእናንተ ብዙዎች አስተማሪዎች አይሁኑ፤ የባሰውን ፍርድ እንድንቀበል ታውቃላችሁና።» ያዕ 3:1-2።

ከዚህ ሌላ ከሌሎች ጋር ስትነጋገሩ ጨዋነትን በተሞላ ሥርዓት ውስጥ ሆናችሁ እንድትናገሩ ትመከራላችሁ። እግዚአብሔር እንድንኖር ከፈቀደ «ዝምታና ንግግር» በሚል ርዕስ አንድ መጽሐፍ ለማዘጋጀት አስባለሁ።

ከቀደሙ የአንደበት ስህተቶችህ ሁሉ ትምህርት ለመውሰድ ሞክር። ከአንተ አንደበት የወጡትን ቃላት በትክክለኛ ሚዛን ላይ አንድ በአንድ መዝናቸው። ቃላትህም ጥቅም የሚሰጡ ይሁኑ!

ምዕራፍ አሥር

የልብ ጭካኔ።

- ሁለት ዓይነት ጭካኔዎች።
- መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በጭካኔ ላይ ያለው ውሳኔ።
- የጨካኝ ልብ ባሕርያት።
- የልብ ጭካኔ ምክንያቶች።
- የጭካኔ መፍትሔ።

ሁለት ዓይነት ጭካኔዎች።

የልብ ጭካኔ በሁለት ይከፈላል። ይህም በእግዚአብሔር ላይ የሚደረግ ጭካኔና በሰዎች ላይ የሚደረግ ጭካኔ ተብሎ ይገለጻል።

- በእግዚአብሔር ላይ የሚደረግ ጭካኔ።

እንዲህ ያለው ጭካኔ እግዚአብሔርን መቃወምና ልብን በእርሱ ላይ መዝጋት ነው። በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ለእኛ ባሳየው ቸርነትና ፍቅር ልባችን አይነካም። ከዚህ በተጨማሪ የልባችንን መዝጊያ ማንኳኳቱም አይታሰበንም።

- በሰዎች ላይ የሚደረግ ጭካኔ።

ይኼኛው ጭካኔ በክፉ ባሕርይ ውስጥ ይገለጣል። ጨካኝ ቃላት፣ ክፉ አመለካከት፣ የጭካኔ ቅጣትና መራር ተግሣጽ የዚህ ባሕርይ መገለጫዎች ናቸው። እነዚህ ነገሮች ሰውነትን በማሰቃየት፤ነፍስን በማጥፋት፣ በማዋረድ፣ በማኮሰስና ተገቢ ባልሆነ መንገድ በመያዝ ሊገለጡ ይችላሉ።

አንድ ሰው በሁለቱም ዓይነት ጭካኔዎች ሊወድቅ ይችላል።

የጭካኔ ተቃራኒዎች ምሕረት፣ ቸርነት፣ እርጋታና ርኅራኄ ናቸው። ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምሕረትን በማስመልከት ብዙ ብሏል። በተራራው ስብከቱ ውስጥ «የሚምሩ ብፁዓን ናቸው፤ ይማራሉና።» (ማቴ 5:7) በማለት ተናግሯል። ከሁሉም በላይ ደግሞ ምሕረት የእግዚአብሔር መንግሥት መውረሻ መሆኗን ገልጧል። ማቴ 25:35-36። ባለጸጋው ነዌ ለድሀው አልዓዛር ሊራራለት ስላልቻለ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመውረስ አለመቻሉን ጌታ ነግሮናል። ሉቃ 16:21።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በጭካኔ ላይ ያለው ውሳኔ።

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለዘማውያንና ለኃጢአተኞች ርኅሩኅ ነበር። በንስሓ ውስጥ ሆነው ዕንባዎቻቸውን በማፍሰስ ወደ እርሱ የመጡትን በርኅራኄ ተቀብሏቸዋል። በዚህ ምክንያት እጅ ከፍንጅ ተይዛ ለመጣችው ዘማዊት ሴት ጌታ ተከላክሎላታል። ዮሐ 8:7።

ከዚህ በተቃራኒ ጨካኝ የሆኑትን ሰዎች ኢየሱስ ክርስቶስ አልተቀበላቸውም፤ ክፋኛ ገሠጻቸው እንጂ። ሃይማኖትን አስጨናቂ በሆነ መንገድ ያስተምሩ ስለነበሩት ጻፎችና ፈሪሳውያን በተግሣጽ ቃል እንዲህ ብሏል፦ «ከባድና አስቸጋሪ ሸክም ተብትበው በሰው ትከሻ ይጭናሉ፤እነርሱ ግን በጣታቸው ስንኳ ሊነኩት አይወዱም።» ማቴ 23:4። በመሆኑም ጌታ እንዲህ ብሏቸዋል፦ «እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን መንግሥተ ሰማያትን በሰው ፊት ስለምትዘጉ ወዮላችሁ፤ እናንተ አትገቡም የሚገቡትንም እንዳይገቡ ትከለክላላችሁ።» ማቴ 23:13።

ብዙ ጊዜ ጭካኔ የልብ መታበይ ውጤት ነው። በመሆኑም መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን እንደሚቃወም ይነግረናል፦ «እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማልና . . .» 1ኛ ጴጥ 5:5፤ያዕ 4:6።

በዚህ መሠረት እግዚአብሔር ልባችን ቸርና ርኅሩኅ እንዲሆን ይጠራናል። ከዚሁ ጎን ለጎን ክፉ የሆኑ ሰዎች በሌሎች ላይ ያደረጉት ክፋት ሁሉ በእነርሱ ላይ እንደሚደርስ እንዲህ በማለት ነግሮናል፦ «እንዳይፈረድባችሁ አትፍረዱ፤ በምትፈርዱበት ፍርድ ይፈረድባችኋልና፤በምትሰፍሩበትም መስፈሪያ ይሰፈርባችኋል።» ማቴ 7:1-2። እንግዲህ ይህን ቃል የሰሙ ጨካኞች በራሳቸው ላይ የሚያመጡትን የጭካኔ ውጤት በማወቅ ይፍሩ!

ጭካኔ የዲያብሎስ ውጊያ ነው። በመሆኑም ጨካኝ የሆነ ሰው ሁሉ በጠባዩ ዲያብሎስን ይመስለዋል። እግዚአብሔር መሐሪና ርኅሩኅ ስለሆነ ጭካኔ የእርሱ ባሕርይ አይደለም። ጭካኔ የሚጠላው በእግዚአብሔር ብቻ አይደለም። እርሱን በመሰሉትና ርኅሩኅ ልብ ባላቸው ቅዱሳን ዘንድም ጭካኔ የተጠላ ጠባይ ነው። አባታችን ያዕቆብ ሁለቱ ልጆቹን ማለትም ስምዖንንና ሌዊን ስለ ጭካኔያቸው እንዲህ በማለት ገሥጾአቸዋል፦ «ቁጣቸው ርጉም ይሁን፤ጽኑ ነበርና፤ ኩርፍታቸውም ብርቱ ነበርና . . .» ዘፍ 49:7።

ቸርና ርኅሩኅ ልብ ለእግዚአብሔር ቅርብ ነው። እንዲህ ዓይነቱ ልብ በእግዚአብሔር እጅ ውስጥ እንደሰለሰለ ሊጥ ስለሚሆን እርሱ እንደ ወደደ ያዘጋጀዋል። ክፋው፣ ጠማሩ፣ ድንጋያማውና ጨካኙ ልብ ግን ለእግዚአብሔር ሥራ መታዘዝ አይደለም በሚታዘዘው ትእዛዝ ላይ ጨርሶ ሊስማማ አይፈልግም። ከእንዲህ ዓይነቱ ጭካኔ እንድንርቅ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ በማለት አስጠንቅቆናል፦ «ዛሬ ድምፁን ብትሰሙት በማስመረር እንደ ሆነ ልባችሁን አልከኛ አታድርጉ።» ዕብ 3:15፤ 8፤4:7።

እግዚአብሔር ኃጢአትን ሁልጊዜ የሚመለከተው እንደ ጠማር ልብ ነው። ገርና በቀላሉ የሚሰማው ልብ ግን ለእግዚአብሔር አልታዘዝም አይልም፤ መዝጊያዎቹንም በእርሱ ላይ አይዘጋም። በመሆኑም ለእግዚአብሔር ድምፅና ጥሪ ንቁ ስለሆነ ምላሹን ፈጥኖ ይሰጣል። የሚሰማው ልብ በእግዚአብሔር ቃልና በጸጋው ሥራ በቀላሉ የሚ ረክ ነው። ይህ ልብ ከእግዚአብሔር መንገድ ወጥቶ ቢሄድም ፈጥኖ ይመለሳል። እንዲህ ዓይነቱን ልብ ትንሽ የተባሰችው ክስተት ልትሰማው ትችላለች። በመሆኑም እግዚአብሔር የሚናገረው እያንዳንዱ ቃል ልቡን ያለሰልሰዋል ወደ እርሱ እንዲመለስም ያደርገዋል።

ከዚህ በተለየ መልኩ የምናገኘው ፈርዖን ግን ልቡ ጨካኝ ነበር። በእርሱ ላይ የወረዱት መቅሠፍታት እጅግ ከባድ ቢሆኑም እንኳ ሊመለስ ወይም ንስሓ ሊገባ አልቻለም። በመሆኑም የጨካኝ ሰው ልብ በቀላሉ ወደ ንስሓ ሊደርስ አይችልም። ልክ እንደዚሁ ለእግዚአብሔር ጸጋ ያለው መሻት ደካማ፣ ጊዜያዊና ኃላፊ ነው። ሌላው ሁሉ ቢቀር አንዳችም የሚሰማው ነገር አይኖርም። ይህ ደግሞ ወደ ሌላ ጠቃሚ ርዕስ ይመራናል።

የጨካኝ ልብ ባሕርያት።

ጨካኝ ልብ ከእግዚአብሔር ጋር የሚያደርገው አካሄድ የሚሰማው አይደለም። ቃሉ እንኳ ልቡን አይነካውም። ለዚህ ምሳሌ የሚሆኑን ስለ እነርሱ እግዚአብሔር ቁጣውን እንደሚያመጣ ሎጥ የተናገራቸው የሰዶም ሰዎች ናቸው። ከተማዋ እንደምትጠፋ ሎጥ ሲናገራቸው የሚያላግጥባቸው መስሏቸው እንደ ነበር መጽሐፍ ቅዱስ ይመስክራል። «ለአማቾቹ ግን የሚያፌዝባቸው መሰላቸው።» ዘፍ 19:14። እነዚህን ሰመሰሉ ጨካኝ ሰዎች የእግዚአብሔር ቃል በጭንጫ ላይ እንደወደቀው ዘር ነው። ማቴ 13።

ልበ ደንዳና ሰው የመንፈስ ቅዱስ ቃል የማይሰማው መሆኑ ብቻ ሳይሆን በሰማው ቃል ላይ ሊዘብትና ሊሳለቅ ይችላል። የአንድ ሰው ልብ ለእግዚአብሔር ያለው አቀራረብ ጨካኝ ከሆነ የእርሱ ቃል ከሚነገርባቸው ቦታዎች ሁሉ ይርቃል። ወደ ቤተ ክርስቲያንና ወደ ጉባኤ አይሄድም። መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብ፣ ጸሎትና ሌሎችም መንፈሳዊ ተግባሮች ሊሰሙት ስለማይችሉ ችላ ይላቸዋል። ለዚህ ሰው የእግዚአብሔር ትእዛዛት ይከብዱታል። በእርግጥ ግን ከብደቱ ያለው ትእዛዛቱ ላይ ሳይሆን ልቡ ውስጥ ነው። የዚህ ሰው ልብ እጅግ ጨካኝ ስለሆነ በማንኛውም መንፈሳዊ መነሣሣት ሊንቀሳቀስ አይችልም። እንዲህ ያለው ነገር የእግዚአብሔር ቸርነት ወይም ማስጠንቀቂያ ወይም ቅጣት ወይም አደጋ ወይም ክስተት ቢሆንም እንኳ ለእርሱ ጉዳዩ አይደለም። ሕመም፣ ብቸኝነት፣ ጸሎትና መንፈሳዊ ቃላት ግድ አይሰጡትም። ለእግዚአብሔር ፍቅርና ቸርነት ውለታ ቢስ ስለሆነ ይህን የሚቆጥረው እንደ ሰብአዊ ምክንያት ነው። በእንዲህ ዓይነቱ ሰው ላይ «. . . ቀኑን ሁሉ ወደማይታዘዝና ወደሚቃወም ሕዝብ እጆቼን ዘረጋሁ . . .» (ሮሜ 10:21) የሚለው ቃል ተግባራዊ ይሆናል።

በዚህ መሠረት ጭካኔ ወዳለመታዘዝና ወደ ተቃውሞ ይመራል። ጥፋት ላጠፋ ሰው ጥፋቱ ምን እንደሆነ በመግለጽ ለረዥም ሰዓታት ስታስረዱት ትቆያላችሁ። እርሱ ግን እንደ እርሱ አመለካከት ምንም የተናገራችሁት አይመስለውም። የእርሱ ልብ ድንጋያማ ስለሆነ ጥፋቱን አይቀበልም ምላሽም አይሰጥም። እንዲህ ዓይነቱን ሰው ጸጋ እግዚአብሔር ቢተወው ምንኛ ይከብደው ይሆን? ይህን አስመልክቶ ጌታ እንዲህ ይላል፦ «አንደ ልባቸው ሥራ ተውኋቸው፤በልባቸውም አሳብ ሄዱ።» (መዝ 80:12)፤ «እግዚአብሔርን ለማወቅ ባልወደዱት መጠን እግዚአብሔር የማይገባውን ያደርጉ ዘንድ ለማይረባ አእምሮ አሳልፎ ሰጣቸው . . . ስለዚህ እግዚአብሔር ለሚያስነውር ምኞት አሳልፎ ሰጣቸው . . .» ሮሜ 1:28 እና 26። የልብ ጭካኔ በዚሁ ከቀጠለ እጅግ አደገኛ ይሆናል። ምክንያቱም እግዚአብሔር ሰውየውን ስለሚረሳውና በገዛ ጥፋቱ ስለሚጠፋ ነው።

የሚሰማው ሰው ዕንባ ቅርብ ነው። ጉዳዩ ምንም ይሁን ምን የጨካኝ ሰው ዓይን በዕንባ የሚረጥበው ግን በጣም ክብዙ ቀናት መካከል በአንዱ ቀን ብቻ ነው። ይህ የሚሆነውም ጨካኝ ሰው ከሰውም ሆነ ከእግዚአብሔር ጋር በሚያደርገው ግኙኝነት ውስጥ ርኅራኄው ስለማይገለጽ ነው። ዕንባ ርኅራኄን ይገልጻልና።

ከዚህ በተቃራኒ ልበ ደንዳናነት ቁጣና ንዴትን ያመነጫል። ጨካኝ ሰው ቁጣው በሌሎች ሰዎች ላይ ፈጥኖ ይቀጣጠላል። እርሱ በሰዎች ላይ ይጮኻል፣ ይነጫነጫል፣ ይዝታል እንጂ ማንም እርሱን በመቃወም ቃል እንዲናገር አይፈልግም። ከዚህ በተጨማሪ ስለ ሰዎች ምንም ግድ ስለማይሰጠው ስሜቶቻቸውን በቀላሉና በፍጥነት ይጎዳቸዋል። እነርሱን አስቀድሞ በመስደብም ፈጥኖ ያዋርዳቸዋል። የተናገራቸው ቃላት ሰዎቹን ምን ያህል እንደሚጎዳቸው ማወቁ ለእርሱ ጉዳዩ አይደለም።

እዚህ ላይ ጨካኝ ሰው ሁለት ተቃራኒ ነገሮችን አንድ ላይ ያስኬዳል። ሰዎች እርሱን እንዲንከባከቡት በጣም ይፈልጋል። ይሁን እንጂ የእርሱ ጠባይ የሌሎችን ስሜት መጉዳቱ አያስጨንቀውም። ይህ ሰው ሰዎችን ሲቆጣ ቁጣው የበዛና ጥልቅ ነው። ሲናደድም ንዴቱ ከባድና ለረዥም ጊዜ የሚቆይ ነው። በጭካኔው ውስጥ ሰዎች እርሱን እንዲችሉት እንጂ እርሱ እንዲችላቸው ወይም በቁጣው እዲነሣሡ አይፈቅድም። ጭራሽኑ እንዲህ ያለውን ነገር ለእነርሱ እንደሚገባ አድርገው እንዲቆጥሩ ይፈልጋል።

ያም ሆነ ይህ ግን ጭካኔ ጥላቻን ያስከትላል። ለጭካኔ ውጊያ እጅ የሚሰጡ ሰዎችን ከማጣታቸውም በላይ በማኅበራዊ ኑሮአቸው ውስጥ የወደቁ ይሆናሉ። ስለዚህ ሁላችንም የልብ ጭካኔን በመቃወም የራሳችን ዘብ ሆነን ልንቆም ይገባናል። ሐዋርያው የሚመክረንም «እርስ በእርሳችሁም ቸሮችና ርኅሩኖች ሁኑ . . .» ኤፌ 4:32። ከዚህ በተጨማሪ የመንፈስ ፍሬዎች የተባሉትን ፍቅር፣ ሰላም፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ ትዕግሥትን ልናስታውስ ይገባናል። ገላ 5:22-23። ይህን ካልን ልብን ስለሚወርሱት ስለ ጭካኔ ምክንያቶች ማወቅ ይገባናልና ወደዚያው እንሸጋገራለን።

የልብ ጭካኔ ምክንያቶች።

በእግዚአብሔር ላይ ስለሚደረገው ጭካኔ ዋና ምክንያት ሆኖ የሚቀርበው የኃጢአት ፍቅር ነው።

- የኃጢአት ፍቅር።

የኃጢአት ፍቅር ልብን በመማረክ ሰውን ከኃጢአት ጋር እንዲጣበቅ ያደርገዋል። በመሆኑም እግዚአብሔርንና ከእርሱ ጋር የሚያገናኙትን ጉዳዮች ሁሉ ይዘነጋል። ይህ ሳይብ ውም እግዚአብሔርን የሚመለከተው ከሚወደው ኃጢአት ነጥቆ እንደሚወስደው ጠላት አድርጎ ነው። ይህ ደግሞ ልቡን ይበልጥ ያደነድነዋል። መጽሐፍ ቅዱስ ለዚህ ምክንያት አድርጎ የሚያቀርበው «. . ዓለምን መውደድ ጥል እንዲሆን አታውቁምን?» (ያዕ 4:4) የሚለውን ቃል ነው።

ባለጸጋው ጎልማሳ ስለ ገንዘብ ፍቅር ልቡ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ስለ ደነደነ እያዘነ ወደ ቤቱ ተመልሷል። ማቴ 19። ሰዶምና ገሞራን የወደደችው የሎጥ ሚስት ልቧ ደንድኖ ነበር። መልአኩ ከዚያ ሊያወጣት እጇን ሲይዝ እንኳ ወደኋላዋ ዘወር ብላ ተመለከተች እንጂ ያዳናትን እግዚአብሔርንና ፍቅሩን አላሰበችም። በመሆኑም የጨው ዓምድ ሆና ቀርታለች። ዘፍ 19:26።

ከዚህ ይልቅ ግልጽ ምሳሌ የሆነው ፈርዖን ልቡ የደነደነው በሥልጣን ፍቅርና በባርነት ውስጥ ከነበሩት ሕዝብ በሚገኘው የጥቅም ፍቅር ነው። በመሆኑም በእርሱ ላይ ከመጡት መቅሠፍታት አንዳችም ሊጠቀም አልቻለም።

ሌሎቹ ምሳሌዎቻችን እግዚአብሔር የለም ብለው በቁስ አካል የሚያምኑትና ሰዓለም ካላቸው ፍቅር የተነሣ ከእግዚአብሔር ትእዛዛት ርቀው የሚደሰቱት ሰዎች ናቸው። እነዚህ ሰዎች ልባቸው እጅግ ስለ ደነደነ የእግዚአብሔርን ሕልውና ክደዋል። የእነርሱ ፈላስፋ «እኔ እንድ ; የእግዚአብሔር አለመኖር ለእኔ የተሻለ ነገር ነው።» በማለት የተናገረ ደፋር ነው።

የኃጢአት ፍቅር በጀግናው ሶምሶን ላይ እንኳ ተጽዕኖውን ገልጧል። በመሆኑም ስጦታውንና ክብሩን እንዲረሳና የኃይሉን መገለጫ ምሥጢር እንዲገልጥ አድርጎታል። በዚያች አጭር ጊዜ ውስጥ ልቡ በእግዚአብሔር ላይ ስለ ደነደነ ሁሉንም ነገር ዘንግቶ ነበር። የልብ ጭካኔ ሰውን ኃጢአት እንዲሠራ የሚያጣድፍና ንስሓን የሚያዘገይ ነው። የእግዚአብሔርን ድምፅ በልቡ ውስጥ ሲሰማ ዲያብሎስ የኃጢአትን ድምፅ እንዲያዳምጥ ያደርገዋል። ከዚህ በተጨማሪ የዓለሙ ፍቅርና ሥጋዊ ምኞት በእርሱ ላይ ይገለጣሉ። ስለዚህ ልቡ ስለሚጠጥር የጸጋን አሠራር ይቃወማል።

- ክፉ ባልንጀራ።

ክፉ ባልንጀርነትና በሰው ላይ የሚያመጣው መጥፎ ውጤት ልብን ሊያደነድን ይችላል።

ንጉሥ አክዓብን ምሳሌ አድርገን በመውሰድ ክፉ ሚስቱ ልቡን ምን ያህል እንዳደነደነችበት መመልከት እንችላለን። ንጉሥ አክዓብ የወይኑን መሬት እንዴት መውሰድ እንደሚችል ስላሳወቀ ተበሳጭቶ ነበር። ክብሯጭቱም የተነሣ «በአልጋውም ላይ ተጋድሞ ፊቱን ተሸፋፈነ፣ እንጀራም አልበላም።» 1ኛ ነገ 20:4። ይሁን እንጂ ሚስቱ ኤልዛቤል ናቡቴ በሐሰት የእግዚአብሔርንና የንጉሡን ስም ሰድቧል ብላ ካስመሰከረችበት በኋላ በድንጋይ ተወግሮ እንዲገደል በማድረግ የወይን መሬቱ ለባሏ ለአክዓብ እንዲሰጥ የሚያበቃውን የሐሰት ዕቅድ አውጥታ አቀረበችለት። ከዚህ በኋላ የአክዓብ ልብ ስለ ደነደነ ንዴቱንና ተስፋ መቁረጡን ወዲያውኑ በመርሳት ከተኛበት ተነሥቶ የሚሰቱን ዕቅድ ተግባራዊ አደረገ። በዚህም ምስኪኑ ናቡቴ በግፍ ተገደለ።

ሌላው የክፉ ባልንጀራ መጥፎ ተጽዕኖ የተገለጠው የንጉሥ ሰሎሞን ልጅ የነበረው ኢዮርብዓም ከእርሱ ጋር ያደጉትን ብላቴኖች ምክር በመቀበል አባቱ

ሰሎሞን በሕዝቡ ላይ የጣለውን ቀንበር አርሱ እጥፍ አድርጎ እንዲያከብደው በማድረግ እንዲቀጣቸው አድርገውታል። ኢዮርብዓም አስቀድሞ ምክር የጠየቃቸው ሽማግሌዎች ግን ለእስራኤል ጉባኤ መልካም የሆነውን ነገር በእርጋታና በፍቅር እንዲናገር አሳስበውት ነበር። እንዲህ ነበር ያሉት፦ «. . . ለዚህ ሕዝብ አሁን ባሪያ ብትሆን ብትገዛላቸውም መልሰህም በገርነት ብትገራቸው በዘመኑ ሁሉ ባሪያዎች ይሆኑልሃል . . .» 1ኛ ነገ 12:7። እነዚያ ብላቴኖች ግን ልቡን በማደንደን ስለ ሥልጣኑና ስለ ክብሩ ያለው ጠቀሜታ ላይ ካተኮረ ሕዝቡ ጸጥ ሰጥ ብለው ሊገዙለት እንደሚችሉ አማክረውታል።

ለኢዮርብዓም ብላቴና የሆኑ ባልንጀሮቹ የመከሩትና እርሱም ተግባራዊ ያደረገው ምክር እንዲህ የሚል ነበር፦ «. . . ታናሺቱ ጣቴ ከአባቴ ወገብ ትወፍራለች። አሁንም አባቴ ከባድ ቀንበር ጭኖባችኋል፤እኔ ግን በቀንበራችሁ ላይ እጨምራለሁ፤አባቴ በአለንጋ ገርፏችኋል፤እኔ ግን በጊንጥ እገርፋችኋለሁ. . .» 1ኛ ነገ 12:10-11። ኢዮርብዓም ያለውን ኃይል ሁሉ በመጠቀም ባልንጀራዎቹ እንደ መከሩት አደረገ። ይሁን እንጂ መንግሥቱ ስለ ተናጋ ከእጁ ሊወጣ በቅቷል።

ለአንድ ወጣት እንግዳ የሆኑ አዳዲስ አሳቦችን በጓደኞቹ በኩል በማስተዋወቅ ልቡን ማደንደን ምንኛ ቀላል ነገር ነው! እነዚህ ባልንጀራዎቹ አዳዲስ የኃይልና የጀግንነት፤ የነጻነትና ሊገኙ የሚገቧቸው መብቶችን ያስተዋውቁታል። በዚህ ምክንያት ይህ ወጣት በቤትም ሆነ በትምህርት ቤት በማንኛውም ሥልጣን ወይም የአመራር አካል ላይ አመፅ ያካሂዳል። በሥርዓቱና በሕጉ ላይም ያምፃል። በግል አመለካከቱ ተጽዕኖ ማሳደሩም ወንድነት ይመስለዋል። በምዕራቡ ዓለም የሚኖሩ ብዙ ወጣቶች የሚያድጉት እንዲህ ያለውን ነገር እንደ ግል ነጻነት በመቁጠር ስለሚሆን ለወላጆቻቸው ለመታዘዝ ፈቃደኞች አይሆኑም።

አንድ ወጣት የአባቱን ምክር የሚቀበለው ሊሆን የሚችልና የማይችል አድርጎ ስለሚሆን ሊቀበለውም ሆነ ላይቀበለው ይችላል። ይህ በመሆኑም ልቡ በወላጅ አባቱ፣ በንስሓ አባቱና በአለቆቹ ላይ ይደነድናል። በዚህ ጊዜ እርሱ ገና ልጅ እንደሆነና ብዙ ልምድ እንደሌለው ሊነግሩት በገዛ አሳቡ ላይ ይጸናል። በዚህ ምክንያት ልጆቻችንን ከሕጻንነታቸው አንስተን ስናሳድጋቸው እንግዳ በሆኑ አሳቦች እንዳይጠለፉ፣ እንዳይበላሹና ልቦናቸው እንዳይደነድን ጥንቃቄ ልናደርግላቸው ይገባናል። ልጆቻችን ተከራካሪዎች የሚያደርጓቸውን አሳቦች ይዘው እንዳያድጉ ልናበረታቸው ያስፈልጋል። ምክንያቱም ክርክሮቻቸው እነርሱ ያቀረቡትን አሳብ ካልሆነ በስተቀር ሌላው ያቀረበውን አሳብ ለመቀበል ፈቃደኞች ስለማያደርጓቸው ነው።

እነዚህ የሰዎች አሳቦች ለእነርሱ የሚገልጹላቸው መታዘዝን እንደ ድካም፣ መሸነፍን እንደ መረታት፣ አርምሞንም እንደ ፍርሃት አድርገው ነው። እነዚህ አሳቦች ሚዛኖቻቸውን በሙሉ ስለሚያዛቡባቸውና በራሳቸው በክንቱ ስለሚተማመኑ ደስታ ይሰማቸዋል። ይህን በማድረጋውም ልቦቻቸው ይደነድናሉ።

በልብ ላይ ስለሚመጣ ክፉ ባልንጀርነት ውጤት ስንነጋገር የምንነጋገረው ስለ ሰው ብቻ አይደለም። መጻሕፍትን፣ የታተሙ ጽሑፎችን፣ የሕዝብ መገናኛ ዎችና ፊልሞችንም ይጨምራል። ስለሆነም እነዚህ ነገሮች መጥፎ አይደሉም ብለን አንከራከርላቸው።

ለወጣቶች የተነገረው ሁሉ በዕድሜ ለበሰሉም ተግባራዊ ይሆናል። እዚህ ላይ ቤተሰብን ምሳሌ አድርገን ልንወስድ እንችላለን። ባል ከመጀመሪያ ሚስቱ በተወለዱ ልጆቹ ላይ ልቡን እንዲያጠፍር የእንጀራ እናት ምክንያት ትሆናለች። አዘውትራ የምትነግረው ስለ ልጆቹ ጥፋትና የእነዚህ ጥፋቶቻቸውን ክብደት ነው። ይህን የምታደርገውም በእነርሱ ላይ በጭካኔ እስኪነሣሣ ድረስ ነው። ከዚህ በተጨማሪ አንዲት ላገባ ልጇ የሚስቱን ጥፋቶች ብቻ በጆሮዎቹ ውስጥ የምታንቆረቁር እናት የዚህ ምሳሌ ናት። ይህን በማድረጓም ልጇ በሚስቱ ላይ ጠባዩን በጭካኔ እንዲለውጥ ታደርገዋለች።

ስለሆነም እያንዳንዱ ሰው ጭካኔ ከሌሎች ልብ ወደ እርሱ እየዳኸ እንዲገባ፣ በልቡ ውስጥ እንዲደራጅና እርሱ የሚለውን እንዲያምን መፍቀድ የለበትም።

- ኩራት።

ኩራት ለልብ ድንዳኔ አንዱ ምክንያት ነው። ሰው ወደ ራሱ ክብር፣ ለራሱ ወዳለው ከፍተኛ አስተያየትና ሰዎች ስለ እርሱ አላቸው ከሚለው አመለካከቱ አንጻር ሲታይ ወደ ጉት ወይም ወደ ትዕቢት የሚመራው ኩራት ነው። ይህ ደግሞ በማንኛውም ዓይነት መንገድ ክብሩን የሚነካበትን ሰው በጭካኔ እንዲመለከት ያደርገዋል። በኩራት ምክንያት የሚመጣ ጭካኔ በፊት ገጽታ፣ በአመለካከት፣ በቁጣ፣ በቃላትና ከሰዎች ጋር በሚደረግ ድርድር ውስጥ ይገለጣል።

- ጠባይና ዘር።

ከዘር የሚወረስ ጠባይ ከጭካኔ ምክንያቶች መካከል አንዱ ነው። እዚህ ላይ ግን አንድ ጥያቄ ሊነሣ ይችላል። ጥያቄውም «ከዘሩ በሚወርሰው ትሕትና ውስጣዊ ጭካኔውን ለመቋቋም ብዙ ጥረት የማያሻው ሰው አለ። ከዘሩ ወይም ከቤተሰቡ በሚወርሰው ጭካኔ በደል የሚሠራ ሰው ደግሞ አለ። ሁለተኛው ሰው ጭካኔውን የወረሰው ከዘሩ ስለሆነ ጥፋቱ ምንድር ነው?» የሚል ነው።

የዚህ መልሱ ጠባይ የተወረሰ ቢሆንም ይለወጣል የሚል ነው። ጠባዩን ለመለወጥ ከፍተኛ ጥረት የሚያደርገው ሰው ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚያገኘው ዋጋ ታላቅ ነው። ይህን በማስመልከት ምሳሌ ሊሆነን የሚችለው ከጭካኔ ሕይወት ወደ ርኅሩኅነት የተለወጠው ሙሴ ጸሊም ነው። እርሱ ትሑት፣ የሚወደድና ሌሎችን የሚያገለግል ሰው ሆኖ አልፏል።

ከላይ የተመለከትናቸው ምሳሌ ሆነው ቀሪቡ እንጂ የጭካኔ ምክንያቶች በዚህ መጽሐፍ ተዘርዝረው አያልቁም። ይህን ምዕራፍ የምናጠቃልለው ስለ ጭካኔ መፍትሔ ጥቂት ብለን ነው።

የጭካኔ መፍትሔ።

ጭካኔን ማከም የሚቻለው ልክ እንደ ሙሴ ጸሊም በንስሓ ሕይወት ውስጥ በማለፍ ነው። ይህ ሲሆን የሚችለውም ትሑትና ይቅርታ አድራጊ በመሆን፣ በሌሎች ላይ መልካም ተጽዕኖ በማሳደርና አርአያ በመሆን የሚታወቅ ሰው ጓደኛ ወይም ወዳጅ በመሆን ነው። ቅዱሳን የሚታወቁት ለሰው ሁሉ በሚያሳዩት ትሕትናቸው፣ ቸርነታቸውና ርኅራኄያቸው ነው። በመሆኑም ሰው ሁሉ ይህን መፍትሔ በማድረግ ብዙ ሊጠቀም ይችላል። ከዚህ በተጨማሪ ሰው ልበ ደንዳና በሆነ ቁጥር ከሚደርስበት ጉዳት ሊማር ይችላል።

የሰውን ልብ ርኅሩኅ ከሚያደርጉት ነገሮች መካከል የኅብረተሰቡን መጎዳት መገንዘቡ አንዱ ሲሆን በዚህ ውስጥ የተቸገሩትን፣ ድሆችን፣ ሕመምተኞችን፣ ደካሞችን፣ አካል ጉዳተኞችን፣ እናትና አባት የሞቱባቸውንና መበለቶችን ማገልገሉ ልብን ያራራታል። የሌሎች ሰዎችን ችግሮች ማቃለል ለጭካኔ መፍትሔ ይሆናል። ርኅሩኅ ስሜትን ለመፍጠርና የተጨናነቁ ነርቮችን ለማርገብ ለስለስ ያሉ መዝሙራትን ማዳመጥ ሌላው መፍትሔ ነው። ይህ ሁሉ ሲሆን የሚችለውም እግዚአብሔር ጨካኝ ጠባይን እንዲለውጥ በጸሎት በመጠየቅ ነው።

ምዕራፍ አሥራ አንድ።

የመንፈስ ዝለት።

- መቃጠልና ዝለት።
- የዝለት ዓይነቶች።
- የዝለት አደገኛ ምልክቶች።
- ከፍቅር ወደ ወረት መውደቅ።

የዝለት ምክንያቶችና መፍትሔዎቻቸው።

- ከእግዚአብሔር ጋር በማያገናኙ ጉዳዮች ባተሌ መሆን።
- ከንስሓ መራቅ።
- ደስታና ዕድገት አለማሳየት።
- የተመረጡ ቦታዎች አደገኛነት።
- በሕይወትህ ውስጥ ያሉ ሌሎች ሰዎች።
- መንፈሳዊ ተግባራትንና በየሰዓቱ የሚደረጉ ጸሎቶችን መዘንጋት።
- መንፈሳዊ ሂደትን እንደ ተራ ተግባር ማሰብ።
- በሰው ሕይወት ውስጥ ያለው ኃጢአት ወይስ ምኞት።
- ኩራት።
- ራስን ለማዋረድ አጭር ጊዜ መስጠትና ለተድላ መጣደፍ።
- ቸልተኝነትና ልልነት።
- ማጠቃለያ።

መቃጠልና ዝለት።

ዝለት የሚመጣው ከመንፈሳዊ መቃጠል ጉድለት ነው። በመንፈስ መቃጠል እንደሚያስፈልገን ሲናገር «በመንፈስ የምትቃጠሉ ሁኑ . . .» ብሏል። ሮሜ 12:11።

በበዓለ አምሳ መንፈስ ቅዱስ በቅዱሳን ሐዋርያት ላይ በኃይል የወረደው በእሳት ሳንቃ ተከፋፍሎ ነበር። እግዚአብሔር አምላክ በቁጥቋጦው ውስጥ ለሙሴ የተገለጠው በእሳት ነበልባል ነው። ዘጸ 3:2። ስለ እግዚአብሔርም እንዲህ ተብሏል፦ «አምላካችን በእውነት የሚያጠፋ እሳት ነው።» ዕብ 12:29። ስለሆነም በውስጡ የእግዚአብሔር መንፈስ ያደረበት ማንኛውም ሰው በመንፈስ ሊቃጠል ይገባዋል።

እንዲህ ባለው ሰው ልብ ውስጥ መቃጠሉ በሚያሳየው ፍቅር፣ በጸሎቱ፣ በአምልኮቱና በአገልግሎቱ ውስጥ ይገለጣል። ሕይወቱን ሁሉ የሚከበው በመንፈስ መቃጠል ነው። ተረጋግቶ በተቀመጠ ጊዜ ሁሉ አካባቢው፣ ድርጊቱና በውስጡ ያለው ቅንዓት ይቀጣጠላል።

መንፈሳዊ ሰው እግዚአብሔርንና ሰውን ይወዳል። መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ ፍቅርን የሚያነጻጽረው ከእሳት ጋር ነው። «ብዙ ውኃ ፍቅርን ያጠፋት ዘንድ አይችልም፤ፈሳሾችም አያሰጥሟትም . . .» መኃ 8:7። በዚህ መሠረት በፍቅር የተሞላ አገልጋይ እንደተናገረው ልክ እንደ እሳት ይቃጠላል። ከዚህ በተጨማሪ የሚቃጠል ሰው ነበልባል ወደ ሌሎች ሰዎች ይተላለፋል።

የእግዚአብሔርን ሥራ በመቃጠልና በድርጊት ስለሚፈጽሙት መላእክትም እንዲህ ተብሎ ተጽፎአል፡- «መላእክቱን መንፈስ የሚያደርግ አገልጋዮቹንም የእሳት ነበልባል።» መዝ 103:4። ይህ ይሁን እንጂ ብዙዎቹ መንፈሳውያን የሆኑ የእግዚአብሔር ልጆች በመንፈስ እየተቃጠሉ ከመቆየት ይልቅ ስለሚዝሉ የመጀመሪያ ፍቅራቸውን ያጣሉ። ወደዚህ የሚመሯቸው ምክንያቶች እንዳሉ ግን ምንም ጥርጥር የለውም።

የሚጸልዩት አስቀድሞ በነበራቸው ተመሳሳይ ፍቅር፣ ጥልቀትና መንፈስ አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስን ቢያነቡትም አይመሰጡበትም። መንፈሳዊ ስብሰባና ቅዳሴ እንደ ቀድሞው በልባቸው ውስጥ የተለየ ተጽዕኖ አያሳድርባቸውም። አምልኮታቸውም መንፈስ እንደሌለው ሥጋ ይሆናል። ስለ እነርሱ እንዲህ ተብሏል፡- «የአምልኮት መልክ አላቸው፤ኃይሉን ግን ክደዋል።» 2ኛ ጢሞ 3:5። ስለ እግዚአብሔር ቢናገሩም ሕልውናውና በእነርሱ ሕይወት ውስጥ መኖሩ አይታወቃቸውም።

እግዚአብሔር ዝለትን እንደሚጠላ የዮሐንስ ራዕይ ገልጾልናል። በሎዶቅያ ላለው የቤተ ክርስቲያን አለቃ እንዲህ በማለት ተናግሮታል፡- «በራድ ወይም ትኩስ እንዳይደለህ ሥራህን አውቃለሁ። በራድ ወይም ትኩስ ብትሆንስ መልካም በሆነ ነበር። እንዲሁ ለብ ስላልህ በራድም ወይም ትኩስ ስላልሆንህ ከአፌ ልተፋህ ነው።» ራዕ 3:15-16።

ከሚዋጋው ሰው አንጻር ሲለካ ዝለት ተነጻጻሪ ነው። ይህም ማለት በታላላቅ ቅዱሳን ዘንድ እንደ ዝለት የሚታየው ነገር ተራ በሆኑ ሰዎች ዘንድ በመንፈስ እንደ መቃጠል ይቆጠራል ማለት ነው። ታላላቅ ቅዱሳንን ዝለት ከነበሩበት ደረጃ ጥቂት ዝቅ ሊያደርጋቸው ቢችልም ከሌሎች ሰዎች ግን እጅጉን ይልቃሉ።

የዝለት ዓይነቶች።

ቅዱሳንን ጨምሮ በሰዎች ሁሉ ላይ የሚታይ የተለመደ ዝለት አለ። መንፈሳዊ ሕይወትን የሚያውክ አደገኛ የዝለት ዓይነትም አለ። ሦስተኛው ዓይነት ዝለት መንፈሳዊው ሰው በሕይወቱ ውስጥ ብርቱ ሆኖ ያሳሰፋቸውን የተለያዩ ጊዜያት በማነጻጸር የሚገለጽ አንጻራዊ ዝለት ነው።

- የተለመደው ተራ ዝለት ወደ ውድቀት በማድላት የተፈጥሮአችንን ሁኔታ የሚገልጸውና ብርቱ በሆነው መንገድ ላይ ሁልጊዜ ግንባር ቀደም ሆኖ ሊገዝ የማይችለው ዝለት ነው።

- አደገኛው ዝለት ያለ ምንም ተግሣጽ በሰው ውስጥ ለረዥም ጊዜ የሚቆየውና ጥልቀት የራቀው ዝለት ነው። ሰው ይህን ዝለት ስለሚለምደው የሰወጣው ዘንድ ምንም ጥረት አያደርግም። እንዲህ ዓይነቱ ዝለት የሚመጣው ብዙ ለምድ ለብሶ ነው። ለዚህ ምሳሌ የሚሆነን ወደ ቤተ ክርስቲያን በልማድ ሚመላለሰው ሰው ነው። ይህ ሰው ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚገባው በማክበር፣ መፍራትና በመራድ ስለማይሆን በዚያ መገኘቱ ለእርሱ ምንም ለውጥ

አያመጣም። በመሆኑም እንደ ፈለገ ያዛል፣ ይከለክላል በቤተ ክርስቲያን ውስጥም ድምፁን ከፍ አድርጎ ይናገራል። ሥርዓት ለማስያዝ በሚል ሰበብ የማይገቡ ቃላትን ይናገራል ይገሥጻማል። ቂሱ ወይም ዲያቆኑ በሚጸልዩበት ጊዜ ቃል ካጎደሉ እነርሱን ለማረም ጸሎቱን ያስቆማል።

እንዲህ ዓይነቱ ሰው መንፈሳዊነቱን ሊፈልግ ቢችልም ምንም ሊያገኝ አይችልም። ምናልባትም ያደረገው ሁሉ ትክክል ነው ብሎ ስለሚያስብ መንፈሳዊነቱን ፈልጎ ለማግኘት አይሞክርም። ይህ ሰው እዚህ ደረጃ ላይ ሲደርስ ምንም በማያውቀው ሁኔታ ከዝለት አልፎ በኃጢአት ይወድቃል። ቢያውቅ እንኳ ለራሱ ምክንያት ይሰጣል። ዝለት የሰውን ትሕትና፣ የዋህነት፣ ለቦታና ለሌሎች ሰዎች ያለውን አክብሮት ያሳጣል።

የዝለት አደገኛ ምልክቶች።

ዝለት የውድቀት ሂደት ነው። ግን እንዴት? ይህ ውድቀት ከፍቅር ወደ ወረት፣ ከመንፈስ ወደ አሳባዊነት፣ ከመንፈሳዊ ተግባር ወደ ሥጋዊ ተግባርና ስለ እግዚአብሔር ከማሰብ ስለ ሰው ወደማሰብ የሚደረግ ውድቀት ነው።

ዝለት በመሀል የሚያልፍ ጊዜ ሊባል ይችላል። ወይም ደግሞ በጥልቀት ሳይገቡ ከእግዚአብሔር ጋር ከላይ ከላይ የሚደረግ ውጪያዊ ግንኙነት ነው። ወይም ደግሞ የቅድስናን ሥራ በጥራት ወይም በጥልቀት ሳይሆን በብዛት ለመፈጸም ማተኮር ሊሆን ይችላል። እነዚህ ሁሉ ነጥቦች ረዘም ያለ ውይይት ቢፈልጉም እያንዳንዳቸውን ባጭር ባጭሩ በመግለጽ ሁኔታቸውንና የዝለትን ምክንያቶች እንገልጻለን።

ከፍቅር ወደ ወረት መውደቅ።

መንፈሳዊ ሕይወት ማለት ፍቅርን ሁሉ ለእግዚአብሔር ማድረግ ማለት ነው። እንዲህ ዓይነቱ ፍቅር ደግሞ ቅድስናን ሁሉ ማጠቃለል አለበት። እግዚአብሔርን ስለምትወደው በጸሎትህ ውስጥ እንዲህ እያልህ ትጸልያለህ፡- «. . . ነፍሴ አንተን ተጠማች፤ሥጋዬ አንተን እንደምን ናፈቀች፤እንጨትና ውኃ በሌለበት በምድረ በዳ።» (መዝ 62:1)፤«አቤቱ ሕግህን እንደምን እጅግ ወደድሁ! ቀኑን ሁሉ እርሱ ትዝታዬ ነው።» (መዝ 118:97)።

ዝለትን አስመልክቶ ግን ጸሎትህ ወደ ተራ ሥራነት ወይም ልትወጣው ወደሚገባህ ግዳጅነት ይቀየራል። ይህ በመሆኑም ሕሊናህ አያውክህም ወይም በዝንጋዔ ምክንያት አይወቅስህም። የምትጸልየው ያለ ፈቃድህ ስለሚሆን በጸሎትህ ውስጥ መነሣሣት ወይም በመንፈስ መቃጠል አይኖርም። ከዚህ በተጨማሪ የምትጸልየው ያለ መረዳት ስለሚሆን በውስጡ መንፈሳዊ ጸሎት የሚያካትታቸውን ነገሮች የማያካትት ይሆናል። ቢፈጸም እንኳ ያለ ትሕትና፣ ያለ መረጋጋት፣ ያለ እምነት፣ ያለ ተመስጦና ያለ ፍቅር ይሆናል። በዚህ ጊዜ ጸሎት ማድረሱ ይበቃል ብትልም እንኳ ጸሎትህ በልማድ የሚደርስ ይሆናል።

በዝለት ምክንያት በጸሎት ላይ የሚመጣው ተመሳሳይ ችግር በሁሉም መንፈሳዊ ተግባራት ላይ ይከሰታል።

በዝለት ውስጥ ስትሆን መጽሐፍ ቅዱስን የምታነበው በልማድ፣ ያሉ መረዳትና ያለ ተመስጦ ነው። በመሆኑም ያነበብኸውን በሕይወትህ ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ አትሞክርም። ብትሞክርም እንኳ ያለ ምንም ልምምድና በምታነበው ቃለ እግዚአብሔር ላይ ምንም ዓይነት ፍላጎት ሳይኖርህ ይሆናል። ነቢዩ ዳዊት ግን ስለ ቃለ እግዚአብሔር ከዚህ በተለየ መልኩ እንዲህ ይላል፡- «ብዙ ምርኮ እንዳገኝ በቃልህ ደስ አሰኘ።» መዝ 118፡162። አንተ ግን ቃለ እግዚአብሔርን የምታነበው እንደ ተራ ልምድ ወይም ሥራ ነው። ምናልባት መንፈሳዊ ሕይወትህን የጀመርከው ለእግዚአብሔር ባለህ ፍቅር ቢሆንም በዚያው ልትቀጥል አልቻልህ ይሆናል። ግን ለምን?

ምናልባት እንዲህ ያለው ዝለት የመጣብህ ስለ ብዛቱ እንጂ ስለ ጥራቱ ስላልተጨነቅህ ሊሆን ይችላል። ይሄ ደግሞ ወደ ተራ አምልኮ ይመራሃል። የተወሰነ መጠን ያላቸው መዝሙራትና ሌሎች ጸሎቶች ማቅረብ ትፈልጋለህ። የተወሰነ ቁጥር ያላቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ምዕራፎችም ልታነብ ትፈልጋለህ። ከዚህ በተጨማሪ የተወሰነ ቁጥር ያላቸውና በጸሎት ውስጥ የሚቀርቡ ስግደቶችን መስገድ ትፈልጋለህ። ይሁን እንጂ እነዚህን ሁሉ እንዴት ማከናወን እንዳለብህ አታውቅም። በዚህ ጊዜ የአንተ ብቸኛ አትኩሮት የሚሆነው ብዛቱ ላይ እንጂ ባለው መንፈስ ላይ አይደለም። ከላይ ከጠቀስናቸው መንፈሳዊ ልምምዶች መካከል ጥቂቶቹን ብታገኝ በዚህ ብቻ ስለምትደሰት እግዚአብሔር በአምልኮት አፈጻጸምህ ተደሰተም አልተደሰተም ግድ አይኖርህም።

ይህን አስመልክቶ ቅዱስ ይስሐቅ «በእግዚአብሔር ፊት የቆምሁት ቃላትን ለመቁጠር አይደለም።» በማለት ይመክርሃል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም እልፍ ቃላትን በልሳን ከምናገር ይልቅ አምስት ቃላት በሕሊናዬ ብናገር እመርጣለሁ ብሎሃል። 1ኛ ቆሮ 14፡19።

አስቀድመን የተናገርናቸውን መንፈሳዊ ተግባራት ለማከናወን ብትፈልግም ጸሎትህን የምታከናውነው በመጣደፍ ስለሚሆን ጸሎትህ የሚጠናቀቀው ያለ ምንም መረዳትና ተመስጦ ይሆናል። እንዲህ ያለው ጸሎት ዋና ተግባርን ለማከናወን የሚደረግ ግዳጅ ይሆናል። ይህ ዓይነቱን ጸሎት መነሳሳት ደንብ ብለው ይጠሩታል። በመሆኑም ከእግዚአብሔር ፍቅር ጋር በመነጋገርህ ደስ ሊልህ ሲገባ ይህ ደንብ የአንተ ዓላማ ሆኖ ይቀራል። ከመንፈሳዊው መንገድ አፈንግጦ የሚወጣው ዓላማ የሚመራህ ወደ ዝለት ነው። ምክንያቱም እንዲህ ያለው ነገር በመንፈስ መቃጠልን ከሚያስገኝልህ መንፈሳዊ ጸሎትህ አንተን ለይቶ መውሰዱ አርግጥ ስለሆነ ነው።

ብዙ ሰዎች በመጀመሪያ ዜማዎችንና የመዝሙራትን ስንኞች ዘልባቸውም አይሿቸውም። ቀስ በቀስ ግን በአነርሱ ላይ ቸ፡መስጦ ስለሚቆዩ በመንፈስ ሆነው ይጸልዩአቸዋል። ከብዙ ልምምድ በኋላ መዝሙራቱንም ሆነ ዜማዎቹን በቃላቸው ስለሚዘአቸው በፍጥነት ይወጧቸዋል። በዚህ ጊዜ ከአንደበታቸው የሚወጡት ቃላት ግን ግልጽ ሆነው አይወጡም።

ከዚህ ሌላ ጸሎትን ማነብነብና ፍጥነት የሚመሩት መረዳት ወደሌለበት፣ መልካም ስሜት ወደማይገኝበትና ተመስጦ ወደማይገለጽበት ሕይወት ነው። አንተ ግን በእነዚህ ሁሉ የምትፈተን ከሆነ ለራስህ እንዲህ በል፡- «ቀራጩ በጥቂት ቃላት ወደ አንተ እንደጸለየውና ከበስተቀኝህ የተሰቀለው ወንበዴ በአንዲት ዓረፍተ ነገር ጸሎቱን ለአንተ እንዳቀረበው እኔም ከአንተ ጋር ከልቤ ለመነጋገር አፈልጋለሁ!»

ለዝለት ምክንያት ከሚሆኑት ነገሮች መካከል አንዱ በጸሎት ሳይሆን በማነብነብ መደሰት ነው። አንተ ከልብህ ተጨማሪ የሆኑ ጸሎቶችን ሳታክል በእነዚህ በተጠኑ ጸሎቶች መደሰትህ ብቻ ተገቢ አይደለም። በአርግጥ መዝሙራትንና ሌሎች የተጠኑ ጸሎቶችን በመረዳት ከልባችን ሆነን የምንጸልያቸው ከሆነ መልእክቶቻቸው ድንቅ ነው። እነርሱ መንፈሳዊ መዛግብት ናቸውና። ከዚህ በተጨማሪ በራስህ ቃላት ከልብ ሆነህ በምትደግማቸው የግል ጸሎቶችህ ውስጥ በእግዚአብሔር ፊት እንደቆምህና እንደምታየው ሆነህ ልትቆም ይገባሃል። በመንፈሳዊ መቃጠል ውስጥ እያለህ በዝለት የምትወጋ ከሆነ እነዚህ የግል ጸሎቶችህን በመጸለይ በሕይወት ውስጥ የሚያመጡትን ለውጥ ተመልከት።

ለብዛት፣ ለፍጥነት፣ ለልማድና ለደንብ ከመገዛት ውጪ ሁን! ይልቁንም በመንፈስ፣ በመረዳትና በመነሣሣት ውስጥ ሆነህ ጸልይ። ከመውደቅ በመጠንቀቅ ለሌሎቹም መንፈሳዊ ልምምዶችህ ተመሳሳይ ድርጊቶችን ፈጽም። የሚሰማህ ወይም የሚታወቅህ ለብ ማለትህ ከሆነ ጥልቅ የሆኑ ጥቂት ጸሎቶችን ጨምር። በመቀጠልም ሌሎች ተመሳሳይ ጥልቀትና ቁጥር ያላቸው ጸሎቶችን ጨምር። ይህን ማድረግ የሚያቅትህ ከሆነ ዝቅተኛ ቁጥር ባላቸው ጸሎቶችህን እየደገምህ ቆይ! ዋናው ቁም ነገር የጸሎትህ ጥልቀት ስለሆነ ከዝለትህ እንድትፈወስ ይረዳሃል።

ዝለት በጸሎት፣ በንባብ፣ በተመስጦና በመንፈሳዊ ልምምዶች ተወስኖ የሚቀር አይደለም። ዝለት ውስጣዊ የልብ ስሜቶችን፣ የተሰያዩ የመንፈስ ፍሬዎችንና መንፈሳዊ ሕይወትን ሙሉ ለሙሉ ሊያጠቃ ይችላል። በመሆኑም አስቀድሞ የነበረው መንፈሳዊ ቅንዓት ይቀንሳል፣ ለበዓላት የነበረው ጉጉት ይቀዘቅዛል፣ ራስን ማዋረድና የንስሓ ሕይወትን መምራት የነበረው ኃይል እየሳሳ ይመጣል።

የዝለት አሠራርና አካሄድ ተመሳሳይ ሊሆን ይችላል። ለዚህ ምሳሌ ከሚሆኑን መካከል ራስን ከእግዚአብሔር ጋር በማያገናኝ ጉዳይ ውስጥ መጥመድ አንዱ ነው። እንዲህ ዓይነቱ ነገር የዝለት ምልክት ወይም ምክንያት ነው ሊባል ይቻላል። ራስን ሳያሻሽሉ በደረሱበት የዕድገት ደረጃ መደሰት ለዝለት ምክንያት ወይም ምልክት ነው። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተነጋገርንበት ከፍቅር ወደ ወረት መውደቅም የዝለት ምክንያት ወይም ምልክት ነው። በመቀጠል የዝለት ምክንያቶችንና መፍትሔያቸውን በማስመልከት እንነጋገራለን።

የዝለት ምክንያቶችና መፍትሔዎቻቸው።

- ከእግዚአብሔር ጋር በማያገናኙ ጉዳዮች ባተሌ መሆን።

አደገኛው ከሆኑት የዝለት ምክንያቶች አንዱ ይህ ነው። ሰው ከእግዚአብሔር ጋር በማያገናኙ ምክንያቶች የሚጠመድ ከሆነ ለእግዚአብሔርም ሆነ ለመንፈሳዊነቱ ጊዜ አያገኝም። በዚህ ጊዜ ሰው ትኩረቱን የሚያደርገው አስቀድሞ ለጀመረው ሥራ እንጂ ለእግዚአብሔር አይደለም። ቅድሚያ የሚሰጠው ለእግዚአብሔር ስላልሆነም ደረሻው የመጨረሻ ይሆናል። ልብን በመንፈስ የሚያቀልጡት መንፈሳዊ ልምምዶች ስለማይኖሩትም ሰውየው ልፍልፍስ ሆኖ ይቀራል።

የቀደሙ ሥራዎች የተለያዩ ናቸው። አንዳንዶች ሥራዎች ዓለማዊ ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ በመንፈሳዊ መስክ ውስጥ የሚገኙ ናቸው። አንድ ሰው አስቀድሞ በቤተሰብ ጉዳይ ወይም በጥናት ወይም በሥራ ወይም በቀልድ ወይም በትርፍ ጊዜ ሥራ ወይም በሌሎች ሥራዎች ስለሚጠመድ ለመንፈሳዊ ልምምዶቹ ጊዜ አያገኝም። ለእንደዚህ ዓይነቱ ሰው ሁለት ጠቃሚ ምክሮች ልንሰጠው እንችላለን። እነርሱም፦

1- ጊዜን ማቀናጀት ወይም ቅድሚያ ለሚሰጣቸው ቅድሚያ መስጠት አለበት።

2- «ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱንም ቢያጎድል ምን ይጠቅመዋል?» (ማቴ 16:26) የሚለውን ቃለ እግዚአብሔር ዘወትር ማስታወስ አለበት።

ጊዜህን ይህን በመሰለ መንገድ የምታቀናብር ከሆነ ከፊል ጊዜህን ለመንፈሳዊ ተግባራት ታውላለህ። ከዚህ በተጨማሪ ለሕይወትህ ጠቃሚ የሆኑ የመንፈሳዊ ልምምዶችን ዋጋና የዘላለማዊነትን ዋጋ ጥቅም ትገነዘባለህ። ይህን ተገንዘብህ ማለት ደግሞ በማንኛውም ሥራ የተጠመድህ ብትሆንም እንኳ ለመንፈሳዊ ተግባሮችህ ጊዜ ለመስጠት ታተኩራለህ።

ከአገልግሎትና ከቤተ ክርስቲያን ጋር በሚያገናኙ ጉዳዮች መጠመድህን ተገንዘብ! ይህ ሕሊናህን በማስደሰት ከመንፈሳዊነት ሊያርቁህ ከሚችሉ ጉዳዮች ሊያወጣህ ይችላልና። መንፈሳዊነት እየቀዘቀዘ ሲሄድ አገልግሎትህ እየላላ መምጣቱንና ፍሬ ማፍራት አለመቻሉን እወቅ። መንፈሳዊነት ተራ እንቅስቃሴ ሳይሆን ከአንዱ ሰው ወደ ሌላው ሰው የሚሸጋገር መንፈስ ነው። ከዚህ በተጨማሪ መንፈሳዊነት ተገልጋዩ ከአገልጋዩ የሚያገኘው ሕይወት ነው።

አገልግሎት በእግዚአብሔርና ከእርሱ ጋር በሚሆን አንድነት መደሰት መሆኑን የማይቀበል አገልግሎት ካልሆነ አገልግሎት አይባልም። ከጸሎት፣ ከተመሰጠና ከእርሱ ጋር ከሚኖረህ ምሥጢራዊ ግንኙነቶች የሚለይህ መንፈሳዊ አገልግሎት እንዲኖርህ እግዚአብሔር አምላክ አይፈቅድም። በመሆኑም አገልግሎቶችህንም ማቀናጀት አለብህ ማለት ነው።

የጠፋው ልጅ ታላቅ ወንድም ለአባቱ ያቀረበውን ወቀሳ አስታውስ። «. . . እነሆ ይህን ያህል ዓመት እንደ ባሪያ ተገዝቼልሃለሁ፤ከትእዛዛትህም ከቶ አልተላለፍሁም፤ለእኔም ከወዳጆቼ ጋር ደስ እንዲለኝ አንድ ጠቦት ስንኳ አልሰጠኸኝም . . .» ሉቃ 15:29። ይህ ልጅ አባቱን ያገለገለባቸው ረዥም ዓመታት መልካም ሆነው ሳሉ ፈቃዱ የአባቱን ፈቃድ የተቃወመበት ተቃውሞ የከፋ ስለነበር መንፈሳዊነቱ ደካማ ሆኗል። ይህ ደግሞ ታናሽ ወንድሙ ወደ አባቱ ቤት ስለ ተመለሰ አባቱ ባደረገለት ግብዣ ላይ እንዲገኝ ፈቃደኛ አላደረገውም። ይህም ከአባቱ ጋር ባደረገው ንግግር ውስጥ ተገልጧል።

አንተም በአባቱ ደስታ ለመደሰት አገልግሎቱ እንዳዘገየው ታላቅ ልጅ አትሁን! እርሱ ራሱንና መንፈሳዊነቱን እኩል ሊንከባከብ ሞክሯል። አንተ ግን የቀደሙ ተግባራትህን በምትችለው አቅምህ መጠን ለመቀበል ሞክር። ስለ መንፈሳዊነትህ ስትል በጥቂት ጉዳዮች ተጠመድ! ይህን ካደረግህ ብዙ ጉዳዮችን ማለትም መዝናናትን፣ ስብሰባዎችንና የበዙ ንግግሮችን በቀላሉ ልታቆማቸው እንደምትችል ታውቃለህ። ምንም እንኳ በሁሉም ጊዜ ውስጥ በሥራ የተወጠርህ ሰው ብትሆንም በማንኛውም ጊዜ ልብህን ወደ እግዚአብሔር ለማንሣት ሞክር። ቀድመው የሚመጡ ተግባሮችህና ጊዜዎችህ ሁሉ ልብህን ሙሉ ለሙሉ አይቆጣጠሩት። ምክንያቱም ይህን ሁሉ ጊዜ ሰብክነት መዳረግ ስለማያስፈልግህ ነው። ይህን ሳታደርግ ቀርተህ ጊዜህን ሁሉ ቀድመው ለመጡ ተግባራቶችህ የምትጠቀምባቸው ከሆነ ለእግዚአብሔር የምትሰጠው ጊዜ ወዴት ሊደርስ ነው?

እግዚአብሔር አምላክ እንኳንስ የሥራህ የሕይወትህ ባለቤት መሆኑን ልንነገርህ የሚያስፈልግ አይመስለንም። ስለሆነም እግዚአብሔር በአንተ ጊዜ ውስጥ ያለውን ድርሻ በማስመልከት ሁለት ጠቃሚ ነገሮችን ልናስታውስህ እንወዳለን። እነርሱም፦

1- ሰንበት የእግዚአብሔር ስለሆነ እርሱን ቀድሰው።

2- ከጊዜ አንጻር የመጀመሪያ ፍሬዎችህን ያስገኙልህ ትእዛዛትን አስታውሳቸው።

የእግዚአብሔርን ቀን (ሰንበትን) ለመጠበቅ ለተነገረው ትእዛዝ ታማኝ ሆነህ ለመገኘትህ እርግጠኛ ሁን። በዚህ እርግጠኛ ከሆንህ ሳምንቱን ሙሉ ከዝለት ይጠብቅህ ዘንድ ከመንፈሳዊ ጎተራህ እያወጣህ የምትመገበው መብል አታጣም። የመጀመሪያ ፍሬዎችህን አስመልክቶ ለወጣው ትእዛዝ ታማኝ ከሆንህ የቀንህን የመጀመሪያ ፍሬ ለእግዚአብሔር ትሰጣለህ። በዚህ ጊዜ የምታገኘው የመንፈስ መቃጠል ቀኑን ሙሉ ከአንተ ጋር ከመዋሉም በላይ ሌሎች ጊዜዎችህን ለመንፈሳዊ ተግባራት እንድታውል ያበረታታሃል።

3- ሌላም ትኩረትህን ለመሳብ የምንፈልግበት ነገር አለ። በዓለማዊ ጉዳዮች ተወጥረህ የምትውል ከሆነ እነዚህ ጉዳዮች ልብህን፣ አሳብህንና ሁለንተናህን ተቆጣጥረውት ይውሳሉ። ከዚህ በኋላ ለጸሎት ስትቆም ሕሊናህ በእነዚህ ጉዳዮች ስለሚሰረቅ ጸሎትህ አጥብቆ ጠያቂ ጸሎት አይሆንም። በተለያዩ ጉዳዮች መጠመድ የዝለት ምክንያት ነው ብለን ስንናገር የምንናገረው በጊዜ ሰለ

መወጠር ብቻ ሳይሆን ስለ አሳብ መወጠርና ስለ ልብ መወጠር ጭምር ነው። እንዲህ ዓይነቱ መወጠር በሰው ውስጥ ዘልቆ ስለሚገባ አደገኛነቱ የከፋ ይሆናል።

፩ በዚህ መሠረት በሌሎች ጉዳዮች መወጠራችንን እንድናቆም ቤተ ክርስቲያን በቀን ውስጥ ሰባት ጊዜ ለጸሎት የምንቆምበትን ሥርዓት አበጅታልናለች። በዚህም በቀን ውስጥ ካሉት ሰዓታት ከፊሉን ከእግዚአብሔር ጋር የምንገናኝበት ጊዜ ሆኗል ማለት ነው። ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እነዚህን ጸሎታት በቀን ወይም በ24 ሰዓት ውስጥ በየሦስት ሰዓቱ ልዩነት የቀመረችልን ሁላችንም በዓለም ውስጥ ስላለው ከንቱ ሕይወት ከማሰብ ተላቀን በእነዚህ ሰዓታት ውስጥ ልባችንን ወደ እግዚአብሔር እንድናነሣና ከእርሱ ጋር እንድንነጋገር ነው። ይህን በማድረጋችንም መንፈሳዊ መቃጠላችንን ጠብቀን እናቆያለን።

በዚህ መሠረት የዕለቱን ጸሎት በማከናወን ታማኝ ሆነህ ከተገኘህ ለብ ያልህ አትሆንም። ምክንያቱም ሕሊናህ ቀኑን ሙሉ ስለ እግዚአብሔር ከማሰብ ቸል የሚልበት ጊዜ ስለማይኖረው ነው።

የዝለት ምክንያቶች ከሆኑት መካከል ለረዥም ጊዜ ከእግዚአብሔር ርቆ መቆየት አንዱ ነው። ሰዎች ለዚህ ዝለት የሚጋለጡት ከጠዋትና ከማታ ጸሎታቸው በስተቀር ሌሎቹን ስለማይጸልዩ ነው። ሌሎቹ ጸሎታት የሚፈጸሙባቸው ሰዓታት በቀን ውስጥ በጣም የማይመቹና በሥራ ባተሌ የምንሆንባቸው ሰዓታት ከመሆናቸውም በላይ ጥቃትና ውጊያ የሚበዛባቸው ሰዓታት ናቸው።

ከዝለት ለማምለጥ ከፈለግህ በየጊዜው ልብህን ወደ እግዚአብሔር በማንሣት ለአንድ ደቂቃ ካልቻልህም ለጥቂት ሴኮንዶች በአንድ ዓረፍተ ነገር የተጠቃለለች አጭር ጸሎት አድርስ።

ክንስሓ መራቅ።

በዚህ ዙሪያ በመንፈስ የሚቃጠሉ ሰዎች ዓይነታቸው ሁለት ነው።

- የመጀመሪያው ሰው በቅርቡ ንስሓ የገባ ከመሆኑም በላይ ትሑትና ራሱን ያዋረደ ሰው ነው። እርሱ በኃጢአት ተምች የተበሉ ዕድሚያቹን ለማካካስ ስለሚፈልግ ዕንባዎቹ ዘወትር ለዐይኖቹ ቅርብ ሆነው ይታያሉ። እንዲህ ዓይነቱ ሰው ዘወትር በመንፈሱ የሚቃጠል ሰው ነው።

- ሁለተኛው ሰው የእግዚአብሔርን ፍቅር የታደሰ ሰው ነው። በመሆኑም ፍቅሩ ዘወትር በልቡ ውስጥ ስለሚንቀለቀል መንፈሳዊ መቃጠል በእርሱ ዘንድ አለ። ይህም በጸሎቱ፣ በአገልግሎቱና በሚያከናውናቸው መንፈሳዊ ተግባራት ውስጥ ተገልጦ ይታያል።

በመካከለኛ ደረጃ ላይ ያለ ሰው ግን ለብ ያለ ነው። እርሱ በምድረ በዳ የነበሩትን እስራኤላውያን ይመስላል። እነርሱ የእግዚአብሔርን ማዳንና ለእነርሱ ያደረጋቸው ተአምራቱን ለመመልከት ከባርነት ሀገር ለመውጣትም ሆነ ማርና ወተት ወደምታፈሰው ወደ ከነዓን ለመድረስ ወይም መና ለመብላት አልቻሉም።

መካከል ላይ ያለ ሰው የሚገጥመው ዕድል ፈንታም ከእነርሱ ጋር ተመሳሳይ ነው። እርሱ በንስሓው አልደመቀም በፍቅሩም አልተቃጠለም። እርሱ ዓይኖቹን አቅንቶ ወደ ሰማይ ሊመለከት እንደ ፈራው ቀራጭ (ሉቃ 18:13) ወይም በፍቅርና በቅርበት ወደ ጌታ ደረት ተጠግቶ እንደ ነበረው እንደ ዮሐንስ ፍቁረ እግዚእ በውስጡ የሚቃጠል መንፈስ የሌለው ሰው ነው። በአጠቃላይ እርሱ በመካከል ያለ ወይም የዛለ ሰው ነው።

ለኃጢአቶቹ የሚያለቅስባቸውን ቀናት ቢናፍቃቸውም ሊያገኛቸው አይችልም። ከዚህ በኋላ እምነቱን የሚፈጽመው መንፈስ ወይም ጥልቀት በሌለውና እንደ ነገሩ በሆነ አምልኮ ነው። ይጸልያል፣ ይጾማል፣ መጽሐፍ ቅዱስ ያነባል፣ መንፈሳዊ ጉባዔ ይካፈላል፣ ንስሓ ይገባል፣ ቅዱስ ቁርባን ይቀበላል ምናልባትም ሊያገለግል ይችላል። ይሁን እንጂ በእነዚህ ውስጥ የልቡን መዋረድ የሚያነሣሣ ነገር አያገኝም። ከመውደቅ የራቀ መስሎ ስለሚሰማው ሕሊናው አይገሥፀውም እንደማይገባ ሰው አድርጎም አይወቅሰውም። ቀስ በቀስም ዕንባውንና ለንስሓ መቃጠልን ያጣዋል። ይህ ይሁን እንጂ መንፈሳዊ ተግባራቱን ያለ ፍቅርና ጥልቀት ማከናወኑን አያቋርጥም። በመሆኑም እርሱ ሰማይን አያገኝም በምድርም ላይ አይቆይም . . . የዛለ ነውና።

እንዲህ ዓይነቱ ሰው ከፍተኛ መንፈሳዊነት ካላቸው ሰዎች ጋር የጠበቀ ግንኙነት በመፍጠር ወይም ስለ እነርሱ ከመጸሐፍት በማንበብ ከእነርሱ ጋር ሊመሳሰል ይገባዋል። በዚህ ጊዜ ስለ ራሱ ምንም ስለማይሰማው የንስሓና ራስን የማዋረድ ስሜት ወደ እርሱ ተመልሰው በመምጣት ወደተቀጣጠለ ንስሓ አነሳስተው ይመሩታል። ከዚሁ በመቀጠል ኃይል ወደሚሰጡትና መንፈሳዊ መቀጣጠሉን ወደሚመልሱለት መንፈሳዊ ተግባራት ይሸጋገራል። ወይም ደግሞ ድካሙ እንዲሰማውና በጥልቀት ልምምድ ማድረግ እንደተሣነው እንዲታወቀው ያደርጉታል። ከዚህ ሁሉ በኋላ በድጋሚ ወደ ንስሓ ሕይወት ይመለሳል። በዚህ ጊዜ ግን መንፈሳዊ ደረጃው ከፍ ይላል።

ስለሆነም በጸሎቱ፣ በጾሙና በሌሎቹም መንፈሳዊ ተግባራቱ ራሱን መንፈሳዊ ለማድረግ ያለማምዳል። ይህ ደግሞ ከተራ ልማድ በማውጣት ከእግዚአብሔር ጋር በጥልቀት ኅብረት እንዲፈጥር ያደርገዋል። እዚህ ደረጃ ላይ ሲደርስ እንደሚገባው እንደማይጸልይ፣ እንደማይጾምና እንደማያነብ ይታወቀዋል። በመሆኑም በተገቢው መንገድ ለመጸለይ፣ ለመጾምና ለማንበብ እንደ አዲስ መማር እንደሚገባው ጠንቅቆ ያውቃል። ከዚህ በኋላ በድጋሚ እውነተኛ የንስሓ ሕይወት ሊኖር ይጀምራል። ይህን የሚያደርገውም አሁን ለጀመረው ትክክለኛ አምልኮ ንስሓ መግባት ስለሚገባው ነው። ይህ ደግሞ በቀጥታ ወደ መንፈሳዊ መቃጠል ይመራዋል።

ንስሓው በተገቢው ወይም በጠንካራው መሠረት ላይ ካልተመሠረተ ግን ዝለት ይገጥመዋል። ስለሆነም በእውነተኛው መቃጠል ውስጥ ይኖር ዘንድ የንስሓውን መሠረት በሚገባ ሊያደራጅ ይገባዋል። ለንስሓ የሚደረገው መነሣሣት ጊዜያዊ ከሆነ የሰውየው ውድቀት በዝለት ይጠቃለላል። በመሆኑም ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ግንኙነት ሊመሠርት የሚገባው ለእርሱ ባለው ፍቅር መሠረት ላይ ነው። ከዚህ በተጨማሪ በመልካም ነገሮችና በመንፈሳዊ

ሕይወት አስፈላጊነት ማመን አለበት። ይህን የሚያደርግ ከሆነ ከዝሉት ያመልጣል።

ለንስሓ የሚደረገው የመጀመሪያው መነሳሻ በመንገድ ላይ ያለው ደረጃ ነው። ስለሆነም አንድ ንስሓ የሚገባ ሰው እዚህ ደረጃ ላይ ሲደርስ መቆም የለበትም። ይልቁንም መንፈሳዊ መነሣሣቱን በማስተካከል በመንፈሳዊ መቃጠሉ ይቀጥላል። ሌላው የዝሉት ምክንያት ያለ ምንም ዕድገት መደሰት ወይም መርካት ነው።

ደስታና ዕድገት አለማሳየት።

እንቅስቃሴ በመንፈስ መቃጠልን ስለሚገልጥ መንፈሳዊ ሰው ዕድገት ባሳየ ቁጥር በመንፈስ መቃጠሉን ጠብቆ ይጓዛል። ይሁን እንጂ አንድ ደረጃ ላይ ሲደርስ ይህን ጉዞውን ካቆመ ስለሚደርቅ ዝሉት ይይዘዋል። እንደዚህ ዓይነቱ ዝሉት ብዙዎችን ይጥጥማቸዋል። እንደነዚህ ዓይነቶቹ ሰዎች ደግሞ ከንስሓቸው በፊት ጸሎት የማይጸልዩ ሰዎች ናቸው። የጸሎትን ጣፋጭ ጣዕም ማጣጣም ሲጀምሩ ግን በልባቸው ውስጥ በመንፈሳዊ መቃጠል የሚሞላ ደስታ ያገኛሉ። እነዚህ ሰዎች ጸሎትን አስመልክቶ አንድ ደረጃ ላይ ሲደርሱ እዚያው ላይ የሚቆሙ ከሆነ ግን በጊዜ መንገድ ውስጥ በደመ ነፍስ መጓዝ ይጀምራሉ። እነዚህ ሰዎች መኪናን ያስታውሱናል። መኪና እስከ ተንቀሳቀሰ ድረስ መሞቁ አይቀርም። ለረዥም ጊዜ ከቆመ ግን ባትሪው ስለሚደክም ድጋሚ መሞላት አለበት። ይህን የሚመስለው ድርጊት የሌለው ሕይወት ደግሞ ወደ ዝሉት ይመራል። እነዚህ ሰዎች እንዲህ ያለውን ነገር የሚፈጽሙት ደግሞ በጸሎታቸው ውስጥ ብቻ ሳይሆን በመንፈሳዊ ጸማቸው፣ በንባባቸውና በአገልግሎታቸው ውስጥ ጭምር ነው።

እዚህ ላይ አስከ ሦስተኛው ሰማይ ድረስ የተነጠቀውን ቅዱስ ጳውሎስ ምሳሌ አድርገን ልንወስደው እንችላለን። ከዚህ ሁሉ በኋላ እርሱ የተናገረው እንዲህ በማለት ነው፦ «ወንድሞች ሆይ፤እኔ ገና እንዳልያዝሁ እቆጥራለሁ፤ነገር ግን አንድ ነገር አደርጋለሁ፤በኋላዬ ያለውን እየረሳሁ በፊቴም ወዳለው እየተዘረጋሁ በክርስቶስ ኢየሱስ ከፍ ከፍ ያለውን የእግዚአብሔርን መጥራት ዋጋ እንዳገኝ ምልክትን እፈጥናለሁ።» ፊል 3፡12-14። ቅዱስ ጳውሎስን የሚያህል ታላቅ ሐዋርያ ገና ምንም እንዳልያዝሁ እቆጥራለሁ ብሎ ለብዙ ጥረት የሚዘጋጅ መሆኑን ስትሰማ ምን ማድረግ እንዳለብህ ታስባለህ?

አጥብቆ ጥረት ማድረግ በማንኛውም ጊዜ ስለማያረካ የተፈለገው ደረጃ ላይ ብትደርስም እንኳ ልታቆመው አትችልም። ስለሆነም በዝሉት እንዳትወድቅ ጥረትህን ሳታቋርጥ መቀጠል አለብህ። ማቆም የሚመራህ ወደ ዝሉት ብቻ ሳይሆን ወደ ውድቀትም ነውና ይህ በጣም አደገኛ ነገር ነው። አብዛኛውን ጊዜ ጥረቱን በመካከል የሚያቆም ሰው ክፋቱ ማቆሙ ብቻ ሳይሆን ወደ ኋላ መጓዙ ነው።

መንፈሳዊ ሕይወት የማያቋርጥ እንቅስቃሴ፣ የማያቋርጥ የመንፈስ መቃጠልና የማያቋርጥ ዕድገት የሚገለጽበት ሕይወት ነው። ዋና ዓላማውም

ሙሉ እስኪሆኑ ድረስ ጥረት ማድረግ ነው። አንድ አማኝ ጥረት ማድረግ ያለበት በመንፈስና እንደ መንፈስ ለመኖር ብቻ ሳይሆን ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው መንፈስ ቅዱስ በሙላት እንዲኖርበት ነው። «መንፈስ ይሙላባችሁ . . .» ኤፌ 5፡18። ሰው በመንፈሱ ሙሉ ከሆነ በዝሉት ከመውደቅ ይድናል። ይሁን እንጂ በዚህ ዕድገትና ሙሉነት መካከል ሌላ የዝሉት ምክንያት እንዳለ ልንገነዘብ ያስፈልጋል። ይኸውም፦

የተመረጡ ቦታዎች አደገኛነት።

አንድ ሰው በመንፈሳዊ ሕይወቱ መጀመሪያ ላይ የሚኖረው በትሕትና፣ ራስን በማዋረድና በጸጋ ስለሚሆን እግዚአብሔር ሁልጊዜ ከእርሱ ጋር ነው። ይህን አስመልክቶ ነቢዩ ዳዊት እንዲህ ይላል፦ «እግዚአብሔር ልባቸው ለተሰበረ ቅርብ ነው . . .» መዝ 33፡18። በዚህ መሠረት ሰው በትሕትና፣ ራስን በማዋረድና በጸጋ እግዚአብሔር ውስጥ ስለሚኖር በመንፈሳዊ መቃጠል ውስጥ ይኖራል።

ይህ ይሁን እንጂ እንዲህ ዓይነቱ ሰው ዕድገት ሲያሳይ የተወሰኑ ኃላፊነቶች በእደራ ስለሚጣሉበት የተመረጠው ቦታ ላይ መቆናጠጥ ይጀምራል። የተመረጠው ቦታ በራሱ እደገኛ አይደሰም። ይሁን እንጂ በእርሱ ውስጥ ልብ ሲታበይ ወይም ከፍ ከፍ ሲል ይጀምራል። በዚህ ጊዜ አንድ ሰው ከጥንቃቄ፣ ከጥብቅነትና ከትሕትና በማፈንገጥ አንድ እርምጃ እንኳ ከተራመደ በዝሉት ይወድቃል።

ሰው ንስሓ በገባበት ሰሞን ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚገባው፦ «አቤቱ ጌታዬ ሆይ! እኔ ከዚህ ጥዑመ ዜማ ጋር ልጣጣም አልችልም፤እኔ የዚህ የቅዱሳን ጉባኤ ተሳታፊ ልሆን አልችልም፤በዚህ የተቀደሰ ቦታ ውስጥ ልገኝ አይገባኝም . . .» እያለ ነው። ቀጠል አድርጎም «እኔ ግን በምሕረትህ ብዛት ወደ ቤትህ እገባለሁ . . .» (መዝ 5፡7) ይላል። ከዚህ በኋላ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሲያስተምር፣ ሲያደራጅና ሊቆጣጠር ይጀምራል። ጥቂት ቆይቶም ልገባ አይገባኝም ወዳለው የእግዚአብሔር ቤት ሁሉን በመርሳት እንደ መሪ ሆኖ ይገባል። በዚህ ጊዜ ወደ ቤተ እግዚአብሔር የሚገባው ያለ ምንም ፍርሃት፣ ስግደትና በዓይኖቹ ውስጥ ጠብታ ዕንባ ሳይታይ ነው።

እርሱ ከዚህ በኋላ ወደ እግዚአብሔር ቤት የሚገባው ለእገሌ ወይም ለእገሊት ትእዛዝ ለመስጠት ወይም ለመገሰጽ ወይም በእንድ ጉዳይ ዙሪያ ለመወያየት ወይም አንድ የሆነ ሥራን ለመቆጣጠር ይሆናል። እርሱ ወደ ቤተ እግዚአብሔር የሚገባው በኃላፊነት የተሰጠውን አገልግሎት ወይም ሥራ ለመወጣት ብቻ ይሆናል። ይሁን እንጂ በዚህ ሁሉ መካከል እግዚአብሔርን ይረሳል በእርሱ ቤት ውስጥ መሆኑንም ሙሉ ለሙሉ ይዘነጋል። በመሆኑም አስቀድሞ «ዚህ የተቀደሰ ቦታ ውስጥ ልገኝ አይገባኝም . . .» በማለት የተናገረውን ቃል ሙሉ ለሙሉ ይረሳል። ምናልባት እንዲህ ዓይነቱ ሰው በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ የሚቆመው በዓል ለማክበር ሳይሆን ይችላል። ስለሆነም እርሱ በዚያ ሲገኝ ከዚህም ከዚያም ጋር ያወራል ከጓደኞቹም ጋር ይሳሳቃል። ከዚህ በተጨማሪ ለቆመበት ቦታ ምንም ክብር ሳይሰጥ ድምፁን ከፍ

በማድረግ የፈለገውን ሰው ይጣራል። በአጠቃላይ ቤተ ክርስቲያን በእርሱ ፊት መፈራቷን ታጣለች።

እንዲህ ያለው ያለ ፍርሃት የሚደረግ እንቅስቃሴ እያደገ ሲሄድ በጸሎታትና በምሥጢራት ላይ ሊገለጥ ይችላል። የቅዳሴው ጸሎት ለእርሱ እንደሚያውቀው ተራ ዜማ ይሆንበታል። ቃላቱን የሚያውቃቸውና ጥልቅ ትርጉማቸውንም የሚረዳቸው ይሆኑበታል። በመሆኑም ለእርሱ ከእግዚአብሔር ጋር የሚነጋገርባቸው ቃላት መስለው አይታዩትም። ታዲያ ከዚህ የሚበልጥ ምን ዓይነት ዝለት ሊገኝ ይችላል? ከሁሉ የሚያስደንቀው ደግሞ ይህ ሰው ለዝለቱ ምክንያት የሆነውን ነገር ለማደባበስ ሲፈልግ ፍርሃትን አውጥቶ የሚጥለውን ፍቅር እንደታደለ አድርጎ ለመናገር ይደፍራል። 1ኛ ዮሐ 4:18።

የዚህ መጨረሻውም ፍርሃትን፣ ትሕትናንና ራስን የማዋረድን ሕይወት ማጣት ስለሚሆን ሰውየው በዝለት ይወድቃል። ወንድሜ ሆይ! ራስህን የቤተ ክርስቲያን ዓምድ አድርገህ ላለመመልከት ለራስህ ዘብ ቁም። ራስህንም አስፈላጊ አድርገህ በመመልከት አንተ በዚያ ቦታ ላይ ከሌለህ ማንም አንተን ተክቶ ሊሠራ እንደማይችል አድርገህም አትቁጠር። የአገልግሎት ሁሉ ኃላፊ ሆኖ ከተመደበው ሰው ጋር በአጋጣሚ ብትጣላ አገልግሎቱን ጥለህ ልትሄድ እንደምትችል አድርገህ ለማስፈራራት አትሞክር። ይህን በማድረግህም የቤተ ክርስቲያንን መሠረት የምታናውጥ ሆነህ አይሰማህ። ከዚህ ሁሉ ጀርባ ራስን ጠቃሚ አድርጎ የመቁጠር ስሜት ከመኖሩም በላይ ለዝለትህ እውነተኛ ምክንያት የሆነው የተደበቀ ኩራት ይገለጣል።

በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር አምላክ አንተን ለተወሰኑ ጊዜያት ከአገልግሎት በማገድ ቤተ ክርስቲያን ያለ አንተ ቤተ ክርስቲያን ሆና እንደምትቀጥል ያሳይሃል። ይህን ስትመለከት ራስህን በማዋረድ ካለህበት የተሳሳተ መንገድ ትወጣለህ። ከዚህ በኋላ በመጀመሪያ በውስጥህ የነበረው መንፈሳዊ መቃጠል ወደ አንተ ተመልሶ ይመጣል።

በቀርሜሎስ ተራራ ላይ የነበረው ታላቁ ነቢይ ኤልያስ የበዓልንና የማምለኪያ ዐፀድ ነቢያትን በዚያ ድል ካደረገ በኋላና ሰማያት በእርሱ ጸሎት ተከፍተው ጠፍቶ የነበረው ዝናብ በድጋሚ መዝነብ ሲጀምር ከእግዚአብሔር ዘንድ አንዲህ የሚል ኋላ የሚነካ ቃል ሰምቷል፦ «. . . በመጣህበትም መንገድ በምድረ በዳ ወደ ደማስቆ ተመለስ . . . በፋንታህም ነቢይ ይሆን ዘንድ የአቤልሞሖላን ሰው የሣፋጥን ልጅ ኤልሳዕን ቅባው . . .» 1ኛ ነገ 19:15እና16። ከዚህ በኋላ ኤልሳዕ የነቢዩ ኤልያስ መንፈስ ሁለት እጥፍ ሆኖ ስለ ወረደበት ከእርሱ የበዙ ተአምራትን ሊያደርግ ችሏል። ምንም እንኳ ከዚህ በኋላ ነቢዩ ኤልያስ ከነ ሥጋው ወደ ሰማይ ቢወሰድም ምድር እንደ ቀድሞው ሆና መቀጠሏን አላቋረጠችም። ይሁን እንጂ ይህ ሁኔታ እግዚአብሔር በአሳት ሠረገሎችና በአሳት ፈረሶች ወደ ሰማይ የወሰደውንና በደብረ ታቦር ተራራ ላይ ከጌታ ጋር እንዲገለጥ የፈቀደለትን የታላቁን ነቢይ የኤልያስን ክብር አልቀነሰበትም።

እግዚአብሔር በሠገባው ውስጥ ብዙ ቀስቶች አሉት። እርሱ ከፈቀደም ከምድር ድንጋዮች መካከል ለአብርሃም ልጆች አድርጎ ማስነሳት ይቻለዋል። ማቴ

ማቴ 3:9። ስለሆነም እግዚአብሔር በአገልግሎት ውስጥ በታማኝነት ሲያስቀምጥህ፦ «አቤቱ ጌታዬ ሆይ! አንተን ካገለገሉህ ቅዱሳን ጋር አቆጠር ዘንድ እኔ ማነኝ? እኔ አፌ ኮልታፋ ምላሴም ጸያፍ የሆነብኝ ሰው ነኝ!» በማለት ተናገር። ዘጸ 4:10። እኔ ለአገልግሎት የማሰናክያ ድንጋይ ልሆን እችላለሁ። ኃላፊነቶቼንም ልዘነጋ እችላለሁ። በእርግጥ ከእኔ የሚበልጡ ብዙ አገልጋዮች አሉህ። ስለሆነም እኔን በወይን አርሻህ ውስጥ ልገኝ የማይገባኝ ባሪያህ አድርገህ ቅጠረኝ።

በተመረጡ ቦታዎች ላይ በዝለት እንዳትያዝ ይህን በመሰለ ትሑት መንፈስ ውስጥ ልትሆን ይገባሃል። ሰዎች የሚያወድሱህ ከሆነ ኃጢአቶችህንና ደካማ ጎኖችህን አስታውስ። የእግዚአብሔር ጸጋ ፈጽሞ እንዳይረሳህና በመንፈስ መቃጠልህ እንዳይቀዘቅዝ ውዳሴን አትቀበል። ይልቁንም ክብርን ሁሉ ለእግዚአብሔር በመስጠት ከሐዋርያው ከቅዱስ ጳውሎስ ጋር ሆነህ «. . . በእግዚአብሔር ጸጋ የሆንሁ እኔ ነኝ . . .» (1ኛ ቆሮ 15:10) በል።

በተመረጡ ቦታዎች ላይ የበላይ ሆነህ ከተመረጥህ የሚከተሉትን መመሪያዎች ከፊት ለፊትህ አስቀምጥ፦

- ከአማኝነት ወደ ሲቅነት እንዳትቀየር ተጠንቀቅ!

- ከንቱ መጻሕፍትን በማንበብ፣ ተራ እውቀትን በመፈለግና የእውቀት ምንጭ ለመሆን በምታደርገው ጥረት በጊዜው ማዕበል ተጠርገህ እንዳትወሰድ ተጠንቀቅ! እውቀታዊ ጉዳዮችን በመከታተል የመንፈስን ጉዳይ ልትዘነጋ እንደምትችል እወቅ! ተራ መጻሕፍትን በማንበብ ስሜትህ ሲማረክም ራስህንና ዘላለማዊነትህን ትዘነጋለህ።

- በሰዎች ጭቅጭቅ መካከል ስትገባ ብዛት ባላቸው የክርክር ጉዳዮች ውስጥ ስለምትወድቅ ለሌሎች ሰዎች ያለህን ፍቅር ታጣለህ። ስለዚህ በንትርክ አትማረክ! ይህን የምታደርግ ከሆንህ ግን አሳብህ ሁሉ ክርክሩን በመርታት ሌሎችን ለማሸነፍ የቆመ ሆኖ ይቀራል። ምናልባትም ከሌሎች ጋር ስትከራከር ራስህን ከፍ አድርገህ የምታስቀምጥ ስለምትሆን አነርሱን ትጫናቸዋለህ፣ ትጎዳቸዋለህ ወይም ታኮስሳቸዋለህ። ወይም ደግሞ በምትናገረው ነገር ላይ ሁሉ በራስህ ትተማመናለህ። በራስህ አሳብ ስለምትደገፍም ውጤት ለማምጣት ፈቃደኛ አትሆንም።

አንተ ያቀረብኸውን አሳብ የሚቃወም ማንኛውም ዓይነት አመለካከት ቢኖር እንኳ ውድቅ አታድርገው። በዚህ ሳቢያ የሚነሣውን ክርክርም ሙሉ ለሙሉ አታጣጥለው። መልስ ስትሰጥም በኩራትና በትዕቢት አይሁን። እንዲህ ያለው ክርክር በዶግማ ዙሪያ ሲመጣ በመንፈሳዊ ዝለት እንድትወድቅ ያደርግሃል። በመጨረሻ ክርክሩን በማስረዳ ልታሸንፍ ብትችልም እንኳ መንፈሳዊ አንተነትህን ልታጣው ትችላለህ። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ክርክሩንም ሆነ መንፈሳዊነትህን ታጣለህ።

ብዙ ሰዎች የእውቀት ጎተራዎች ሲሆኑ ቢችሉም መንፈሳዊ ማዕዳቸው ግን ባዶ ነው። ስፉ እውቀት ይዘህ ጥቂት ተግባራዊ ሕይወት ከሚኖርህ ይልቅ

ጥቂት እውቀት ኖሮህ ሰፊ ተግባራዊ ሕይወት ቢኖርህ ይሻላል። በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስ ስታነብ የተወሰኑ ምዕራፎችን ያለ ጥልቅ መረዳት፣ ተመስጠ፣ ተግባራዊ ልምምድና ያለ ጸሎት ለማንበብ ከሞከርህ ምንም ዓይነት መንፈሳዊ ጥቅም አታገኝም። ብዙ ብታነብም እንኳ ሕይወትህ የዛለ ከመሆን አያመልጥም። ስለሆነም ዋናውና አስፈላጊው ቁም ነገር ያለው ብዙ ማንበባችን ላይ ሳይሆን ንባባችንን መንፈሳዊና ጥልቅ ማድረጋችን ላይ ነው።

ስለዚህ ለአስተዳደራዊ ወይም ለሳይንሳዊ ወይም ደግሞ ለአመራራዊ ሥራ ካልሆነ በስተቀር የተመረጡ ቦታዎችን ለመያዝ ወይም ለማግኘት አትፈልግ። ምንጊዜም ቢሆን ራስህን ታናሽ አድርግ እንጂ ስለ ሁሉም ነገር ለማወቅ አትጓጓ። አንተ የማታውቃቸው አንዳንድ ጉዳዮች እንዳሉ በግልጽ መናገርህ ምንም ዓይነት ስህተት እንደሌለበት እወቅ!

ሌላው የዝለት ምክንያት በሕይወትህ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ናቸው።

በሕይወትህ ውስጥ ያሉ ሌሎች ሰዎች።

ከእግዚአብሔር ይልቅ ሰዎችን የመንፈሳዊ ሕይወትህ ዓላማ አድርገህ መከተልህ አደገኛ ነገር ነው።

ገና ክርስትናን ስትጀምረው በመንፈሳዊ ሕይወትህ ፊት የምታስቀምጠው ዘላለማዊነትህንና ለእግዚአብሔር ፍቅር ያለህን መነሣሣት ነው። ዕድገት እያሳየህ ስትመጣ ግን ሌሎች ወደ አንተ ሕይወት በመግባት የዓላማዎችህ አንድ ክፍል ይሆናሉ።

በመንፈሳዊው መንገድህ ውስጥ ዋናውና ተቀዳሚው ዓላማህ ሊሆን የሚገባው ለሌሎች ሰዎች ምሳሌ መሆንህና ጥቃትን ከአንተ ማስወገድህ ነው። በዚህ ጉዳይ ውስጥ መልካም የምታደርገው ለመልካም ነገር ወይም ለእግዚአብሔር ፍቅር ስላለህ ሳይሆን ለሰዎች ምሳሌ ለመሆን ወይም የመንፈሳዊ ሕይወት ምሳሌ ለመሆን ወይም በጨለማ ውስጥ ለሚጓዙት ብርሃን ለመሆን ብቻ ነው።

ለተመሳሳይ ምክንያት ስትል ያለ ምንም ጥላቻ ወይም ኃጢአት ለሌሎች የማሰናከያ ድንጋይ እንዳትሆን ለአነርሱ ማብራትህን ልታቋርጥ ትችላለህ። በዚህ ጊዜ ማንንም የማጠቃበት መንገድ አይደለም በሚል መንፈስ ኃጢአትን በምሥጢር የምትቃወምበትን መንገድ ችላ ልትለው ትጀምራለህ። ይህን በምታደርግበት ጊዜ መንፈሳዊ መነሣሣትህ የሚመጣው ከውስጥህ ሳይሆን ከውጪ ስለሚሆን ትዝላለህ። በዚህ ጊዜ ሁለት ዓይነት ተፈጥሮ ይኖርሃል። የመጀመሪያው ከሰዎች ራስህን ትጠብቅ ዘንድ ለራስህ ዘብ እንድትቆም ሲያሳስብህ ሁለተኛው ደግሞ እነርሱ እስካላዩህ ድረስ ብታደርገው ችግር የለውም በማለት ቸልተኛ የሚያደርግህ ይሆናል።

የተናገርኸውን ወይም ያደረግኸውን ሰዎች እንዴት እንደሚመለከቱት ወይም እንደሚፈርዱበት ለማወቅ ትታወካለህ። በዚህም ምክንያት እነርሱን

ለማስደሰት ስትል የምትችለውን ነገር ሁሉ ስለምታደርግ ቀስ በቀስ የአንተ ጉዳይ ስለ ሰዎች ብቻ ይሆናል። እዚህ ላይ መንፈሳዊ ዓላማህ ስለሚጠፋ ሕይወትህ በዝለት የተሞላ ይሆናል። በማኅበር ጸሎት ላይ የምትጸልየው የሚያስደስቱህን የሰዎች አስተያየት በመከተል ስለሚሆን ጸሎትህ ስለ ሰዎች እንጂ ስለ እግዚአብሔር ተብሎ አይቀርብም።

በጸሎት ላይ እያለህ ዕንባህ የሚመጣው ለእግዚአብሔር ካለህ ፍቅር አንጻር ሳይሆን ሰዎች በጸሎት ውስጥ ያለህን መንፈሳዊነት እንዲያወድሱልህ ወይም በራስህ ስለምትደሰት ነው። በዚህ ሁሉ መካከል ታዲያ እግዚአብሔር በአንተ ሕይወት ውስጥ ሐልውና አይኖረውም። ሰውን ሁሉ ማስደሰት እንደማይቻል በማስመልከት አንዲት ቅድስት እናት «እያንዳንዱን ሰው ለማስደሰት ከፈለግሁ የአያንዳንዱን ሰው መዝጊያ በመቆርቆር መንገዴ ሊጠፋብኝ ይችላል።» በማለት የተናገረችው ቃል እውነት ነው። ለሰዎች ትክክለኛነትን በስፋት ማስብና እኛም እነርሱን ለማስደሰት ስንል ከትክክለኛው ነገር ማፈንገጣችን ምንኛ ቀላል ነው?

ለሰዎች በምታቀርበው የበዛ ሰላምታ ሕይወትህ በዝለት ሊያዝ ይችላል። ስለ እነርሱ ስትል የበዛ ጊዜህን ያለ ምንም ጥቅም ታሳልፋለህ፤ስለ እነርሱ ስትል ችግር በሚፈጥሩ ወሬዎችና ውይይቶች ውስጥ ተሳታፊ ትሆናለህ፤ስለ እነርሱ ስትል ከጸሎትና ከተመስጦ ጊዜህ ትዘገያለህ። ይህን አስመልክቶ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የተናገረው ጥልቅ ቃል ከልብህ ሆነህ አንብበው፦ «. . . ሰውን ደስ ላሰኝ እፈልጋለሁን? አሁን ሰውን ደስ ባሰኝ የክርስቶስ ባሪያ ባልሆንሁም።» ገላ 1:10።

በዚህ መሠረት ከሰዎች ጋር የሚኖሩህ ግንኙነቶች በመንፈስ ሰብ ያልህ እንድትሆን እንዳያደርጉህ ከመንፈሳዊው ድንበር አታሳልፋቸው።

መንፈሳዊ ተግባራትንና በየሰዓቱ የሚደረጉ ጸሎቶችን መዘንጋት።

በአንድ ሰው መንፈሳዊ ሕይወት ውስጥ በስፋት ከተጠቀሱት ዝለቶች ሌላ መንፈሳዊ ተግባራትንና በየሰዓቱ የሚደረጉ ጸሎታትን መዘንጋት ተጨማሪው የዝለት ዓይነት ነው። እነዚህ ተግባራት ሰው እግዚአብሔርን እንዲያስብ ያስታውሱታል። ከዚህ በተጨማሪ ለመንፈሳዊ ሥራዎች ያነሳሱታል ልቡንም ያበረቱለታል። ይሁን እንጂ ሰው እነዚህን ተግባራት ከዘነጋ ደካማና ልፍልፍስ ይሆናል።

መንፈሳዊ ተግባራት የምንላቸውም ጸሎት፣ ንባብ፣ ተመስጦ፣ ጾም፣ ንስሓ፣ ቅዱስ ቁርባን፣ መንፈሳዊ ስብሰባዎች፣ አገልግሎትን አለማቋረጥና በቤተ ክርስቲያን ዘወትር መገኘት ናቸው። እነዚህ ሁሉ ታዲያ መንፈሳዊ በሆነ መንገድ መፈጸም አለባቸው። እዚህ ላይ ግን አንድ ሰው «እነዚህን ተግባራት ብፈጽምም ሰብ ያልሁ ሰው ነኝ። ለዚህ ምክንያቱ ምንድር ነው? መፍትሔውስ?» በማለት ሊጠይቅ ይችላል። ለዚህ መልስ የሚሆኑን የሚከተሉት ነጥቦች ናቸው . . .

1- ልትፈጽማቸው የሚገቡህን በመረዳት፣ በትኩረት፣ በስሜትና በንቁ መንፈስ መሆኑ ቀርቶ በልማድ ወይም በተሳሳተ መንገድ ከፈጸምካቸው የዝለት ችግር ይገጥምሃል።

2- ወይም ደግሞ ውጪያዊ ውጊያን በማለፍ ላይ ትሆናለህ። በዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ከሆንህ እግዚአብሔር ከዚህ ውጊያ እስኪያወጣህ ወይም እንድታሸንፈው እስኪረዳህ ድረስ በትዕግሥት ልትጠብቀው ይገባሃል። ከዚሁ ጎን ለጎን መንፈሳዊ ሥራዎችን ሳታቋርጥ ልታከናውን ይገባሃል።

3- መንፈሳዊ ተግባራትን ከመፈጸም አኳያ በዝለት ውድቀት መጣ ማለት ግን እነዚህን ተግባራት መፈጸምህን አቁም ማለት አይደለም። ይህን የምታደርግ ከሆነ ግን ራስህን በማሻሻል ፋንታ ሰበሰጠ ውድቀት የተጋለጥህ ትሆናለህ።

በተመደቡላቸው ሰዓታት የሚቀርቡት ጸሎታት መንፈሳዊ ተግባራትን ለመፈጸም ሁነኛ ዘዴዎች ናቸው። ሰው እነዚህን ጸሎታት ጠብቆ የሚጸልይ ከሆነ ሕሊናው ሰዓታቱ ሲደርሱ በጸሎቱ ውስጥ ያሉትን ቃላት ስለሚያስታውስ ይነግሣል። የጸሎቱ ሰዓት ሲደርስ ወዲያውኑ የማይነቃቃ ከሆነም ጥቂት ቆይቶ ይነቃቃል።

ለምሳሌ፦ በየሰዓቱ የምንጸልያቸው ጸሎታት ስለ ሞት፣ ስለ እርግማንና ስለ ዘላለማዊነት ያሳስቡናል። ከዚህ በተጨማሪ ኃጢአተኛነታችንንና ቸልተኛ ነታችንን በማስታወስ ንስሓ እንድንገባና ይቅርታ እንድንጠይቅ ይጠሩናል። ከዚህ ሌላ ቀኑን በመልካም ሁኔታ እንድንጀምርና በቀኑ ውስጥ በመንፈስ እንድንራመድ ያስታውሱናል። ሌሎቹም ጸሎታት መንፈሳዊ ውጤት አላቸው። በመሆኑም ሰው በሚጸልይበት ጊዜ ለጸሎቱ ትኩረት የሚሰጥ ከሆነ በእርግጥም ሕሊናው ይነቃቃል። ምንም ዓይነት ውጤት ካልመጣም በቆይታ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ይመጣል። ሰው በጸሎቱ ውስጥ እንዲህ ብሎ ሊጸልይ ይችላል፦ «ከማለዳው ሰዓት ጀምሮ እስከ ሌሊት ነፍሴ በእግዚአብሔር ታመነች።» መዝ 129፡6። ወደሚቀጥለው የዝለት ምክንያት እንሸጋገራለን።

መንፈሳዊ ሂደትን እንደ ተራ ተግባር ማሰብ።

አንዳንድ ሰዎች መንፈሳዊ ሕይወትን የሚመለከቱት እንደ ቀላል ጸሎት፣ ጾም፣ ንስሓ፣ ቁርባን፣ ጉባኤና አገልግሎት ነው። በመሆኑም ለሚፈጽሟቸው መንፈሳዊ ተግባራት ዕቅድ ለማውጣት የሚሞክሩት ለእነርሱ ሕሊና በሚመች መንገድ ብቻ ነው። ይሁን እንጂ እነዚህ ሰዎች በዝለት ይወድቃሉ። የዚህ ምክንያቱ ምንድር ነው?

የዚህ ምክንያት እነዚህ ሰዎች የልብ ንጽሕናን በመዘንጋት ራሳቸውን በእነዚህ ተግባራት መወሰናቸው ነው። የልብ ንጽሕና ደግሞ ለመንፈሳዊ ተግባራት ትክክለኛ መሠረት ስለሆነ ሰውየው በዝለት ይወድቃል። የመንፈስ ፍሬዎች ከውስጥ የማይገለጡባቸው ተራ መንፈሳዊ ተግባራት ልክ እንደ ፈሪሳዊው በግብዝነት የሚያስታብዩ ይሆናሉ። ፈሪሳውያን ልባቸው ከእውነተኛ

መንፈሳዊ ተግባር የራቀ ሆኖ ሳለ አብዝተው የሚጨነቁት በውጪ ስላሰው ተራ ድርጊት ነው። እነርሱን ሊመለከቷቸው በውጪ ኖራ የተቀባ መቃብርን ይመስላሉ።

ስለሆነም አንተ ጉዳይህ በውስጣዊ ሥራዎችህ ላይ የሚያተኩር ይሁን። እነዚህ ታላላቅ የቅድስና ሥራዎችም ፍቅር፣ እምነት፣ ትሕትና፣ የዋህነት፣ ንጽሕና . . . ወዘተ ናቸው። በዚህ ጊዜ ጸሎትህ ከንጹሕ ልብህ ውስጥ ለእግዚአብሔር ፍቅርና ለቅድስና የሚወጣ መንፈሳዊ ነበልባል ይሆናል።

አንድ ሰው በእርሱና በሌላ አንድ ሰው መካከል ከፍተኛ ጠብና ሙግት እያለ ጸሎት ሊያደርስ ይቆማል። ይህ ጸጸት የሚያስፈልገው ጉዳይ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ልቡ በቁጣ፣ በንዴት፣ በኩራት . . . ወዘተ ተሞልቶ ይጸልያል፣ ያነባል፣ ይሰብካል፣ ያስተምራልም። ታዲያ ልቡ ከመንፈስ ቅዱስ ተራቁቶ ጸሎቱ በመንፈስ ሊቃጠል የሚችለው እንዴት ነው? ልቡ በቁጣ፣ በክፋትና በጠብ ምክንያት ከእግዚአብሔር ርቆ እንዴት ከእርሱ ጋር በጸሎት ሊገናኝ ይችላል?

ስለሆነም ዝለትን ከአንተ ለማራቅ ከፈለግህ መንፈሳዊ ተግባሮችህን በውስጥህ ባሉ የመንፈስ ፍሬዎች (ገላ 5:22) ላይ ለመመሥረትህ እርግጠኛ ሁን። በምትፈጽማቸው ድርጊቶችህ ውስጥ ሁሉ እግዚአብሔር «ልጄ ሆይ ልብህን ስጠኝ . . .» (ምሳ 23:26) እያለ ያሳስብሃል። አይሁድንም እንዲህ እያለ ይገሥጻቸዋል፦ «እጃችሁንም ወደ እኔ ብትዘረጉ ዓይኔን ከእናንተ እሰውራለሁ፤ ልመናንም ብታበዙ አልሰማችሁም፤ እጆችሁ ደም ተሞልተዋልና ።» ኢሳ 1:15።

ይህ ደግሞ ወደሚቀጥለው ነጥብ ይመራናል።

በሰው ሕይወት ውስጥ ያለው ኃጢአት ወይስ ምኞት?

አንድ ሰው በመንፈሳዊው መንገድ ውስጥ እንደሚገባው ሆኖ መጓዝ ይችላል። በዚህም ጉዞውን ጥቂት ሊገፋ ይችላል። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን የሆነ አንድ ምኞት ወይም ፍቅር ልቡንና ስሜቱን ሙሉ ለሙሉ በመቆጣጠር በልቡ ውስጥ ለእግዚአብሔር ያለውን ቦታና ለእርሱ ያለውን ፍቅር ያሳጣዋል። በዚህ ጊዜ ይህ ሰው በዝለት ይወድቃል። ሰውየው የመጀመሪያ ፍቅሩን ሲተው መንፈሳዊ መቃጠል ስለሚረሳው በዝለት ይወድቃል።

ስለሆነም እግዚአብሔርን ከልብህ ውስጥ ቦታ ያሳጣው እንግዳ ነገር ምን እንደሆነ ለማወቅ ትጋ። ኃጢአት ወደ ውስጥህ እየዳኸ የገባው በግልጽ ነው ወይስ ተሰውሮ? ወደ አንተ የመጣውስ የበግ ለምድ ለብሶ ነው ወይስ በቅድስና ስም ሊያታልልህ በመፈለግ ነው? ኃጢአት ካልታወቀበት በቅንዓት፣ እውነትን በማስጠበቅና ለተሐድሶ ፍቅር በሚል ሰበብ አሞበርብሮ ወደ ሰው ይዘልቃል።

አንድ ሰው በጥላቻ መንፈስ ከሌሎች ሰዎች ጋር ሊጋጭ ይችላል። ይህን የሚያደርገውም እውነትን ለማስጠበቅ በሚለው ሰበብ እነርሱን ያለ ምንም ፍቅር፣ ምሕረትና መረዳት በመቆጣትና በመገሠጽ ነው። ተሐድሶን ማምጣት በሚል ሰበብም ሰዎችን ይተቻል፣ ይወቅሳል ይሰድባልም። ክፉ ሰው ስለሚሆንም ልክ እንደ እሳት ያገኘውን ነገር ሁሉ ያነዳል። ከዚህ በኋላ ዐይኖቹ በሰዎች ላይ ከስህተት በስተቀር ሌላ ምንም ዓይነት መልካም ነገር የማይመለከቱ ይሆናሉ። ሰውን ሁሉ ይጠረጥራሉ በሐሰትም ይወነጅላሉ።

ከእነዚህ ሰዎች ጋር የሚመደበው ሰው እርሱ ራሱ እንክርዳድ ሆኖ ሳለ ራሱን እንክርዳዱን እንደሚለቅም የሚያስመስል ሰው ነው። እርሱ መንፈሳዊነቱን ለማግኘት ቢሞክርም ሕይወቱ በዝለት ስለ ወደቀ ሊያገኘው አይችልም። «በራድ ወይም ትኩስ ስላልሆንህ ከአፌ ልተፋህ ነው።» (ራእ 3:16) የሚለው የጌታ ቃል በእርሱ ላይ ተግባራዊ ይሆናል። ይህን ማለት ግን ሰው ተሐድሶ ማካሄድን፣ ቅንዓት ማሳየትንና እውነትን ማስከበርን ሊያስፈጽም አያስፈልገውም ማለት አይደለም። ይሁን እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ «በእናንተ ዘንድ ሁሉ በፍቅር ይሁን።» (1ኛ ቆሮ 16:14) ብሎ እንደ ተናገረ ሰው ሁሉ እንደዚህ ዓይነቱን ነገር በመንፈሳዊ መንገድ በመረዳትና በጥበብ ሊያከናውን ይገባዋል።

ከዚህ በተጨማሪ መጽሐፍ ቅዱስ ይህን አስመልክቶ እንዲህ ይላል፦ «ከእናንተ ጥበበኛና አስተዋይ ማን ነው? በመልካም አነዋወሩ ሥራውን በጥበብ የዋህነት ያሳይ። ነገር ግን መራራ ቅንዓትና አድመኝነት በልባችሁ ቢኖርባችሁ አትመኩ፤ በእውነትም ላይ አትዋሹ። ይህ ጥበብ ከላይ የሚወርድ አይደለምና . . .» ያዕ 3:13-15። በመንፈስ መታደስ ማለት ይህ ነው። ይህ መታደስ የሚመጣው በፍቅርና በየዋህነት ጥበብ ነው። እንዲህ ባለ መንገድ በሚመጣው ቅንዓት ሰው ቢቀና በመንፈሱ ልፍስፍስ ሊሆን አይችልም።

ተሐድሶን በማስመልከት ሐዋርያው የተናገረው ቃል ምንኛ ድንቅ ነው! «ወንድሞች ሆይ፤ ሰው በማናቸውም በደል ስንኳ ቢገኝ መንፈሳውያን የሆናችሁ እናንተ እንደዚህ ያለውን ሰው በየውሃት መንፈስ አቅኑት፤ አንተ ደግሞ እንዳትፈተን ራስህን ጠብቅ። ከእናንተ እያንዳንዱ የአንዱን ሸክም ይሸክም . . .» ገላ 6:1-2።

ብዙዎች ንስሓቸውን የሚጀምሩት በመንፈሳዊ መቃጠል ስለሚሆን ሰዎች እነርሱን በማድነቅ ለአገልግሎት ይመርጧቸዋል። ወደ አገልግሎት ሲገቡ ለእግዚአብሔር ቅንዓት ቢኖራቸውም ቅንዓታቸው በመንፈስ እንጂ በእውቀት እንዲሆን አያስፈልግም። ሮሜ 10:2። በእውቀት የሚሆን ቅንዓት መንፈሳዊ መቃጠልን ስለሚያጠፋ እነዚህ ሰዎች በዝለት ይያዛሉ።

በእርግጥ ሰው ትኩረቱን ሁሉ ሰዎችን በማቅናት ላይ ቢያደርግ ብዙ ሰዎችን ሊጎዳ ይችላል። ሌሎች ሰዎችን ማቅናት ወይም ማረም የሚወድ ሰው ሁልጊዜ የሚያስበው ስለ እነርሱ ኃጢአት እንጂ የራሱ ኃጢአት እስከነጭራሹ ትዝ አይለውም። በዚህም ምክንያት ቸልተኛ ይሆናል። አስቀድሞ ንስሓ ሲገባ ያስብ የነበረው ስለ መንፈሳዊነቱና ስለ ድኅነቱ ነበር። ወደ አገልግሎት ሲገባ ግን ራሱን ሙሉ ለሙሉ ስለረሳ ትኩረቱ ሁሉ በሌሎች መዳን ወይም

በኃጢአታቸው ወይም ማኅበረሰቡን በማቅናት ላይ ይሆናል። ይህን የሚያከናውነውም ፍቅር በጎደለው በተሸሸገ ውስጣዊ ኩራት ውስጥ ራሱን አስቀምጦ ነው።

እንደዚህ ዓይነቱ ሰው ስለ ዝለት ምክንያቶች ሊጠይቅ ይችላልን? አይችልም። ቢጠይቅም እንኳ እንዲህ ያለው ነገር ዐመሉ ነው ከማለት ውጪ ሌላ የምንሰጠው መልስ ሊኖረን አይችልም። ከዚህ ይልቅ የራሱን ድኅነት በትሕትና ውስጥ ሆኖ በመፈለግ ቢኖር ለእርሱ የተሻለ ይሆናል። ወንድሜ ሆይ! አንተ ሰዎችን በመንፈስ እንዲዝሉ ያደርጓቸውን ምክንያቶች ለማቅናት ከመነሳትህ በፊት ራስህን ልታቀና የሚገባህ ሰው መሆንህን ልታውቅ ይገባሃል። አንተ ሌሎችን ስለ ቅንዓት በሚል ሰበብ በማረም ላይ እንዳለህ ለአንተ ዝለትና ስህተትህ ምክንያት ከሆኑት ምክንያቶች መካከል አንዱን ዝግ ብለን በጆሮህ ብንነግርህ ምን ልትናገር እንደምትችል አናውቅም!

ምናልባት አንተ የማታውቀው ጭካኔ በውስጥህ ሊኖር ይችላል። በመሆኑም ከእግዚአብሔር ጋር መኖር ስትጀምር ይህ ጭካኔ ቀስ በቀስ በውስጥህ ከተነሣሣ በኋላ በቅንዓትህና በእግዚአብሔር ስም በሚደረግ ማቅናትህ ውስጥ ሊገለጥ ይጀምራል። እዚህ ላይ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በመንፈስ ለወለደው ልጁ ለጢሞቴዎስ «. . . ዝለፍና ገሥጽ ምከርም . . .» (2ኛ ጢሞ 4:2) በማለት የተናገረውን ቃል በማስተዋል ልትመለከቱት ያስፈልጋል። እንዲህ ያለውን ነገር ቅዱስ ጳውሎስ ምን ያህል ጊዜ እንዳደረገውም አስቡ!

በአንድ ወቅት በኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይኖሩ የነበሩትን ቀሳውስት በሚሊጢን በኩል ካስጠራቸው በኋላ እንዲህ ነበር ያላቸው፦ «. . . ሦስት ዓመት ሌሊትና ቀን በዕንባ እያንዳንዳችሁን ከመገሠጽ እንዳላቋረጥሁ እያሰባችሁ ትጉ።» ሐዋ 20:31። ቅዱስ ጳውሎስ ሕዝቡን ከመገሠጽ ቸልተኛ ያልሆነው በዚህ ምክንያት ነው። አስቀድሞ ከዕንባ ጋር አስጠንቅቋቸው ነበር። በእነዚህ ዕንባዎች ውስጥ ደግሞ ፍቅርና ርኅራኄ ነበሩ።

ጭካኔ ለዝለት ምክንያት እንደ ሆነ ሁሉ ሌሎችን መኮነንም ሌላው የዝለት ምክንያት ነው። በሁለቱም ምክንያቶች ጸጋ እግዚአብሔር ከሰዎች ይርቃል። የእግዚአብሔር ጸጋ ሰውን ከተወው ደግሞ በዝለት በቀላሉ ይወድቃል።

መንፈሳዊ መቃጠል በሰው ውስጥ ያለ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ እንጂ ተራ የሰው ተግባር አይደለም። በመሆኑም ሰው በጭካኔውና በክፉ ሥራዎቹ ምክንያት ከመንፈስ ቅዱስ ሥራ ከራቀ በዝለት ይጠቃል። ከዚሁ ጋር ተመሳሳይ የሆነው ነጥብ የሚከተለው ነው።

ኩራት።

የኩራት ዓይነቱ ብዙ ነው። ይህን ለመጀመር ከመጽሐፍ ቅዱስ ቃል እንነሣለን። «ትዕቢት ጥፋትን፤ ኩሩ መንፈስም ውድቀትን ይቀድማል።» ምሳ 16:18። ኩራት ወደ ጥፋትና ውድቀት የሚመራ ከሆነ ወደ ዝሰት መምራቱ አጠያያቂ ሊሆን አይችልም።

• ለኩራት ምሳሌ ሊሆነን የሚችለው ሰው ዓላማዬን ፈጽሜያለሁ ብሎ በሚያስብበት ጊዜ የሚገጥመው ቸልተኝነት ነው። ለምሳሌ፡- አንድ ሰው ወደሚሄድበት ቦታ ለመድረስ ጉጉት ስላደረበት ባቡር ላይ ይሳፈራል። ወደሚፈልገው ቦታ ሲደርስ ወይም እንደደረሰ ሲታወቀው አስቀድሞ የነበረው ጉጉት ከውስጡ ይጠፋል።

ሌሎች ደግሞ እንዲሠሩ የታዘዙትን ሁሉ በፈጸሙ ጊዜ ራሳቸውን ዝቅ አድርገው «. . . የማንጠቅም ባሪያዎች ነን» ይላሉ። እንደነዚህ ዓይነቶቹ ሰዎች መሄድ ወደሚፈልጉበት ቦታ ለመድረስ ስለሚጓጉ አይዝሉም። ከእነርሱ መካከል አንዱ የፍጽምና ደረጃ ላይ ሊደርስም እንኳ እንዲህ ይላል፡- «አሁን እንዳገኘሁ ወይም አሁን እንደ ተፈጸምሁ ላይደለም፤ ነገር ግን ስለዚያ በክርስቶስ ኢየሱስ ደግሞ የተያዝሁ ያን ደግሞ እይዛለሁ ብዬ አፈጥናለሁ። ወንድሞች ሆይ እኔ ገና እንዳልያዝሁ እቆጥራለሁ . . . ኋኋላዬ ያለውን እየረሳሁ በፊቴም ወዳለው እየተዘረጋሁ . . .» ፊል 3:12-13።

እንደዚህ ያለው ታላቅ ጥረት ዝለትን የሚያጠፋ ነበልባል ነው። ታላቅ ጥረት የሚያደርግ ሰው የተፈለገው ደረጃ ላይ ቢደርስም እንኳ ወደፊት በተዘረጋ ቁጥር የሚያስታውሰው በዝለት የተሞላ የቀደመ ሕይወቱን ስለሆነ ይህ በራሱ የበለጠ ጥረት ለማድረግ ያነሣሣዋል። በመንፈስ መቃጠሉም የዚህኑ ያህል እየጨመረ ይሄዳል።

• ሌላው የኩራት ዓይነት ሰለባ በዙሪያው ያሉት ሰዎች ታናናሾች ሆነው እርሱ ታላቅ እንደሆነ አድርጎ በማሰብ እንደ ታላቅነቱ እንዲመለከቱት፣ እንዲያከብሩት፣ እንዲታዘዙትና እርሱ የሚላቸውን እንዲፈጽሙለት የሚፈልገው ሰው ነው። እንዲህ ዓይነቱ ሰው ንስሓ በገባበት ሰሞን ራሱን ያዋረደና ስለ ታናሽነቱ አይገባኝም የሚል ሰው ነበር። አሁን ግን ራሱን ከፍ ከፍ ሲያደርግ ጸጋ እግዚአብሔር ስለሚተወው የዛለ ሰው ይሆናል። ሲዝል ድካሙ የሚሰማው ከሆነ ትሑት ይሆናል።

በመንፈስ መቃጠል ከኩራት ጋር በአንድ ቦታ ላይ ሊገለጥ አይችልም። ከተገለጠም አንዱ ከሌላው ተለይቶ ቦታ መፈለግ አለበት። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ «አንተ ግራውን ብትወስድ እኔ ወደ ቀኝ እሄዳለሁ፤ አንተም ቀኙን ብትወስድ እኔ ወደ ግራ እሄዳለሁ።» (ዘፍ 13:9) የሚለው ቃል ከዚህ ጋር ይሄዳል።

ይህ ይሁን እንጂ በመንፈሳዊ ተሰጥኦና በአእምሮ ብቃት የታደሉት ሰዎች ክርስትናን በመልካም ሁኔታ ይጀምሩታል። ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን ስለሚፈተኑ በዝለት ይወድቃሉ። በዚህ ምክንያት የሰው ልጆችን የሚወደው

እግዚአብሔር ስጦታዎቹን ለእያንዳንዱ ሰው አልሰጠም። ይህን ቢያደርግ ግን ሰው ሁሉ እነዚህን ስጦታዎች ሊሸከማቸው ባልቻለም ነበር። ስጦታዎች ሁሉ ከእግዚአብሔር የተቸሩት ሰው ቢኖር ልቡ በኩራት ከፍ ከፍ ስለሚል ፈጥኖ በዝለት ይወድቃል።

ይህን በማስመልከት አንድ አባት የተናገራቸው ቃላት ምንኛ እውን ናቸው! «እግዚአብሔር ስጦታ ከሰጠህ ትሸከመው ዘንድ የሚያስችልህን ትሕትና ከእርሱ ጋር አብሮ ያድልህ። ይህ ካልሆነ ግን ከአንተ እንዲወሰደው ለምነው።» ነቢዩ ዳዊት የተናገራቸው ቃላትስ ምንኛ ጥልቅ ናቸው! «ሥርዓትህን እማር ዘንድ ያስጨነቅኸኝ መልካም ሆነልኝ።» መዝ 118:71። ከዚህ በተጨማሪ እንዲህ ይላል፡- «እግዚአብሔር ልባቸው ስለሰበረ ቅርብ ነው . . .» መዝ 33:18። በዚህ መሠረት ትሑትና ልብህ የተሰበረ ሰው ከሆንህ እግዚአብሔር ወደ አንተ በመቅረብ የሚቃጠል መንፈሱን ስለሚሰጥህ ዝለት በአንተ ውስጥ ሊኖር አይችልም።

አሁን ወደሚቀጥለው ነጥብ እንሸጋገራለን።

ራስን ለማዋረድ አጭር ጊዜ መስጠትና ለተድላ መጣደፍ።

አንድ ሰው የንስሓ ሕይወትን በጀመረበት ለሙን ራሱን ያዋርዳል፣ ትሕትና ያሳያል፣ ስለ ኃጢአቶቹም አብዝቶ ያለቅሳል። በዚህ ሁኔታ ላይ እያለ አንዱ ወደ እርሱ መጥቶ 'ጌታ ኃጢአትህን ይቅር ስላለህና እንድትደሰት ስለ ጠራህ ይህን ኀዘንህን ማቆም አለብህ።' በማለት ምክር ያካፍለዋል። ይህ ሰው ይህንን ሲሰማ አስቀድሞ በመንፈስ እንዲቃጠል ያደረገውን ራሱን የማዋረድ መንገድ እርግፍ አድርጎ ይተዋል። ከጊዜ በኋላም ዝለት ይጥለዋል።

ራስ ማዋረድን የሚቃወም ማንኛውም ዓይነት ኃጢአት ተመልሶ ሊመጣ የሚችል ኃጢአት ነው። የሰውየው ሕሊና ይህን ለማድረግ ፈቃደኛ ካልሆነ ግን ከዚህ ጋር እየተላመደ ስለሚሄድ ለብ ያለ ሰው ይሆናል። በመንፈሳዊነቱ ታላቅ ደረጃ ላይ የደረሰው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንኳ ራስ ማዋረድን እስከ መጨረሻው ድረስ ካለማቆሙም በላይ ኃጢአቶቹን ፈጽሞ አልዘነጋቸውም ነበር። በመሆኑም እንዲህ ይል ነበር፡- «እኔ ከሐዋርያት ሁሉ የማንስ ነኝና፤ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ስላሳደድሁ ሐዋርያ ተብዬ ልጠራ የማይገባኝ ነገር ግን በእግዚአብሔር ጸጋ የሆንሁ እኔ ነኝ።» 1ኛ ቆሮ 15:9።

ነቢዩ ዳዊትም ለኃጢአቱ ይቅርታ እንደሚያገኝ ሲያውቅ ዘወትር ኃጢአቱን በፊቱ በማድረግ ሌሊቱን ሙሉ መኝታውን በዕንባዎቹ ያጥብ ነበር። መዝ 6 እና 50። ቅዱስ ጳውሎስና ነቢዩ ዳዊት ልባቸውን ስላዋርዱና መንፈሳዊ መቃጠላቸውን ስለ ጠበቁ በዝለት ሊወድቁ አልቻሉም። ስለሆነም ለደስታ ሕይወት አትፍጠን! ይልቁንም ደስታ ሲያጋጥምህ «ይህ ለእኔ አይገባኝም!» በል። ይህን ልትል ባትችልና በደስታ መንፈስ ውስጥ ልትገባ ብትችልም ልብህን በትሕትና አዋርደው።

ወደ ሌላው የዝለት ምክንያት እናልፋለን።

ቸልተኝነትና ልልነት።

እነዚህ ሁለት ምክንያቶች ወደ ዝለት እንደሚመሩ ግልጽ ነው። መንፈሳዊ ጥረትን ስለሚቃወሙም ወደ ፍጽምና በሚያደርሰው መንገድ ላይ ማሰናከያ ይሆናሉ። ሰው ለእነዚህ የዝለት ምክንያቶች ከተጋለጠ በጸሎቱና ራሱን በመጠበቁ ውስጥ ቸልተኛ ከመሆኑም በላይ ራሱን አጥብቆ ለመጠበቅ የሚያስችለውን ኃይል ማግኘት ያቅተዋል።

የእግዚአብሔር መንግሥት የምትሰጠው ለሚጥሩት እንጂ ለሰነፎቹ አይደለም። ይህን አስመልክቶ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦ «የእግዚአብሔርን ሥራ በቸልታ የሚያደርግ ርጉም ይሁን . . .» ኤር 48፡10።

ማጠቃለያ።

በዚህ ማጠቃለያ ውስጥ ልንናገር የምንወደው [illegible] ትምህርት ስለሆነ ሁሉንም ተናግሮ መጨረስ ብዙ ጊዜ መውሰድ ስለሆነ ነው። በመሆኑም ትምህርቱን እዚህ ላይ እንገታዋለን። እግዚአብሔር ከፈቀደ በሌላ መጽሐፍ እንመለስበታለን።

ምዕራፍ አሥራ ሁለት።

የኀዘን ውጊያ።

- ቅዱስ ኀዘን።
- የተፈጥሮ ኀዘን።
- የተሳሳተ ኀዘንና ምክንያቶቹ።
- ተገቢ ያልሆነ ኀዘን።
- ምልክቶቹና መፍትሔዎቹ።
- ኀዘን ለችግሮችህ መፍትሔ ሊሆን አይችልም።
- በሥራ መጠመድ።
- የመድኃኒትና የአካል ህክምና።
- ጤናማ ያልሆነ ቅድስና።
- የኀዘን መንፈሳዊ መፍትሔዎች።
  - እምነት እንደ መፍትሔና እንደ ጥበቃ።
  - ተስፋ ለኀዘን ያለው መፍትሔ።
  - ትዕግሥት ለኀዘን ያለው መፍትሔ።
  - ዓለምንና በዓለም ያሉትን አለመውደድ።
  - የምስጋና ሕይወት እንደ ጥበቃና መፍትሔ።
  - ደስታ እንደ ጥበቃና መፍትሔ።
  - እውነታ።
  - ኀዘንን በቅድስና ማከም።
- ማጠቃለያ።

ኀዘን ምንድር ነው? ምልክቶቹና ምክንያቶቹ ምንድር ናቸው? ውጤቱና መፍትሔዎቹስ? ዛሬ የምናወራችሁ በሚገባ ኀዘንና በማይገባ ኀዘን መካከል ያለውን ልዩነት ነው። ከዚህ በተጨማሪ ኀዘን ውጊያ ነው ወይስ በሽታ የሚለውን እንመለከታለን።

ቅዱስ ኀዘን።

በመንፈሳዊ መነሣሣት የሚፈጸም ቅዱስ ኀዘን እንዳለ ምንም ጥርጥር የለውም። ለዚህ ኀዘን የተጋለጠ ሰው ኀዘኑን የሚፈጽመው መንፈሳዊ በሆነ መንገድ ነው። እንዲህ ዓይነቱ ኀዘን ጊዜያዊ ወይም ቋሚ ሊሆን ይችላል።

1- ለዚህ ምሳሌ የሚሆነን የኢየሩሳሌም ቅጥር መፍረሱን፣ በሮችዋ መቃጠላቸውን፣ ሕዝቡም በታላቅ መከራና ስድብ ውስጥ መውደቃቸውን የሰማው ነህምያ ያዘነው ኀዘን ነው። «ይህንንም ቃል በሰማሁ ጊዜ ተቀምጬ አለቀስሁ፤አያሌ ቀንም አዝን ነበር በሰማይም አምላክ ፊት እጸምና እጸልይ ነበር . . .» ነህ 1፡4። ይህን ኀዘኑን የተመለከተው ንጉሥ አርጤክስስ «ይህ የልብ ኀዘን ነው እንጂ ሌላ ነገር አይደለም . . .» (ነህ 2፡2) ሲለው ነህምያ የመለሰለት፦ «. . . የአባቶቼ መቃብር ያለባት ከተማ ተፈትታለች፤በሮችዋም በእሳት ተቃጥለዋልና ፊቴ ስለ ምን አይዘን?» (ነህ 2፡2-3) በማለት ነበር።

እንዲህ ዓይነቱ ኀዘን ነህምያን ያነሳሳው እንዲጸም፣ እንዲጸልይና ሌሎች መንፈሳዊ ሥራዎች እንዲያከናውን ነው። ይህ ደግሞ የእርሱንና የሕዝቡን ኀዘን ስላጠፋ በመጨረሻ ከሕዝቡ ጋር በታላቅ ደስታ ሊደሰት በቅቷል። ነህ 12:43።

2- ከዚህ ጋር የሚመሳሰለው ምሳሌ የሕዝቡን መተላለፍ ተመልክቶ በጸም፣ በጸሎትና በኀዘን የቆየው ዕዝራ ነው። እርሱ ሕዝቡ ንስሓ እንዲገቡና ለበደላቸው መሥዋዕት እንዲያቀርቡ ስላደረጋቸውና በዚህ ስለተሳካለት ኀዘኑ ጠፍቶለታል።

3- "The Paradise of the Monks" በተባለው መጽሐፍ ውስጥም ዕንባቸው ምሳሌ የሚሆን የቅዱሳን አባቶችን ታሪክ እናገኛለን። በእነርሱ የተነገረውንና «በአትህ ውስጥ ተቀመጥና ስለ ኃጢአቶችህ አልቅስ!» የሚለውን ብሒል የምናገኘው ከዚሁ መጽሐፍ ውስጥ ነው።

4- ከዚህ በተጨማሪ ጸምና ንስሓን የሚያስከትል ሥነ-መጻሕፍት እናነባለን። እንዲህ ዓይነቱ ኀዘን ሰውን ልቡ የተሰበረና ትሑት ያደረገ ነው። ለዚህ ምሳሌ የሚሆኑን፦ በኢዩኤል 2:12-17 የተጠቀሰው ጾም፣ ማቅ ለብሰው በአመድ ላይ ተቀምጠው ራሳቸውን በማዋረድ የጸሙት የነነዌ ሰዎች (ዮና 3) እና መኝታውን በዕንባዎቹ ያጠበው የቅዱስ ዳዊት ንስሓ ናቸው። መዝ 6።

የኃጢአተኞች ኀዘን ብዙ ጊዜ ወደ ንስሓ ከተለወጠ በኋላ በልብ ውስጥ በሚደረግ መደላደል ይጠቃለላል። ይህም ሁለንተናቸውን እንዲያርሙና እንዲያስተካክሉ ይረዳቸዋል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ «. . . ከፊት ኀዘን የተነሣ ልብ ደስ ይሰኛልና።» (መክ 7:3) ተብሎ የተጻፈው ቃል ከዚህ ጋር የሚዛመድ ነው።

በአገልግሎት መስክ ውስጥ ኀዘን አንዳለም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ፦ «. . . በሁሉ እንገፋለን እንጂ አንጨነቅም. . .» (2ኛ ቆሮ 4:8) በማለት ገልጸልናል። ይሁን እንጂ በአገልግሎት ውስጥ ላለው ኀዘን መጽናናት እንዳለው ሳይገልጽልን አላለፈም፦ «እርሱ በመከራችን ሁሉ ያጽናናናል፤ ስለዚህም እኛ ራሳችን በእግዚአብሔር በምንጽናናበት መጽናናት በመከራ ሁሉ ያሉትን ማጽናናት እንችላለን።» 2ኛ ቆሮ 1:4።

እጅግ በጣም ቅዱስ ከሆኑት ኀዘናት መካከል ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በጌቴሴማኒ የአትክልት ቦታ የተከዘው ትካዜና ያዘነው ኀዘን አንዱ ነው። በዚያን ጊዜ ጌታ እንዲህ ነበር ያለው፦ «ነፍሴ እስከ ሞት ድረስ እጅግ አዘነች . . .» ማቴ 26:37-38። ስለ መድኃኒታችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ በነቢዩ ኤርምያስ ሰቆቃ ውስጥ የተነገሩት የትንቢት ቃላት ለቅዱስ ኀዘን ምሳሌ ይሆናሉ።

ይህ ይሁን እንጂ ኢየሱስ ክርስቶስ ለተማሪዎቹ፦ «. . . ነገር ግን እንደገና አያችኋለሁ፤ልባችሁም ደስ ይለዋል፤ደስታችሁንም የሚወስድባችሁ የለም።» ብሏቸዋል። በዚህ መሠረት ቅዱስ ኀዘን የሚመጣው በመንፈሳዊ ምክንያቶች ሲሆን ብዙ ጊዜ በመጽናናትና በተስፋ ታጅቦ በደስታ የሚጠቃለል ነው። ከዚህ በተጨማሪ ይህ ኀዘን ጊዜያዊ ነው እንጂ ዘላቂ አይደለም።

የተፈጥሮ ኀዘን።

እንዲህ ዓይነቱ ኀዘን ማርታና ማርያም ለወንድማቸው ለአልዓዛር በመቃብሩ ላይ እንዳዘኑት ያለ ለሚወዱት ሰው የሚደረግ ኀዘን ነው። ጻድቁ ኢዮብ ከልጆቹ ሞት፣ ከቤቱ ውድመትና ከሀብቱ ጥፋት በኋላ ያዘነው ኀዘን የዚህ ምሳሌ ነው። ያዕቆብም ልጁ ዮሴፍን አውሬ እንደ በላው በሰማ ጊዜ ያዘነው ኀዘን የዚህ ተመሳሳይ ነበር። ዘፍ 37:34።

የተሳሳተ ኀዘንና ምክንያቶቹ።

የተሳሳተ ኀዘን ኃጢአትን በውስጡ ያዘለ ነው። ይህንንም ከዚህ ቀጥሰን እንመለከታለን፦

1- ሰው በልቡ ውስጥ ያለውን የኃጢአት ምኞት ሳይገነዘብ የሚያዝነው ኀዘን የተሳሳተ ኀዘን ነው።

ለዚህ ምሳሌ የሚሆነን የንጉሥ አክዓብ ኀዘን ነው። እርሱ የኢይዝራኤላዊውን የናቡቴን የወይን ቦታ ሊወስድ ባለመቻሉ አዝኖና ተክዞ ወደ ቤቱ ሄዷል። 1ኛ ነገ 20:4። ከዚህ በኋላ ኀዘኑ ምኞቱን ያሳካለት ዘንድ እንዲዋሽ፣ ሰው እንዲገፋና እንዲገድል አብቅቶታል።

2- በቅንዓትና በምቀኝነት የሚመጣ ኀዘን።

ለዚህ ኀዘን ምሳሌ የሚሆነን በታናሽ ወንድሙ መገኘት ምክንያት በአባቱ ቤት በተደረገው ደስታ ውስጥ ተካፋይ ላለመሆን አልገባም ያለው ታላቅ ወንድሙ ነው። እርሱ ለአባቱ እንዲህ ነበር ያለው፦ «. . . ለእኔም ከወዳጆቼ ጋር ደስ እንዲለኝ አንድ ጠቦት ስንኳ አልሰጠኸኝም፤ነገር ግን ገንዘብህን ከጋለሞቶች ጋር በልቶ ይህ ልጅህ በመጣ ጊዜ የሰባውን ፍሪዳ አረድህለት . . .» ሉቃ 15:18-30።

ከዚህ በተጨማሪ ለዚህ ኀዘን ምሳሌ የሚሆነን እርሱ ካገኘው የሚበልጥ ያገኘውን ሰው ከእርሱ የበለጠ መብት እንዳለው አድርጎ በመመልከት የሚያዝነው ሰው ነው።

3- በውድቀት የሚመጣ ኀዘን።

ኀዘን ለውድቀት መፍትሔ ሊሆን አይችልም። መፍትሔ ሊሆን የሚችለው የውድቀቱ ምክንያት የሆኑትን ነገሮች ማወቅና እነርሱን ቀና በሆነ መንገድ ማከም ነው። ተራ ኀዘን በውድቀት ላይ መፍትሔ የሚያስፈልገው ሌላ ችግርን ይጨምራል እንጂ መፍትሔ አይሆንም።

አንድን ኃጢአት ለመፈጸም በሚደረግ እንቅስቃሴ ውስጥ ውድቀት ከተከሰተ እንዲህ ያለው ኀዘን እደገኛነቱ የከፋ ይሆናል። አምኖን በእህቱ በትዕማር ላይ በመጀመሪያ ኃጢአት ሊፈጽም ሞክሮ ውድቀት ሲያጋጥመው ያዘነው ኀዘን፣ አክዓብ የናቡቴን የወይን ቦታ ለመውሰድ ያደረገው የመጀመሪያ ሙከራ ውድቀት ሲያጋጥመው ያዘነው ኀዘን፣ ፈተና ላይ እያለ ሊያጭበረብር ሞክሮ ውድቀት

ያጋጠመው ተማሪ ኀዘን ወይም ለዘመዶቹ በግድያ ሊበቀልላቸው ምክር ውድቀት ያጋጠመው ሰው ኀዘን ለዚህ ምሳሌ ሊሆኑን ይችላሉ። ኃጢአት መፈጸም ውድቀት ሲሆን ለውድቀት ማዘን ደግሞ ሌላው ኃጢአት ነው።

4- ተስፋ በመቁረጥ የሚመጣ ኀዘን።

ለዚህ ምሳሌ የሚሆነን ኀዘን ብኩርናው በወንድሙ እንደተወሰደበት ከአባቱ አንደበት ከሰማ በኋላ ምንም ተስፋ እንደማይኖረው ያወቀው ዔሳው ተስፋ በመቁረጥ ያዘነው ኀዘን ነው። አባቱ ይስሐቅ ለዔሳው የነገረው እንዲህ ብሎ ነበር፦ «. . . ወንድምህ በተንኰል ገብቶ በረከትህን ወሰደብህ አለ። . . . እነሆ ጌታህ አደረግሁት . . . ለአንተ ግን ልጄ ሆይ፤ ምን ላድርግ?» ዘፍ 27:33-38። ዔሳው ይህን ቃል ሲሰማ ድምፁን አሰምቶ በመጮኽ ምርር ብሎ አልቅሷል።

5- መከራ ሲገጥም ዝም ከማለት የሚመጣ ኀዘንና ያለ ተስፋ የሚደረግ ኀዘን።

እንዲህ ባለ ኀዘን ውስጥ ያለ ሰው መፍትሔ ያገኝ ዘንድ ከመዝሙረኛው ዳዊት ጋር ሆኖ «ነፍሴ ሆይ ለምን ታዝኛለሽ? ለምንስ ታውኪኛለሽ? የፊቴን መድኃኒት አምላኬን አመሰግነው ዘንድ በእግዚአብሔር ታመኚ።» (መዝ 41:11።) በማለት ዘምሯል።

በእግዚአብሔር ሳታምንና ምንም ተስፋ ሳይኖርህ ችግሮችህን በፊትህ ቆልለህ ያለ መፍትሔ በኀዘን ውስጥ ቆመህ አትመልከታቸው። ይልቁንም «ነገር ግን ወንድሞች ሆይ ተስፋ እንደሌላቸው እንደ ሌሎች ደግሞ እንዳታዝኑ . . .» (1ኛ ተሰ 4:13) የሚለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል አስታውስ። ምንም እንኳ ምክንያቱ የተፈጥሮ ሆኖ ለአንድ ሰው የሚደረግ ኀዘን ቢሆን ወይም ደግሞ መንፈሳዊ ሆኖ ኃጢአት ከሠሩ በኋላ በማልቀስ የሚፈጸም ኀዘን ቢሆንም ኀዘን በውስጡ ተስፋ ከሌለው የተሳሳተ ኀዘን ነው።

ስለሆነም በችግሮች ብትከበብም እንኳ እነርሱን ከፊትህ በማስወገድ በአንተና በችግሮችህ መካከል እግዚአብሔርን አስገባ። በዚህ ጊዜ እነርሱ በነው ሲጠፉ እግዚአብሔር ይገለጣል።

6- ከመጠን ያለፈ ጥንቃቄ በማድረግ የሚመጣ ኀዘን።

ክብሩን ወይም መብቱን አስመልክቶ ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚያደርግ ሰው ሊኖር ይችላል። እንደዚህ ዓይነቱ ሰው በማንኛውም ምክንያት ወይም በትንሹ ምክንያት ወይም ደግሞ ያለ ምንም ምክንያት ሊበሳጭ ይችላል። እርሱ የሚፈልገው በተለየ መንገድ እንክብካቤ እንዲደረግለት ነው። ይህም በሥርዓት፤ በጥንቃቄና በምቹ ሁኔታ እንዲደረግለት ይፈልጋል። እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ የሚገጥመው አልፎ አልፎ ቢሆንም እንደዚህ ዓይነቱ ሰው ይህ ካልተደረገለት ኀዘን ውስጥ ይገባል።

7- የእነዚህ ሰዎች ኀዘን እውነትን በመሰረዝ ከአጠገባቸው ካራቀባቸው በኋላ ለራሳቸው በነደፈላቸው ነገር ግን በማያገኙት የአሳብ ቅዠት ውስጥ እንዲኖሩ የሚያደርጋቸው ኀዘን ነው። እነዚህ ሰዎች ያሉበትን ሁኔታ ይቃወሙታል ወይም ያወግዙታል። ይሁን እንጂ የሚፈልጉትን ነገር እንዲገነዘቡ ወደሚያደርጋቸው ተግባራዊ መንገድ በመግባት ለመለወጥ ግን አይሞክሩም። በመሆኑም ባሉበት የዓመፃ መንገድ ውስጥ በሁሉም ነገር ቅር እንዳላቸውና እንዳዘኑ መገዛቸውን ይቀጥላሉ።

እነዚህ ሰዎች አንዳንድ ጊዜ ደስ ቢላቸውም በቁም ቅዠት ውስጥ ሆነው ባለመሯቸው የአሳብ መስመሮች ውስጥ እንዲያገኟቸው በፈለጓቸው ፍላጎቶቻቸው ዙሪያ ባሉ ቅዠቶቻቸው ነው። ይሁን እንጂ ከቅዠቶቻቸውና ከአሳባዊው ዓለም ሲባንኑ ራሳቸውን አስቀድመው በነበሩበት ቦታ ያገኙታል። በዚህ ጊዜ ይበልጥ ቅር ይላቸዋል ያዝናሉም። ስለሆነም እነዚህን ሰዎች የምንመክራቸው እንዲደሰቱ፤ በቃን እንዲሉ፤ እንዲረኩና ላሏቸው ነገሮች እንዲያመሰግኑ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ያሉበትን ሕይወት ተግባራዊ በሆነ መንገድ ባመለወጥ በኀዘን ውስጥ ከመቆየት እንዲወጡ አንመክራቸዋለን።

8- ትዕግሥት በማጣትና በቁጣ የሚመጣ ኀዘን።

ግልጽ የሆነውና ሰፋ ያለ አመለካከት ያለው ሰው አላስፈላጊ ጉዳዮችን ከማውጣትና ከማውረድ ይልቅ ልቡ ውስጥ ቀልጠው ይቀሩ ዘንድ ብዙ ነገሮችን እንዳለየ ሆኖ ያልፋል። ይህን ሊታገሱ የማይችሉ ሰዎች ግን ራሳቸውን ለኀዘን አሳልፈው የሰጡ ናቸው። ሰፋ ያለ አመለካከት ለኀዘን ዓይነተኛ መፍትሔ ነው። ሰፋ ያለ አመለካከት ያለው ሰው ቡኀዘን ከመቆራመድ ይልቅ ለኀዘኑ መፍትሔ ይፈልጋል።

ብልኀ ሰው ከችግር ወይም ከመከራ ጋር ሲጋፈጥ ከመበሳጨትና ከማዘን ይልቅ ለገጠመው ችግርና መከራ መፍትሔ ለማግኘት ይጥራል። መፍትሔ ሲያገኝ ስለሚደሰት የችግሩ ቋጠሮ ይፈታል። መፍትሔ ካላገኘም በትዕግሥት ይጠባበቃል። ትዕግሥተኛ ያልሆነ ሰው ቁጡ ለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም። ትዕግሥት ከሌለው ደግሞ ኀዘኑ እየጨመረ ይሄዳል።

9- ያለ ምንም ግልጽ ምክንያት በተቃዋሚ በሚከፈት ውጪያዊ ውጊያ የሚደርስ ኀዘን።

ተቃዋሚ በአንድ ሰው ውስጥ ችግር የሚፈጥር ነገር ሊተክል ወይም ሊፈጥር ይችላል። ከዚህ ሌላ ወደ ኀዘን የማያደርሱ ርባና ቢስ ምክንያቶችን ለሰውየው አግዝፎ ካሳየው በኋላ ጉዳዩን ቀላል አድርጎ ያቀርብለታል። ከዚህ በኋላ ሰውየው ባገኘው ደረጃ መደሰቱን ሲመለከት ከዚህኛው የሚሻሉ የሚመስሉ ሌሎች ደረጃዎችን እያባበለ በማሳየት ወደ እርሱ ይስበዋል። እነዚህን አዳዲስ ደረጃዎች ሲያገኝም በሌሎች አዳዲስ ደረጃዎች ወይም በመጀመሪያዎቹ ይስበዋል። በመጨረሻም ተቃዋሚ ወይም ጠላት ይህን በማድረግ ሰውየውን ወደ ጥርጥርና አለመረጋጋት ይመራዋል። በዚህም ኀዘን ውስጥ ይገባል።

ለምሳሌ ጠላት ዲያብሎስ በምናኔ የሚኖር አንድ መነኩሴ ሊያገኝ የድል አክሊል የተዘጋጀው የእግዚአብሔርን መንግሥት በአገልግሎት ለሚገነቡት ቅዱሳን እንደ ሆነ አድርጎ ያባብለዋል። መነኩሴው በአገልግሎት ላይ መሆኑን ሲገልጽለትም በብቸኝነት፣ በተመስጦ ሕይወት፣ በአርምሞ፣ በማያቋርጥ ጸሎትና በእግዚአብሔር ሕልውና በመደሰት ሊያባብለው ይሞክራል። በዚህ ጊዜ መነኩሴው በአንድ ጊዜ በአንድ ነገር ላይ ሊጸና ስለማይችል በጎዘን ይዋጣል።

10- ጥርጣሬ በሰው ሕይወት ውስጥ የሚቆይ ከሆነ ነፍስን እየጎዳ ወደ ጭንቀትና ጎዘን ይመራታል።

አንድ ሰው የባልንጀራውን ታማኝነት ወይም የሚስቱን ታማኝነትና ንጽሕና ወይም የእግዚአብሔርን ጥበቃና እርዳታ ሊጠራጠር ይችላል። ጥርጥር የሚቃጣው በእምነት ላይ ወይም አንድ ሰው እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በመንዙና ባለ መንዙ ላይ ነው። ከዚህ በተጨማሪ አንድ ሰው ምንም በማያውቀው መንገድ በእርሱ ላይ ሴራ እንደ ተጠነሰሰ አድርጎ ይጠረጥራል።

በጥርጥር የተሞሉ አሳቦች ምንጭ ሕሊና ነው። እነዚህ አሳቦች የሚታቀዱት ችግር ለመፍጠርና ሰውየውን የተሳሳተ ጠባይ ውስጥ ለመክተት ነው። ይህ ደግሞ እንዲህ ካለው ጥርጥር ስለታምነት ጋር የተስማማ ይሆናል። ለምሳሌ:- የሚስቱን ንጽሕና የሚጠራጠር ባል የቤቱን በሮችና መስኮቶች በላይዋ ላይ ከመቆለፉም በላይ ስለ እርስዋ ወሬ ይለቃቅማል። ከዚህ በተጨማሪ የእርሷን ደብዳቤዎች ለማንበብ፣ መሳቢያዎች ለመበርበርና ጥርጥሩን አስመልክቶ ማንኛውንም ዓይነት ጥያቄ ለመጠየቅ ራሱን ባለ መብት ያደርጋል። ከዚህ ሌላ በሳቀች፣ በተነጋገረች፣ በተሰበሰበችና በተንቀሳቀሰች ቁጥር ይገሥጻታል። ይህን በማድረጉም ምንም ዓይነት ጥፋት የሌለባት ሚስቱን ከባድ ሥቃይ ውስጥ ይከታታል። በዚህ ምክንያት የእርሱም ሆነ የእርሷ ሕይወት ወደ ሲኦልነት ይቀየራል። እዚህ ላይ የጎዘን ውጤቱ የከፋ ይሆናል።

በዚህ መሠረት ጎዘን የሚታወቅና ታላቅ ውጊያ ነው። ከዚህ በመቀጠል ወደ አራተኛው የጎዘን ዓይነት እንሸጋገራለን።

ተገቢ ያልሆነ ጎዘን:

ወደ ጎዘን የሚመራ ጥርጥር በሽታ ወደ መሆን ያድጋል። ጎዘን ደግሞ ወደ በሽታነት ሊለወጥ ይችላል።

ጎዘንን በማስመልከት አሳብ በሰው ላይ ጫና ሲፈጥር ሰውየው ደስታውን በማጣት ከመንፈስ ቅዱስ ውጪ ይሆናል። የጎዘን አሳብ በታመመው ሰው ሕሊና ላይ ከተጣበቀ ቶሎ አይለቀውም። ሲቀመጥ ወይም ሲራመድ፣ ሲተኛ ወይም ሲነቃ - የሚነቃው በመሰላቸት፣ በጭንቀት፣ በፍርሃት፣ አሳዛኝ ሥዕላት በሕሊናው እንደተሣሉና ያለ ምንም መፍትሔና ተስፋ ነው።

እንደዚህ ዓይነቱ ጎዘን ከሰው ሕይወትና መንፈሳዊነት በተጨማሪ ነፍሱንና ሕሊናውን ያጠፋል። ይህንንም ሲያደርግ መጥፋቱንና ተስፋ አለማግኘቱን እያሳመነው ነው። ለምሳሌ:-

1- አንድ ሰው መንፈስ ቅዱስን በመስደብ ኃጢአት ከሠራ ኃጢአቱ ሊሠረይለት እንደማይችል ያስባል። ማቴ 12:31። ይህን አሳብ ዲያብሎስ በተሳሳተ መንገድ ወደ ሕሊናው የሚያስወነጭፈው ዘላለማዊነቱን እንዳጣና እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ቃል ለድኅነቱ ምንም መንገድ እንደማይኖረው በማሳየት ተስፋ በማስቆረጥ ሊጥለው ነው። ከዚህ በተጨማሪ ዲያብሎስ በዚሁ ተመሳሳይ አሳብና ጎዘን ውስጥ እንዳለ ለዔሳው የተነገሩትን «. . . በፅንባ ተግቶ ምንም ቢፈልገው ለንስሓ ስፍራ አላገኘምና።» (ዕብ 12:17) የሚሉትን ቃላት ያስታውሰዋል።

በዚሁ ተመሳሳይ ሰዓት ከዚህ በታች የተጠቀሱትና እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን እንደሚቀበል የሚገልጡትን ቃላት ይሸሽገበታል። «. . . ወደ እኔም የሚመጣውን ከቶ ወደ ውጪ አላወጣውም . . .» (ዮሐ 6:37)፤«ሰዎች ሁሉ ሊድኑና እውነቱን ወደ ማወቅ ሊደርሱ በሚወድ በእግዚአብሔር በመድኃኒታችን ፊት መልካምና ደስ የሚያሰኝ ይህ ነው።» 1ኛ ጢሞ 2:4።

ቀደም ሲል ከጠቀስነው በተጨማሪ ዲያብሎስ «. . . ንስሓም እንድትገ ጊዜ ሰጠኋት፤ከዝሙትዋም ንስሓ እንድትገባ አልወደደችም።» (ራእ 2:2 የሚለውን ቃል በማስታወስ ለሰውየው ለንስሓ የተወሰነ ጊዜ እንዳለና ይህ ጊዜ አሁን እንዳለፈበት አድርጎ ይነግረዋል። ከዚህ በኋላ ነቢዩ ዳዊት «ብዙ ሰዎች ነፍሴን አምላክሽ አያድናትም አልዋት።» (መዝ 3:2) በማለት የተናገረውን ቃል ዲያብሎስ በመጥቀስ ማንኛውንም ዓይነት ተስፋውን ሁሉ ከውስጡ ያሟጥጥበታል። ከዚህ በተጨማሪ በዕብ 6:4-6 የተጠቀሰውን ቃል ቡትኩረት እንዲመለከት ያሳስበዋል። «. . . እንደገና ለንስሓ አነርሱን ማደስ የማይቻል ነው . . .»።

ሰዎችን ተስፋ ማሳጣትና በጎዘን መጣል የዲያብሎስ መንገድ ነው። በእርግጥ ቀደም ሲል የጠቀስነው ጥቅስ ራሱን የቻለ ትርጉም ቢኖረውም እንዲህ ዓይነቱ ሰው ቃሉ ምን ለማለት እንደ ተጠቀሰ ትርጉሙን የሚያስረዳው ሰው ያስፈልገዋል። የእግዚአብሔር ፍቅር ወሰን እንደሌለውም የሚነገረው ሰው ያስፈልገዋል። ጌታ ከእርሱ በስተቀኝ የተሰቀለው ወንበዴ ቤሕይወቱ የመጨረሻ ደቂቃዎች ውስጥ እያለ ያለ ምንም ቀጠሮ ተቀብሎታል።

ተስፋ የቆረጠ ሰው ከፊቱ ጎዘን የተነሣ ልቡ ደስ እንደሚለው ሰው ያለ ጎዘን ሊያዝን አይችልም። መክ 7:3።

2- ጤናማ ያልሆነ ጎዘን ምክንያት የጥፋተኝነት ስሜት ሊሆን ይችላል።

ለምሳሌ አንድ ሰው አባቱን ወይም ልጁን በሞት ቢያጣ እርሱ ለሞታቸው ምክንያት እንደሆነ አድርጎ ሊያስብ ይችላል። በመሆኑም ይህ ያለማቋረጥ እንዲረበሽና እንዲያዝን ያደርገዋል። «የሞተው እኔ ላደርግለት የሚገባኝን እንክብካቤ ላደርግለት ስላልቻልሁ ነው!» በማለት ራሱን ያሳምናል። በዚህ ጊዜ አንድ የሚቀርበው ሰው ወደ እርሱ ጠጋ ብሎ ሊያገኘው የሚገባውን እንክብካቤ እንዳደረገለትና የታዘዙለትን መድኃኒቶች እንደ ገዛለት ሲገልጽለት ጎዘኑ ጤናማ ጎዘን ስላልሆነ «ምናልባት ከዚህኛው የሚሻል ሐኪም እንዲያየው

ባደርግ ናሮ አይሞትም ነበር . . . ወይም ደግሞ ለሕክምና ወደ ውጪ ቢሄድ ይድን ነበር!» እያሰ በዘንቱ ይቆጫል።

3. አንድ ሰው ኀዘኑ ሊመጣ የቻለው ሊድን አይችልም ብሎ ካሰበው በሽታው እንደሆነ አድርጎ ያስባል።

እንዲህ ዓይነቱ ሰው አሳቡ በሕሊናው ውስጥ የሚሥልለትን አስቸጋሪ ሁኔታ በመመርከዝ እደኛኛ ውጤቶችን ሊጠብቅ ይችላል። ጤናማ ወዳልሆነ ኀዘን የሚመሩ ምክንያቶች ብዙ ናቸው። ሰው እንዲህ ካለው ኀዘን በቀላሉ ሊላቀቅ ካለመቻሉም በላይ ራሱን ከዚህ የሚያድንበትን ዕድል ለማግኘት ፈጽሞ አይጥርም።

ምልክቶቹና መፍትሔዎቹ።

ጤናማ ያልሆነ ኀዘን ያለበት ሰው ገጽታው በምን ዓይነት ሁኔታ ላይ እንዳለ አይታወቀውም። ይህ ሰው ሁልጊዜ ያለቅሳል፣ ያማርራል፣ ጨለማ በሆኑ አሳቦች ይዋጣል፣ ተስፋ ይቆርጣል፣ ተስፋውንም ያጣል። በመሆኑም በላሰማዊነቱን፣ ራሱን፣ ሥራውንና ጤናውን እንደ አጣ አድርጎ ያስባል። ከዚህ ቡተጨማሪ ለሰላው መጥፋት ምክንያት እንደሆነና በዚሁ ምክንያት ከፊቱ የሚበልጥ ቅጣት እንደሚጠብቀው አድርጎ ያስባል።

አንተ ይህን አሳቡን ለማስተካከል ብትሞክርም ይቃወምሃል። ብቻ ተስፋ በመቁረጥ ትኩር ብሎ ይመለከትህና ማልቀስ ይጀምራል። ከአንተ የሚሰማው ነገር በሕሊናው ውስጥ እንዳለፈ ነገር ግን ዋጋ ቢስ እንደሆነ ይነግርሃል። ከዚህ ቡተጨማሪ ስለ ኀዘኑ ለሰዎች ቢናገርም አብረውት ሊያዝኑ እንደማይችሉ በመገመት ለእነርሱ ምንም ላሰመናገር ይወስናል።

ሌላው ሰው ግን መፍትሔ አገኛለሁ በሚል አሳብ ችግሮቹን ሁሉ ለሰዎች ይናገራል። የዚህ ዓይነቱ ሰው ችግር መፍትሔ ካላገኘ ይበልጥ የማዘኑ ጉዳይ የማይቀር መሆኑ ነው። ይህን መፍትሔ አገኛለሁ በሚል ሰበብ ይህ ሰው ወደ አንድ ሰው ዘንድ አዘውትሮ ይሄዳል። በሄደ ቁጥር ከዚህ ከሚያጽናናው ሰው ጋር ለረዥም ሰዓታት ያለ ማቋረጥ ከማውራቱም በላይ ከእርሱ ርቆ እስኪሄድ ድረስ አጥብቆ ይከታተለዋል። ይህ በራሱ መጽናናት የሚሰጠው ልቡን እንዲያጣ ስለሚያደርገው የባሰ ችግር ውስጥ. በመግባት እጅግ ያዝናል።

መፍትሔን አስመልክቶ ጤናማ ባልሆነ ኀዘን ውስጥ ያሉ ሁለት ዓይነት ሰዎች አሉ። እነርሱም፡-

1ኛ/ የመጀመሪያው ሰው መጽናናትንና ማንኛውንም ዓይነት መረዳት የማይቀበል ሰው ነው።

2ኛ/ ሁለተኛው ሰው በራሱ አሳብ የሚደገፈው ነው። እንዲህ ዓይነቱ ሰው ሊረዳ ቢችልም ወደዚያው ተመልሶ ይገባል። ቢሻለውም የበለጠ ለመታመም ይተቸል።

በመሆኑም ራሱን የማጥፋት አሳብ በምናቡ ውስጥ ይገለጣል። ይህን ቢፈጽም ካለበት ህመምና ተስፋ መቁረጥ የሚገላገል መስሎ ይታየዋል። ከዚህ በኋላ ይህን አሳቡን ተግባራዊ ያደርጋል ወይም በዘላለማዊነት ስለሚያምን እንዲህ ያለው አሳብ የተሳሳተ መሆኑን ይረዳል ወይም ከሞት ኀዘንን ይመርጣል። ወይም ደግሞ በራሱ አሳብ ለችግሮቹ ሁሉ መፍትሔ ለማግኘት በመሞከር በቁም ትገቦት ውስጥ ይኖራል።

ያም ሆነ ይህ ኀዘን በጤናው ላይ ከባድ ተጽዕኖ ያመጣል። የኀዘን አሳቦች ስለሚያጨናንቁት በነፍሱም ሆነ በሥጋው ፍጹም የዛለ ሰው ይሆናል። በዚህ ዓይነት መንገድ በአንድ አሳብ ውስጥ ስለሚጠቃለል ከዚያ ለመውጣት በጣም ይቸገራል። እንዲህ ያለው ነገር ራሱን፣ በዙሪያው ያሉትን ሰዎች፣ ሐኪሙንና የንስሓ አባቱን የሚያውክ በሽታ ይሆናል። በዚህ ጊዜ የንስሓ አባቱ እርሱን ለማስተናገድ እጅግ ይቸገራሉ።

ታዲያ በዚህ ጊዜ መፍትሔው ምንድር ነው?

ኀዘን ለችግሮችህ መፍትሔ ሊሆን አይችልም።

ለዚህ የመጀመሪያ መፍትሔ ሊሆን የሚችለው ኀዘን ለችግሮችህ መፍትሔ ሊሆን አለመቻሉን በሙሉ ልብህ ማመንህ ነው። በማንኛውም ሰው ላይ እንደሚደርሰው ችግር በአንተም ላይ በመድረስ ልብህን ሊሰብረው ይችላል። ሌሎችን እንደሚያስጨንቃቸው አንተንም ሊያስጨንቅህ ይችላል። ይሁን እንጂ ሰዎች የገጠመህ ኀዘን በሰዎች ዘንድ ያለ የተፈጥሮ ኀዘን አስከማይመስል ድረስ በአንተ ውስጥ ቡተሰየ መልኩ ሊቆይ ይችላል።

በዚህ ጊዜ ሰዎች ሊያጽናኑህና ሊያረጋጉህ ቢሞክሩም አንተ እንዲህ ያለውን መጽናናት ለመቀበል እሻፈረኝ ትላለህ። ይህ ደግሞ ሊያጽናኑህ የሚመጡት ሰዎች ከአንተ ጋር እንዳይነጋገሩ ስለሚያሰላቻቸው ይበልጥ ለኀዘን እንድትጋለጥ ትተውህ ይሄዳሉ። እዚህ ላይ ጥቂት ጥያቄዎችን ልጠይቅህ እወዳለሁ፡- «ኀዘንህ ያስገኘልህ ምንድር ነው? ችግርህን አቃሎልሃል? ውስጣዊ መጽናናት ሰጠህ ወይስ ችግርህን አበዛብህ? ከሰዎች ጋር ያለህን ግንኙነት አዳበረልህ ወይስ አቆረቆዘብህ? እኔ ግን በኀዘን ውስጥ በመኖርህ ከጠበቅኸው በላይ ያለህን እንደምታጣ እርግጠኛ ነኝ።»

ይህን በመሰለ መንገድ የምታዝነው ኀዘን ካዘንህበት ኀዘን ይልቅ ችግሩ የከፋ ይሆናል። የመጀመሪያ ችግርህ ያለ መፍትሔ እንደ ተቀመጠ የኀዘን ችግር ራስ ወዳድነትንና በሌሎች ላይ ክፉ የመናገር ችግሮችን አስከትሎ ይመጣብሃል። በዚህ ጊዜ አስቀድመህ የኖርህበት ጥሞናህን ስለምታጣው ሰዎች በአንተ ዘንድ ያልነበሩ መጥፎ ጠባዮችን በግልጽ መመልከት ይጀምራሉ። ይህ እንክን በአንተ ላይ የሚመጣው መከራን የመቀበልና ችግርን በጽናት የመቻል ችሎታ ስለሌለህ ነው።

በኀዘን ስትከበብ ለችግሮችህ መፍትሔዎች ለማግኘት ትኾል ዘንድ ትክክለኛ ሰው ሁን! መፍትሔ ባታገኝም እንኳ እግዚአብሔርን ጠብቅ ወይም

ሁሉንም በጽናት በመታገስ ኑሮህን ለመግፋት ሞክር፤ በሰው ተፈጥሮ የምታዝን ከሆነ እንዲህ ያለው ኀዘን በውስጥህ ለረዥም ጊዜ አታቆየው። ሰዎች አንተን ተመልክተው እንዳያዝኑ ወይም ባለመሻሻልህ ተስፋ እንዳይቆርጡ ስሜትህን በሰዎች ፊት አትግለጥ።

ከችግሩ ይልቅ አንተ ብርቱ ለመሆን ሞክር። ካልቻልህ ግን ሁሉንም ነገር ማድረግ በሚቻለው በኃያሉ አምላክ ፊት ችግርህን አቅርብ። ማቴ 19:26። ከዚህ በኋላ ሁሉንም በእርሱ እጅ ላይ በመጣል ስለ ችግርህ ማሰብህን ታቆማለህ።

በእምነት፣ እጅ በመስጠትና በጸሎት መፍትሔ ሊያገኙ የሚችሉ ብዙ ችግሮች አሉ። ይሁን እንጂ በኀዘን ሊቃለል የሚችል ምንም ዓይነት ችግር የለም። ስለሆነም ሁሉንም መመልከት የሚችለው ኃያል አምላክ እንዳለና በእርግጥም እጆቹን እንደሚዘረጋልህ ማመን አለብህ። ከእርሱ የሚሰወር ምንም ነገር ስለሌለ ልጅ አንተነትህን ከምታውቀው የበለጠ እርሱ ስለ አንተ ችግሮች ያውቃል። አንተ ለራስህ ካለህ ኀዘን የበለጠ እርሱ ለአንተ ያዝናል።

እግዚአብሔር ለአንተ ያስባልና ችግሮችህን አንተ ከምትሸከማቸው ይልቅ በእርሱ እጆች ላይ ጣላቸው። በዚህ ዓይነት መንገድ የምታቃልላቸው ችግሮች አሉ። ሌሎች ደግሞ ልትረሳቸው የሚገቡህና መፍትሔያቸው ይህ ብቻ የሆነ ችግሮች አሉ። ምናልባት መፍትሔ የሳቸውም የምትሳቸው ችግሮችህ እንደነዚህ ያሉት ሊሆኑ ይችላሉ።

ምናልባት 'ችግሬን እንዴት ልረሳ እችላለሁ?' ብለህ ልትጠይቅ ትችላለህ። ቆዳዬ ከሥጋዬ ጋር የተጣበቀውን ያህል በሕሊናዬ ውስጥ የተጣበቁትን ችግሮች እንዴት ልረሳቸው እችላለሁ? ስሄድና ስቀመጥ፤ ብቻዬንና ከሰው ጋር ስሆን ችግሮቼን ሁልጊዜ አስባቸዋለሁ። ከዚህ ሌላ የማስበው ነገር የለኝም። ሳነብ አሳቤን ስለሚበትንብኝ ከእርሱ ሌላ የማስበው ነገር የለም። አሳቤ ስለ እርሱ ብቻ ይሆናል። እኔ ባውቀውም ባላውቀውም ይህ ነገር ለእኔ አየር እንደማስገባትና እንደማስወጣት ሆኗል።

እዚህ ላይ ተግባራዊ የሆኑ መፍትሔዎች አሰጥሃለሁ።

በሥራ መጠመድ።

በማንኛውም ጊዜ ራስህን በሥራ በመጥመድ በውስጥህ ካለው የኀዘን አሳብ ራቅ። ስለ አንድ ችግር ማሰብ ብዙ ጉዳት እንደሚያስከትልብህ እመን። ችግሩ [illegible] ሥነ ልቦናዊ ችግር ነው። ስለሆነም ያበላጭሃል ያደክምሃልም። ችግሩ እየከፋ ሊመጣም ለችግሩ መፍትሔ የማግኘቱ ነገር እየጠበበ ይመጣል። በዚህ ጊዜ ጤናማ ካልሆነው ከዚህ አሳብ ራስህን አላቀህ ለራስህ «ምንም ሊጠቅመኝ የማይችለውና ችግር የሚያመጣብኝ አሳብ ይበቃኛል!» በለው።

ይህን ማድረግ ካልቻልህ ግን በራስህ ላይ ችግር የሚፈጥርብህን አሳብ መርሳት በሚያስችልህ በማንኛውም ዓይነት ሥራ ራስህን ጥመድ። በኀዘን

ለሚጎዱ ሰዎች የማያቋርጥ ሥራ በጣም ጠቃሚ ነው። እነርሱ ሥራቸውን ያለ ማቋረጥ ከሠሩ በኋላ ስለሚደክማቸው አእምሮአቸውን በሰላም አሳርፈው ይተኛሉ። በዚህ ጊዜ ነርቮቻቸው ከአሳብ ጫና ይላቀቃሉ።

ከዚህ በተጨማሪ ሥራ አንድን ሰው መሥራቱንና ኃላፊነትን ሊሸከም መቻሉን ያሳውቀዋል። ይህ ደግሞ መጽናናትን ስለሚሰጠው የሥራውን ፍሬ በመመልከት እንዲደሰት ያደርገዋል። በዚህ ሁሉ መካከል አሳብ ከእርሱ እየራቀ ይሄዳል። ይሁን እንጂ አንዳንድ ሰዎች ነፃ ሆኖ ለማሰብ በሚል ሰበብ ሥራ መሥራትን ያቆማሉ። እዚህ ላይ ሊታሰብ የሚገባው ነገር ጤናማ ያልሆነ አሳብ ለአንዳንድ ሰዎች ሊያስወግዱት የማይችሉት ደረጃ ድረስ ጥቅም ያለው መሆኑ ነው። እነዚህ ሰዎች በማንኛውም ጊዜ ስለ ችግሮቻቸው በማሰብ በዚህ መጨረሻ በሌለው ክበብ ውስጥ ሊሽከረከሩ ይፈልጋሉ።

እነዚህ ሰዎች ሥራ ለመሥራት ፈቃደኞች ከሆኑ ይህ ጤናማ ምልክት ነው። ለጥቂት ጊዜያት በሥራ ሰበብ ከአሳብ መላቀቃቸው ለእነርሱ ጥሩ ምልክት ነው። በግዴጅ የሚያደርጉት ቢሆኑም እንኳ ሥራ ለመሥራት ፈቃደኞች መሆናቸው መልካም ነው። በደስታ ለመሥራት ፈቃደኞች ሆኑ ማለት በዚህ ደስተኞች ሆነዋል ማለት ስለሚሆን ራሳቸውን ያሻሽላሉ።

አንዳንድ ጊዜ አካላዊ ብቃቱ ሳይኖር ነርቮቻችን ተነቃቅተዋል በሚል ሰበብ ብቻ ሥራ ሥሩ ሲባሉ ፈቃደኞች አይሆኑም። እንደዚህ ያለው ይቅርታ ለጥቂቶች እውነት ቢሆንም በሌሎች ዘንድ ሐሰት ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ አንድ ሰው ሥራ በተሰጠው ጊዜ ሁሉ ድንገተኛ አካላዊ ድካም ሊሰማው ይችላል። ይህ ደግሞ ሥራ ላለመሥራት የሚያሳየው ውስጣዊ ምኞቱን ነው። በዚህ መሠረት አንድ ሰው ሥራ ለመሥራት ፈቃደኛ መሆን ያለበት በአትሙ ልክ ሲሆን ነው። ከዚህ በተጨማሪ በአትሙ ልክ መሥራት ያለበት ለመሥራት ያለው ፍላጎት ኀዘኑ ከደረሰበት ሰው ጋር ሊመጣጠን ሲችል ነው። ከዚህ ሌላ ይበልጥ የሚስማማውን የሥራ ዓይነት ለመምረጥ ዕድሉ እንዲኖረው ማድረጉ የሚሻል ይሆናል። እንዲህ ዓይነቱ ሰው የጉልበት ሥራ ለመሥራት ካልቻለ ሌሎች ሊሳተፍባቸው የሚችላቸው ተግባራት ሊኖሩት ይችላሉ። ከእነዚህም መካከል የተለያዩ ጨዋታዎች፣ መዝናኛዎች ወይም ሕሊናን ወጥረው የሚይዙ ንባባት ይገኙበታል።

የመድኃኒትና የአካል ህክምና።

አንድ የታመመ ሰው ሲደናገጥ ወይም ማንኛውንም ዓይነት መረዳት ለመቀበል ስነ ልቦናዊ ዝግጅት ሊጎድለው ወይም ተከራካሪ ሊሆን ወይም በገዛ አመለካከቱ ላይ ግትርነት ሊያሳይ እርሱን በመድኃኒት ማከም ተቀባይነት ያለው ነገር ነው። በዚህ ጊዜ ለሰውየው መድኃኒቶች የሚሰጡት እንዲረጋጋና እንዲፍታታ ከመሆኑም በላይ ሥነ ልቦናዊ ሕክምና እንዲያገኝ ነው። የታመመውን ሰው አብዝተው የሚያሰላቹት፣ በነርቮቹ ላይ ጫና የሚፈጥሩትና ሊቋቋመው የማይችለውን ጡጫ በውስጡ የሚሰነዘሩበት ጥቂት አሳቦች ሊኖሩ ይችላሉ። አብዝቶ ማሰብ እንቅልፉን ከእርሱ ስለሚያርቅበትም የሚረጋጋበትንና ሰላሙን የሚያገኝበትን ዕረፍት ገንዘቡ ለማድረግ ይጓጓል ይቸኩላልም። በዚህ ጊዜ

መድኃኒቶችና አደንዛዥ ክኒኖች እንቅልፉን ለማስመጣትና ከአሳብ እንዲገላገል ይሰጡታል::

እንደነዚህ ዓይነቶቹ መድኃኒቶች የሚሰጡት ሰዎችን ለሚያውክ፣ መታመሙን ለማይቀበልና ማንኛውንም ዓይነት መፍትሔ ለመቀበል ፈቃደኛ ላልሆነ ሰው ነው:: እዚህ ላይ ግን እነዚህ የተለያዩ መድኃኒቶች በሰው ላይ የጤና ጉዳት እንደሚያመጡ ሳንገነዘብ ቀርተን አይደለም:: ይሁን እንጂ ይህን በመሰለው አስቸጋሪ አጋጣሚ ውስጥ ከእነዚህ መድኃኒቶች ሌላ መፍትሔ ልናገኝ አንችልም:: ይህን ከማለት ይልቅ ግን የሚከተለውን ማለት እንወዳለን::

መድኃኒቶች የማያቋርጡ ወይም ዘላቂ መፍትሔ መሆን የለባቸውም:: በወቅቱ ከተሰጠ ሥነ ልቦናዊ ሕክምና እጅግ የተሻለ ነው:: አንድ በሽተኛ ሰው ከሚያስጨንቀው አሳብ ለመገላገል ሲል ማስታገሻ፣ ማደንዘዣና የሚጫጫኑ መድኃኒቶች ይወስዳል:: እንቅልፍ ሲወስደው አሳቡ ሊረጋጋ ቢችልም ከእንቅልፉ ሲነቃ ወይም ራሱን ሲያውቅ የቀደመ አሳቡ ወደ እርሱ ተመልሶ ይመጣል:: ስለሆነም እነዚህኑ መድኃኒቶች በድጋሚ ይወስዳል:: እንዲህ ያለው ድግግሞሽ ሳያቋረጥ ይቀጥላል:: መድኃኒቱ ጥሩ ውጤት ካሳየ በሽተኛው የሚወስዳቸው መድኃኒቶች መጠን ይጨምራል ወይም አስቀድሞ ከሚወስደው መድኃኒት የተለየ ወይም ብርታት የሚሰጥ ወይም ከማስታገሻ ይልቅ የሚያደነዝዝ መድኃኒት ይሰጠዋል:: ይህን ማደንዘዣ አብዝቶ መውሰድ ሲጀምር ልፍልፍስ ወይም ደካማ ወይም የደነዘዘ ይሆናል:: እዚህ ደረጃ ላይ ደርሶም ታዲያ አሳቡን አያቋርጥም::

ከዚህ በመቀጠል አንድ እውነታ እንነግራችኋለን:: መድኃኒቶች መፍትሔ የሚሆኑት ለውጤት እንጂ ለምክንያት አይደለም:: ምክንያቶች የሚሆኑት አሳቦችና ወደ ኀዘን የሚመሩ ስሜቶች ወይም እነዚህን የሚመስሉ አሳቦችና ስሜቶች ናቸው:: ከዚህ ሌላ የሥነ ልቦናው ዓይነትና ሕሊና ወሳኝነት አላቸው::

ለዚህ ሁሉ መድኃኒቶች የሚፈይዱት ምንድር ነው?

መድኃኒቶች አንዱን ሊያድኑ ቢችሉም ሌላውን ያጠፋሉ:: መድኃኒቶች የታመመው ሰው ያለበትን አሳብ እንዲረሳ ቢያደርጉትም ትውስታውን ሙሉ ለሙሉ ሊያዛቡበት ይችላሉ:: ሥነ ልቦናዊ ሕክምና በጥልቀት ከተሰጠ የኀዘንን ምክንያቶች ሊያስወግድ ይችላል:: ይሁን እንጂ የሕክምናው ችግር ረዥም ጊዜ መውሰዱ ነው:: በሽተኛው የሚያስጨንቀውንና በውስጡ ያለውን አሳብ ሙሉ ለሙሉ አውጥቶ መናገር ይፈልጋል:: ይህ ደግሞ ረዥም ሰዓት ስለሚወስድ ሐኪሙ ይህን የሚያደርግበት ሰፊ ጊዜ አያገኝም:: ከዚህ በተጨማሪ በሽተኛው ማለቂያ የሌላቸው ወጎችን ማውራት ይፈልጋል:: በዚህ ጊዜ የሕክምናው ባለሙያ ስለሚሰላች ጊዜው በከንቱ እንዳይጠፋበት ስጋት ላይ ይወድቃል::

የሐኪሙ መሰላቸት በሽተኛው የሚተርክለትን እንዳያዳምጥ ስለሚያደርገው ሕክምናው እዚህ ላይ ይገታል:: በሽተኛው ተመሳሳይ ታሪኩን ወይም ማማረሩን ለሐኪሙ ደጋግሞ ቢተርክለትና በዚሁ ምክንያት ቢማረር አንፈርድበትም:: ከዚህ በኋላ ሐኪሙ ለበሽተኛው ቀጠሮ መስጠቱ ጥቅም እንደማይኖረው ያስባል:: ምክንያቱም ካሁን በኋላ ቀጠሮ ቢሰጠው በሽተኛው

ተመሳሳይ ትረካውን እንዲቀጥል ስለሚያበረታታው እርሱን ሊጎዳው ስለሚችል ነው:: ከዚህ በተጨማሪ በሀኪሙና በበሽተኛው መካከል መቀራረብ ስለሚፈጠር በሽተኛው በሥራ ሰዓቱም ሆነ በእረፍት ጊዜው ያለማቋረጥ ስልክ እየደወለ ያደክመዋል::

በዚህ መሠረት ሥነ ልቦናዊ ሕክምና ረዥም ጊዜና ትዕግሥት ከመጠየቁም በላይ የሰውን ነፍስ ጥበብና እውቀት መረዳት እንደሚፈልግ ምንም ጥርጥር የለውም:: በሽተኛው በበሽታው ላይ ያለው ጥርጥር እውነት አለመሆኑን፣ ችግሩን ያመጡበት ምክንያቶች የተጋነኑ መሆናቸውንና ሙሉ ለሙሉ ከእውነት የራቁ መሆናቸውን ሀኪሙ በሚገባ ያውቃል:: ሀኪሙ ለበሽተኛው ይህን ጉዳይ ፊት ለፊት ሲገልጽለት በገዛ ራሱ አሳብ ላይ ይጸናል:: ይባስ ብሎም ሀኪሙን፣ ብቃቱንና ታማኝነቱን ይጠራጠራል:: ይህ በራሱ በሽታ ነው::

በዚህ አካሄድ ኀዘን ከውስጣዊ ወይም ከውጪያዊ ውጊያ ወደ በሽታነት ይለወጣል:: ይህን ሁሉ ማከም ይቻል ዘንድ ምርመራ ልናካሂድበት ያስፈልጋል:: ለኀዘን የምንወስደው ሌላ መፍትሔ መንፈሳዊ መፍትሔ ነው:: ስለዚህ መፍትሔ ከመነጋገራችን በፊት አንድ ነጥብ ልናነሳ እንወዳለን::

ጤናማ ያልሆነ ቅድስና::

ጤናማ ያልሆነ ቅድስና የተለያዩ ምክንያቶችና ምልክቶች ቢኖሩትም እኛ ለሚከተሉት ነጥቦች ትኩረት በመስጠት እንመለከታለን::

1/ ኀዘንን እንደ መንፈሳዊ መንገድ መውሰድ::
2/ በራስና በሌሎች ላይ ጭካኔን ማሳየት::
3/ ከአቅም በላይ የሆነ አሳባዊነት::

ብዙ መንፈሳዊ ሰዎች «. . . ከፊት ኀዘን የተነሣ ልብ ደስ ይሰኛል::» (መክ 7:3) ለሚለው ቃል አጽንኦት ይሰጡታል:: ከዚህ በተጨማሪ "The Paradise of the Monks" በተባለው መጽሐፍ ውስጥ «ወደ በአትህ ግባና ስለ ኃጢአቶችህ አልቅስ!» ተብሎ ለተገለጸው የቅዱሳን አባቶች ቃል አጽንኦት ይሰጡታል:: እነዚህ ሁሉ በራሳቸው ጊዜ ጥቅም የሚሰጡ መንፈሳዊ ንግግሮች ናቸው::

ይሁን እንጂ ኀዘን አንዳንድ ጊዜ ጥቅም ቢኖረውም በሕይወት ዘመን ሁሉ እንደ ቋሚ መንገድ ሊወሰድ አይገባውም:: ይህን የማይፈጽሙ መንፈሳዊ ሰዎች ስለ ደስታ ፈጽሞ አያወሩም:: ሰዎቹ ደስታን ለንስሓ የማያደርስ እንቅፋት አድርገው ሊቆጥሩት ይችላሉ:: ሌላው ቢቀር ሳቅን እንደ መንፈሳዊ ድካም ይወስዱታል::

እነዚህ ሰዎች ደስታን አስመልክተው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ:- «ሁልጊዜ በጌታ ደስ ይበላችሁ፤ ደግሜ እላለሁ ደስ ይበላችሁ::» (ፊል 4:4)፤«የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም . . .» (ገላ 5:22) ተብለው የተጠቀሱትን ቃላት የዘነጉ ሰዎች ናቸው:: ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ

ክርስቶስም እንዲህ ብሏል፦ «. . . ነገር ግን እንደገና አያችኋለሁ፤ልባችሁም ደስ ይለዋል፤ደስታችሁንም ማንም አይወስድባችሁም።» ዮሐ 16:22። በዚህ መሠረት አስቀድሞ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ «. . . ከፊት ኀዘን የተነሣ ልብ ደስ ይሰኛል።» (መክ 7:3) ተብሎ የተጠቀሰው ቃል ድንቅ መሆኑን እንመለከታለን።

ከዚህ በተጨማሪ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ እንዲህ የሚል ቃል ተጽፎ እናነባለን፦ «ለሁሉ ዘመን አለው . . . ለማልቀስ ጊዜ አለው፣ ለሳቅም ጊዜ አለው . . .» መክ 3:1እና4። ከመጠን የበዛ አከራረኑትና ስለ ኀዘን ሳያቋርጡ ማውራት ኀዘንን በሰው ውስጥ ይተክላል። አንዳንዶች ከዚህ ዓይነቱ አካሄድ በጥበብና በብልሃት ሲርቁ በአንዳንዶች ውስጥ ግን በሽታ ሆኖ ይቀራል። በእነዚህ ሰዎች ፊት ማንኛውም ነገር ወደ ኀዘን የሚመራ ነው።

ነቢዩ ዳዊት መኝታውን በየዕለቱ በዕንባዎቹ ያርስ ስለ ነበር ኀዘን ለንስሓ እንደሚያደርስ አውቀናል። ነቢዩ ኤርምያስ በሰቆቃው ውስጥ እንደ ቆየ ነህምያም ለኢየሩሳሌም አልቅሷል። በዚህ መሠረት አገልግሎት ለኀዘን ይጠራል ማለት ነው። ነቢዩ ዳዊት በመዝሙራት መጽሐፉ ውስጥ «ሕግህን ከተዉ ከኃጢአተኞች የተነሣ ኀዘን ያዘኝ።» ብሏል። መዝ 118:53።

ትሕትና በኀዘን መታጀብ አለበት። አንድን ሰው በጸሎት ሳይ እያለ ስትመለከቱት የፊቱ ገጽታ ከመከለከሉ የተነሣ መቃብር ይመስላል። ይህ ገጽታው እናንተን ሊያስጨንቃቸሁና ሊያውካችሁ ይችላል።

መንፈሳዊ ኀዘን ቢኖርም በመጽናናት ይታጀባል፤ቅዱስ ኀዘን ቢኖርም በተስፋ ይታጀባል። በመሆኑም በጌታ መደሰት የእነዚህ ሁሉ ስሜቶች ቅንብር ነው። በሌላ በኩል ያለ መጽናናትና ያለ ተስፋ ወይም ያለ ጌታና ያለ ሥራዎቹ በሚሆን ኀዘን ላይ አጽንኦት የሚሰጡ ሰዎች ክርስትናንም ሆነ መልካም ዜና የተባለውን መጽሐፍ ቅዱስን የማይረዱ ሰዎች ናቸው።

እነዚህ ሰዎች ለሰዎች የሚያቀርቡት ምሳሌ የሚያሳዝን ነው። አንዳንድ ሰዎች ደስታ፣ ፈገግታ፣ ሳቅና የሚያበራ ገጽታ ወደሌለበት ቅድስና በመግባት ፊታቸውን እንዳያጠቁሩና ገጽታቸውን እንዳይከሰክሱ በመፍራት ከእነዚህ ሰዎች ርቀው ይሄዳሉ። ለነዚያኖቹ ሰዎች መንፈሳዊነት ማለት የማይቋረጥ ዕንባና ሊገለጽ የማይቻል ጥብቅነት ነው። እነዚህ ሰዎች ወደ ደስታ በሚመራው መንፈሳዊ ዕንባና ነፍስን ወደ ድቅድቅ ጨለማ በሚመራው ዕንባ መካከል ያለውን ልዩነት እንዲያውቁ ይመከራሉ። ከእግዚአብሔር ጋር መወዳጀት ማለት መጽናናት የሌለበትና የማያቋርጥ ኀዘን የሚገለጽበት መወዳጀት ማለት ነው? ሰውን ወዳጁና ርኅሩኑ እግዚአብሔርስ ዘወትር ስናዝንና ስናለቅስ ሊመለከተን ይፈልጋል ማለት ነው? ልብን ደስ የሚያሰኘው ኀዘን ልብ ከተሻለው በኋላ ማዘኑን መቀጠል አለበት ማለት ነው? እንዲህ ዓይነቱ ኀዘን ለደስታና ለሰላም የሚሰጠው ቦታ የለውም ማለት ነው? ለሁሉም መልሳችን ኦሎታዊ ነው።

ሌላው ነጥብ አሳባዊነት ነው።

አሳቦችን ማሰብ ሙሉ ለሙሉ አላስፈላጊ አይደለም። ይሁን እንጂ አሳብ የምንፈልገው የብቃት ደረጃ ላይ መድረስ አለመቻላችንን ስለሚያሳየን የማያቋርጥ ኀዘን ውስጥ ይከተናል። ከዚህ በተጨማሪ የብቃቱ መንገድ ረዥም መሆኑንና በእርሱ ላይ ለመንገዝ ከፍተኛ ጥረትና ትዕግሥት እንደሚያስፈልገው ያሳየናል። በዚህ መንገድ ላይ ወደፊት በምንራመደው በእያንዳንዱ እርምጃ ልንደሰት ይገባናል። ለሚቀሩን እርምጃዎችም ልናዝንና ልንተክዝ አይገባንም። እንደዚህ ዓይነቱ ደስታ ኩራትንና የልብ ትዕቢትን እንደሚደብቅ አድርጋችሁ አታስቡ። ምክንያቱም የምንደሰተው በሰብአዊው ኃይላችንና ጥረታችን ላይሆን በሚረዳን አምላካችን ስለሆነ ነው። ስለሆነም ለኀደለን ነገር ከምናዘን ይልቅ እግዚአብሔር ድካማችንን እንዲያግዝና ለብቃት ደረጃ እንዲያደርሰን ወደ እርሱ እንጸልይ። ኀዘን እንቅፋት እንጂ መፍትሔ ሊሆነን አይችልም። ይልቁኑም ጠላታችን ዲያብሎስ እኛን ተስፋ ለማስቆረጥ የሚጠቀምበት መንገድ ሊሆን ይችላል።

ከዚህ በመቀጠል ስለ መንፈሳዊ መፍትሔዎች እንነጋገራለን።

የኀዘን መንፈሳዊ መፍትሔዎች።

መንፈሳዊ ሰው ጤናማ ካልሆነ ኀዘን ሙሉ ለሙሉ ነጻ ነው። አንዳንድ ጊዜ ቢያዝንም ኀዘኑ ለጥቂት ጊዜ የሚቆይ መንፈሳዊ ወይም ተፈጥሮአዊ ኀዘን ነው። የእርሱ ኀዘን መሠረቱ መንፈሳዊ ስለሆነ ጤናማ ላልሆነ ኀዘን ቦታ የለውም። ከዚህ በመቀጠል መንፈሳዊ ኀዘን የሚታወቅባቸውን ሰባት የቅድስና መንገዶች እንዘረዝራለን። በእግዚአብሔርና በሥራው ማመን፣ ተስፋ፣ ይበቃኛል ማለትና ምድራዊ ነገሮችን መናቅ፣ የምስጋና ሕይወት፣ ደስታና ፈገግታ፣ እውነተኝነት፣ ትዕግሥትና ራስን መግዛት ናቸው።

ከዚህ በመቀጠል ስለ እያንዳንዱ የቅድስና ደረጃ ባጭር ባጭሩ እንነጋገራለን። ከዚህ በተጨማሪ እያንዳንዱ ቅድስና ከኀዘን ጋር ስላለው ግኑኝነት፣ ስለ ኀዘን መፍትሔና ከኀዘን ስለ መጠበቅ እንወያያለን።

እምነት እንደ መፍትሔና እንደ ጥበቃ።

እግዚአብሔር ዓለምን የሚገዛና ልጆቹን የሚጠብቅ ኃያል አምላክ መሆኑን እናምናለን። እርሱ ልጆቹን ከመውደዱም በላይ ስለ እነርሱ ስለሚያስብ በእጁ መዳፎች ውስጥ ቀርጾአቸዋል። ኢሳ 49:16። ከዚህ በተጨማሪ ያለ እርሱ ፈቃድ ከፀጉራቸው አንዲቱ እንኳ ልትጠፋ አትችልም። ሉቃ 21:18። እርሱ ካልፈቀደ ምንም ዓይነት መከራ ሊደርስባቸው አይችልም። ቢደርስባቸውም መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚናገር ወደፊት ለበጎ እንዲሆንላቸው ነው። «እግዚአብሔርንም ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን።» ሮሜ 8:28።

ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብም ይህን አስመልክቶ እንዲህ በማለት ተናግሯል፦ «ወንድሞቼ ሆይ የእምነታችሁ መፈተን ትዕግሥትን

እንዲያደርግላችሁ አውቃችሁ ልዩ ልዩ ፈተና ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቁጠሩት።» ያዕ 1:2። መከራና ፈተና በአማኝ ውስጥ ደስታን እንጂ ጭንቀትን አይፈጥሩም። መጽሐፍ ቅዱስ ይህን አስመልክቶ፡- «. . . ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በብዙ መከራ እንገባ ዘንድ ያስፈልገናል።» (ሐዋ 14:22) በማለት ይመክረናል።

አንድ አማኝ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ጎብረት ይፈጥር ዘንድ በመከራው ሊካፈለውና በሞቱ ሲመስለው ያስፈልጋል። ፊል 3:10። ከዚህ በተጨማሪ መስቀሉን በመያዝ ትእዛዛቱን ይይዛል። «. . . መስቀሉንም የማይዝ በኋላዬም የማይከተለኝ ለእኔ ሊሆን አይገባውም።» ማቴ 10:38። በጠባቢ ደጅ እንድንገባ የተሰጠን ትእዛዝም አለ፡- «ወደ ሕይወት የሚወስደው ደጁ የጠበበ መንገዱም የቀጠነ ነውና የሚያገኙትም ጥቂቶች ናቸው።» ማቴ 7:14።

በዚህ መሠረት አንድ አማኝ የሚያዝነው ፈተና ሲገጥመው ሳይሆን የሚገዝበት የክርስትና መንገድ ከፈተና የጸዳ ሲሆን ነው። እንዲህ ያለው አካሄድ በእርሱ ዘንድ ጤናማ አይደለም። ስለሆነም ያለ ማቋረጥ በዕረፍት ውስጥ የሚኖር ከሆነ ይህን በመጠርጠር 'ምናልባት መንገዱን ስቼ ሳልወጣ አልቀረሁም!' ይላል።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንደ ተናገረ አንድ እውነተኛ አማኝ ፈተና ሲገጥመው ይደሰታል። «ስለዚህ ስለ ክርስቶስ በድካም፣ በመንገላታትም፣ በችግርም፣ በስደትም፣ በጭንቀትም፣ ደስ ይለኛል . . .» 2ኛ ቆሮ 12:10። ስለሆነም መከራና ፈተና ሲገጥመው ቅዱሳን ሐዋርያት፣ አባቶችና ነቢያት በተገዙበት ተመሳሳይ መንገድ ላይ እየተገዘ መሆኑ ይታወቀዋል። በዳድቁ ኢዮብና በድሀው አልዓዛር መንገድ ይደሰታል። የሚደሰተውም በዚህ መንገድ ላይ በዛ ያሉ መጽናኛዎች እንደሚጠብቁት ስለሚያውቅ ነው።

ስለሆነም እውነተኛ አማኝ ዋጋውን ወይም የእርሱን መልካም ነገሮች የሚቀበለው በዚህ ምድር ላይ ባለው ሕይወቱ እንዳልሆነ ያውቃል። እርሱ የሚጠባበቀው ተስፋ «እግዚአብሔር የሠራትንና የፈጠራትን ከተማ . . .» ነው። ዕብ 11:10። ይህን ሁሉ ታግሦ የሚጠባበቀውም በደስታ ውስጥ ሆኖ ነው።

አንድ አማኝ ስለ እግዚአብሔር ፍቅር፣ ቸርነት ርኅራኄና ለልጆቹ ስለ ገባው ቃል ኪዳን የተጻፉ ጽሑፎችን ያነባል። ለምሳሌ በረሀቡ ዘመን ለነቢዩ ኤልያስና ለመበለቷ ሴት፣ በተራቡ አናብስት ጉድጓድ ውስጥ ለተጣለው ለዳንኤልና በአባቱ ነበልባል ውስጥ ለተጣሉት ሦስት ወጣቶች ስላዘነላቸው ከመከራ አድኗቸዋል። 1ኛ ነገ 17፣ዳን 3 እና 6። ከዚህ በተጨማሪ አንድ እውነተኛ አማኝ እግዚአብሔር ለመናንያንና ለባሕታውያን ስላደረገው ጥበቃ፣ ስለ ለማዕታት፣ ስለ ነቢያት፣ ስለ ቅዱሳንና እግዚአብሔር ንስሓዎቻቸውን ስለ ተቀበላቸው ሰዎች የተጻፉ ጽሑፎችን ያነባል።

ከዚህ እምነት ጎን ለጎን በእግዚአብሔር ሥራዎችና መደፊት ለእርሱ በሚያደርጋቸው ነገሮች ላይ ተስፋ ያደርጋል።

ተስፋ ለጎዘን ያለው መፍትሔ።

ተስፋ ማለት ስለ ወደፊቱ መልካም አመለካከት ማሳደር ማለት ነው። የተፈለገውን ያህል ሁኔታዎች ጫና ቢያሳድሩና ጉዳዮች የተወሳሰቡ ቢሆኑ አንድ ሰው ተስፋ ሊቆርጥ አይገባውም። በተስፋ የሚኖር ሰው በቅርቡ በሚያገኘው መፍትሔ ሐሴት ያደርጋል እንጂ አሁን ባለው መከራ አይታወክም። ይህ ደግሞ ሰውየውን ሁልጊዜ መልካም አመለካከት እንዲኖረው ያደርገዋል፣ ሁሉም ስህተት ሊታረም እንደሚችል ያሳየዋል፣ ማንኛውም መዝጊያ እንደሚከፈትም ያሳውቀዋል።

ተስፋ መቁረጥ ጎዘንን እንደሚያመጣ ሁሉ ጎዘንም ተስፋ መቁረጥን ያመጣል። አንዱ ለሌላው ምክንያትም ውጤትም ነው። እውነተኛ አማኝ ግን ከሁለቱም የራቀ ነው። በተስፋ ውስጥ መፍትሔውን ይመለከታል። ይህ ደግሞ ሐዋርያው «በተስፋ ደስ ይበላችሁ . . .» (ሮሜ 12:12) ብሎ እንደተናገረው ልቡን በደስታ ይሞላል። ይህ በተስፋ የሚገኝ ደስታ ውጤቱ በእምነት ውስጥ ስለሚጠበቅ ሰውየውን ትዕግሥተኛና ራሱን የሚገዛ ያደርገዋል።

ትዕግሥት ለጎዘን ያለው መፍትሔ።

ለችግሮቹ ፈጣን መፍትሔ የሚፈልግ ሰው በቀላሉ በጎዘን ይወድቃል። ለዚህ የሚበቃውም ችግሮቹ ላይቃለሉ ቀናቱ እየነጎዱ ሲሄዱ ሊመለከት ነው። ቻይ ሰው ግን ለችግሩ መቃለል ጊዜ ይሰጣል። እግዚአብሔር ባጭር ጊዜ ውስጥ እንደሚመጣ ቢያምንም ለረዥም ዓመታት ሊጠብቀው ዝግጁ ነው። **የሚጠብቀውም ያለ መለላቸት፣ ያለ ጎዘንና ያለ መቻኮል** ነው። እርሱ ጌታውን **የሚጠብቀው በደስተኛና ሙሉ ለሙሉ** በእርሱ በሚተማመን ልብ ነው።

ስለዚህ «በእርግጥ ጌታ ይመጣል . . . መቼ እንደሚመጣ ግን አላውቅም። ከእኔ የሚጠበቀው የሚመጣበትን ቀን ማወቅ ሳይሆን እንደሚመጣ ማመን ነው።» ይላል። በመሆኑም እግዚአብሔር የሚመርጠው ጊዜ ከሁሉ የሚሻለውንና ምቹ የሆነውን ጊዜ ነው። ይህ ጊዜ የሚመረጠው በእግዚአብሔር ጥበብና በመለኮታዊ አሠራሩ ነው። ይህን አስመልክቶ ነቢዩ ዳዊት እንዲህ ይላል፡- «እግዚአብሔርን ተስፋ አድርግ፣በርታ ልብህም ይጽና፣እግዚአብሔርን ተስፋ አድርግ።» መዝ 26:14።

ይህን ስታነብ «እስከ መቼ?» ብለህ ትጠይቅ ይሆናል። መዝሙረኛው «ከማለዳው ሰዓት ጀምሮ እስከ ሌሊት ነፍሴ በእግዚአብሔር ታመነች።» ይልሃል። መዝ 29:6። «እኔ ትዕግሥት ከሌለኝ እንዴት ልቀይ እችላለሁ?» ስትል የሰማሁህ መሰለኝ። የምሰጥህ መልስ ችግሮቹ ትዕግሥትን ያስተምሩህ የሚል ነው። እምነትና ተስፋም ትዕግሥተኛ መሆንን በተግባር ያለማምዱህ። በትዕግሥት መጠበቅ ካልቻልህ ትደክማለህ ታዝናለህም። ትዕግሥት የሚሻል ቢሆንም በመተማመንና በእግዚአብሔር ሥራ በማመን ይሁን።

ዓለምንና በዓለም ያሉትን አለመውደድ።

ይህ ኀዘንን ሙሉ ለሙሉ የሚያስወግድ ቅድስና ነው። ምክንያቱም ማንኛውንም ዓይነት ምኞትና ፍላጎት መተው የሚችል ሰው እንዳችም የሚያዝንበት ምክንያት አይኖረውም። በየዕለቱ በቤተ ክርስቲያን በሚደረገው ቅዳሴ ውስጥ «ዓለምን ወይም በዓለም ውስጥ ያሉትን አትውደዱ . . . ዓለሙም ምኞቱም ያልፋሉ . . .» (1ኛ ዮሐ 2:15-16) እንላለን።

ክብሩ፣ ዝናው፣ ሀብቱ፣ ሥልጣኑና ሌሎቹም ነገሮች በሙሉ ጊዜያዊ ናቸው። አንድ አማኝ ሰው እነዚህንና እነዚህን የመሰሉትን ባለማግኘቱ ተስፋ ሊቆርጥና ሊያዝን አይገባውም። ቅዱስ ጳውሎስ ሐዋርያ ይህን አስመልክቶ ሲናገር «. . . በእርሱ እገኝ ዘንድ ሁሉን እንደ ጉድፍ እቆጥራለሁ።» (ፊል 3:8) ብሏል። በእርግጥም ሁሉን ነገር እንደ ጉድፍ የሚቆጥር ሰው ምንም ቢያጣ አያዝንም። ቅዱስ አውግስጢን «በውስጤ ምንም ዓይነት ነገር እንደማልፈራና ምንም እንደማልመኝ ሲታወቀኝ በዓለም ጫፍ ላይ የተቀመጥሁ ይመስለኛል።» በማለት ተናግሯል።

አንድ ሰው እንደዚህ ሁሉን ነገር ንቆ የመተው ቅድስና ባይኖረውም እንኳ ባለው የመርካት ቅድስና ይኑረው። ባለው ይደሰት፣ የሌለውን አይፈልግ፣እግዚአብሔር እንዲኖረው የፈቀደለት ብቻ ይኑረው። እርሱ ስለ ራሱ ማሰብ ከሚገባው በላይ ራሱን አማዝፎ አያስብ። ይህን አስመልክቶ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦ «እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ የእምነትን መጠን እንዳካፈለው እንደ ባለ አእምሮ እንዲያስብ እንጂ ማሰብ ከሚገባው አልፎ በትዕቢት እንዳያስብ . . . በተሰጠኝ ጸጋ እናገራለሁ።» ሮሜ 12:3። እንዲህ ዓይነቱ ሰው በጭራሽ አያዝንም። ይልቁንም በደስታ ውስጥ ሆኖ «ሰውን የሚወድ እግዚአብሔር በዚህ ጉዳይ የሚደሰት ከሆነ እኔም እደሰታለሁ!» ይላል። ይህ የሚረዳው ኀዘንን እንዲያስወግድ ብቻ ሳይሆን የምስጋና ሕይወትንም እንዲመራ ነው።

የምስጋና ሕይወት እንደ ጥበቃና መፍትሔ።

የምስጋና ሕይወትን ለመምራት የተለማመደ ሰው በጭራሽ አያዝንም። ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ይለናል፦ «. . . ስለ ሁሉ አመስግኑ።» (ኤፌ 5:20)፤«ሁልጊዜ ደስ ይበላችሁ . . . በሁሉ አመስግኑ . . .» 1ኛ ተሰ 5:16 እና 18።

ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ማንኛውም ጸሎት በምስጋና ጸሎት እንዲጀመር ያደረገችው እንድንጸልየው ብቻ ሳይሆን በምስጋና ሕይወት ውስጥ እንድንኖርም ጭምር ነው እግዚአብሔርን የምናመሰግነው ስለ ሁሉም፣ ለሁሉምና በሁሉም ጉዳዮቻችን ውስጥ ነው። በጣም የምንወደው አንድ ሰው ቢሞት እንኳ ጸሎታችንን የምንጀምረው ምስጋና በማቅረብ ነው። ምስጋና የምናቀርብ ከሆነ ለምንድር ነው የምናዝነው?

ጸሎቱን ሳይኖሩበት እንዲሁ በአንደበታቸው የሚያነበንቡት ሰዎች እንዳሉ እርግጥ ነው። አንተ ግን የምስጋና ሕይወት ለመምራት ራስህን

አስለምድ። በማንኛውም አጋጣሚ የሆነ ችግር ቢያጋጥምህ እንኳ ለእግዚአብሔር ምስጋና በማቅረብ ለራስህ እንዲህ በል፦ «እኔ ባላውቀውም ከዚህ ችግር በስተጀርባ አንድ በጎ ነገር አለ . . . ማንኛውም ዓይነት መጥፎ ነገር ቢኖርም እንኳ አንተ ቸርና ሰውን የምትወድ አምላክ ስለ ሆንህ ለበጎ አድርገህ ትቀይረዋለህ።»

በምስጋና ሕይወት የሚመራ ሰው በእግዚአብሔር ቸርነት፣ በጎነት፣ ፍቅርና ጥበብ የሚያምን እውነተኛ አማኝ ለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም። እንደዚህ ዓይነቱ አማኝ አመስጋኝነቱን ሊያጣና ለመለኮታዊው ፈቃድ ለመገዛት ሊያቅተው በኀዘን ስለሚወድቅ እምነቱ ከፉኛ ይናጋል። በሌላ በኩል ስለ ማንኛውም ነገር ምስጋና የሚያቀርብ ሰው ከኀዘን ወሰን በላይ ነው። ከዚህ በተጨማሪ የደስታ ሕይወትን ጨምሮ ይጎናጸፋል።

ደስታ እንደ ጥበቃና መፍትሔ።

በጌታ የሚደሰት ሰው በሚኖርበት ዘመኑ ሙሉ ሕይወቱ በኀዘን አይጠቃም። እርሱ እግዚአብሔርን ስላገኘ ይደሰታል። ከእርሱ ሌላ ምንም አይፈልግም። እርሱ ከእግዚአብሔር ጋር ስለሆነ ስለ ምንም ነገር አያዝንም። በደስታ ሕይወት ውስጥ መኖርን የተለማመደ ሰው ከኀዘንና ከምክንያቶቹ ማምለጥ ይችላል። ከችግር ጋር በተጋፈጠ ቁጥር ስለ እርሱ ብዙ አያስብም ወደ ጥልቅ ሕማሙም ዘልቆ አይገባም። ይልቁንም ደስታው እንዳይታወክበት ኀዘንን ከእርሱ ላይ አሽቀንጥሮ ይጥላል።

ዲያብሎስ ደስታውን ከእርሱ በመውሰድ በተሰፋ መቁረጥ ውስጥ ሊጥለው ሲፈልግ የሚቃጣው ኀዘንን እንደ ሆነ ይገነዘባል። በዚህ ጊዜ እጹን ለዲያብሎስ ከመስጠት ይልቅ ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያቱ የተናገረውን ቃል ያስታውሳል፦ «. . . ደስታችሁንም የሚወስድባችሁ የለም።» ዮሐ 16:22።

ስለሆነም የደስታን ሕይወት በመኖር ኀዘንን የሚጠራብህን ጤናማ ያልሆነ ቅድስና ከአንተ አርቅ። ለደስታ የሚጠሩህን ጥቅሶች በቃልህ በማጥናት ችግር ባጋጠመህና በኀዘን በተጠቃህ ቁጥር አስታውሰህ አዚማቸው። አንተ ከደስታ ጋር ስትሆን ለሌሎች የጤናማ ቅድስና ምሳሌ ከመሆንህም በላይ የደስታ ፍሬ በልብህ ውስጥ ይጎመራል። በዚህ ጊዜ ሰዎች አንተን ደስተኛ ወደ አደረገህ ሃይማኖት ይሳባሉ። ከዚህ በተቃራኒ ሌሎች ሰዎች ከዚሁ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ኀዘን ሲደርስባቸው ኀዘንን በመፍራት የሰዎችን ሕይወት ጤናማ ወዳልሆነ መንገድ ይመራሉ።

«ደስታ» ብለን ስንናገር የምንናገረው ስለ ዓለማዊው ደስታ ሳይሆን ጥልቅና እውነት ስለ ሆነው ስለ እግዚአብሔር ደስታ ነው። ይህ ደስታ ውስጣዊ ሰላምንና እምነትን የሚያጎናጽፍ ነው። በመሆኑም በፊቱ ላይ የሚንበለበለው ሐሴት ደስተኛ ሕይወትን በመምራት የሚኖር ሰው መሆኑን በሰው ሁሉ ፊት ይመሰክራል። ደስተኛ ሰው መከራዎች ቢኖሩበትም እንኳ ሁልጊዜ በደስተኛ ገጽታው ኑሮትን ያጽናናል። እርሱ በችግር ቢከበብም ችግሩን ከልቡ ውስጥ ፈጥኖ ያስወጣዋል እንጂ ጠልቆ እንዲቀመጥ አይፈቅድለትም።

እርሱ ከተወሳሰቡ ነገሮች የራቀ ስለ ሆነ ችግሮችን የሚመለከተው አቅልሎ ነው። ከአንድ ችግር ጋር ሲጋፈጥ በሚችለው አቅሙ መፍትሔውን ለማግኘት ይሞክራል። ከዚህ በኋላ ችግሩን ሙሉ ለሙሉ በጌታ ላይ በመጣል ደስታውን ጠብቆ ይኖራል።

ሴላው የኀዘን መፍትሔ እውነታ ነው።

እውነታ።

እውነታ ብለን ስንናገር ሰው ሊኖር የሚገባው በእውነት እንጂ በአሳብ ወይም በአሳብ ዓለም አለመሆኑን ለማመልከት ነው።

በፊት ለፊትህ በአሳባዊ ሕይወት እኖራለሁ ብለህ አታስብ። ሌሎችም በአሳባዊ አኗኗር እንዲኖሩ አትፈልግ። ይህ አሳባዊ ኑሮ ተግባራዊ መሆን ሲሳነው በኀዘን ትወድቃለህና።

በጣም የምትወደውን ሰው በሞት ብታጣ ወይም አንድ ዕድል ቢያመልጥህ ወይም የሆነ ነገር ብታጣ ወይም በበሽታ ብትታመም ትክክለኛ ሰው ሁን። ልታደርገው የሚገባህን ነገር ካደረግህ በኋላ ሌላውን ለእግዚአብሔር ተወው። አንተ ሊኖረኝ ይገባኛል ያልከውን የአሳብ ሥልጣን በማስላሰል በኀዘን ውስጥ አትኑር። አንድ ሰው አደጋ ደርሶበት እጁ ወይም እግሩ በህክምና ቢወገድ ቀሪ የሕይወት ዘመኑን በኀዘን ማሳለፍ አለበት ማለት ነው? እንደዚህ ያለው አሳብ ትክክል አይደለም።

ሴላው ምሳሌ ወይም ነጥብ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችን ጨምሮ በሰው ሁሉ ዘንድ አሳባዊ አስተሳሰብ እንደሌለ አድርገህ አታስብ። እነዚህ አገልጋዮች ሰዎች መሆናቸውን ባለመገንዘብ ከዚህ አስበልጠህ ስትመለከታቸው ከቆየህ በኋላ ከዕለታት አንድ ቀን የሚሳሳቱ ሰዎች መሆናቸውን ስትገነዘብ ትደነግጣለህ ወይም ታዝናለህ ወይም ትጠፋለህ። ከእነርሱ መካከል አንዱን ሲሳሳት ከተመለከትኸው ጸልይለት እንጂ በእርሱ ምክንያት አትታወክ። መጽሐፍ ቅዱስ የሐዋርያትን፣ የነቢያትንና የቅዱሳን ሰዎችን ስህተት መግለጡንና ከእነዚህ ስህተቶቻቸው በኀሳፊ ሊመለሱ ደግሞ በእግዚአብሔር ዘንድ ሞገስ ማግኘታቸውን መዘገቡን አስታውስ። የሰዎች ስህተት ሊሆን የሚችል ነገር መሆኑን አስብ። የሰው ልጆች ተፈጥሮ ደካማ ስለሆነ ይህ የሰዎች ስህተት አንተን አያጥፋህ።

ብዙ ሰዎች በሌሎች ሰዎች ጠባይና ስህተት ይታወካሉ። እነዚህ ሰዎች አለመሳሳት የእግዚአብሔር ባሕርይ ብቻ መሆኑን የዘነጉት ይመስላሉ።

ኀዘንን በቅድስና ማከም።

ለዚህ ምሳሌ አድርገን የምናቀርበው ጥቂት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን በትክክል ባለመረዳት አንድ ሰው የፈጸመው ኃጢአት ይቅርታ የለውም ብሎ ድምዳሜ ላይ መድረስን ነው። ሰው እነዚህን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች በሚገባ ሊረዳ ይገባዋል። ወደ መረዳት ሊደርስ ካልቻለ ግን እውቀቱ ያላቸውን ሰዎች መጠየቅ አለበት። አንዱ ያስረዳውን ሊያምን ካልቻለ ወደ ሌላው ይሂድ። ይህን በማድረጉ ግን ኀዘን ውስጥ መውደቅ የለበትም።

ለዚህ ምሳሌ የሚሆኑን ጥቂት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የሚከተሉት ናቸው።

1/ መንፈስ ቅዱስን የመስደብ የሚመጣ ኃጢአት።

አንድ ሰው መንፈስ ቅዱስን በመሳደቡ የወደቀበት ኃጢአት ተስፋ እንደሌለውና ከቅጣት ሊያመልጥ እንደማይችል ጤናማ ያልሆነ የኀዘን ስሜቱ

ሊያሳስበው ይችላል። ለዚህ ዓይነቱ ሰው የመንፈስ ቅዱስን አምላክነት የካዱ ሰዎች ኀጢአት ሲገቡ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንደ ተቀበለቻቸው እንነግረዋለን።

የእግዚአብሔርን ስም መስደብ ማለት በመንፈስ ቅዱስ ላይ ክፉ ማሰብ ወይም በእርሱ ላይ ክፉ ቃላትን መሰንዘር ማለት አይደለም። ይህን ያደረጉ ሰዎች ይቅር ተብለዋልና። ይቅርታ ሊያገኝ የማይችለው ኃጢአት ኀጢአት ብቻ ነው። መንፈስ ቅዱስን መስደብ ማለት የመንፈስ ቅዱስን አሠራር በሕይወት ዘመን ሙሉ በልብ ውስጥ መቃወም ማለት ነው። በመሆኑም ኀጢአት የሚገኘው በመንፈስ ቅዱስ አሠራር ውስጥ ስለሆነ ኀጢአት ልትገባ አትችልም ማለት ነው።

ኀጢአት አለመግባት ማለት ደግሞ ይቅርታ ማግኘት አለመቻል ማለት ነው። ከብዙ ዓመታት በኋላ ኀጢአት ብትገባም የቀደመ ተቃውሞህ እስከ ሕይወትህ ፍጻሜ ድረስ አብረውህ ሊኖሩ ስለማይችሉ ስድብ ተብለው አይቆጠሩብህም።

2/ ሰዎችን ከሚያውኳቸው ጥቅሶች መካከል ስለ ዔሳው የተነገረው ጥቅስ ሌላው ምሳሌያችን ነው።

ጥቅሱ እንዲህ ይላል፦ «. . . በእንባ ተግቶ ምንም ቢፈልገው ለንስሓ ስፍራ አላገኘምና።» ዕብ 12:17።

ይህ የተጠቀሰው ለኃጢአት ሳይሆን ዔሳው ክርስቶስ ከበኩር ልጅ እንደሚመጣ እያወቀ ብኩርናውን ስለ ሸጠ ነው። ይህ በመሆኑም ክርስቶስ በአንድ ጊዜ ከያዕቆብም ሆነ ከዔሳው ልጆች ሊወለድ ስለማይችል የዔሳውን ብኩርና ከወሰደው ከያዕቆብ ልጆች ተወልዷል። ዔሳው ንስሓ የገባበት ምክንያት ይህ ቢሆንም ንስሓ የገባው በንስሓው ሊጠቀም የሚችልበት ጊዜ ካመለጠው በኋላ ስለ ነበር ነው።

የተቀሩት ሌሎች ንስሓዎች ይቅርታ እንዳላቸው ለማመልከት ኢየሱስ ክርስቶስ «. . . ወደ እኔ የሚመጣውንም ወደ ውጭ አላወጣውም።» (ዮሐ 6:37።) በማለት ተናግሯል። ስለሆነም በማንኛውም ጊዜ ንስሓ ለመግባት ወደ እርሱ ብትቀርብ እርሱ ወደ ውጭ እንደማያወጣህ በመለኮታዊ ቃል ኪዳኑ አረጋግጦልሃል።

3/ አንዳንዶች ከሚወድቁባቸውና ወደ ኀዘን ከሚመሯቸው ስህተቶች መካከል በእግዚአብሔር ፍቅር ላይ ከማተኮር ይልቅ በኃጢአት ላይ የማተኮራቸው ነገር ነው። ይህን በማስመልከት እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ «. . . ኃጢአታችሁ እንደ አሰላ ብትሆን እንደ አመዳይ ትሆናለች . . .» ኢሳ 1:18።

ይህን አስመልክተው አንድ አባት ሲናገሩ በሰዎች ዘንድ ያለው ኃጢአት ሁሉ ከእግዚአብሔር ቸርነትና ምሕረት ጋር ሲነጻጸር በውቅያኖስ ውስጥ እንደ ተጣለ ፍንጣቂ ሟቃ ይቆጠራል ብለዋል። በዚህ መሠረት ቀሳውስት፣ መነኮሳትና ሰባክያን አንድን ሰው በተሰፋ መቁረጥ አፋፍ ላይ ቆሞ ቢያገኙት ስለ ኃጢአቱ አስከፊነት በመግለጽ ጫና ከሚጥሉበት ይልቅ ቸር፣ ሰውን ወዳጅ፣ ርኅሩኅና

ይቅርታውን ለኃጢአተኞች ስለ ገለጠው እግዚአብሔር ቢነግሩት ነፍሱን ሊያድኗት ይችላሉ።

4/ ሊገኝ ስለማይቻል ብቃት ማውራት ሌላው ወደ ጎዘን የሚመራ መንገድ ነው።

ሰዎች ስለ ብቃት ደረጃ ከመናገር ይልቅ ዋጋ አይኖረውም የተባለውን እነስተኛ ነገር ስለሚቀበለው እግዚአብሔር ሊያወሩ ይገባቸዋል። አምላካችን እግዚአብሔር የሚያወድሰው አንድ ብርጭቆ ቀዝቃዛ ውኃ የሚያጠጣውን ሰው፣ የሰሎሞንን ጥበብ ለማየት ከደቡብ የመጣችውን ንግሥትና ሁለት ሳንቲም በሙዳይ ምጽዋቱ ውስጥ የጣለችውን መበለት ነው።

5/ አንዳንዶች የቅዱሳንን ዕንባ አስመስለው ለማንባት ሲሞክሩ ካልተሳካላቸው ጎዘን ውስጥ ይወድቃሉ። የቅዱሳን ዕንባ የንስሓና የፍቅር ዕንባ ቢሆንም እነርሱ ደስታቸውን በሰዎች ሁሉ ፊት እንደሚገልጡ ማወቅ አለብን። ለዚህ ምሳሌ የሚሆነንም የቅዱስ አባ እንጦንስ፣ የአባ መቃርስና የአባ ሴራጲዮን ሕይወት ነው።

ማጠቃለያ።

ሰዎች ሁሉ ከመንፈሳዊ ሕይወታቸው ውስጥ ብኩንነትን ያስወግዱ ዘንድ ትኩረታቸውን ወደሚከተለው እውነታ እንስባለን።

የአሁኑ ዓለም ክችግር የተላቀቀ አይደለም። ስለሆነም እውነተኞችና ሁሉን ዓይነት መከራ ቢገጥመን ሐሴት ለማድረግ ራሳችንን ያስለመድን እንሁን። እያንዳንዱ ችግር መፍትሔ ስላለው የችግሮቻችንን መጠን አናጉላው ወይም ለችግሮቻችን መፍትሔ የማግኘቱን ነገር አስቸጋሪ አድርገን አናሳድገው።

አንድ ሰው በጎዘን ከወደቀ ምክንያቱ ምንም ይሁን ምን ከዚህ ውድቀት ውስጥ መውጣት አለበት። ለጎዘን ተላልፎ መሰጠት ሰውን ያስጨንቀዋል፣ ያሳምመዋል ለመንፈሳዊ ሕይወቱም እንቅፋት ይሆንበታል። ይህ ደግሞ ከአካባቢው ማኅበረሰብ ጋር ባለው ግንኙነት ውስጥ ደንቃራ ያስቀምጣል። ለጎዘን መጋለጥ ችግርና በሽታን ስለሚያስከትል በሰው ውስጥ ሊቆይ አይገባውም።

ምዕራፍ አሥራ ሦስት።

የውዳሴና የክብር ፍቅር።

- እንዲወደሱ የማይፈልጉ ሰዎች።
- እንዲ ኖሩ የሚፈልጉ ሰዎች።
- ውዳሴን ከመውደድ የሚመጡ ክፉ ነገሮች።
- ውዳሴና ክብር መውደድን ማስወገድ የሚቻልባቸው መፍትሔዎች፦
  1- የዓለማዊ ክብር ከንቱነት።
  2- ማንኛውም ውዳሴ ጊዜያዊ ነው።
  3- ራስን ማድነቅን ማስወገድ።
  4- ኃጢአቶችህን አስታውስ።
  5- ከፍ ያሉ ደረጃዎችን አስታውስ።
  6- በአንተ ውስጥ የሚሠራውን ጸጋ እግዚአብሔር አስታውስ።
  7- የሌሎችን ተግሣጽ ታገሥ።
  8- የሰውን ቅድስና መደበቅ።
  9- የበላይ ከመሆን ፍቅር ሽሽ።

ቀደም ሲል ስለ ውጪያዊ ገጽታ ፍቅር ተነጋግረናል። እንዲህ ያለው ፍቅር የከንቱ ክብር ፍቅር ሲሆን በውስጡም የውዳሴና የክብር ፍቅር አለ። በዚህኛው ምዕራፍ ውስጥ ትኩረታችሁን ወደ አንድ ጠቃሚ እውነት ለመሳብ እንሞክራለን።

ውዳሴ አንድ ነገር ሲሆን ውዳሴን መውደድ ደግሞ ሌላ ነገር ነው። አንድ ሰው ኃጢአት ስለማይሠራ ሊወደስ ይችላል። ይህን ውዳሴ መውደድ ሲጀምር ግን በስህተት ይወድቃል። ታላላቅ ሰዎች፣ የተከበሩ ሰዎችና በስጦታ የታደሉ ሰዎች በሕይወት ዘመናቸው ሙሉ እንደሚወደሱ ምንም ጥርጥር የለውም። ነቢያት፣ ሐዋርያትና አባቶች ውዳሴ ቢቀርብላቸውም ይህን በመስማት አልወደቁም። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ስለ እርሱና ዖለ ወንድሞቹ አገልግሎት ሲናገር «. . .በክብርና በውርደት፣ በክፉ ወሬና በመልካም ወሬ ራሳችንን እናሚጥናለን።» ብሏል። 2ኛ ቆሮ 6:8። በዚህ መሠረት እነርሱ ቢከበሩና ስለ እነርሱ መልካም ቢነገርላቸውም አልወደቁም።

ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተደጋጋሚ ውዳሴ ቀርቦለታል። ይሁን እንጂ ሰዎች በሚናገራቸው ቃላትና በትምህርቱ ይደነቁ ስለ ነበር እንዲህ ያለ ነገር ሰምተን አናውቅም ቢሉም ጌታ ይህን ከምንም በመቁጠር «እኔ ግን ከሰው ክብርን አልቀበልም . . .» (ዮሐ 5:41) ይላቸው ነበር።

እንዲወደሱ የማይፈልጉ ሰዎች።

1ኛ/ የመጀመሪያው ሰው ውዳሴን የሚሰማው ምንም እንዳልሰማ በመቁጠር ነው። ታላቁ መቃርስ ይህን አስመልክቶ ሲናገር «ክብርንም ሆነ ውርደትን አትቀበላቸው!» ብሏል። እርሱ ሰሁለቱም የሞተ ሰው ነበር።

2ኛ/ ሁለተኛው ሰው ከሰዎች፣ ከውስጡና ከዲያብሎስ የሚቀርቡለትን ውዳሴዎች የሚሸሽ ሰው ነው።

3ኛ/ ሦስተኛው ሰው ውዳሴን ከሚገባው በላይ የሚጠላ በመሆኑ የሌለበትን እንክን በራሱ ላይ የሚያመጣ ነው።

ለዚህ ምሳሌ የሚሆኑን ሞኞች፣ አላዋቅና ያልታወቁ መስለው የሚኖሩት ቅዱሳን መነኮሳት ናቸው። ቅዱስ ዳንኤል ስለ እነርሱ ሲናገር «አንተ ሞኞች የምትላቸውን ሰዎች ታላላቅ የቅድስና ደረጃ አመለክትህ ዘንድ ወደ እኔ ና!» ብሏል።

እንደነዚህ ዓይነቶቹ ሰዎች በሚሰሙት በማንኛውም የተግሣጽ ቃል ሐሴት የሚያደርጉ ናቸው። ይህ ደግሞ የሚበልጠውን የቅድስና ደረጃ ይሸውም ትሕትናን ገንዘባቸው እንዲያደርጉ ይረዳቸዋል።

እንዲወደሱ የሚፈልጉ ሰዎች።

እነዚህ ሰዎች እንደ ስህተቶቻቸው መጠን በስድስት ዓይነት ይከፈላሉ።

- **የመጀመሪያው ዓይነት።**

ውዳሴ ወደ እነዚህ ሰዎች የሚመጣው ከእነርሱ ምንም ዓይነት ጥረት ሳይቀርብ ነው። ይህ ቢሆንም በውዳሴ ይደሰታሉ ሐሴትም ያደርጋሉ። እንደነዚህ ዓይነቶቹ በሦስት ይከፈላሉ፡-

ሀ- ይህ ሰው በውዳሴ የሚደሰት ከመሆኑም በላይ ውዳሴውን በጥሞና በማድመጥ በልቡ የሚደሰት ነው። እንዲህ ያለውን ስሜቱን ግን ማንም አያውቅበትም።

ለ- ይኼኛው ሰው ውዳሴን በጥሞና ማድመጡ ሳይበቃው ሌሎች ሰዎች እርሱን ይበልጥ ለማወደስ የሚያስችሏቸውን ነገሮች እያነሳ እንዲወደስ የሚጋብዝ ሰው ነው። እርሱ ሰዎች ሊያወድሱት የጀመሩትን ውዳሴ የሚያቋርጣቸው ከዚህ የበለጠ ውዳሴ እንዲያቀርቡለት በመሻት ነው። ከዚህ በተጨማሪ እነርሱ የዘነጉት ዝርዝር ሁኔታዎች በማስታወስ በአዲስ መልክ እንዲያወድሱት ያደርጋል።

ሐ- ይኼኛው ደግሞ እንዲወደስ ይፈልጋል በመወደሱም ደስታ ይሰማዋል። ይሁን እንጂ ይህ ሰው ሰዎች ይበልጥ እንዲያመሰግኑት የሚያደርገው ራሱን ውዳሴ እንደማይቀበል አድርጎ በማስመሰል የሚያቀርብ ነው። ሰዎች ከቀደመው ይበልጥ ስለ እርሱ እንዲናገሩ የሚያደርገው ራሱን በመውቀስ ነው። እዚህ ላይ የውዳሴ ፍቅር ከግብዝነት ጋር ተቀላቅሎ ይቀርባል።

- ሁለተኛው ዓይነት።

በዚህ ውስጥ የሚገኘው ሰው ውዳሴን መስማት ይወዳል ይፈልገዋልም። ይህ ሰው ካልተወደሰ ነገሮች አስቸጋሪ ይሆኑበታል። በመሆኑም በአንድ ወይም በሁለት መንገድ ጠባዩን ይገልጣል።

ሀ- እንዲወደስ ቢፈልግም እንዲወደስ የሚያደርጉት ነጥቦች ወደ እርሱ እስኪመጡ ድረስ ዝም ብሎ ይቆያል። እንዲወደስ የሚፈልግበት ጉዳይ ላይ ሲደርስ ግን መናገሩን ይጀምራል። ሰዎችን ስለ እርሱ ትኩረት ሰጥተው እንዲያስቡ የሚያደርጋቸው ነጥብ ላይ እስኪደርሱ ድረስ ንግግሩን ሳያቋርጥ ይቀጥላል።

ለ- ይኼኛው ሰው ደግሞ ውዳሴውን ከሰዎች የሚፈልገው በእግዚአብሔር ፊት ብቻ ሊፈጽማቸው የሚገቡትን ነገሮች በሰዎች ፊት በመፈጸም ነው። ማቴ 6:1።

- ሦስተኛው ዓይነት።

የዚህኛው ውዳሴ ፈላጊ ሰው ጉዳይ ከቀደሙት ከሁለቱ የሚከብድ ነው። ይህ ሰው እንዲወደስ ቢፈልግም ውዳሴን ሊያገኝ አይችልም። ስለሆነም ሌሎች እንዲያወድሱት የሚያስችላቸውን መንገድ ሥራዬ ብሎ ይፈልጋል። ይሁን እንጂ ፍላጎቱን ሊያሟላ አይችልም። በዚህ ምክንያት በማያወድሰው ሰው ላይ ጥላቻ ያድርበታል፣ እንደ ጠላት ይመለከተዋል፣ ከእርሱ ጋር ያለውን ግንኙነትም ያቋርጣል። ምንም እንኳ ይህ ሰው የእርሱን ቁጣ የሚቀሰቅስ ሥራ ባይፈጽምም በመልካም ቃላት ሊቀበለው፣ እንደቀድሞው ሊሆንለትና ሊያከብረው አይፈልግም።

ያላወደሱትን ሰዎች የሚጠላ ይህ ሰው የሚወቅሱትን ሰዎች ምን ሊያደርጋቸው እንደሚችል መገመት ነው።

አንድ ሰው ካላወደሰውና ዝም ካለው በእርሱ ዘንድ የሚጠላ ከሆነ በሚወቅሱት ላይ የሚኖረው ስሜት ምን ሊሆን ይችላል? በእርግጥም እንደዚህ ዓይነቱ ሰው ሊታጀብ የሚችለው በሚወዱት፣ በሚያደንቁትና በሚመኙት ጓደኞቹ ብቻ ይሆናል።

- አራተኛው ዓይነት።

ይኼኛው ሰው የቀደሙትን ሦስት ዓይነቶች የሚያጠቃልልና ከእነርሱም የሚያልፍ ነው። እንዲወደስ ይፈልጋል፣ ሰዎች ሲያወድሱት መስማት ይወዳል፣ የማያወድሱትንም ይጠላል። እርሱ ስለ ራሱ ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ያወራል ጉራውንም ይነዛል። ጉራውን የሚነዛውም ተራ አውነቶችን በመግለጥ ነው።

- አምስተኛው ዓይነት።

ይኼኛው ዓይነት ሰው ከቀደመው ይበልጥ የከፋ ነው። የቀደመው ጉራውን የሚነዛው በትክክል ከፈጸማቸው ሥራዎች በመነሣት ሲሆን ይህንንም የሚያደርገው ሰዎች ሥራዎቹን እንዲመለከቱለትና ከፍተኛ ክብር እንዲሰጡት በማሰብ ነው።

ይኼኛው ዓይነት ሰው ግን ባላገኛቸው ነገሮችና በሌሉት ቅድስናዎች ራሱን የሚያወድስ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ራሱን የሚያወድሰው በማጋነን ከመሆኑም በላይ የሰዎችን ቅድስና ወይም ሥራ ለራሱ ይሰጣል።

ከዚህ ፍጹም በተለየ መልኩ ከሚገባው መጠን በላይ ራሱን የካደ አንድ መነኩሴ አስታውሳለሁ። ይህ መነኩሴ ምስጋና የሚያሰጠውን አንድ ሥራ የሚሠራ ከሆነ ሥራው ሊጠናቀቅ ጥቂት ሲቀረው የቀረውን ሥራ ሌላ መነኩሴ እንዲሠራው ያስረክባል። ይህ አባት በመጨረሻ ስለ ሥራው ሲጠየቅ «አባ እገሌ የተባረኩ አባት ናቸው፤እርሳቸው በዚህና በዚህ ሥራ ባይረዱኝ ኖሮ አዚህ አልደርስም ነበር።» በማለት ለእርሱ ሊሰጥ የነበረውን ውዳሴ ሳገዘው አባት እንዲሰጥ ያደርጋል።

ለዚህ ሌላ ምሳሌ የሚሆኑን ምስጋናውን በቡድን ለተጫወቱት ሰዎች ሁሉ እንጂ ለአንዱ ተጫዋች ብቻ የማይሰጡት ተጫዋቾች ናቸው። ይህ ሳይሆን ቀርቶ አያንዳንዱ ተጫዋች በተናጠል ኳሷን እየነዳ በመውሰድ ራሱን ለማስወደስ ግብ ለማስቆጠር ቢሞክር ቡድኑ እንደሚሸነፍ ምንም ጥርጥር የለውም። ይሁን እንጂ ግቡን ማንም ያስቆጥረው ማን ግቡ እስከሚቆጠር ድረስ አንደኛው ተጫዋች ለሌላኛው ተጫዋች ሌላኛው ደግሞ ለሌላኛው እያሉ ኳሷን ቢቀባበሉ ውጤታማ ይሆናሉ። ይህ ደግሞ ከውዳሴ በተቃራኒው ራስን እንደ መካድ ይቆጠራል።

በሌላ በኩል የሌሎችን ድርሻ በመዘንጋት ትኩረቱን ሁሉ ሙሉ ለሙሉ ወደ ራሱ የሚያደርግ ሰው የእግዚአብሔርን እርዳታና በውስጡ ያለውን የጸጋ ሥራ ይረሳል። እንዲህ ዓይነቱ ሰው ምንም ዓይነት መልካም ሥራ ቢሠራም ሁሉንም ነገር እርሱ እንደተወጣው አድርጎ ያስባል እንጂ የእግዚአብሔርን ስም አይጠራም።

መጥምቁ ዮሐንስ ግን ጌታን ሊገልጥ ስለ ወደደ ራሱን ሸሽጓል። መዝሙረ ዳዊት የሚነግረንም ይህንኑ ነው፦ «ለእኛ አይደለም፤አቤቱ ለእኛ አይደለም፤ነገር ግን ለስምህ፤ስለ ምሕረትህ ስለ እውነትህም ምስጋናን ስጥ።» መዝ 113:9። እኛ የምንሠራው ማንኛውም ዓይነት የጽድቅ ሥራ የሚከናወነው በእኛ ብርታት ብቻ ሳይሆን በመለኮታዊው ኃይል እርዳታ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን አስመልክቶ ሲናገር እንዲህ ይላል፦ «እግዚአብሔር ቤትን ካልሠራ ሠራተኞች በከንቱ ይደክማሉ፤ እግዚአብሔር ከተማን ካልጠበቀ ጠባቂ በከንቱ ይተጋል።» መዝ 126:1።

የማንኛውም ሥራ ስኬታማነት የሚለካው በሚሠራው ሰው አይደለም። ሰውየው ሥራውን እንዲያከናውን ከሚያግዙት ውጪያዊ ሁኔታዎች ሌላ ሁኔታዎች የተቃኑ እንዲሆኑ የፈቀደውና ለእርዳታ እጁ የተዘረጋው እግዚአብሔር እንዳለ መዘንጋት አያስፈልግም።

- ስድስተኛው ዓይነት።

ይኼኛው ዓይነት ሰው ከሁሉም የከፋው ነው። ይህ ሰው የቀደሙትን ሁሉ ከማጠቃለሉ በተጨማሪ ውዳሴን ከመውደዱ የተነሣ እርሱ ብቻ እንዲወደስ የሚፈልግ ነው።

እንዲህ ዓይነቱ ሰው ሌላ ሰው ከተወደሰ በጣም ይናደዳል። ውዳሴውን የሚያቀርብውንም ሆነ ውዳሴውን የሚቀበለውን ሰው ይጠላቸዋል። የተወደሰውን ሰው ከመጥላቱ ሌላ በእርሱ ይቀናል። ስለሆነም በእርሱ ላይ እንከን ይፈልጋል ይቃወመዋልም።

እነዚህን በስድስት የተከፈሉ ውዳሴ ፈላጊ ሰዎች ባጭሩ ከተመለከትን ወደሚቀጥለው ነጥብ እንሸጋገራለን።

ውዳሴን ከመውደድ የሚመጡ ክፉ ነገሮች።

እነዚህ ክፉ ነገሮች ብዙ ቢሆኑም እኛ ግን አሥራ አራት ያህሉን በመቀጠል እንጠቅሳለን።

1/ ግብዝነት።

ውዳሴን የሚወድ ሰው መልካም ሥራውን የሚፈጽመው በሰዎች እንዲታይ ስለሆነ ግብዝ ይሆናል። እርሱ መልካም የሚያደርገው መልካም ስለ ማድረግ ብሎ አይደለም። መልካም የሆነውን የሚወደውም ስለ መልካምነቱ አይደለም፤ ለታይታ እንጂ!

2/ ንዴትና ትዕግሥት ማጣት።

ውዳሴን የሚወድ ሰው ሁልጊዜ እንከኑን ይደብቃል። በመሆኑም ማንኛውንም እንከኑን የሚነግሩትን ሰዎች ሊታገሥ አይችልም። ሂስ መቀበልን ስለሚጠላ ሂስ የሚሰጠውን ማንኛውንም ሰው ሊሸከም አይሆንለትም። ሌላው ቢቀር ይናደዳል፣ ይጨናነቃል፣ ይቆጣልም። ምክር ወይም ትእዛዝ በእርሱ ውስጥ ያለውን እንከን ስለሚገልጠው ሊያውከው ይችላል። እርሱ በራሱ ዐይን ፊት ሁልጊዜ ትክክል ነው። በመሆኑም እርሱ ትክክል ነኝ እንዳለ እንዲቀጥል እንከኑን በሚነግረው ሰው ይቆጣል። የቁጣ ዓይነቱ ብዙ ቢሆንም ሁሉም ሊድን የሚችለው ግን የተሰጠውን ሂስ ወይም ትእዛዝ እንደ ስድብ በሚቆጥረው ሰው ዘንድ ያለውን የውዳሴና የክብር ፍቅር አክሞ በማዳን ነው። ይህን ማድረግ ካልተቻለ ግን ጉዳዩ ወደ ጥላቻ ይሸጋገራል።

3/ ጥላቻ።

በጥላቻ ውስጥ ያለ ሰው ጥላቻውን የሚያሳየው ሂስ ለሰጡት ሰዎች ብቻ ሳይሆን ላላወደሱትም ጭምር ነው። ከዚህ በተጨማሪ እርሱ የጠላውን ሰው ሌሎች ሲያወድሱት ከተመለከተ ጥላቻው ይበረታል። እርሱ የሚፈልገው ክብርን ሁሉ ለራሱ ብቻ ለማድረግ ነው።

4/ ቅናት።

ውዳሴና ክብር የሚወድ ሰው እርሱ ያሰበትን ቦታ በሚመኙ ሰዎች ይቀናል። ማንም ከእርሱ አንዲሻል አይፈልግም።

5/ ሌሎችን መንቀፍና ማዋረድ።

ሌሎችን ሁሉ ለመብለጥና ሌሎች ከእርሱ በታች መሆናቸውን ለማሳየት የሚፈልግ ሰው ስብእናቸውንና ሥራቸውን ይነቅፋል። በመሆኑም እርሱ ከሌሎች ጋር ሲነጻጸር የተሻለ መስሎ ለመታየት ስለሚፈልግ የሚያወራው ዝግ ብሎ ነው።

6/ የሰዎችን ፍቅር ያጣል።

ሰዎች ጉራና መኩራራት ይጠላሉ። በመሆኑም ውዳሴን የሚወድና በዚህ መንገድ ውስጥ ያለ ሰው የሌሎችን ክብር ያጣል። ከዚህ በተጨማሪ ሰዎችን አዋርዶ ራሱን የሚያወድስ ሰው የሰዎችን ፍቅር ያጣል።

7/ ውዳሴን የሚወድ ሰው የተመረጡ ቦታዎችን ይወዳል።

እርሱ ታላቅነትን ይወዳል፣ ጉራን ይወዳል፣ ሰዎች ለእርሱ ያላቸውን ፍላጎት ማግኘት ይወዳል። የወሬያቸው አጀንዳ እርሱ እንዲሆንም ይፈልጋል። ይህ ደግሞ ከሌሎች ጋር እንዲከራከርና እንዲነታረክ ያደርገዋል። በዚህ ጊዜ አንድ የተከበረ ሰው ካገኘ ሊያንኳስሰው ወይም ስለ እርሱ ክፉ ሊናገር ይሞክራል።

8/ በውሸት ሊወድቅም ይችላል።

ውሸት ውዳሴን ሊያስገኝለት ስለሚችል ለውሸት ዘውትር የተዘጋጀ ነው። አንዳንድ የውሸት የቅድስና ሥራዎችን ሰራሁ ያደርጋል። በእርግጥም በሌሰው የዚህ የአሳብ ገጽታው ተጠቅሞ ሌሎችን ያሳምናል። አንዳንድ እንከኖችን በሌሎች ላይ በውሸት ያላክካል ለሌሎች የሚገባውን መልካም ሥራም ሰራሁ ይወስዳል።

9/ ሌራዎችንና ደባዎችን ሊጠነስስ ይችላል።

በክብር ይቃወመኛል ብሎ ባሰበው ሰው ላይ ሁሉ ያደባል። የእርሱ ዋና ዓላማ እንደነዚህ ዓይነቶቹን ሰዎች ከመንገዱ ላይ በማስወገድ ክብርን ሁሉ የራሱ ማድረግ ነው።

10/ በክፋት ሊሞላም ይችላል።

የሌላውን ሰው ቦታ ለመያዝ ሲል ለእርሱ ሞቱን በክፋት ሊመኝለት ይችላል። የሌሎችን ሥልጣን ለማግኘት ሲልም ውድቀታቸውንና ጥፋታቸውን ይመኝላቸዋል። አንድ የሥራ ባልደረባው ለአለቆቹ ቁጣ እንዲጋለጥ ይመኛል። ወይም ደግሞ እርሱ ተቃዋሚ እንደሌለውና ከሌሎቹ ይበልጥ የተሞገስ መስሎ እንዲታይ ባልደረባው የሚከሰስበትን መንገድ ያመቻቻል። እርሱ ክሶችን ባያቀርብም እነዚህ ክሶች በሌሎች ከተነሡ ውስጣዊ ደስታ ይሰማዋል።

11/ ውዳሴን የሚወድ ሰው ብዙጊዜ በማኅበረሰቡ ውስጥ ችግር የሚፈጥር ይሆናል።

የዚህን ሰው ጠባይ ሌሎች እንዲረግሙት ወይም እንዲጠሉት የሚያደርግ ስለሆነ ሁልጊዜ ለማኅበረሰቡ ሽክም እንደ ሆነ ይኖራል። የእርሱ ሙከራ ሁሉንም ነገር ለራሱ ለማድረግ ነው። ሁሉንም ውዳሴ ለራሱ ለማድረግ ስለሚሻም ለሌሎች ማንኛውንም ዓይነት ዕድል ለመስጠት አይፈልግም። ስለሆነም ከእርሱ ጋር የሚሠራ ሰው ችግር ውስጥ ይገባል።

ማንኛውንም ዓይነት ምክር ስለማይቀበልም ማንም ሊያቃልለው የማይችል ችግር ይሆናል። መታመሙን ቢገልጽም መፍትሔውን አይቀበልም ወይም እንዳልታመመ ሆኖ ይሰማዋል። በትንሿ ነገር ስለሚጠቃ ለማጉረምረም የተዘጋጀ ነው። እርሱ ከሌላ ሰው ጋር እንደ ተቀመጠ አንድ ሌላ እንግዳ ሰው መጥቶ ከእርሱ ይልቅ ከእርሱ ጋር ለተቀመጠው ሰው ሞቅ ያለ ሰላምታ ከሰጠው ይናደዳል።

12/ ውዳሴን የሚወድ ሰው ተለዋዋጭ እንጂ የረጋ ጠባይ የለውም።

እርሱ ግልጽ በሆነው መንገድ ላይ ከሚሄድ ይልቅ ውዳሴን በሚያስገኝለት በማንኛውም መንገድ ላይ መጓዝን ይመርጣል። በዚህም ሰዎች እንደሚሰጡት ገጽታ የሚለዋወጥ ሰው ይሆናል።

ከሚከበረው ጋር ሲሆን የሚከበርና ጠቢብ መሆን ይፈልጋል፤ከደስተኛው ጋር ሲሆንም ከመጠን ያለፈ ደስተኛ ይሆናል። ዝም ማለትን ከሚመርጡት ጋር ሲሆን ዝምታን ይመርጣል። ማውራት ከሚወዱት ጋር ሲሆን ደግሞ ሰፊ እውቀቱን ለማሳየት ስለሚፈልግ አብዝቶ ያወራል። እርሱ የሚያግዝለት ሰው ውዳሴን የሚያስገኝለት ከሆነ ለእርሱ ያግዛል። የአንድን ሰው ክፋት በማውራት ክብር የሚያገኝ መስሎ ከታየውም ይህን ማድረጉን አጉልቶ ይፈጽማል።

በሌሎች ሰዎች ፊት ጀግና የሚያስብለው ከሆነ እውነትን ይክዳል። ይህን በማድረጉ ጉዳት የሚደርስበት ከሆነ ወይም ሌሎች የሚያወግዙት ከሆነ ወይም የሚያንኳስሱት ከሆነ ለራሱ እንዲህ ይላል፦ «ስለዚህ ክፉ ዘመን ነውና በዚያ ዘመን አስተዋይ የሚሆን ዝም ይላል።» አሞ 5፡13።

ምክንያቶቹ እርስ በእርሳቸው የሚቃረኑ ቢሆኑም እንኳ እርሱ የሚፈልገው መወደሱን ብቻ ነው። የምናኔ ሕይወት የሚመራ ሰው ሲያገኝ በእርሱ ፊት ከምግብ ይቆጠባል። ራሱን ለማዝናናት የሚፈልግ ሰው ሲያገኝ በጠረጴዛው ላይ የተለያዩ ምግቦች ይደረድርለታል። የእርሱ ዋና ዓላማ የሰዎችን ማረጋገጫ፣ መተማመኛና ውዳሴ ማግኘት ነው። ከዚህ በተጨማሪ ሲያገኝ የሚወደው የተከበረ ሥልጣን ነው። ከዚህ ሌላስ?

13/ ውዳሴን የሚወድ ሰው በኩራትና በድንቁርና ውስጥ ይወድቃል።

ኩራት ውጤታቸው መጥፎ ወደ ሆኑ ነገሮች ስለሚመራ ሰውየው በዚህ ይወድቃል። አስቀድሞ ከነበረው ኩራት ጋር የሚመሳሰለውን ኩራት በትሕትና ሊያገኘው የሚችል መስሎ ቢታየውና በሰዎች ዘንድ ቢከበር በክብሩ ውስጥ ውዳሴን ስለሚያገኝ ትሑት ከመሆን ወደ ኋላ አይልም።

14/ ውዳሴን የሚወድ ሰው መንፈሳዊ ሕይወቱን ሙሉ ለሙሉ ስለሚያጣ ሰማይና ምድርንም ያጣል።

የሚያጣቸው ከዚህ በላይ በተዘረዘሩት ምክንያቶችና መንፈሳዊነታቸውን ባጡ መልካም ሥራዎች ነው። ይህ ሊሆን የሚችለውም ዓላማቸው ውዳሴን ወደ መውደድ ሲያዘም ነው። ይህ ደግሞ መልካም ሥራውቹን መልካም ሥራ ሊያሰኛ ቸው አይችልም። ምንም ቢያደርግና የተፈለገውን ያህል ቢጥር በእግዚአብሔር ፊት የሚቆመው ባዶ እጁን ስለሆነ ከእርሱ ምንም ሊያገኝ አይችልም። ምክንያቱም ይህ ሰው ዋጋውን በምድር አግኝቷል።

እርሱ መልካም ሥራዎቹን ሁሉ ለኩራት፣ ለከንቱ ውዳሴና ለክብር ሲል ሸጧቸዋል፤ለውጧቸዋልም። ስለሆነም የአባታችን የአብርሃም ቃላት በእርሱ ላይ ተግባራዊ ይሆናሉ . . . «. . . አንተ በሕይወትህ ሳለህ መልካም እንደተቀበልህ አስብ . . .» ሉቃ 16:25። ይህ ሰው ስለ እግዚአብሔር ብሎ የሠራቸው የቅድስና ሥራዎች የሉትም ማለት ነው። ስለሆነም ዘላለማዊነትን፣ ምድርንና ክብርን አያገኝም። ስለ ወደቀባቸው ኃጢአቶች ዘላለማዊነትን ያጣል። የሰዎችን ፍቅርና ክብር በማጣት በምድር ላይ ጎስቋላ ሆኖ ይኖራል። በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ውዳሴን ማግኘት ስለሚፈልግ ከሌሎች ጋር በሚያደርገው ፉክክርና ቅናት ውስጥ ውስጣዊ ሰላሙን ያጣል።

ይህን አስመልክቶ ቅዱስ ይስሐቅ የተናገራቸው ቃላት ምንኛ ድንቅ ናቸው! «ክብር የሚሸሸው የሚፈልገውን ነው፤የሚፈልገውም የሚሸሸውን ነው።»

ውዳሴና ክብር መውደድን ማስወገድ የሚቻልባቸው መፍትሔዎች፡-

ከዚህ በመቀጠል የምንሰጥህ ጥቂት ምክሮችንና ተግራባዊ ልምዶችን ስለሆነ ከእነዚህ መካከል ለእንተ ይበልጥ የሚስማሙህን መርጠህ መውሰድ ትችላለህ። ምክንያቱም ውዳሴን የመውደድ ምልክቶችና ምክንያቶች ከሰው ወደ ሰው ስለሚለያዩ ለእንዱ የሚስማማው ምክር ለሌላው ሊስማማው ስለማይችል ነው።

1/ የዓለማዊ ክብር ከንቱነት።

የሰዎች ውዳሴ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊመራህ እንደማይችል ማወቅ ይገባሃል። ይልቁንም እንዳታገኘው እንቅፋት ይሆንብሃል። ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የምትገባውም እንደ ሰዎች ፍርድ ሳይሆን እንደ እግዚአብሔር ፍርድ ነው።

በእርግጥም የሰዎች ውዳሴ ሐሰት ነው። አንዳንዶቹ የሚያወድሱህ በይሉኝታ ሲሆን አንዳንዶቹ ደግሞ ያለ ምንም ምክንያት ሊያበረታቱህ ነው። ሌሎቹ የራሳቸውን ዓላማ ለማሳካት ወይም ለመቀለድ ወይም ውዳሴ መቀበል እንደምትወድ ስለሚያውቁ በዚህ ሊያስደስቱህ ነው። በእነዚህ ውዳሴዎች እንዳትታለል ይሁን። በእነዚህ ውዳሴዎች ውስጥ የተነገረውንም አትመን። እውነትም ይሁን ሐሰት በውዳሴ አትደሰት። ውዳሴ ከንቱ ክብርን በውስጥህ ከመፍጠሩ በፊትና በዘላለማዊነትህ ላይ እደጋ ከማስከተሉ አስቀድመህ ከአንተ ዘንድ አስወግደው። ምስጋና ይግባውና ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ «ከሰው ክብርን አልቀበልም . . .» (ዮሐ 5:41) በማለት አስተምሮናል።

መልካም ሥራዎችን ብትሠራም እንኳ ለራስህ እንዲህ በል፡- 'በዚህች በምታልፍ ምድር ላይ በድካሜ ያገኘሁት ውዳሴ ወይም ክብር ወይም ሥልጣን ምንም ሊጠቅመኝ አይችልም። ምክንያቱም በዘላለማዊው ሕይወት ውስጥ «. . . አንተ በሕይወትህ ሳለህ መልካም እንደተቀበልህ አስብ . . .» (ሉቃ 16:25።) የሚሉትን አስፈሪ ቃላት ስለምሰማ ነው። በዚህ መሠረት በሰማይ ምንም ዓይነት ድርሻ አይኖረኝም።'

በእርግጥም ይህን ዓለም ለመግዛት ሲባል ዘላለማዊ ሕይወትን መሸጥ ምኞ አደገኛ ነገር ነው!

2/ ማንኛውም ውዳሴ ጊዜያዊ ነው።

ዛሬ ያወደስህ ሰው ነገ ላያወድስህ ይችላል። ነገ ያላወደስህ ደግሞ ከነገ ወዲያ ስለ አንተ ክፉ ሊያወራ ይችላል። የሰዎች ውዳሴ የሰከነ ካለመሆኑም በላይ ውዳሴው ውሸት ሊሆን ይችላል። እውነት ቢሆንም እንኳ የሚያወድሱት አንድ ሊለወጥ የሚችል ሁኔታን ነው።

አንዳንድ ሰዎች በአንተ ፊት መልካም የሆነውን ቢያወሩልህም ከበስተጀርባህ የሚያወሩት የአንተን ክፉ ነው። አንተ ወቀሳቸውን ባትሰማም ሌሎች ይሰሙታል። አንተን ስላለህ ደረጃ፣ ክብርና ሥልጣን የሚያከብሩህ ሰዎች የሚያከብሩት ሥልጣንህን እንጂ አንተን አይደለም። ይህን ሥልጣን በፈቃድህ ወይም ተገደህ ብትለቀው አስቀድመው ያከብሩህ የነበሩት ሰዎች አያከብሩህም። ሌሎቹ ሰዎች ደግሞ ከመጠን ባለፈ ሁኔታ ሲያወድሱህና በከፍተኛ ደረጃ ሲያከብሩህ ቢቆዩም ይህ ውዳሴያቸው ዘለቄታ ላይኖረው ይችላል። እነዚህ ሰዎች በሌሎች ሌራ ሊለወጡ ይችላሉ።

አንዳንድ ሰዎች ባገኘኸው ነገር ሊቀኑ ይችላሉ። በሆነ ምክንያት ጠላቶች ሊሆኑህ ስለሚችሉ የሌሎችን ፊት ወደ አንተ ሊመልሱ የሚችሉ ሐሜቶች በአንተ ላይ ያስወራሉ። ብዛት ያላቸው ውሸቶችና የተዛቡ ወሬዎች በሕዝቡ መካከል በስፋት ሊናፈሱ ይችላሉ። በዚህ ጊዜ ሌሎች ዝቅ አድርገው እንደሚያከብሩህና ይሄ ነው በማይባል ሁኔታ እንደሚመለከቱህ ታውቃለህ።

ከሁሉ በኋላ አስቀድመው በማይገባ መንገድ ያከበሩህ ሰዎች አሁን ደግሞ በማይገባ መንገድ እንዲያቃልሉህ ትገደዳለህ።

ስለዚህ ዋናው ጉዳይህ እግዚአብሔርን በማስደሰት ሰማያዊውን ዋጋ ለማግኘት ይሁን። ትኩረትህ ሰዎች በሚሰጡህ የተሳሳተ ወይም ጊዜያዊ ክብር ላይ አይሁን።

3/ራስን ማድነቅ ማስወገድ።

ሰውን የሚዋጋው እጅግ በጣም አደገኛ ውዳሴ ራስን ማድነቅ ነው። ይህን አስመልክቶ መጽሐፍ ቅዱስ «በራስህ አስተያየት ጠቢብ አትሁን . . .» (ምሳ 3:7) ይላል። ከዚህ በተጨማሪ እንዲህ ይላል፦ «ባለጠጋ ሰው ለራሱ ጠቢብ የሆነ ይመስለዋል . . .» ምሳ 28:11። ሰው በራሱ አስተያየት ፊት ጥቢብ መሆኑ የተሳሳተ ከሆነ ራስን በሰው ፊት ማጽደቅ ደግሞ ይበልጥ .. ነው . . . «ኢዮብም ራሱን ጻድቅ አድርጎ ነበርና . . .» ኢዮ 32:1።

እንዲህ ዓይነቱ ኩራት የራሱ የሆኑ ጉዳቶችና ከውስጡ የሚወጡ የበዙ ከንቱ ውጤቶች አሉት። ከትዕቢትና ከከንቱ ክብር ሌላ ሌሎች ብዙ ጉዳቶች አሉት። ለምሳሌ፦ በራስህ ዐይን ፊት ጠቢብ የምትሆን ከሆነ የሌሎችን ጥበብ ስለምትንቅ ከእነርሱ ጋር የምትነጋገረው በመጀነን ይሆናል። እንዲህ ባለ መንፈስ ውስጥ ከሆንህ ምንም ዓይነት ሂስ ወይም ምክር ልትቀበል አትችልም። ከሚቃወሙህ ጋር ሁሉ ትጋጫለህ ታጠቃቸዋለህም። የአስተሳሰብ ውል ስለሚጠፋብህም አንተን በመቃወም የተሰነዘሩ አስተያየቶች ሁሉ አንተን ለማጥቃት የተሰነዘሩ አድርገህ ትወስዳቸዋለህ።

በራስህ ዐይን ፊት ጠቢብ የምትሆን ከሆነ ከላይ የሚመጣውን ጥበብም ሆነ ከሌሎች ሰዎች የሚገኘውን ጥበብ አትፈልግም። በመሆኑም በራስ ወደ መደሰት ደረጃ ስለምትሸጋገር ዕድገትህ እዚህ ላይ ያቆማል። ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን አስመልክቶ ለአባቱ የተናገራቸው ቃላት ምንኛ ድንቅ ናቸው! «አባት ሆይ፤የሰማይና የምድር ጌታ ይህን ከጥበበኞችና ከአስተዋዮች ሰውረህ ለሕፃናት ስለ ገለጥህላቸው አመሰግንሃለሁ . . .» ማቴ 11:25።

በዚህ ቃል መሠረት ጥበብን ከእርሱ ለመቀበል ከፈለግህ ትዕቢትህን አስወግደህ በፊቱ ቁም። ከዚህ በተጨማሪ እግዚአብሔር የሚከለክልህ ጥበብ ካልሆነ በስተቀር የማንኛውንም ሰው ጥበብ አትናቅ። መጽሐፍ ቅዱስ ከጉንዳንና ከምድር አበቦች እንድንማር ስለሚነግረን ከሰዎች ሁሉ ለመጠቀም ራስህን አትጋ። በጥበብና በአውቀት የተፈለገው ደረጃ ላይ ብትደርስም እንኳ «በራስህ አሳብ አትደገፍ . . .» (ምሳ 3:5) የሚለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል አስታውስ።

በራሱ ዐይን ፊት ጠቢብ የሆነው ሰው እርሱ ስለ ራሱ ያለውን አውነታና የጽድቅን መሥፈርት ገና ያላወቀ ሰው ነው። እንዲህ ዓይነቱ ሰው ራሱን ከማጽደቅና ራሱን ከማድነቅ በሽታ ይፈወስ ዘንድ የሚከተሉትን ምክሮች ሊከተል ይገባዋል . . .

4ኛ/ ኃጢአቶችህን አስታውስ።

በራስህና በሰዎች በምትወደስበት ጊዜ ሁሉ ኃጢአቶችህን፣ ጉድለቶችህን፣ ውድቀቶችህንና እንከኖችህን አስታውስ። በሙሉ አውነት ውስጥ ሆነህ ለራስህ «ሰዎች የሚያወድሱኝ ስለማያውቁኝ ነው . . . ጥቂት ጉድለቶቼን ቢያውቁ እኮ ለእኔ ያላቸው አቀባበል ይቀየር ነበር።» በል። ከዚህ በተጨማሪ «አምላኬ ሆይ! ስለ ጠበቅኸኝ አመሰግንሃለሁ። አንተ የሰዎችን ውዳሴ እንዳልቀበል ባትጠብቀኝ ኖሮ ኃጢአቶቼንና እንከኖቼን በመዘንጋት ራሴን አወድስ ነበር።» በል።

ኃጢአቶችህን ማስታወስህ ራስህን ይበልጥ እንድታወድስ አያደርግህም። ይልቁንም ራስህን በማወደስህ በአንተ ላይ የሚመጣውን ተጽዕኖ ያጠፋልሃል። ይህም በውስጥህ ያለውን ሚዛን ሳያዛባ ስለሚጠብቅልህ ውዳሴን የመውደድ ወጥመድን ከአንተ ያርቅልሃል። ይህም አውነተኛው ማንነትህን እንድታውቅ ስለሚያነቃህ ራስህን ማድነቅህን አንድ የተወሰነ ቦታ ላይ ያቆምልሃል።

የቀደሙ ኃጢቶችህን የማታስታውስ ከሆነ ቢያንስ ቢያንስ ተከትለው በሚመጡ ኃጢአቶች ላለመውደቅ ፍራ! ይህን አስመልክቶ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦ «ትዕቢት ጥፋትን ኩሩ መንፈስም ውድቀትን ይቀድማል።» ምሳ 16:18። ራስህን በውዳሴ ተደሰቶ ስትመለከተው ለራስህ እንዲህ በል፦ «አሁን ለውደቀት ተቃርቤያለሁ። እንዲያውም በዚህ ውዳሴ ወድቄያለሁ። ራሴን በትሕትና ብዝሃ ለእኔ የተሻለ ነው። በጽድቅ ፍሳጻ ከተወጋሁ ኃጢአቶቼን አስታውሳለሁ፤በጥበብና በአውቀት ከተወጋሁም በአሳቤ የወደቅሁባቸውን ኃጢአቶችና የጎደለኝን አውቀት አስታውሳለሁ።»

ሌላው መፍትሔ ከፍ ያሉ ደረጃዎችን ማስታወስ ነው።

5ኛ/ ከፍ ያሉ ደረጃዎችን አስታውስ።

አለኝ በምትለው በሆነ የጽድቅ ሥራ ወይም አውቀት የምትወጋ ከሆነ ከአንተ የሚጠበቀውን ያልፈጸምህና ሌሎች ያገኙትን ከፍተኛ ደረጃ ለማግኘት የማትበቃ ከንቱ መሆንህን አስታውስ። እግዚአብሔር አምላክ ለእያንዳንዱ የቅድስና ደረጃ ከእኛ መረዳት በላይ የሆኑ ቅዱሳንን ስለ ሰጠን እናመሰግነዋለን። እኛነታችንን ከነእርሱ ጋር ስናነጻጽረው ምንም አለመሆናችንን እንመለከታለን። እውቀትን አስመልክቶም አባቶቻችንና ምሳሌዎቻችን ከእኛ እጅግ የሚበልጥ ደረጃ ላይ መድረሳቸውን እንመለከታለን።

ስለሆነም ራስህን ማነጻጸር የሚገባህ አንተን ከሚበልጡህ ጋር ነው እንጂ በደረጃ ከአንተ ዝቅ ከሚሉት ጋር መሆን የለበትም። ምክንያቱም የፊተኛው ትሕትናን የጎለኛው ደግሞ ትዕቢትን ስለሚያጎናጽፍህ ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘ በሌላ ምክንያት ውጊያ ሊገጥምህ ይችላል። በዚህ ጊዜ «በእርግጥም ሕይወታቸውን ታሪክ ከሚነግረን ከቅዱሳንና ከጻድቃን አንጻር እኔ ደካማና በደረጃ ዝቅ ያልሁ ብሆንም ራሴን በዙሪያዬ ካሉት ሰዎች ጋር ሳነጻጽረው በከፍተኛ ደረጃ ላይ እገኛለሁ። ታዲያ እንዴት አድርጌ ነው ራስን ከማላደግ ውጊያ ልላቀቅ የምችለው?» ትላለህ።

አንተ ከደረጃ ዝቅ አድርገህ የምትመለከታቸውና የምትተቻቸው ሰዎች ምናልባት በአንተ ዘንድ የሌሉ ቅድስናዎችና ብቃቶች ሊኖሯቸው እንደሚችል ይህን አንድ ነገር ልነግርህ እችላለሁ። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለፈሪሳውያን ይህን በማስመልከት አስተምሮአቸዋል።

ራሱን ከቀራጩ ጋር አነጻጽሮ በመመልከት የተኩራራው ፈሪሳዊ ወደ እግዚአብሔር ጸሎቱን ያቀረበው «. . . እንደ ሌላ ሰው ሁሉ ቀማኞችና ዓመፀኞች፤ አመንዝሮችም ወይም እንደዚህ ቀራጭ ስላልሆንሁ . . .» (ሉቃ 18:11) በማለት ነበር። ይህ ፈሪሳዊ ቢጸምና አሥራት ቢያወጣም ጌታችን የተመለከተው በትሑቱና ልቡ በተሰበረው ቀራጭ መበለቱን ነው። ጌታን በቤቱ ምሳ ከጋበዘው ፈሪሳዊ ይልቅ እግሩን በእንባዋ ያጠበችው ኃጢአተኛ ሴት በእርሱ ዘንድ ታላቅ ናት። እርሷ ፈሪሳዊውን በፍቅሯ፣ በለጋስነቷና በትሕትናዋ በልጣዋለች። ሉቃ 7:44-47።

በመሆኑም ራስህን ከሌላ ሰው ጋር የምታነጻጽር ከሆነ፣ እርሱን የምትበልጥባቸውን አንዳንድ ነጥቦች በአንተ ዘንድ የምታገኝ ከሆነ እርሱ አንተን የሚበልጥባቸውን አንዳንድ ነጥቦች ለማግኘትም ሞክር። «በእውቀት እገሌን እበልጠዋለሁ!» አትበል። ይልቁኑም «እርሱ በትሕትናና በንጹህ ልብ ይበልጠኛል!» በል። ከዚህ በተጨማሪ «በጸምና በጸሎት እገሌን እበልጠዋለሁ!» አትበል። ይልቁኑም «እርሱ ራስን በመግዛትና በትዕግሥት ይበልጠኛል!» በል።

አንተ ኩራትህን ሙሉ ለሙሉ ከረሳህ ብዙ ሰዎች አንተ የሚጎድሉህን ቅድስናዎች እንደሚያገኙ ትመለከታለህ። ለምሳሌ፦ ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ ራስዋን ካብለጨለጨችና ከኪሰች ኃጢአተኛ ሴት ውስጥ እርሱ የጎደለውን ቅድስና አግኝቷል። ቅዱስ አንጦንስም ገላዋን ለመታጠብ ልብሶቿን በፊቱ ባወላለቀችው ሴት ውስጥ እግዚአብሔር ለእርሱ ያስተላለፈውን ቃል አድምጧል። ቅዱስ መቃርስም ከአረኛው ስለ ተማሪ ለሕይወቱ የሚጠቅመውን ነገር ከእርሱ አግኝቷል። ሙሴ ጻሊም በብላቴናው በዘካርያስ ውስጥ የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ ሊመለከት ችሏል።

ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር ታላላቆቹን ለመገሠጽ ሲፈልግ ታናናሾች በተባሉት ይጠቀማል። እርሱ ታላቅ ነቢይ የነበረው ዮናስን ለመገሠጽ ሲፈልግ የመረጠው ከአሕዛብ ወገን የሆነውን የመርከብ መሪ ነው። ዮና 1:6። እግዚአብሔር አምላክ የኖረችበትን ትውልድ እምነት የነቀፈው በክነናዊቷ ሴት እምነት ነው። እግዚአብሔር ታላቁን ባለጸጋ ሰው ለመገሠጽ የመረጠው ድሀውን አልዓዛር ነው። እርሱ ጥበበኞችን እንዲያሳፍር የመረጠው የዓለምን ሞኝ ነገር፣ የዓለምን ደካማ ነገርና የዓለምን ምናምንቴ ነገር ነው። 1ኛ ቆሮ 1:27-28።

ስለሆነም ራስህን እንደ ታላቅ ተራራ ብትቆጥርም እንኳ በዘሩባቤል ፊት ደልዳላ ሜዳ ትሆናለህ። ዘካ 4:7። ራስህን ታላቅና ኃያል አድርገህ ብትቆጥርም በሳል ልምድ ያለው ዲያብሎስ ታላላቆችና ኃያላን የሆኑትን ሰዎች መጣል እንደሚያስደስተው መዘንጋት የለብህም። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚናገረውም እነዚህን ሰዎች የሚዋጋቸው በታላቅ ኃይልና ጡጫ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ

ኃጢአትን አስመልክቶ ሲናገር እንዲህ ብሏል፦ «ወግታ የጣለቻቸው ብዙ ናቸውና፤ እርሷም የገደለቻቸው እጅግ ብዙ ናቸው።» ምሳ 7:26።

ይሁን እንጂ ከዚህ ሁሉ በኋላ ራስህን ጻድቅ አድርገህ የምትቆጥርና ለመውደቅ የማትፈራ ከሆንህ የሚከተለውን ምክር እንሰጥሃለን።

6/ በአንተ ውስጥ የሚሠራውን ጸጋ እግዚአብሔር አስታውስ።

አስከ አሁን ድረስ የማትናወጥና የማትወድቅ ነህን? ይህ ሊሆን የቻለው በአንተ ብርታት ሳይሆን በሚረዳህ በእግዚአብሔር ጸጋ ነው። ስለሆነም ባለህ ኃይል ከንቱ ጉራ አትንዛ። ምክንያቱም ጸጋ እግዚአብሔር ከተወህ በምንም ይሁን በምን አንተም እንደ ወደቁት ሰዎች ስለምትወድቅ ነው። በመዝሙረ ዳዊት እንዲህ የሚል ቃል ተጽፎአል፦ «. . . እግዚአብሔር ከተማን ካልጠበቀ ጠባቂ በከንቱ ይተጋል።» መዝ 126:1።

ከዲያብሎስ ጥቃቶች ማምለጥህን ስታውቅ እግዚአብሔርን ስለ እርዳታው እንዲህ እያልህ አመስግነው፦ «እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ባይሆን፤ ሰዎች በእኛ ላይ በተነሡ ጊዜ ቁጣቸው በላያችን በነደደ ጊዜ፤ በዚያን ጊዜ ሕያዋን ሳለን በዋጡን ነበር . . .» መዝ 123:2-3። አንተ እግዚአብሔር መልካም የሆነውን ነገር የሚሠራብህ የእጁ መሣሪያ ነህ። ታዲያ የሚሠራብህን እጅ ዘንግተህ እንዴት መሣሪያው ላይ ታተኩራለህ? እንደምንስ በውስጥህ ያለውን የጸጋ ሥራ በመርሳት እግዚአብሔር የሠራውን አንተ እንደሠራኸው አድርገህ ትቆጥራለህ?

ስለዚህ ሁልጊዜ ለራስህ 'እኔ ማነኝ? እኔ እኮ ብናኝ አፈርና አመድ ወይም የድካም ቋጥኝ እንጂ ምንም አይደለሁም! የእግዚአብሔር ጸጋ ከተወኝ ደግሞ ሙሉ ለሙሉ ከንቱ እሆናለሁ! እስቲ ለራሴ «ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና . . .» (ዮሐ 15:5) የሚለውን የኢየሱስ ክርስቶስ ቃል ላስታውሰው!' በል። ከዚህ በመቀጠልም 'በኩራት ምክንያት ጸጋ እግዚአብሔር እንዳይተወኝ እፈራለሁ . . . ከዚህ በኋላ ስወድቅ በእርግጥም በሰዎች ሁሉ ፊት ደካማ መሆኔ ይገለጣል።' በል።

እግዚአብሔር በአንተ ውስጥ ሥራ በሠራ ቁጥር ለዚህ ሥራው ለእርሱ ክብርና ምስጋና ማቅረብህን በመዘንጋት ከሰዎች ውዳሴ የምትቀበልበት ከሆነ እግዚአብሔር ሥራህን ብቻህን እንድትሠራው በመተው በውስጥህ ያኩራራህን ኃይልና ውዳሴ ዝም ብሎ ይመለከታል። በዚህ ጊዜ ያለ እርሱ ምንም ልታደርግ ስለማትችል ያለ ጥርጥር ትወድቃለህ።

ስለሆነም ጸጋ ከአንተ ጋር እንዲሠራ ከፈለግህ ራስህን አታወድስ የሌሎችንም ውዳሴን አትቀበል። ያሰዎችን ውዳሴ አትቀበል ስንል ሞራሽ አትስማው ማለታችን አይደለም። ይህን ላድርግ ብትልም እንኳ አይሆንልህም። አልቀበልም ብትልም ሰዎች አብዝተው ስለሚያወድሱህ ውጤቱ ተቃራኒው ይሆናል። እኛ ልንነግርህ የምንወደው ውዳሴ ወደ ልብህ ዘልቆ እንዳይገባ፣ በእርሱ እንዳትደሰትና እንዳትተማመንብት ነው።

ሌላው ምክር ተግሣጽን መታገሥ ነው።

7/ የሌሎችን ተግሣጽ ታገሥ።

አንዳንድ ሰዎች ከውዳሴ ለማምለጥ ይሞክራሉ። ይህን ለማድረግም ራሳቸውን በሰዎች ፊት ይገሥጻሉ። ይህ ደግሞ ወደዱም ጠሉም የበዙ ውዳሴዎችን ያመጣባቸዋል። ታላቁ አባት ቅዱስ ሰራጲዮን ከእርሱ ምክር ለመቀበል ፈቃደኛ ባለመሆኑ ፊቱ የቀላውን ወጣት መነኩሴ ሲመለከት እንዲህ ነበር ያለው፡- «ራስህን በውሸት አትውቀስ። አንተን የሚገሥጸህ የማስመሰል ትሕትና ሳይሆን የሌሎችን ተግሣጽ ለመቀበልና ለመሸከም የሚያስችልህ እውነተኛው ትሕትና ነው።»

አንድ ሰው ስለ ራሱ «እኔ ደካማና ኃጢአተኛ ሰው ነኝ» ማለቱ በጣም ቀላል ነገር ነው! ይሁን እንጂ ይህንኑ ሰው ሌሎች ሰዎች «አንተ ደካማና ኃጢአተኛ ሰው ነህ!» ሲሉት ይህን ለመስማት ትዕግሥት አይኖረውም። ታዲያ እንደዚህ ዓይነቱ ሰው ራሱን ለመገሠጽ በተጠቀማቸው ቃላት አላመነም ማለት ነው? ወይስ ይህን የሚያደርገው እርሱ ትክክለኛ ግብዝ ሆኖ ላለ ትሑት መስሎ ለመታየት በመፈለግ ነው? ወይስ ስለራሱ እንዲህ የሚለው ለራሱ ያቀረበው ተግሣጽ ሳይጎዳው ቀርቶ ሌሎች የተናገሩት ስለ ጎዳው ነው?

ከልቡ ትሑት የሆነ ሰው ተግሣጽን ይቀበላል። ይህን በማድረጉም ኃጢአቱን በሰዎች በኩል እንደሚናዘዝ ሆኖ ይሰማዋል። ተግሣጽን የሚቀበለውም አስቀድሞ በተቀበለው ውዳሴ ፈንታ ይሆናል። ቅድስናዎቹን ለመደበቅም ይህን ሊፈጽም ይችላል። ከዚህ በተጨማሪ ተግሣጽን የሚቀበለው ለሚያውቃቸውም ሆነ ለማያውቃቸው የቀደሙ ኃጢአቶቹ እንደ ምድራዊ ቅጣት አድርጎ ነው።

ተግሣጽን ከሌሎች በደስታ መቀበልን አባቶች የሚቆጥሩት ሁለተኛውን ጉንጭ እንደማዞር ነው። ይህን በማስመልከት ቅዱስ እንጦንስ እንዲህ ብሏል፡- «በሌሎች ሰዎች በተገሠጽህ ቁጥር በውስጥ ያለ አንተነትህን መውቀስ ያለብህ በውስጥህና በውጪህ ያለውን ሚዛን በማቀራረብ መሆን አለበት። በዚህ ጊዜ ሁለት ነገሮች ይገኛሉ። ውስጥህ አይታወክም በውጪህ ላሉትም በስድብ አትመልስም።»

ውዳሴና ክብርን የሚወድ ሰው ስድብን ሊሸክም አይችልም። ስለሆነም ለተሰደበው ስድብ በተለያዩ ዘዴዎች በስድብ ይመልሳል።

ሀ/ ስህተት የሆነው ቀላሉ መንገድ ራስን ለመከላከልና በተነቀፉበት ክስ ውስጥ ራስን ነጻ ለማውጣት ሲባል በስድብ የሚሰጥ መልስ ነው። ራስን ትክክል ወይም ስህተት ለማለት የሚቻለው በመነሻው አሳብ ላይ በመንተራስ ነው። መነሻው ንጹህ ነው ወይስ ጉድፍ . . . ?

ለ/ አንድ ሰው ለተሰደበበት ስድብ ምላሽ የሚሰጠው ከተሰደበበት ስድብ ጋር የሚመሳሰል ስድብ ወይም ከዚያ በሚከፋ ስድብ በማቅረብ ነው። ሰውየው ለውዳሴ ስላለው ፍቅር ሲል ራሱ በመበቀል «ክፉውን አትቃወሙ . . .» (ማቴ

5:39) የሚለውን የእግዚአብሔር ትእዛዝ ይጥሳል። ከዚህ በተጨማሪ «ተወዳጆች ሆይ፤ ለራሳችሁ አትበቀሉ . . .» (ሮሜ 12፤19) የሚለውንም ቃል ይረሳል። እንዲህ ዓይነቱ ሰው «ፍቅር . . . ብቻዬን ይድላኝ አይልም . . . ሁሉንም ይታገሣል . . .» (1ኛ ቆሮ 13:5አና7) የሚሉትን ቃላት በመዘንጋት ከትክክለኛው መንገድ ወጥቶ ይዳክራል።

ሐ/ አንድ ሰው ለስድብ የሚሰጠው ምላሽ ሌሎችን በማማረርና በማዋረድ ሊሆን በዚህም ሰዎች እርሱ እንደ ተገፋ አድርገው እንዲያስቡና ሊበቀሉት እንደሚፈልጉት አድርጎ ለማሳየት ይሞክራል። በዚህ ዓይነት መንገድ እርሱ ብቀላውን ከመውሰዱም በላይ በሌሎች የኃጢአት ዓይነቶች ይወድቃል። ሌላው ነጥብ አንድ ሰው ሁልጊዜ እንደ ተገፋ አድርጎ የሚያስብ ከሆነ ራሱን ሊያስተካክል አይችልም። ምክንያቱም ሁልጊዜ የሚፈርደው ለራሱ ስለሆነ ነው።

መ/ ለስድብ በልቡ ምላሽ ሊሰጥ ይችላል። የሰደበውን ሰው የሚመለከተው እንደ ጠላት ሲሆን የሚያስተናግደውም በዚህ ዓይነት መልኩ ነው። በመሆኑም ከእርሱ ጋር ይሟገታል፤ከእርሱ ጋር ያለውን ግንኙነትም በዚሁ ያቋርጣል። እርሱ ስድብ ነው ብሎ ለተቀበለው ቃል ይህ እንደ አንድ በጎ ነገር የሚቀርብ ምላሽ ነው። ይህ ሁሉ የሚመጣው ለክብር በሚሰጥ ፍቅር ነው።

በተቃራኒው ለምድራዊ ክብር የማይጨነቁ ሰዎች ለዚህ ሁሉ ካለመጨነቃቸውም በላይ ይህን በጎ አድርገው አይቀበሉትም። ትሑት ሰው እያንዳንዱን ተግሣጽ እንደ ስድብ አይቆጥርም። ይልቁኑም ራሱን ስለሚገልጥለትና መፍትሔ የሚያስፈልገው እንከኑን አጉልቶ ስለሚያሳየው በዚህ የገሠፁትን ሰዎች ያመሰግናል። ስለሆነም ሂስ የሚሰነዝሩለትን፣ የሚገሥጹትና በጠባዩ ውስጥ ያሉትን እንከኖች የሚገልጡለትን ሰዎች በጠላትነት ጎራ ውስጥ አይፈርጃቸውም። ይልቁንም በሙሉ ፍቅርና ትሕትና ውስጥ ሆኖ እነዚህ እንከኖች እንዳሉበትና እንደሌሉበት ለማወቅ ራሱን በሚገባ ይመረምራል። በዚህ ዓይነት ሁኔታ በተግሣፅ እንከኖቹን እንዲያውቅና ድኅነትን እንዲያገኝ የመራው ሰው በእርግጥም እርሱን ረድቶታል።

ቅዱስ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ይህን አስመልክቶ ሲናገር «የአንተ ባልንጀራ ጉድለትህን የሚነግርህ ሰው ነው።» ብሏል።

8/ የሰውን ቅድስና መደበቅ።

ውዳሴን የማይፈልግ ሰው ሰዎች እንዲያወድሱት ስለማይፈልግ የቅድስና ሥራዎቹን ከሰዎች ፊት ይሸሽጋል። እርሱ መልካም የሆነውን ሁሉ በተገኘው ዘዴና በቀና አመለካከት እንደ ጌታ ትእዛዝ የሚፈጽመው በምሥጢር ነው። በእርግጥም መልካም የሆነውን የምትሠራው ስለ እግዚአብሔር እንጂ ስለ ሰዎች ካልሆነ ሰዎች ይህን ሥራህን ቢያዩትም ባያዩትም አንተን የሚያስጨንቅህ ምንድር ነው?

እዚህ ላይ አንድ የማስታውሰው ታሪክ አለ። ቅድስት ሚላኒያ የተባለች ሴት መነኩሲት ከመሆኗ በፊት ባለ ጠጋ ስለ ነበረች ከፍተኛ ዋጋ የሚያወጡ ወርቆች ይዛ ወደ አባ ፔምዋ ከመጣች በኋላ በበረሀው መካከል ለሚኖሩት መነኮሳት ችግር ይዋል ብላ ትሰጠዋለች። በዚህ ጊዜ ይህ ቅዱስ ሰው ተማሪውን ጠርቶ የወርቁን ኮሮጆ እንደ ተቋጠረ ከሰጠው በኋላ ወርቁን በበረሀው ውስጥ ላሉት መነኮሳት እንዲያከፋፍል ይነግረዋል።

በዚህ ጊዜ ቅድስት ሚላኒያ በአግራሞት ውስጥ ሆና «አባቴ ሆይ! ግን እኮ የወርቁን መጠን ለማወቅ ኮሮጆውን አልከፈትኸውም!» አለችው። በዚህ ጊዜ አባ ፔምዋ ትኩር ብሎ ከተመለከታት በኋላ «ልጅ! ይህን ወርቅ የሰጠሽው ለእግዚአብሔር ከሆነ በእርግጥ እርሱ መጠኑን ያውቀዋል።» ብሏታል። ከንቱ ክብር ቅድስት ሚላኒያ ያቀረበችውን ከፍተኛ መጠን ያለው ወርቅ በእርስዋና በቅዱሱ ሰው ፊት በማሳየት እንዳይጥላት ከዚህ ጥልቅ መንፈሳዊ ትምህርት ወስዳለች።

እዚህ ላይ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረውን ቃል እናስታውሳለን። «አንተ ግን መልካም ስታደርግ ምጽዋትህ በስውር እንዲሆን ቀኝህ የምትሠራውን ግራህ አትወቅ . . .» ማቴ 6:3። የዚህ መለከታዊ ትእዛዝ ትርጉም ምንድር ነው? ምንኛስ ጥልቅ ነው!? ይህ ቃል የተነገረው የሠራኸውን ሥራ ሌሎች ሰዎች እንዳያውቁብህ አድርግ ለማለት ብቻ ሳይሆን የራስህን ቅድስና ራስህ እንድታውቀው አታድርግ- ከራስህም እንኳ ሸሽጋቸው ለማለት ነው። ከዚህ በተጨማሪ የቅድስና ሥራዎችህን አትጥቀሳቸው፣ አታስታውሳቸው፣ አታስባቸውም ማለት ነው።

አንዳንድ ሰዎች ለነዳያን የሚሰጡትን ሳንቲም ማወቅ ስለሚፈልጉ ሳይቆጥሩ አይዘክሩም። በመሆኑም ትእዛዙን በትክክል አይፈጽሙም። አንዳንዶቹ ደግሞ ከሰጡ በኋላ የሰጡትን በትክክል ላለማወቅ ይሞክራሉ ወይም በተወሰነ ጊዜ ውስጥ የሰጡትን ተቀራራቢ የሳንቲም ድምር ያሰላሉ።

እግዚአብሔር ለአንተ የሚሰጠውን ስለማይቆጥር አንተም የምትሰጠውን አትቁጠር። ያደረግኻቸውን መልካም ሥራዎች እርሳቸው። ጭራሹኑ አታስታውሳቸው። በሰዎች ፊት አታንሳቸው በውስጥህም አታስባቸው። ሰዎች የሰጠኸውን እንዲያዩልህ ማድረግ የአንተ ዓላማ እንዲሆን አትፍቀድ ወይም ላደረግኸው ነገር ሁሉ እንዲያወድስህ አትሻ።

ይህን ማለት ግን ሰዎች ስለሚያዩኝ መልካም መሥራት አልችልም ብሎ ከመልካም ሥራ መቆጠብ ማለት አይደለም። ይህን ማድረግህ ግን በመንፈሳዊ ሕይወትህ ውስጥ እንደ ቸልተኛ ያስቆጥርሃል። መልካም የሆነውን ማድረግ ያለብህ መልካም ለምታደርግላቸው ሰዎች ካለህ ፍቅርና መልካም የሆነውን እንድትፈጽም ላውቀቱን ለሰጠህ ለእግዚአብሔር ካለህ ፍቅር አኳያ ሊሆን ይገባል።

አንዳንድ ጊዜ በሰዎች መታየት ሰውን መልካም እንዲሠራ ያነሣሣዋል። ይሁን እንጂ እንዲህ ያለው መነሣሣት ውዳሴን ለማግኘት የሚያነሣሣ ውዳሴ እንጂ መንፈሳዊ መነሣሣት አይደለም። እዚህ ላይ በሴቲት በረሀ ውስጥ የኖረ የአንድ ሶሪያዊ መነኩሴ ታሪክ እናስታውሳለን። ከዕለታት አንድ ቀን ይህ መነኩሴ ወደ ታላቁ አባት ወደ ቅዱስ መቃርስ ቀርቦ «አባቴ ሆይ፤በሀገሬ ሳለሁ ሙሉ ቀን ሳልበላ በጾም እውል ነበር። ወደዚህ ምድረ በዳ ከመጣሁ በኋላ ግን ገና ፀሐይዋ ሳታዘቀዝቅ ይርበኛል። ይህ የሚሆነው በምን ምክንያት ነው?» በማለት ይጠይቀዋል። ቅዱስ መቃርስም «በሀገርህ ሳለህ ሰዎች ጾምህን ስለሚመለከቱልህ የምትጾመው ከንቱ ውዳሴን በመመገብ ነበር። በዚህ ምድረ በዳ ውስጥ ግን ማንም ስትጾም ስለማያይህ ይርብሃል።» በማለት መልሶለታል።

ቅድስናን በመሸሸግ ውስጥ አማኝ የሆነ ሰው ምሳሌ ሆኖ ለመቅረብ በሚያደርገው ጥረት በፍላጎት ሊወጋ ይችላል። ትሑት ሰው ግን ራሱን ምሳሌ አድርጎ አይቆጥርም። ምክንያቱም እርሱ በውስጡ አለኝ የሚለው ነገር ስለሌለው ሌሎች እንዲከተሉት የሚያበቃው ነገር የለውም። በጸሎቱ ውስጥም እግዚአብሔርን እንዲህ ይለዋል፦ «አቤቱ ጌታዬ ሆይ! አንተ ሕይወቴ ምን ያህሉ ኃጢአተኛ እንደ ሆነ ታውቃለህ! አንተ ስለምትጠብቀኝ በሰዎች ፊት ልትገልጠኝ አትፈልግም። ታዲያ እኔ በዚህ ጥበቃህ በመጠቀም እለከምችለው ድረስ ራሴን ምሳሌ አድርጌ መጓዝ አለብኝ ማለት ነው? ለመሆኑ ምሳሌ የምሆን እኔ ማነኝ?»

ምንም እንኳ ምሳሌ ለመሆን ዓላማችንን ምሳሌ ማድረግ ቢኖርብንም ይህንንም ያለ የእግዚአብሔር ፈቃድ ማድረግ አንችልም። ምሳሌ ለመሆን ራሱን የሚያነጣጥር ሰው በኩራትና በግብዝነት ይወድቃል። በሰዎች ፊት የሚቆመውም በተሳሳተ መልክ ነው። እርሱ ስህተቶቹን በመደበቅ ጽድቁን የሚገልጥ ሰው ነው። ምሳሌ ከመሆን የሚሸሸው ትሑት ሰው ግን ለሰዎች የሚገልጠው እንከኖቹንና ደካማ ጎኖቹን ነው።

ቅዱስ ቢሾይ የሚከተለው መንፈሳዊ መንገድ በሌሎች ሰዎች ከታወቀበት እርሱን በመተው ሌላ በሰዎች ዘንድ የማይታወቅ መንፈሳዊ አካሄድ ይጀምር ነበር። ይህን ማለት ግን የምትከተለውን መልካም አካሄድ መተው አለብህ ለማለት አይደለም። ይህ በእርግጥ ጉዳት ሊያመጣብህ ይችላል። ከዚህ ይልቅ መንፈሳዊ መሻሻልን በሚያመጣልህና በምትከተለው መልካም አካሄድ ላይ በጽናት ቆይ። ይህን የምታደርገው ግን በሰዎች ለመታየት ብለህ መሆን የለበትም። ቅድስናህን ስትደብቅም በጥበብ አድርገው።

10/ የበላይ ከመሆን ፍቅር ሽሽ።

እግዚአብሔር አምላክ በመላእክት መካከል ያለውን የሥልጣን ደረጃ ስላስቀመጠ ከፍተኛ ሥልጣን በራሱ ኃጢአት አይደለም። ሰው አለታ ሆኖ ከፍተኛ ሥልጣን ቢኖረውም ልበ ትሑትና የዋህ ሊሆን ይችላል። ጥፋቱ ያለው ሥልጣኑ ላይ ሳይሆን ለሥልጣኑ ያለው ፍቅር ላይ ነው። ከፍተኛ ሥልጣን የሚናፍቅ ሰው የሚፈልገው የራሱን ክብር ነው። ድጋፍ እንዲሆነው የሚፈልገውም የዓለሙን ፍቅር እንጂ መንፈሳዊውን ሕይወት አይደለም። እንዲህ

ዓይነቱ ሰው ከፍተኛ ሥልጣን ካገኘ ልቡ ስለሚታበይ ይጠፋል። ስለ ራሱ የሚያስበው ከፍተኛ ጥቅም እንዳለው አድርጎ ስለሆነ ሰዎችም እንደዚህ እንዲያስቡት ይፈልጋል።

መሪ ለመሆን የሚናፍቅ ሰው በቁም ቅዠት ውስጥ ይወድቃል። እርሱ በውስጡ የሚያልመውና የሚቆጥረው እገሌን እንደሆነ አድርጎ ስለሆነ ሰዎች በውዳሴ፣ በሙገሳና በክብር እንዲቀበሉት ይመኛል። ማንም ሊያደርጋቸው የማይችለውን ታላቅ ሥራ እርሱ እንደሚያደርግም ያልማል። ይህን የሚያደርገው ግን ይህን ሥልጣን ካገኘ ነው። እነዚህ ሁሉ ቅዠቶች የሚመጡት ማንም ሊያከናውናቸው የማይችላቸውን ነገሮች እርሱ እንደሚችላቸው አድርጎ የሚያሳየው ከንቱ ክብር ነው።

እግዚአብሔር ለዚህ ሰው የተወሰኑ ኃላፊነቶችን ሊሰጠው ቢችልም ሊሸከማቸው ስለማይችል ይወድቃል። ምክንያቱም ሕሊናው የሚያልመው ሊያደርገው ከሚችለው በላይ እንደሚያደርግ አድርጎ ስለሚያሳየው ነው። ለዚህ ምሳሌ የሚሆነን በከንቱ ክብር በመወጋት ላይ ያለ አንድ መነኩሴን የጎበኘ የአንድ አረጋዊ አባት ታሪክ ነው። ይህ አባት ይህንን መነኩሴ በጎበኘው ጊዜ ስብከት በመስበክ ላይ እንዳለ አድርጎ በማለም ላይ ነበር። የሚሰብከው ድምፁን አውጥቶ ስለ ነበር በውጪ የቆመው አረጋዊ አባት ያዳምጠው ነበር። በቅዠት የተሰበከው ስብከት ማብቂያ ላይ መነኩሴው ሕዝቡን በመባረክ በሰላም ሂዱ ብሎ ያሰናብታቸዋል።

ከዚህ በኋላ አረጋዊው መነኩሴ ደጃፉን ሲቆረቁር ወጣቱ መነኩሴ ይከፍትለታል። ከዚያም ይህ አረጋዊ መነኩሴ ከሰማው ምን ሊሰው እንደሚችል በማሰብ ጥቂት ግራ ተጋብቶ ከቆመ በኋላ፡- «አባቴ! ከመጡ በኋላ ለረዥም ጊዜ በደጃፉ ላይ ስለ ቆሙ ይቅርታ አድርጉልኝ።» ይላቸዋል። አረጋዊው አባትም ፈገግ ብለው «ልጄ! እኔ የመጣሁት ሕዝቡን ስታሰናብት ነው።» አሉት። በዚህ መሠረት የቁም ቅዠቶችን ተጠንቀቃቸው። የሌሉህን የሕልም ሀብቶችም አስወግዳቸው።

የአሲያቱ ቅዱስ ዮሐንስ በአንድ ወቅት፡- «አፈንጋጮችን ለማደስና የክፋትን ፍጻሜ ለማምጣት ለአንድ ሰው ማዕረግና ሥልጣን መስጠት ተገቢ ነውን?» ተብሎ ተጠይቆ ነበር። ይህ ቅዱስ ሰው ሲመልስም፡- «ተገቢ አይደለም። ምክንያቱም ይህ ሰው ከሥልጣንና ከማዕረግ ርቆ ሳለ ታላቅ ለመሆን ከናፈቀ እንደዚህ ያለውን ሥልጣንና ማዕረግ ሲያገኝ ምን ሊያደርግ ይችላል? ራሱን በማዋረድ ትሑት ሊሆን ያልቻለ ሰው ታላቅ ከሆነ ምን ሊያደርግ ይችላል?» ብሏል። ቀጠል አድርጎም እንዲህ ብሏል፡- «አንድ ሰው ምንም ዓይነት ሥልጣን ሳይኖረው በባዶ የሚኩራራ ከሆነ ታላቅ ሲሆን ምን ሊያደርግ ይችላል?» ብሎ መልሷል።

ከፍተኛ ሥልጣን በመንፈሳዊነት በጎለመሱት ላይ ምንም ጉዳት አያመጣም። ምክንያቱም እነርሱ በትሕትና ሊያሸንፉት ስለሚችሉ ነው። በመንፈሳዊነት ላልጎለመሱት ግን ጎጂ ነው።

የቅዱስ ጳኮሚዮስ ረድዕ የነበረው ቅዱስ አሮሲዮስ «ላልበሰሉ ሰዎች ሥልጣን ጎጂ ነው።» በማለት ተናግሯል። ይኸው ቅዱስ አባት ይህን አባባሉን በምሳሌ ሲያስረዳ እንዲህ ብሏል፡- «በአሳት ያልተቃጠለ ሽክላን ውኃ ውስጥ

ብትክቱት ይሟሟል። ሽክላው በእሳት ከተቃጠለ ግን ውኃውን ሊቋቋም ስለሚችል ምንም ካለመሆኑም በላይ ይበልጥ ይጠነክራል። ብስለት ሳያገኝ (በእሳት ሳይቃጠል ወይም የዓለሙ በቂ ልምድ ሳይኖረው) ሥልጣን የሚጨብጠውም ልክ እንደዚህ ነው። እንዲህ ያለው ሰው ከንቱ ክብርን ሊያስወግድ ያልቻለ ሰው ስለሆነ ለጥፋት የተዘጋጀ ነው። ከንቱ ክብርን በሚወድ ሰው ሥልጣን ሥር የሚሠሩ ሰዎች ጎስቋሎች ናቸው። ይህ ሰው ስለሚፈልገው ከንቱ ክብር ሲል ራሱንና ሌሎችን ያጠፋል።

በዚህ መሠረት የዓለምን ክብር ለሚወዱ ሰዎች የአገልጋይነትን ኃላፊነት መስጠት በጣም አደገኛ ነገር ነው። አንተ ልበ ትሑት ሰው ካልሆንህ በስተቀር የክህነትን ሥልጣን አትፈልግ። በሌሎች የምትጠበቅ የመንጋው በግ ለመሆን ተመኝ እንጂ መንጋውን የምትጠብቅ እረኛ ለመሆን አትመኝ። አንተ ራስህን ማሸነፍ ያቃተህ ሰው ሆነህ ሳለህ እንዴት ለጌታ ብዙ ነፍሳትን ልታድንለት ትችላለህ? ምንም ዓይነት ሽክም ላይኖርብህ ሕይወትህን መምራት ካቃተህ ታላቅ ቁጥር ያላቸውን ሰዎች እንዴት ከዓለሙ ጥፋት ልታድን ትችላለህ? የራሱን ድኅነት የሚፈልግና የሌሎችን ጉዳይ መከታተል እንደማይሆንለት የሚያውቅ ሰው ከክህነት ሥልጣን ይሸሻል። ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ካህን መሆንህን ፈልጎ ከመረጠህ የሚያግዝ ኃይሉን እንዲያድልህ ጠይቀው።

የቤተ ክርስቲያንን ፍላጎት ሊያሟላ የሚያስችል ሥልጣን ከተሰጠህ በኃይልህና በተሰጥኦዎችህ አትታመን። ይልቁንም እግዚአብሔር ከአንተ ጋር፣ በአንተ ውስጥና በአንተ ይሠራ ዘንድ ዝቅ ብለህ ራስህን አቅርብለት። አንተ ለእርሱ በጥበቡ ጥልቀት ውስጥ የሚጠቀምብህ መሣሪያ ሁን። የቤተ ክርስቲያን አለቃ ብትሆን ወይም ሥልጣን ቢኖርህ ልበ ትሑት ሰው ሁን። ራስህን የቤተ ክርስቲያን ዓምድ እንደሆንህ አድርገህ አትቁጠር። በትዕቢት ምንም አታድርግ። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሐዋርያቱን እግር ዝቅ ብሎ እንዳጠበ አንተም ራስህን እንደ አንድ አገልጋይ ባሪያ ቁጠር። እርሱ ስለ ራሱ እንዲህ ብሏል፡- «. . .
የሰው ልጅም ሊያገለግልና ነፍሱን ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም።» ማር 10:45።

ከዕለታት አንድ ቀን በቅርብ የተሾመ አንድ ካህን የአገልግሎቱ ተጠቃሚ ይሆን ዘንድ ምክር ሊጠይቀኝ «በወንድሞችህ መካከል እንደ ልጅ፣ በልጆችህም መካከል እንደ ወንድም ሁን!» ብዬዋለሁ። ይህን ያልሁት ሰውየው ራሱን ሳያስታብይ በዚሁ ይቀጥል ለማለት ፈልጌ ነው። በተሰጠው ሥልጣን ውስጥ ባለው ክብር ራሱን የሚያስደስት ከሆነ ግን ራሱን ያጠፋል። ሥልጣን የአገልግሎት መንገድ እንጂ ራስን ማስታበያ አይደለም። ይህን ሥልጣን ይዞ እንደ አገልጋይ የሚያገለግለውንና ራሱን የማያስታብየውን ሰው እግዚአብሔር ከፍ ከፍ ያደርገዋል።

ይህን በማስመልከት ቅዱስ ቤርሶናፊዎስ ሲናገር እንዲህ ብሏል፡- «በማንኛውም ጉዳይ ውስጥ ራስህን ከፍ አድርገህ አታስብ፤ሌሎችም አንተን ከፍ አድርገው እንዲያስቡ አታድርጋቸው። ይህን የምታደርግ ከሆነ ነገሮች ይመቹሃል።» ይህ ሊሆን የሚችለውም ሰዎች ትሑታንን ስለሚወዱና ክብር

የሚወዱትን ስለሚጠሉ ነው። አለቃ ለመሆን የሚወደውም ከእርሱ ጋር ተመሳሳይ ፍላጎት ካላቸው ሰዎች ጋር ወይም በመቀናቀን ከሚበልጠው ሰው ጋር ይጋጫል። ዝቅተኛውን ስፍራ የሚመርጠው ሰው ግን አንዳችም ተቀናቃኝ የለውም።

አለቃ ከሆንህ ሁሉንም በእኩል ዐይን ተመልከት እንጂ ማንንም አትበድል። አንተ ማወቅ ያለብህ በሥራ ላይ መሆንህን ነው። አንተ በሰዎች ሁሉ ስብእና ላይ የበላይ አልሆንህም። ለሰብእናቸው ማንኛውንም ዓይነት ክብርና ፍቅር ስጥ! አንተና እነዚህ ሰዎች በእግዚአብሔር ፊት አንድ ናችሁ። ምናልባትም ከእነርሱ መካከል ጥቂቶቹ በእግዚአብሔር ፊት የሚሻል ማዕረግ ሊኖራቸው ይችላል። ስለዚህ አለቃቸው ብትሆንም እንኳ በውስጥህ ጓደኛቸው እንደ ሆንህ አስብ። ከእነርሱ ጋር ስትነጋገርም በፍቅርና በገራገርነት ይሁን።

ለሰዎች ሥልጣን የሚሰጣቸው አንድ የሆነ ሥራን ለመቆጣጠር እንጂ የራሳቸውን የግል ክብር ለማስጠበቅ አይደለም። አንድ ሰው ሥልጣኑን የሚጠቀመው ራሱን ከፍ ከፍ ለማድረግ ከሆነ ከዋናው ዓላማው ከማፈንገጡም በላይ ለሥልጣኑ ከሚያስፈልገው ትሕትና ይርቃል። እንዲህ ያለው ጉዳይ በቤተሰብና በቤተሰብ ውስጥ በሚገኘው አባት፤ በአስተማሪና በተማሪ፤ በመሪዎችና በተመሪዎች፤ በመንጋውና በእረኛው መካከል ሊፈጠር ይችላል።

ቅዱስ ጳኮሚዮስ መንገድ ሲሄድ ተማሪዎቹ ዓዙን ይሸከሙለት ዘንድ ሲጠይቁት በጀ አይልም ነበር። በማንኛውም አገልግሎት ውስጥ ከእነርሱ ጋር እኩል ያገለግል ነበር። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ይህን አስመልክቶ ሲናገር እንዲህ ብሏል፦ «. . . እነዚህ እጆቼ በሚያስፈልገኝ ነገር ለእኔና ከእኔ ጋር ላሉት እንዳገለገሉ ታውቃላችሁ።» ሐዋ 20፡34።

በዚህ አካሄድ አባቶች ለልጆቻቸው በአገልግሎትና በትሕትና ምሳሌ ሆነዋል። ይህን በማድረጋቸውም ፍቅራቸውንና መታዘዛቸውን ሊያገኙ ችለዋል። እነርሱ ራሳቸውን መሪ አድርገው አይመለከቱም ነበር። እነዚህ አባቶች በልግሣና በርኅራኄ የተሞላ ልብ ስለነበራቸው ሥልጣናቸውን አያስታውሱትም ነበር። ቅዱስ ቢሾይ ያስተምረው ዘንድ አንድ ተማሪ ቢሰጠውም ትእዛዝ አዝዞት አያውቅም ነበር። አባቶች በዚህ ምክንያት ሲወቅሱትም «እኔ ትእዛዝ እሰጠው ዘንድ የእርሱ የበላይ አይደለሁም። እርሱ ለመማር ከፈለገ እኔ የምሠራውን እየተመለከተ ሊሠራ ይችላል።» በማለት ይመልስላቸው ነበር።

በመሆኑም የልብ ትሕትና በመሪነት ሥልጣን ላይ ለሚቀመጥ ሰው እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው። በመሪነት ሥልጣን ላይ የተቀመጠ ሰው በአመራሩ መጥፎ ምሳሌ ሊሆን አይገባውም። በመሆኑም ሌሎችን በፍቅር፤ በማስተማርና በመልካም አርአያነት መምራት አለበት እንጂ በሥልጣን፤ በትእዛዝና በአገዳ መሆን የለበትም።

እግዚአብሔር በአመራር ሥልጣን ላይ ካስቀመጠን የልብ ትሕትናን ልንይዝ ይገባናል። እኛም የአለቅነትን ተግባር እንፈጽም እንጂ አለቅነትን አንውደድ።

ምዕራፍ አሥራ አራት።

ጠብ ወይም አለመስማማት።

- ጠብ ድብልቅ ኃጢአት ነው።
- ጠብ ድካምን ይገልጣል።
- የጠብ ዓይነቶች።
- የጠብ ምክንያቶች።
- የተሳሳተ አለመስማማትና ትክክለኛ አለመስማማት።

ጠብ ድብልቅ ኃጢአት ነው።

በምንም ዓይነት መንገድ ቢሆን ክርስትና ጠብን አይደግፍም። ጠብ መንፈሳዊ ጠባይ ካለመሆኑም በላይ በውስጡ የተለያዩ ኃጢአቶችን ይዟል። እነርሱም፦

1/ ጠብ ድብልቅና የተጠላ ኃጢአት ነው።

ጠብ በሰዎች ሁሉ የተጠላ ነው። ጠብን የሚያነሣ ሰው ሁሉ ማንንም ሊያሸንፍ አይችልም። ከዚህ በመቀጠል ጠብ በውስጡ ያካተታቸውን ኃጢአቶች ለማገናዘብ እንሞክራለን።

2/ ጠብ ጨካኝ ልብን ይገልጣል።

ቅን ልብ ያለው ሰው ጠበኛ ሊሆን አይችልም። ይልቁንም ነገሮችን በእርጋታ ያከናውናል። ቃላቱም የተረጋጉና በጥንቃቄ የተመረጡ ናቸው። እርሱ የማንንም ስሜት ለመጉዳት አይፈቅድም።

3/ የጠብ ተቃራኒ የዋህነት ነው።

ጠበኛ ሰው የዋህነቱን ፈጥኖ ያጣል። በመሆኑም ክርስትና ሰዎችን ለየዋህነት፤ ለጨዋነትና ለእርጋታ ይጠራል። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ብፅዕና ባስተማረበት የተራራው ስብከቱ ውስጥ የዋህነትን የጠቀሰው በመጀመሪያዎቹ ተርታ ሲሆን እንዲህ ነው ያለው፦ «የዋሆች ብፁዓን ናቸው፤ምድርን ይወርሳሉና።» ማቴ 5:5።

ፍጹም የሆነውን የእርሱን ባሕርያትና ቅድስና እንድንመስል ሲነግረን እንዲህ ብሎናል፦ «. . . ከእኔም ተማሩ እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝና . . .» ማቴ 11፡29። እርሱ ፍጹም የዋህና ከጠብ የራቀ አምላክ ስለሆነ ስለ እርሱ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዲህ ተብሎ ተጽፎአል፦ «. . . የተቀጠቀጠን ሸንበቆን አይሰብርም፤የሚጤስን የጥዋፍ ክርም አያጠፋም።» ማቴ 12:20።

4/ ጠብ ከፍቅር ጋር ሊጓዝ አይችልም።

ክርስትናችን ፍቅር፣ የዋህነትና ቸርነት የመንፈስ ፍሬዎች እንደ ሆኑ ያስተምረናል። ገላ 5:22። ስለ ፍቅር እንዲህ ተብሏል፦ «እግዚአብሔር ፍቅር ነው፤በፍቅርም የሚኖር በእግዚአብሔር ይኖራል፤እግዚአብሔርም በእርሱ ይኖራል።» 1ኛ ዮሐ 4:16።

መንፈሳዊ ሰው ችግሮቹን የሚፈታው በፍቅር እንጂ በጠብ አይደለም። ስለሆነም እርሱ እግዚአብሔርንና ሰውን በፍቅር ያሸንፋል። ለጠብ የሚነሣ ከሆነ ግን ሁሉንም ያጣል።

5/ ጠብ ክፉ ኃጢአት ነው።

ጠብ ጫሪነት የተሳሳተ ተግባር መሆኑን ክርስትና ይገልጽልናል፦ «ክፉውን በመልካም አሸንፍ እንጂ በክፉ አትሸነፍ።» ሮሜ 12:21። ከዚህ በተጨማሪ እንዲህም ይላል፦ «የሚያሳድዱአችሁን መርቁ፤መርቁ እንጂ አትርገሙ . . . ለማንም ስለ ክፉ ፈንታ ክፉን አትመልሱ . . . ቢቻላችሁስ በእናንተ በኩል ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ . . . ራሳችሁ አትበቀሉ . . . ጠላትህ ግን ቢራብ አብላው፤ ቢጠማ አጠጣው . . .» ሮሜ 12:14:20።

ቁጣን የማይቀበለው ክርስትና ጠብን ወይም ሁከትን ሊቀብል አይችልም። ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ እንዲህ ይላል፦ «. . . ሰው ሁሉ ለመስማት የፈጠነ፣ ለመናገርም የዘገየ፣ ለቁጣም የዘገየ ይሁን፤የሰው ቁጣ የእግዚአብሔርን ጽድቅ አይሠራምና።» ያዕ 1:19-20። ከዚህ ሌላ መጽሐፍ ቅዱስ «መራርነትና ንዴት፣ ቁጣም፣ ጩኸትም፣ መሳደብም ሁሉ ከክፋት ሁሉ ጋር ከእናንተ ዘንድ ይወገድ።» (ኤፌ 4:31)፤«ከቁጡ ሰው ጋር ባልንጀራ አትሁን፣ ከወፈፍተኛም ጋር አትሂድ።» (ምሳ 22:24።) ይላል።

ቁጣ - ለሁከት፣ ለጠብና ለግድያ የመጀመሪያ እርምጃ ስለሆነ ክርስትና ቁጣን ይቃወማል። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተራራው ስብከቱ ውስጥ «በወንድሙ ላይ የሚቆጣ ሁሉ ፍርድ ይገባዋል . . .» (ማቴ 5:22) በማለት ተናግሯል። ያለ ምክንያት ከሥጋና ከነርቮች መቃጠል የሚመጣ ቁጣ ስለ እግዚአብሔር ሊባል ከሚመጣ ቁጣ የተለየ ነው።

6/ ጠብ ጥላቻን ይገልጣል።

ቁጣ ወደ ጥላቻ ሲያድግ ጥላቻ ደግሞ ወደ ሁከት፣ ጠብና በሰዎች ላይ ክፉ ወደ ማድረግ ይጎለምሳል። በዚህ መሠረት መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፦ «ወንድሙን የሚጠላ ሁሉ ነፍሰ ገዳይ ነው . . .» 1ኛ ዮሐ 3:15። ምንም እንኳ በድርጊት ባይገደለውም የዚህ ኃጢአት ቅርንጫፎች ከሆኑት በአንዱ ይሸውም በአሳብ ግድያ ገድሎታል።

7/ ጠብ ለብቀላ ያለ ፍላጎትን ይደብቃል ወይም አለመቻቻልን ይገልጣል። ጠብ ትዕግሥት የሌለው ሰው ጠባይ ስለሆነ ሰውየው መብቱን

ለማስከበር ሲል ብቀላን እንዲወስድ ያደርገዋል። እርሱ መብት ብሎ የሚቆጥረውም በራሱ ክንድ በመተማመን የሚፈጽመውን ብቀላ ነው። እርሱ «በቀል የእኔ ነው፤እኔ ብድራቱን እመልሳለሁ . . .» (ሮሜ 12:19) በሚለው በእግዚአብሔር እጅ ላይ ጉዳዩን ሊጥል አይፈልግም። ወይም ደግሞ ጉዳዩን ለሕግና ለማኅረሰቡ አይተውም። ክርስትና ለትዕግሥት ብቻ አይጠራም። ትዕግሥት የሚከብድ ቅድስና ቢሆንም ወደ ፍቅር የሚያደርስ ቅድስና ነው። መጽሐፍ ቅዱስ «ፍቅር ያሥታግሳል፣ ያስተዛዝናል . . . ብቻዬን ይድላኝ አይልም. . .» (1ኛ ቆሮ 13:4-7) ስለሚል ፍቅርና ጥላቻ አብረው ሊጓዙ አይችሉም።

በጠብ ውስጥ ፍቅር ሲጠፋ በምትኩ ሌላ ይተካል። ይኸውም . . .

8/ ጠብ ሲመጣ ራስ ወይም እኔነት ይገለጣል።

ሰው በጠብ የሚጠቀመው ለራሱ ለመሟገትና ራሱን ለመከላከል ነው። በተመሳሳይ ጊዜ ሌሎች እንዲታዘዙለት ይፈልጋል። ክርስትና በግልጽና በጥብቅ እኔነትን ይዋጋል። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይህንን በግልጽ አስቀምጦታል። «እኔን መከተል የወደድ ቢኖር ራሱን ይካድ . . .» ማቴ 16:24። በእርግጥ ግን ጠብ ለራሱ ሊሟገት አይችልም። ይልቁንም ደካማነቱን ይገልጥበታል። ይህ እንዴት ሊገለጽ ይችላል?

9/ ጠብ ሲፈጠር ሰው ራሱን መቆጣጠር አይችልም።

የተረጋጋ ሰው ራሱን መቆጣጠር ይችላል። ጠበኛ ሰው ግን ራሱን፣ ነርቮቹንና ቁጣውን መቆጣጠር አይችልም። አሳቡንና ሕሊናውን መቆጣጠር ስለማይችልም ተገቢ ያልሆነ ጠባዩ በሰዎች ሁሉ ፊት ይገለጣል። መጽሐፍ ቅዱስ የሚነግረን ግን «ትዕግሥተኛ ሰው ከኃያል ሰው ይሻላል፤በመንፈሱም ላይ የሚገዛ ከተማ ከሚወስድ ይበልጣል።» (ምሳ 16:32) በማለት ነው።

10/ ጠብ የድካም ማረጋገጫ ነው።

ጠብ ድካምን ይገልጣል።

የሰው ልብ በፍቅር ካልተሞላ፣ ችግሮችን በጥበብና በአርጋታ ማቃለል ካልቻለ፣ አርቆ ማሰብ ካልሆነለትና ነርቮቹን ሊቆጣጠር ከተሳነው ጠብን ይመርጣል። ጠብ እዚህ ደረጃ ላይ ሲደርስ አቅም ስለሚያጣና ችሎታ ስለሚያንሰው ተገቢ ያልሆነ ጠባይ ያሳያል። ብዙ ጠበኛ ሰዎች ደካማ እንደሆኑ እርግጥ ነው። እነዚህ ሰዎች ብርቱ ነርቮች ስለሌሏቸው ሊታገሡ ካለመቻላቸውም በላይ አርቆ የሚያስብ ሕሊና የላቸውም። ከዚህ በመቀጠል ለዚህ ጥቂት ምሳሌዎችን እሰጣችኋለሁ።

ከተማሪዎቹ ጋር የሚጣላ አስተማሪ ደካማ ነው። እርሱ በቁጣ ስለሚገነፍል በተማሪዎቹ መካከል ሥርዓት ሊያስጠብቅ አይችልም። ከዚህ በተጨማሪ ተማሪዎቹን ይደበድባል፣ ያባርራል፣ ይሳደባል፣ ይቀጣልም። እርሱ ደካማ ሰው ስለሆነ ነው እንጂ ደካማ ሰው ባይሆን ኖሮ እንዲህ ያለ ጠባይ አያሳይም ነበር። እርሱ ክፍሉን ሊቆጣጠር የሚገባው በብርቱ ስብእናው፣

በእውቀቱ፣ በሚስብ ገለጻው፣ በፈገግታው፣ በጨዋነቱና ተማሪዎቹ ለአርሱ ባላቸው ፍቅር ነው። እነዚህ ሁሉ የሚያስደስቱ ባሕርያት የጎደሉት አስተማሪ ግን ከድካሙ የተነሣ ጠብን ይመርጣል።

ሌላዋ ምሳሌያችን ልጆቿን የምትደበድብ እናት ናት። ልጇ ሲጮኽ፣ እየተሯሯጠ ሲጫወት ልትቆጣጠረውና በዚሁ ዓይነት መንገድ እንዲጫወት ልትተወው ያልፈለገችው እናት ከእርሱ ጋር ጠብ ትፈጥራለች። በመሆኑም ትመታዋለች፣ ትሰድባዋለች ካልሆነም በተገኘው ዘዴ ታስፈራራዋለች። ይህን ሁሉ የምታደርገው ልጆችን የመንከባከብ እውቀቱም ሆነ ልምዱ ስለሌላት ነው። ይህ ቢኖራት ኖሮ ልጇን ያለ ጠብ ልታሸንፈው ትችል ነበር። እዚህ ላይ ጠብ የእውቀት ወይም የአቅም ማጣት መሸፈኛ ሆኖ ይገለጣል ማለት ነው።

ከዚህ በተጨማሪ ጠብ ምንም ጽናት የሌለው የውስጥ ድካም መሸፈኛ ሊሆን ይችላል። አዋቂ ሰው ችግሮቹን በቀላሉ ሊያሸንፋቸው ይችላል። የሚያሸንፋቸውም በጥበብና አርቆ በማሰብ ነው። ደካማ ሰው ግን ጠብን ይመርጣል። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ይህን በማስመልከት እንዲህ ይላል፦ «እኛም ኃይለኞች የሆንን የደካሞችን ድካም እንድንሸከም ራሳችንንም ደስ እንዳናሰኝ ይገባናል።» ሮሜ 15፡1።

የጠብ ዓይነቶች።

1- ዓይነቱ የበዛ ጎጂ ጠብ።

እንዲህ ዓይነቱ ጠብ ድብደባን፣ የተለያዩ ግድያዎችን፣ ማስደንገጥንና ማስፈራራትን ጨምሮ ሁሉንም ዓይነት አካላዊና ሥነ ልቦናዊ ሥቃይን የሚያጠቃልል ጠብ ነው። ይህ ጠብ የነርቭ ጠብ በመባል ይታወቃል።

2- ሌላው ዓይነት ጠብ ማስፈራራት ነው።

እንዲህ ዓይነቱ ጠብ ሰው፣ አውሮፕላንና መርከብ መጥለፍን፣ ተቀጣጣይ ፈንጂዎችንና ተሽከርካሪዎችን ማፈንዳት፣ የተለያዩ ሕንጻዎችንና ቦታዎችን ማውደምና ሽብር መፍጠርን ያጠቃልላል። እነዚህ ሁሉ አስከፊ ወንጀሎች ናቸው።

3- ጦርነቶችም የጠብ ዓይነቶች ናቸው።

ጦርነቶች የሚታወቁት ከጥንት ጊዜ አንስቶ ነው። እነዚህ ጦርነቶች ለመከላከል ሳይሆን ለማጥቃት ከተቃጡ ጠብ ጫሪዎች ይሆናሉ። ከፍተኛ ጠብ የሚያስከትሉ የጦርነት ዓይነቶች አሉ። እነዚህም የኒውክለር ጦርነቶች ወይም በመርዝ ጋዝ የሚካሄዱ ጦርነቶች ወይም በንዳይና በሚያቃጥሉ መሣሪያዎች የሚካሄዱ ጦርነቶች ናቸው። ከዚህ በተመሳሳይ ከተሞችን ሙሉ ለሙሉ የሚያወድሙ፣ የሥልጣኔን ድምጥማጥ የሚያጠፉ፣ ብዙዎችን አካለ ጎደሎዎችና ጡረተኞች አድርገው የሚያስቀሩ አስከፊ ጦርነቶች አሉ።

4- በግለሰብ ደረጃ የሰዎችን ስሜቶች የሚያጠፋ ጠብ አለ።

ለዚህ ዓይነቱ ጠብ ምሳሌ የሚሆኑን አሳፋሪ ወቀሳ፣ ጨካኝ ተሟጋች፣ ያለ ማቋረጥ በሰው ስህተት ላይ ማተኮርና የሰውየውን ስብእና ማጥፋት ናቸው።

5- ጠብ ጫሪ ስድቦች።

መራር ማንኳሰስ፣ ማንቋቀሽሸ፣ ማዋረድ፣ ስድብ፣ ሐሜት፣ ግንኙነትን ማቋረጥና ሌሎችም ምራልንና አእምሮን የሚያጠፉ ግድያዎች በዚህ ውስጥ የሚጠቃለሉ ናቸው። እነዚህ ሁሉ በሚፈታተኑ ቃላት ሊታጀቡ ይችላሉ።

6- ጠብ ጫሪ ወቀሳ።

ይህ በጭካኔ የተሞላና የሚያም ወቀሳን የሚያካትት ጠብ ቢሆንም መነሻው ተራ ነገር ነው። እንዲህ ዓይነቱ ወቀሳ ሰረዝም ጊዜ ሊቆይ ከመቻሉም በላይ በሰዎች ፊት ሊገለጥ ይችላል። ከዚህ በተጨማሪ በቁጡ ጠባይና ጸያፍ በሆኑ ቃላት ሊታጀብ ይችላል። እንዲህ ዓይነቱ ጠባይ በቆይታ ልማድ ስለሚሆን ሰውየው ባልንጀሮቹን እስኪያጣ ድረስ ለትንሹም ሆነ ለትልቁ ወቀሳ ያቀርባል።

አንድ ባለ ቅኔ እንዲህ ብሏል፦ «ባልንጀራህን በሁሉም ነገር ከወቀስኸው፣ በመጨረሻ የምትወቅሰው ሰው ታጣለህ። ስለዚህ ከባልንጀራህ ጋር በመልካም ሁኔታ ውስጥ ሁን ወይም ብቻህን ኑር። ምክንያቱም እርሱ አንድ ጊዜ ወንጀለኛ ሌላ ጊዜ ደግሞ ንጹሕ ሰው ሊሆን ስለሚችል ነው። መራራ ውኃን ከአፈር ጋር የማትጠጣ ከሆንህ ትጠማለህ፣ማንም ሁልጊዜ ንጹሕ ውኃ ሊጠጣ አይችልምና።»

7- አሉታዊ ጠብ።

አምንታዊ ጠብ ሊያሳይ የማይችል ሰው ወደ አሉታዊ ጠብ ይጠጋል። ይህም የማያቋርጥ ጎዘን፣ የማያቋርጥ ልቅሶ፣ ከምግብ መታቀብ፣ በጎዘን ዝምታን መምረጥና መለየት ናቸው። ይህን የመሰሉ የዝምታ ጠቦች ሌላውን ሰው ይጎዳሉ።

8- የምኞት ጠብ።

ሰው ሙሉ ለሙሉ እስከሚጠፋ ድረስ ክፉኛ የሚጣሉት ውጊያዎች አሉ። ጥቂቶቹ የምኞት ምሳሌዎች የሚከተሉት ናቸው፦ ሰው እጅግ ቢያገኝ ወይም ቢሰበስብ ፈጽሞ የማይረካው በስስት ስለሆነ ስስት ክፉ ምኞት ነው። አደንዛዥ ዕፅና ኩራትም የምኞት ምሳሌዎች ናቸው። ምኞቶች እስኪረኩ ድረስ አይቀዘቅዙም . . . ቢቀዘቅዙም ቀጣይነታቸው አይቋረጥም።

ምኞት በሕሊና ላይ በሚታተሙ አፍራሽ አሳቦች ይታጀባል። እነዚህ አሳቦች ደግሞ ሰውየው እስኪጠፋ ድረስ ከእርሱ ጋር ይቆያሉ። በጣም ኮባድ

በሽታዎች ስለሆኑም ሰዎች የሕሊና ዕረፍት ማግኘት ሲፈልጉ በመድኃኒት ያስታግሷቸዋል።

የጠብ ምክንያቶች።

1- ጨካኝ ጠባይ።

ጥቂት ሰዎች በጠባያቸው ጨካኝ ስለሚሆኑ ከሰዎች ጋር የሚደራደሩት በጭካኔ ነው። ይህ ጭካኔ ይበልጥ እየከፋ ከመጣ ወደ ጠብ ይለወጣል። ጭካኔ የሚመጣው ሰውን ከሚከቡት ማኅበራዊ ጉዳዮችና በዙሩ በኩል በውርስ ሊወርድ ሲዋረድ ከሚመጣ ጠባይ ነው።

2- ከድካም የተነሣ የሚመጣ የነርቭ መዛባት።

እንዲህ ባሉ ሁኔታ ውስጥ የሚገኝ ሰው በሽታውን መሸከም ስለማይችል ምላሹና ጠባዩ በጭካኔ የተሞላ ይሆናል።

3- ጠብ ደጋፊ ከማጣት ወይም አስቀድመን እንደተናገርን ድካምን ከመሸሸግ ሊመጣ ይችላል።

4- ጠብ ከነርቭ መዛባትና ከአእምሮ በሽታ ሊመጣ ይችላል። የኢጣልያ የሥነ ልቦና ተመራማሪዎች በደረሱበት ፅንሰ አሳብ እያንዳንዱ ወንጀለኛ በሽተኛ ነው ብለው ስለሚያስቡ ወንጀል እንዲፈጽም በሚመራው በሽታ ዙሪያ ምርምር ይዘዋል። አንዳንድ የአእምሮና የነርቭ በሽታዎች በጠብ እንደሚታጀቡም በሚገባ የሚታወቅ ነው።

ይሁን እንጂ አያንዳንዱ ወንጀል የሚፈጸመው ከአእምሮ በሽታ ነው ለማለት ይከብዳል። ምክንያቱም በጭካኔ የተሞላ ወንጀል ፈጽመው ምንም ዓይነት የአእምሮ በሽታ የሌለባቸው ወንጀለኞች ስለተገኙ ነው። ይህ ባይሆን ኖሮ ግን ለማንኛውም ወንጀል ተጠያቂ የሚሆን ሰው ባልተገኘም ነበር።

5- ፍርሃት በጭካኔ የተሞላ ጠብ ለመፍጠር ምክንያት ሲሆን ይችላል። ለዚህም የወንጀሉ መታወቅ የሚያስከትለው ፍርሃት ምላሹ ሲሆነን ይችላል። አንድ ሌባ ወደ ሰው ቤት የሚገባው ለመስረቅ እንጂ ለመግደል አይደለም። ይሁን እንጂ ሲሰርቅ አንድ ሰው ነቅቶ ካየው ልያዝ እችላለሁ በሚል ፍርሃት ግድያ ይፈጽማል።

በቡድን የተደራጁ ሌቦች በመካከላቸው የእነርሱ አባላት ሆነው እየኖሩ ምሥጢር የሚገልጡባቸው መስለው የሚታዩአቸውን ባልንጀሮቻቸውን ይገድላሉ።

ከዚህ በተጨማሪ በእርሱ ላይ ወጥመድ ያጠመደበት መስሎ የሚታየውንና ወጥመዶቹን የሚፈራቸው ከሆነ አጠመደብኝ ያለውን ሰው ክፉኛ ይጣላዋል።

6- በራስ ችሎታና በጉልበት መመካት፣ ኃይልን በአግባቡ መጠቀም አለመቻልና በሳል አለመሆን ጠብን ሊፈጥር ይችላል። ለዚህ ምሳሌ የሚሆነን ሌሎችን በጉልበት እንደሚበልጣቸው ለማሳየት በፊለን ጊዜ ሁሉ እነርሱን እንደፈለገ የሚደበድባቸው ጉልበተኛ ሰው ነው። ከዚህ ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ድርጊቶች በአንዳንድ ጎረምሶች፣ አምባገነኖችና ቡድኖች ይፈጸማሉ። ይህ የሚሆነውም የቡድናቸው አባላት የእነርሱን ትእዛዝት እንዲቀበሉ ሲያስገድዷቸው ነው።

7- የጠብ ምክንያት ምቀኝነት ሲሆን ይችላል። ምቀኛ የሆነ ሰው ምቀኝነቱን የሚወጣው ጠብ በመፍጠር ነው። ለምሳሌ አንድ ሰው ሌላው ሰው ሀብቱን እንደሚወርሰው ወይም ሥልጣኑን እንደሚቀማው ሲያውቅ በጭካኔ ይጣላዋል። ቅናትም ወደዚህ ይመራል። የዚህ ምክንያቱ ደግሞ ጠብን በጠብ የመከፈል ምኞት ሲሆን ይችላል።

8- አለመረዳት የጠብ ምክንያት ሲሆን ይችላል። መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያቱ ከአይሁድና ከጨካኞቹ ሮማውያን ስለሚደርስባቸው መከራ ሲነግራቸው፡- «. . . የሚገድላችሁ ሁሉ እናንተን እንደሚያገለግል የሚመስልበት ጊዜ ይመጣል።» ብሏቸዋል። ዮሐ 16፡2።

ባለመረዳት የቤተሰቡን ውርደት ለማጥፋት በሚል ሰበብ የብቀላ እርምጃ የሚወስድ ሰው አለ።

9- አንዳንዶች ጠብን እንደ ቀላልና አስቸኳይ መፍትሔ ይወስዱታል። ይሁን እንጂ ቀላል የሆነው መፍትሔ ሁልጊዜ የሚሻል ሲሆን አይችልም። ይህን የማያስቡ አንዳንድ ሰዎች ግን ጠብን የሚመለከቱት እንደ ብቸኛ መፍትሔ አድርገው ስለሆነ እንዲህ ይላሉ፡- «እንዲህ ዓይነቱ ነገር ከጠብ በስተቀር ምንም መፍትሔ የለውም!» ወይም «እንደዚህ ዓይነቱን ሰው በጠብ ካልሆነ በምንም ሊያሸንፉት አይቻልም!» ብለው ይናገራሉ።

10- ጠብ የብልጣ ብልጥነትና የማጭበርበር ዘርፍ ሲሆን ይችላል። «በእንተ ቁጥጥር ሥር ያለውን ሰው ስትመታ ከአንተ ቁጥጥር ውጪ ያለው ይፈራሃል።» የሚለው አባባል እዚህ ላይ ሊጠቀስ ይቻላል።
መጽሐፍ ቅዱስ ይህን አስመልክቶ ሲናገር እንዲህ ብሏል፡- «እረኛውን ምታ፤በጎቹም ይበተናሉ።» ዘካ 13፡7። በዚህ ጉዳይ ውስጥ ጠብ ዓላማ ባይሆንም የዓላማው መንገድ ነው።

11- ጠብ እውነተኛውን ነገር ለመሸፈን ሲባል ሊመጣ ይችላል። እንደዚህ ዓይነቱ ጠብ የእውነት ጠብ አይደለም። ለምሳሌ፡- አንድ አባት ልጁ እንዲታዘዘው ሲፈልግ የተናደደና ሊመታው የሚችል መስሎ ይነሣበታል። አንድ ሥራ ቀጣሪ በሠራተኞቹ ላይ የማያመጣውን ቅጣት እንደሚያመጣው አድርጎ በመዛት ሠራተኞች የታዘዙትን ሥራ እንዲሠሩ ያስገድዳቸዋል። ይህን የሚያደርገውም ሠራተኞቹ እንዲፈሩትና ጠባያቸውን እንዲያርሙ ነው።

12- የተጣመረ ጠብ::

በዚህ ጉዳይ ውስጥ የሚጠቀሰው ሰው በቀጥታ ጠበኛ ባይሆንም በተዘዋዋሪ ጉዳዩን ለጠበኞች በማስተላለፍ ራሱን ነጻ ለማድርግ የሚሞክር ሰው ነው:: ጠቡ ተዘዋዋሪ ነው ማለት ነው::

የተሳሳተ አለመስማማትና ትክክለኛ አለመስማማት::

ማንኛውም የጥል አካሄድ ኃጢአት ነው ማለት አንችልም:: ጥል ወይም አለመስማማት የሚያስፈልጋቸው አንዳንድ ሁኔታዎች አሉ:: ለምሳሌ ግድየለሽ ኃጢአተኞችን መቅጣት ወይም ጎብረተሰቡን ለማጥፋት በወንጀል የሚያስፈራሩ ወይም ባህሉንና ሞራሉን ከሚያጠፉ ሰዎች ጋር መጣላት አስፈላጊ ነው::

እግዚአብሔር ራሱ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሌሎችን ለመገደብና ለሚቀጥለው ትውልድ መማሪያ ለማድረግ አንዳንድ ከባድ ቅጣቶችን ጠቅሶልናል:: የማያቋረጥ ልልነት ወደ ግድየለሽነት ይመራል::

ለዚህ ከብሉይ ኪዳን ውስጥ ምሳሌ ከሚሆኑን መካከል ምድር ተከፍታ ቆሬን፣ ዳታንንና አቤሮንን የዋጠችበት ጥፋት (ዘኁ 16) አንዱ ነው:: የአዲስ ኪዳን ምሳሌያችን ግልጽ የሆነው የሐናንያና የሰጲራ ጥፋት ነው::

ከዚህ በተጨማሪ ጥፋተኞችን ስለሚበቀለው ስለ እግዚአብሔር አገልጋይ የተጠቀሰ ቃል አለ:: «በክንቱ ግን ሰይፍ አይታጠቅምና ክፉ ብታደርግ ፍራ፤ቁጣውን ለማሳየት ክፉ አድራጊውን የሚበቀል የእግዚአብሔር አገልጋይ ነውና::» ሮሜ 13:4::

ወንጀሉችን የሚፈጽሚቸው ሰዎች ግድየለሾችና ለሌሎች መጥፎ አርኣያ ስለሚሆኑ እነርሱ ከጠብ የማይቆጥሯቸው አንዳንድ ወንጀሎች በእነርሱ ዘንድ ሊደጋገሙ ይችላሉ:: ይሁን እንጂ እነዚህ ጉዳዮች ጥብቅና ወሳኝ በሆነ ሁኔታ ከተያዙ ጎብረተሰቡ ሊነጻ ይችላል::

ከዚህ በመቀጠል አንድ ጠቃሚ መንፈሳዊ መመሪያ ለመስጠት እንወዳለን::

በጎብረተሰብና በግለሰብ መብቶች መካከል ልዩነት አለ:: ስለ ትሕትና፣ ስለ ፍቅር፣ ስለ ሰላምና ስለ ይቅርታ ስንል የግል መብቶቻችንን ችላ ልንላቸው እንችላለን:: የጎብረተሰቡን መብት በተመለከተ ግን ቸልተኞች ልንሆን አንችልም:: እንዲህ ያለው መብት የመላው ጎብረተሰብ ስለሆነ እኛ ልንቀማው አንችልም:: ከዚህ በተጨማሪ ብርቱው ደካማውን እንዳያጠቃ ጎብረተሰቡ ጥበቃ ይፈልጋል::

በነውን ሁሉ ለእኛ ያደረገና የሚያደርግ እግዚአብሔር ስሙ የተመሰገነ ይሁን!

ከዚህ ቀደም በተርጓሚው ተተርጉመው ለአንባቢያን የቀረቡ መጻሕፍት፡-

1ኛ/ የተራራው ስብከት
2ኛ/ የዲያብሎስ ውጊያዎች
3ኛ/ የነፍስ አርነት
4ኛ/ ሀብታምና ድሀ
5ኛ/ የተስፋ ሕይወት
6ኛ/ መንፈሳዊው ሰው

ከመጽሐፉ የተወሰደ

በዝለት ውስጥ ስትሆን መጽሐፍ ቅዱስን የምታነበው በልማድ፡ ያለ መረዳትና ያለ ተመስጦ ነው። በመሆኑም ያነበብኸውን በሕይወትህ ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ አትሞክርም። . . . ምናልባት እንዲህ ያለው ዝለት የመጣብህ ስለ ብዛቱ እንጂ ስለ ጥራቱ ስላልተጨነቅህ ሊሆን ይችላል። ይሄ ደግሞ ወደ ተራ አምልኮ ይመራሃል። . . . የተወሰነ መጠን ያላቸው መዝሙራትና ሌሎች ጸሎቶችን ማቅረብ ትፈልጋለህ። የተወሰነ ቁጥር ያላቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ምዕራፎችንም ልታነብ ትፈልጋለህ። ከዚህ በተጨማሪ የተወሰነ ቁጥር ያላቸውና በጸሎት ውስጥ የሚቀርቡ ስግደቶችን መስገድ ትፈልጋለህ። ይሁን እንጂ እነዚህን ሁሉ እንዴት ማከናወን እንዳለብህ አታውቅም። . . . ከላይ ከጠቀስናቸው መንፈሳዊ ልምምዶች መካከል ጥቂቶቹን ብታገኝ በዚህ ብቻ ስለምትደሰት እግዚአብሔር በአምልኮት አፈጻጸምህ ተደሰተም አልተደሰተም ግድ አይኖርህም።

❖❖❖

ከእግዚአብሔር ይልቅ ሰዎችን የመንፈሳዊ ሕይወትህ ዓላማ አድርገህ መከተልህ አደገኛ ነገር ነው። ገና ክርስትናን ስትጀምረው በመንፈሳዊ ሕይወትህ ፊት የምታስቀምጠው ዘላለማዊነትህንና ለእግዚአብሔር ፍቅር ያለህን መነሣሣት ነው። ዕድገት እያሳየህ ስትመጣ ግን ሌሎች ወደ አንተ ሕይወት በመግባት የዓላማዎችህ አንድ ክፍል ይሆናሉ። . . . በዚህ ጊዜ ሁለት ዓይነት ተፈጥሮ ይኖርሃል። የመጀመሪያው ክሰዎች ራስህን ትጠብቅ ዘንድ ለራስህ ዘብ እንድትቆም ሲያሳስብህ ሁለተኛው ደግሞ እነርሱ እስካሳዩህ ድረስ ብታደርገው ችግር የለውም በማለት ቸልተኛ የሚያደርግህ ይሆናል። . . . በዚህም ምክንያት እነርሱን ለማስደሰት ስትል የምትችለውን ነገር ሁሉ ስለምታደርግ ቀስ በቀስ የአንተ ጉዳይ ስለ ሰዎች ብቻ ይሆናል።

❖❖❖

ከዲያብሎስ ጥቃቶች ማምለጥህን ስታውቅ እግዚአብሔርን ስለ እርዳታው እንዲህ እያልህ አመስግነው፡- "እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ባይሆን፡ ሰዎች በእኛ ላይ በተነሡ ጊዜ ቁጣቸው በላያችን በነደደ ጊዜ ፣ በዚያን ጊዜ ሕያዋን ሳለን በዋጡን ነበር . . . " መዝ 123፡ 2-3። አንተ እግዚአብሔር መልካም የሆነውን ነገር የሚሰራብህ የእጁ መሣሪያ ነህ። ታዲያ የሚሠራብህን እጅ ዘንግተህ እንዴት መሣሪያው ላይ ታተኩራለህ? እንደምንስ በውስጥህ ያለውን የጸጋ ሥራ በመርሳት እግዚአብሔር የሠራውን አንተ እንደሠራኸው አድርገህ ትቆጥራለህ?

በብራና ሚቲሚያ ድርጅት ታትሞ
ዋጋው ብር 17.00